አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር

# በወረባቦ ወረዳ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ

በ

ዘቢባ መንግስቴ

ሰኔ 2008 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በወረባቦ ወረዳ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎችጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርኃ ግብር


ለአማርኛ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ዘቢባ መንግስቴ



ሰኔ 2008 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በወረባቦ ወረዳ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ

በ

ዘቢባ መንግስቴ

ሰኔ 2008 ዓ.ም

| የፈተና ቦርድ አባላት | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|
| የአማካሪ ስም | | |
| …………………….. | ………………… | ………… |
| የውስጥ ፈታኝ ስም | | |
| …………………….. | ………………… | ………… |
| የውጭ ፈታኝ ስም | | |
| …………………….. | ………………… | ………… |

# ምስጋና

ጥናቱ ከጅምሩ እስከ ፍጻሜው አቅጣጫ በመስጠትና በማረም ይህን ቅርጽ ይዞ እስኪወጣ ድረስ ከፍተኛ እገዛ ያደረጉልኝን መምህሬና አማካሪዬን አቶ ዘሪሁን አስፋው ከማንም በላይ አመሰግናለሁ፡፡

በተጨማሪም ጊዜህን መስዕዋት አድርገህ መረጃዎችንና ፎቶዎችን በማሰባሰብ፣ ሀሳብና አርትኦት በመስጠት ከጎኔ ላልተለየኸኝ ምንጊዜም የማከብርህና የማፈቅርህ ባለቤቴ ሰይድ አሊ አመሰግናለሁ ለአንተ በቂ አይደለም፡፡ ቢሆንም ጀዛክ አላሁ ኸይረን ከማለት ውጭ ምን ቃል አለኝ!

በሁለት ዙር የመስክ ሥራዬ በቂና ዝርዝር መረጃዎችን በማቀበል ይህን ጥናት ሙሉ ያደረጋችሁት የወረባቦ ወረዳ ነዋሪዎችና የክዋኔው ተሳታፊዎች ከፍ ያለ ምስጋና ይገባችኋል፡፡

የትምህርት ዕድሉን ለሰጠኝ ለደብረ-ብርሀን ዩኒቨርሲቲ እና የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናየ ከልብ ነው፡፡

በህይወቴ ሁሉ ስኬቴን ለማየት በምታሳዩኝ ጉጉት ገፍታችሁ እዚህ ላደረሳችሁኝና በዱአና በምርቃን ለስኬት ያበቃችሁኝ ቤተሰቦቼ አላህ ጀዛችሁን ይክፈላችሁ፡፡

**ማውጫ**

ምስጋና ........................................................................ i
ሙዳየ ቃላት........................................................................ v
መግለጫዎች........................................................................ vii
አጠቃሎ........................................................................ x
ምዕራፍ አንድ........................................................................ 1
መግቢያ ........................................................................ 1
1.1.የጥናቱ ዳራ........................................................................ 2
1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........................................................................ 6
1.3.የጥናቱ ዓላማዎች ........................................................................ 7
1.4.የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች........................................................................ 8
1.5.የጥናቱ አስፈላጊነት........................................................................ 8
1.6.የጥናቱ ወሰን........................................................................ 9
1.7.ጥናቱ ውስንነት ........................................................................ 9
1.8.የጥናቱ አጠናን ዘዴዎች........................................................................ 10
1.8.1.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ........................................................................ 10
1.8.1.1. ምልከታ........................................................................ 10
1.8.1.2. ቃለ መጠይቅ........................................................................ 12
1.8.1.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት........................................................................ 12
1.8.2. የመረጃ አመራረጥ ዘዴ........................................................................ 13
1.8.3. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ........................................................................ 13
1.9. የመስክ ተሞክሮ እና በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና
የተወሰዱ መፍትሄዎች........................................................................ 14
1.9.1. የመስክ ተሞክሮ........................................................................ 14
1.9.2. በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች......... 18
1.10. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ........................................................................ 19
ምዕራፍ ሁለት........................................................................ 21
ክለሳ ድርሳን........................................................................ 21
2.1. የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት........................................................................ 21

2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ........................................................ 25
2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ.................................................. 25
ምዕራፍ ሦስት............................................................... 39
የገፈራ ምንነት እና የሥርአተ-ክዋኔው ዝግጅት .............................. 39
3.1. የገፈራ ምንነት........................................................ 39
3.1.1. የዛር አሰፋፈር..................................................... 40
3.1.2. የዛር መንፈስ ምልክቶች.......................................... 42
3.1.3. ክዋኔው ቅድመ ዝግጅት .......................................... 46
3.1.3.1. የገፈራ መከወኛ ጊዜን መለየት...................... 46
3.1.3.2.ለገፈራ የሚደረግ የልመና ስነ-ስርአት............... 48
3.1.3.3. በብቅል ውሀ የሚደረግ ትጥበት.................. 51
3.1.3.4.የገፈራ አጠቃላይ የመጠጦች፣የምግቦች እና ቁሳቁሶች ዝግጅት፣ አገልግሎትና ትርጉም.......... 51
3.1.3.5.የስፍራ መሰናዶ............................... 62
ምዕራፍ አራት.............................................................. 65
የገፈራ ክዋኔ ሀድራና ቃል ግጥሞች ምንነትና ክዋኔ ......................... .65
4.1. የሀድራ ምንነት...................................................... 65
4.2. የገፈራ ቃል ግጥሞች አደራረስ፣ተስተላልፎና ክዋኔ............. 65
4.3. የገፈራ የመጀመሪያ ቀን ክዋኔ........................................ 66
4.3.1. የገፈራ ክዋኔ ሀድራ አጀማመር ............................ 66
4.3.2. ለዛር መንፈስ የሚደረግ ተለማምኖ........................ 68
4.3.3. የጨሌ አነካከር ሂደት ስነ-ስርአት.......................... 71
4.3.4 የቅንጨ (አመንካኮ)ና የቡና ስነ-ስርአት.................... 73
4.3.5. የዛር መንፈስ ሹመት ስነ-ስርአት.......................... 75
4.3.6. የራት ስነ-ስርአት፣የጫት ጀባታ፣ የዱአ እና የሙዳ ስነ-ስርአት............................................... 77
4.4. የገፈራ ሁለተኛ ቀን ክዋኔ.............................................. 108
4.5.የገፈራ ሦስተኛ ቀን (የጠረጋ ቀን) ክዋኔና ቃል ግጥሞች............ 109
4.6.የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ... 114

4.7.የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ፎክሎራዊ ተግባራት.............................. 114
4.7.1.የመትከልና የማጠናከር ተግባር................................. 115
4.7.2.የማምለጥ ተግባር................................................ 115
ማጠቃለያ........................................................................ 116
ዋቢ ጽሑፎች........................................................................ 120
አባሪዎች........................................................................ 128

## ሙዳየ ቃላት

### የአርበኛ ቃላትና ፍቻቸው

ሀድራ ፡- በጭብጨባ፣በድቤ፣በቃል ግጥም፣ወዘተ የደራ(ሞቀ) ባህላዊና ሀይማኖታዊ ክንውን
ሀጃ ፡- ጉዳይ
ሂረዋጫ (አውራጫ)፡- ጫት
ለበይክ፡- አቤት
ሊላሁ፡- ለአላህ ስል
ላስታ፡-ያልቀለጠ ቅቤ
ላኢላሀኢለሏህ ፡- ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም
መሊካ፡- መላዕክ
መረባ ፡- ይሁን
መርሀባ ፡- እሺ
መሻር ፣ሊያሽርልን፣ያሽራት፡- መዳን፣ሊያድንልን፣ያድናት
መቅቡል ፡- ተቀባይነት ያለው፣የተወደደ ስራ ወይም ተግባር
መታረቅ፡- አለማመም፣መስማማት፣አለመቆጣት
መወከል፡- የእረድ ስርአት ያለው ለዛር የሚደረግ ድግስ (ለዛር ማድማት)
መጀን ፡- መመካት፣መመኪያ
ሙስበሁ፡- ስንድድ ሆኖ ከጨሌ በመጠኑ የሚበልጥ
ሚስክ ፡- በጣም ጥሩ መአዛ ያለውና ነጭ ሆኖ የተፈጨ ጨው የሚመስል የጭስ አይነት
ማሏረፍ፡- ማቃመስ፣ማስታረቅ
ሶብር፡- ትዕግስት
ሏሂቡ፡- ወዳጁ (ዋና ቃሉ ሏሂብ ሲሆን ትርጉሙም ወዳጅ ማለት ነው)
ረቢአል አወል፡- የመጀመሪያ ዕለት(ሰኞ)
ራህመት፡- እሳት፣እዝነት
ርዚቅ፡-ሲሳይ
ሹመት፡- ስልጣን
ቀልብ፡- ማስተዋል፣ማስተዋል የሚያስችል የአዕምሮ ክፍል
ቀሽር፡-ያልተፈለፈለ ቡና
ቀንበጥ፡-ለምለም ጫት
ነድ ፡-ሰንደል
ነጃሳ፡-ቆሻሻ
ነፍስ፡- ራስ(እኔነት)
ኑር፡-ብርሀን
አህላቸው፡- ሁኔታቸው፣ማንነታቸው
አማን፡- ሰላም
አምስት አውቃ፡- የአምስት ወቅት ሰላት(በቀን አምስት ሰላት)
አሰላም አለይኩም፡- ሰላም በአንተ፣ በአንቺ፣በእናንተ ላይ ይሁን
አሏራፊ፡-አስታራቂ

አረቦቹ ገንዳ፡- አረቦቹ አገር
አርሂብ፡- ግቡ፣ተጋበዙ
አደብ፡-ስርአት፣ጠባይ
አጀብ፡-ጉድ(ግርምት)
አጅር፡- ምንዳ ማለትም ለጥሩ ተግባር ከፈጣሪ የሚሰጥ ወይም የሚቸር ጸጋ
አፍያ፡- ጤና
ኢማም፡- መንፈሳዊ የእስልምና ትምህርት መሪ፣አስተማሪ
ኢማን፡-የተሟላ እምነት (አላህን በሙሉ ልብ መቀበል፣ብቸኛ ፈጣሪነቱን በምላስ በመናገርና ህግጋቱን በተግባር በመግለጽ ማመን)
ከራማ፡- ጠባቂ
ካዳሚ፡- አስተናጋጅ
ኸልቅ፡- ፍጡር
ወአለይኩም ሰላም፡-ሰላም በእናንተም ላይ ይሁን
የኸለቀው፡-የፈጠረው
ዱአ፡-ጸሎት
ጀሀነም፡- ገሀነም
ጀመዓ፡- ህብረት
ጀባ፡- መስጠት
ጀባታ፡-ስጦታ
ጀነት፡- ገነተል ፊርዶስ(ገነት)
ጀዛክ አላሁ ኸይረን፡- ለውለታህ አላህ በጎውን(ጥሩውን) ሁሉ ይስጥህ
ጀዛ፡-ውለታ
ጡሀራ፡-ንጹህ

## የአማርኛ ቃላትና ፍቻቸው

መቅሉህ፡- የዶሮ ሰገራ መውጫ የአካል ክፍል
መታረቅ፡- አለማመም፣መስማማት፣አለመቆጣት
መገን ፡- አይ (ማዘን፣መፀፀት)
ሚዜ፡- ባለ ጉዝጓዟን(ሙሽራዋን) የሚያጅቡ ሌሎች ጨሌ ያስነከሩ ባለ ጉዝጓዞች
ማሷረፍ፡- ማስታረቅ
ማር፡- ሻይ
ማሯ ፈላላት፡- ሻይ ፈላላት
ሰቀላ፡- ፎቅ ቤት
ቀየ ፡- የቤት ውጭ፣ደጅ
ቁኒ ቀዳዳ፡- ከቅል የተሰራች ትንሽ የቁኒ መቁጠሪያ
ቁኒ፡-ለቅቤ ሽታ ማጥፊያ ሚያገለግል ደረቅና አረንጓዴ ቅጠል
ቂመሀ፡- ጫት እየቃሙ ዱአ ማድረግ
ቂምሀ፡- ጫት እየቃሙ ዱአ ማድረግ
በረኛ፡- በር ዳር የተቀመጠ ሰው
ቡቅሪ፡-ከገብስ ብቻ የሚዘጋጅ የማያሰክር መጠጥ
ቡን፡-ቡና
ተለማምኖ፡-ተደጋጋሚ ልመናና ማባበያ
ናትራ(ነጭ አሽኩቲ)
አመንካኮ፡-ቅንጨ

አሚኖች፡-ያልተፋቱ ባለትዳሮች የ"አሚን" ብዙ ቁጥር
አቦሬ(ፎሌ)፡-ከቅል የሚዘጋጅ የጠላና ቡቅሪ መጠጫ
አውገረድ፡-ሚስት(ብዙ ቁጥር ሲሆን አውገረዶች)
እርፎ ፡- ሴቶች
እርፎ መረባ፡- በሴቶች ይሁን
ወለል በይ፡- ተነተጎራደጅ፣ስትደሰች ታይ
ዋድ እንነጋገር፡- ስለ ወደፊቱ አደራ እንነጋገር
የምንሻው፡- የምንፈልገው
የዛር አፍ፡- በገፈራ ክዋኔ ወቅት ዛር የሰፈረባቸው ሰዎች ዛሩ ሲነሳ የሚናገሩት በማንኛውም ቋንቋ የማይመደብና ትርጉም የሌለው ንግግር
የዛር ግብር፡- ለዛር የሚሰጥና ሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ
የጤሰውን ቤት፡-ሰላም ያጣውን ቤት
ደንቡይ፡- ቆሪ(ከእንጨት ተቦርቡሮ የሚሰራ ጎድጓዳ ዕቃ)
ደጅ፡- የቤት ውጭ(ደጅ)
ገል፡- የሸክላ ስባሪ
ገፈታ፡-የጠላና የቡቅሪ የላይ የላዩ(ከላይ ያለው)
ጉሪያ፡-ውዝዋዜና ጭፈራ
ጉሽርጥ፡- ድንች የሚመስል እግርና እጅን ለማቅላት የሚያገለግል የማይበላ የስራስር አይነት
ግጥምህ ይሁን፡-ይስማማህ
ጎጥ፡-ሰፈር
ፍንድ፡-ፈንድሻ

## የኦሮምኛ ቃላትና ፍቻቸው

ነገያ፡-ሰላም
ሙዳ፡- ቅቤ
አሙማ፡- ቶሎ
አበጋር፡- አለቃ
ወዳጃ፡- በህብረት የሚደረግ ዱአ
ጨሌ፡-በተለያዩ ቀለማት ያጌጤ ስንድድ
ዱበርቲዎች፡-ቡና እየጠጡና ጫት እየቃሙ ዱአ የሚያደርጉ በዕድሜ የገፉ ሴቶች ስብስብ
ሚጄ፡- የመጀመሪያ ባሏን ያለልፈታች (ከመጀመሪያ የትዳር አገሯ ጋር በመኖር ላይ ያለች) ባለትዳር ሴት

## የአርጎብኛ ቀላትና ፍቻቸው

ተኮበሪ፡-ተቀመጭ
የምታኮብር፡- የምታስከብር

## የጣሊያነኛ ቃል እና ፍቺ

ባኒ፡-በማሽን ተጋገረ የነጭ ዱቄት ዳቦ

## መግለጫዎች

ምስል 1. የደቡብ ወሎ ዞን ካርታ

ምስል 2. የወረባቦ ወረዳ ካርታ

ምስል 3. በገፈራ ክዋኔ ላይ የቀረበ ርጥብ ቡና እና ጫት

ምስል 4. አሷራፊ አብዱ ረያን ድቤ እየመታ

ምስል 5. አደም እንድሪስ ማሲንቆ እተጫወተ

ምስል 6. ጨሌ

ምስል 7. ሙስበሀ

ምስል 8. ጭሳጭስ

ምስል 9. አሷራፊዋ ባለጉዝጓዟንና ተሳታፊዎችን ቅቤና ሽቶ ስትቀባ

## አባሪዎች

አባሪ 1. የገፈራ ክዋኔ የቃል ግጥሞች

አባሪ 2. በገፈራ ክዋኔ ላይ ተመረቁ ምርቃቶች

አባሪ 3. ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች


አባሪ 4. ፎቶዎች

አባሪ 5. ማረጋገጫ

# የደቡብ ወሎ ዞን እና የወረባቦ ወረዳ ካርታ




ምስል1.የደቡብ ወሎ ዞን




ምስል2.ወረባቦ ወረዳ

ከወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ "የወረባቦ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ በ2007 ዓ.ም" ከሚለው ሰነድ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በወረባቦ ወረዳ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ላይ ያተኮረ በዚህ ርዕስ ጉዳይ እንዳጠና ያነሳሱኝ ምክንያቶች በክዋኔው ላይ የሚታዩት ድርጊቶችና ተከታታይ ሁነቶች ፎክሎራዊ ገፅታ እንዳላቸው መገንዘቤ እና በርዕስ ጉዳዩ ላይ በወረዳው ቀዳሚ ጥናት እንዳልተካሄደ በመረዳቴ ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ላይ አውድ ተኮር ትንታኔ ማድረግ ሲሆን አውዱን መሰረት ባደረገ መልኩም ክዋኔው በቅደም ተከተል ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ከክዋኔው ጋር የሚመጡ ቃል-ግጥሞች ተግባርና ቁሳዊ ባህሎች ትርጉም ታይቷል፤ የክዋኔውም ፋይዳ ተዳሷል፡፡

በዚህ መሰረት ጥናቱ የተሟላ እንዲሆን ቀዳማይና ካልኣይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ ከጥር መጨረሻ እስከ መጋቢት ወር ድረስ በወረዳው አራት ቀበሌዎች በሁለት ዙር የመስክ ቆይታ ስድስት የገፈራ ክዋኔዎችን በስድስት ቤቶች በመገኘት መረጃዎች በንቁ ተሳትፏዊ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ እንዲሁም በድምፅ ብቻ ፣ በምስል ብቻ እና በድምፅና ምስል (ቪዲዮ) መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተገኙት መረጃዎችም በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በመታገዝ በገለጭ የትንተና ስልት ተተንትነዋል፡፡ በትንተናውም ክዋኔው የቅድመ ዝግጅት፣የሀድራ (የዛር ተለማምኖ፣ጨሌ ነከራ፣ የቅንጨና የቡና ስነ-ስርአት፣የዛር መንፈስ ሹመትና የራት ስነ-ስርአት) እና የጠረጋ ቀን(የዛር ሸኝት ስነ-ስርአት) የሚባሉ ተከታታይ ሁነቶች ድምር ውጤት እንደሆነ ማንሳት ተችሏል፡፡

የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ስነ-ልቦናዊ ህመምን መፈወስ፣የርስበርስ ትስስርን የማጎልበት ግለሰባዊና ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ እንዳለው በጥናቱ ግኝት ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ዋና ዋና ቁሳዊ ባህሎቹ(ድቤ)፣ማሲንቆ፣ጨሌ፣ ቅቤ ፣ ጭሳጭስ እና ጉዝጓዝ ) የተፈጥሯዊና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት፣ታሪክ ነቃሽነት እና የበለጠ ወካይነት የሚሉ ባህሪያትን ይዘው ተገኝተዋል፡፡ ይህ ከበራ የመንፈስ ውህደት(በዛር መንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን) ከሚገለፅባቸው ከበራዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን የዛር መንፈስ የተዋሀዳቸው ሰዎች ስነ-ልቦናዊ(መንፈሳዊ) ንፅህና(መፅዳትን) እና የአዕምሮ እርካታ ለማግኘት ሲሉ ለዛር መንፈስ የሚያቀርቡት የግብር ድግስ ስነ-ስርአት ሲሆን ዓላማው ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ፈውስ ማስገኘት መሆኑ በጥናቱ ታውቋል፡፡ ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት የክዋኔ ሂደት አንፃር በድቤ፣ በመሲንቆና በጭብጨባ የሚዜሙ፣እጉርጉሮዎች፣ የተለማምኖ ንግግሮች ሲሆኑ የዛር መንፈሶችን የሚያሞግሱና የሚማፀኑ ናቸው፡፡ ከበራው የማምለጥ እና የመትከልና የማጠናከር ፎክሎራዊ ተግባር እንዳለው ተገልጿል፡፡ በመጨረሻም ባህሉ በመጥፋት ላይ ስለሚገኝ የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ለቀጣይ ትውልድ ሊተላለፍ የሚችልበትን ይሁንታ ሀሳብ ቀርቧል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ለዛር የሚደረገው ሰፊ ድግስ (መወከል) እና የመረዳዳት ባህል የሆነው ጀባታ ራሳቸውን ችለው መጠናት እንደሚችሉ ጥናት ማካሄድ ለሚሹ ሰዎች ጥቆማ ተሰጥቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

የመንፈስ መዋሀድ(በመንፈስ ቁጥጥር ስር የመሆን)/spirit possession/ ፅንሰ ሀሳብ በሁሉም የዓለም ሀገራት የሚነሳ ሲሆን የመንፈስ አምልኮ (possession cult) ሰፋፊ ፅንሰ ሀሳቦች በውስጡ ይነሳሉ (Lewis,1971,117)፡፡ የመንፈስ አምልኮ ጉዳይ ሲነሳ የሚመለከት የመንፈስ አይነቶች መጠቀሳቸው አይቀሬ ነው፡፡ ከመንፈስ አይነቶች ውስጥ ደግሞ አንዱ የዛር መንፈስ ነው፡፡ የዛር መንፈስ በተለያዩ ሀገራትና ቦታዎች ከበራ ሲካሄድለት ይስተዋላል፡፡ በተለያዩ ሀገራትና ቦታዎች የሚካሄድ ከበራ መኖሩ ደግሞ የከበራው ክዋኔ ስርአቱ ላይ ልዩነት እንዲስተዋል አድርጎታል፡፡ ከበራው በመንፈሳዊ ገፅታው የተወሰነ ተመሳሳይነት ቢታይበትም የአከዋወን ስርአቱ ግን እንደ አካባቢው የባህል፣የአኗኗር እና የአስተሳሰብ ዘይቤ ይለያያል፡፡ እነዚህ ልዩነቶች ደግሞ የማህበረሰቡ የባህልና የአኗኗር መገለጫ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት የወረባቦ ወረዳ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ላይ ሲሆን ከከዋኔው ጋር አብረው የሚመጡ ቃል ግጥሞች እና ቁሳዊ ባህሎችንም ያነሳል፡፡ እንዲሁም የክዋኔው ማህበራዊ፣ባህላዊና ፎክሎራዊ ፋይዳ ይጠቅሳል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ በመሆኑ ገላጭ የትንተና ዘዴን በመጠቀም በክዋኔው ፎክሎራዊ ገፅታ ላይ አውድ ተኮር ትንታኔ የሚያደርግ ነው፡፡

በአጠቃላይ አራት ዋና ዋና ክፍሎችን የያዘ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማዎች፣ ክልልና ገደብ፣ አስፈላጊነት፣ የናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ መተንተኛ ዘዴ፣ የመስክ ተሞክሮና አካባቢያዊ ዳራ ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ፅሁፎች እና ጥናቱ የሚከተለው ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ ተዳሰዋል፡፡ በጥናቱ ሦስተኛ ምዕራፍ ደግሞ የገፈራ ምንነትና የስርዓተ ክዋኔው እና በክዋኔው ዝግጅት የተብራራበት ሲሆን የገፈራ ምንነት፣የዛር አሰፋፈርና ተያያዥ ጉዳዮችም ተዳሰዋል፡፡ በምዕራፍ አራት የገፈራ ክዋኔ ሀድራና ቃል ግጥሞች ሁለንተናዊ ገፅታ ላይ አውድ ተኮር ትንታኔ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳብ ተሰጥተው ዋቢ ፅሁፎች እና አባሪዎች ተጠቅሰዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የመንፈስ መዋሀድ (በመንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን) /Spirit possession/ የንቃተ ህሊናን መለወጥ ወይም ከተለመደው እንቅስቃሴና ተግባር ውጭ መሆን እና ራስን የማግለል ሁኔታ የሚያሳዩ አካላዊና አዕምሯዊ የሆኑ ምልክቶችን የሚገልፅ ነው፡፡ በመንፈሱ ዓለም እምነት መንፈሶች ሁልጊዜም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን ለብዙ ክበራዎች መፈጠር ምክንያት እንደሆኑ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

> Spirit possession is a term used to describe physical and mental states that indicate ephiphenomenalism such as 'out-of-the ordinary' experiences or 'altered states of consciousness, dissociated state. Belief in a world of spirits has always been present in human societies and forms an important part of many ceremonies and rituals. (Al-Adawi እና ሌሎችም 2001, 47)

ባህላዊ አምልኮ ከሚገለጽባቸው መንገዶች ዋነኛው የመንፈስ መዋሀድ(በመንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን) ነው፤ መንፈሳዊ ውህደት የአምልኮ ምስጢራዊነት መሰረት ነው፡፡ የዚህ መንፈሳዊ ውህደት እምነት በተለያዩ ኃይማኖት ተከታዮች ዘንድም ጎልቶ እንደሚታይ Maria Cruz እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡ "The Concept of Spirit possession exists in many religion, including Christianity, Buddhism, Haitian Vodou, Wicca , Hiduism, Islam and South East Asia and African traditions" (Spirit possession-wikipedia).

ከሃይማኖዊ መልኩ ይበልጥ በባህላዊ መንፈሳዊ ሀይል አምልኮ ወቅት ተፈላጊነቱ ያይላል ፤ በመሆኑም መንፈሳዊ ውህደት በቀላሉ የሚታይ ሳይሆን ውስብስብ እና ሊጨበጥ የማይችል መንፈሳዊ እምነት ነው፡፡ መንፈሳዊ ውህደት አንድ ሰው በሃይማኖትና በባህላዊ የኑሮ ዘይቤ ከተለመደው ማንነት በመለወጥ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲያደርግ ከራሱ በላይ በሆነ መንፈሳዊ ሀይል ቁጥጥር ስር እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ለመንፈሳዊ ውህደት ትልቁን ሚና የሚጫወተው ክዋኔው ሲሆን የከዋኙንና የተደራሲውን የአብሮነት መንፈስ በመፍጠር በሚካሄደው ተግባር ክንውኑ አሳማኝና ትክክለኛ እንዲመስል ያግዛል፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማህበረሰብ ዘንድም የሚካሄደውን የገፈራ ሥርአተ-ክዋኔ ከዋኞች ምንም እንኳ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም በዋናነት ከሚከሉት ሀይማኖት

በተጨማሪነት የዛር መንፈስን በማመን ከበራዎችን ሚያካሂዱ አንዳንድ ግለሰቦች መኖራቸው በዚህ ጥናት ተረጋግጧል፡፡ ነገርግን በዋናነት የሚመሩበት የእስልምና ሀይማኖት ይህን ከበራ እንደሚቃወም የሀይማኖቱ ተከታዮች ይገልጻሉ፡፡

> አዎ አንዳንድ ሰዎች የሀይማኖቱ መመሪያ ቁርኣን የሚያዘውን በሚገባ ሳይረዱ በመቅረት ቁጥብ፣ ቆሌ፣ እና ሌላል በማለት ከአሏህ (ሱ.ወ)[1] ጋር በማጋራት ያመልካሉ፡፡ይህ ድርጊታቸው ግን የተከለከለ ነው ማለትም በእስልምና ሀይማኖት ምንም አይነት መሰረት የሌለው ነው፡፡ ያው ግልጽ የሆነ ሽርክ ነው፤ከአላህ ጋር ሌላን አካል ማጋራት ነው፡፡(ቀ.መ. ሸኽ ሰይድ አደም፣ቤሬ፣ 1/10/08 )

ስለዚህ ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው ይህ ከበራ በእስልምና ሀይማኖት ዘንድ ምንም አይነት መሰረት የሌለውና የሀይማኖቱ መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርኣን የማያዘው ነው፡፡ እንዲሁም በተውሂድ[2] አስተምህሮት የተከለከለና የጠላ ነው፡፡ በመሆኑም ከበራውን ሚያካሂዱት ሰዎች ከሀይማኖታቸው ጋር በተለጣፊነት የሚያከብሩት እንጂ በእስልምና ሀይማኖት ድንጋጌ መሰረት አልባ ነው፡፡ ይህንንም ይበልጥ ከሚከተለው የሀይማኖቱ መመሪያ ጥቅስ መረዳት ይቻላል፡፡

> በል፡- እርሱ አሏህ አንድ ነው፡፡
>
> አሏህ የሁሉ መጠጊያ ነው፡፡
>
> አልወለደም፤አልተወለደምም፡፡ (ቅዱስ ቁርኣን፣ትርጉም፣ሱረቱ አል-ኢኽላስ (የፍጹምነት ምዕራፍ)፣ 1997፣841፣ቁ.1-3)

ከጥቅሱ መረዳት እንደሚቻለው አሏህ(ሱ.ወ) በፈጣሪነትና በአምላክነቱ ብቸኛ ፤አጋር የለሽ እንደሆነና ለማንኛውም ችግር መጠጊያና መመኪያ እሱ ብቻ መሆኑን በቁርኣኑ ተናግሯል፡፡ በመሆኑም በእስልምና ሀይማኖት ድንጋጌ መሰረት ለማንኛውም ችግርም ሆነ ህመም መፍተሄው አሏህ(ሱ.ወ) ብቻ ነው፡፡ ይህንኑ ሀሳብ ቅዱስ ቁራን ተርጓሚዎች እንደሚከተለው አብራርተውታል፡፡

> ሙዐዝ ኢብኑ ጀበል(ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ሙዐዝ ሆይ! አሏህ በባሪያዎቹ ላይ ያለውን ሀቅ ታውቃለህ" አሉ፡፡ እሱም "አሏህና መልዕክተኛው

---

[1] (ሱ.ወ) ሰተነተን ሱብሀነ ወተአላ ማለት ሲሆን ቃሉ አረብኛ ሲሆን በእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ዘንድ በፈጣሪነት የሚታወቀው ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይል "አሏህ" የሚለው ስም ሲጠራ ተከትሎ የሚመጣ ነው፡፡ ትርጉሙም "ለአሏህ ጥራት ይገባው" ማለት ሲሆን ማንኛውም ሙስሊም የሆነ ሰው የአሏህ ስም ሲጠራ ከሰማ እና ራሱም አሏህን ስም ሲጠራ እና ሲጽፍ ሱብሀነ ወተዓላ ማለት አለበት፡፡

[2] ተውሂድ ማለት በእስልምና ሀይማኖት ውስጥ አንድ የአስተምህሮት አይነት ሲሆን ትርጉሙም አሏህን በብቸኝነት ማለትም ያለምንም አይነት ማጋራት(ሽርክ) ማምለክ ማለት ነው፡፡

ከማንም ይበልጥ ያውቃሉ" ብሎ መለሰ። እሳቸውም " **(የአሏህ ሀቅ) ባሪያዎቹ እርሱን ብቻ እንዲገዙና ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር እንዳያመልኩ ነው"** አሉ። ቀጠል አድርገውም ሙዐዝ ሆይ! በአሏህ ላያለውን የእነሱን (የባሪያዎቹን ሀቅ) ታውቃለህ ሲሉ ጠየቁት። እሱም "አሏህና መልዕክተኛው ከማንም ይበልጥ ያውቃሉ በማለት መለሰላቸው። እሳቸውም (የእነሱ ሀቅ እንዳይቀጣቸው ነው" አሉት።"(ቡኻሪ ዘግበውታል) (ቅዱስ ቁርኣን፣ተርጓሚ ሸኽ መሀመድ ሳዲቅ እና ሀጂ መሀመድ ሳኒ ሀቢብ፣2004፣841፣የግርጌ ማስታወሻ)። (አጽዕኖቱ የእኔ ነው)

ስለዚህ የእስልምና ሀይማኖት መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርኣን የሚያዘውም ሆነ ነብዩ መሀመድ(ሱ.ዐ.ወ)[3] ያስተማሩት አሏህን ያለምንም ሽርክ(ማጋራት) በብቸኝነት መገዛትን ነው። በመሆኑም የዛር መንፈስ አምልኮና የአምልኮው መገለጫ ከበራዎች በሀይማኖቱ ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም። በመሆኑም በወረባቦ ወረዳ የገፈራ ከበራን የሚያካሂዱት ሰዎች ምንም እንኳን እስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ቢሆኑም የሀይማኖቱን ቀኖና በመጣስ የሚያካሂዱ እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል።

በተለያየ የሃይማኖት ጥላ ሥር ያሉ ሰዎች በተለይም ሴቶች አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት አንዳች ጥቅም ለማግኘት ሲሉ በመንፈስ ያምናሉ፤ የተለያየ ከበራም ያደርጋሉ። ከዚህ በተያያዘ ሴቶች በበሽታ ሲያዙ ወደ መንፈስ አምልኮ እንደሚገቡ እና በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ምክንያት ሲታመሙ የዛር ዝግጅት በማድረግ እንደሚፈወሱ (Kennedy፣1967፣185) ይገልጻሉ። እንዲሁም የወንዶች የበላይነት በሚታይባቸው አንዳንድ የኢስላም ሀይማኖት በተስፋፋባቸው ሀገራት ሴቶች መጨቆናቸውን የሚገልጹትና ከጭቆና የሚወጡት የመንፈስ አምልኮ ስርአት በማካሄድ እንደሆነ (Smith፣1954፣271) ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ሴቶች በወንድ መንፈሶች ሲያዙ ወንዶች ደግሞ በሴት መንፈሶች እንደሚያዙ በመጠቆም ወንዶችም በመንፈስ አምልኮ ውስጥ እንደሚገኙ (Lewis፣1966፣310) እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> … For, whether it is men or women who are the victims of possession and of course, I am not claiming that it is only women who are thus

[3] (ሰ.ዐ.ወ) ሲተነተን ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ሲሆን ትርጉሙም ሰላትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን ማለት ነው። በእስልምና ሀይማኖት የሀይማኖቱ ተከታይ (ሙስሊም) የሆነ ሰው የነብዩ መሀመድ ስም ሲጠራ (ሰ.ዐ.ወ) የማለት ግዴታ አለበት። ይህም ለነብዩ ያላቸውን ፍቅርና ከበሬታ ይጠቁማል። ይህም ማለት ልክ ማዕረግ ያላቸው ሰዎችን በማዕረጋቸው ጭምር መጥራት እንዳለብን ሁሉ ይህም የነብዩ ስም ሲፃፍም ሆነ ሲነገር መቅረት የለለበት በመሆኑ ነብዩ "መሀመድ(ሱ.ዐ.ወ)" ተብሎ ነው።

> affected the intrusive familiar is frequently of the opposite sex to its host. With this high incidence of the possession of men by female spirits, and of women by male spirits.

የመንፈስ ውህደት ከሰዎች አካላዊ ገፅታና ንግግር ጋር በመዋሀድ ማንነትን የሚያሳጡ እና ለህመም ምክንያት የሚሆኑ መገለጫ መልኮች አሉት፡፡ በአንድ በኩል መንፈሶች በአንድ ሰው አካልና ንግግር ውስጥ በመኖር የግለሰቡን ማንነት በመለወጥ እንዲደሰት ሲያደርጉ በሌላ በኩል ደግሞ የመንፈሶች መኖር ለመስማት አለመቻል፣ለሰውነት አለመታዘዝ፣ወዘተ ህመም ምክንያት እንደሚሆኑ ምሁራን እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> Least two principal forms. On the one hand, spirits would inhabit a person's body, speaking through the person to reveal their identity. On the other hand, there were beliefs that entailed the causal attribution of illness or malady (e.g. deafness, paralysis, etc.) to the presence of the possessing spirit in the person's body. A superficial analysis of the component features of these two descriptions of possession could point to any one of a considerable number of differences, including the presence or absence of trance. (Emma & Justin፣2008፣5)

መንፈሳዊ ውህደት ረቂቅ መሆኑ ይታመናል፡፡ የረቂቅነቱ ማጠናከሪያ ሰዎች ከሚፈጥሩት ሀሳብና እምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሀሳብና እምነት ሲባል ሰዎች መንፈሳዊ ሀይል መኖሩን አምነው መቀበላቸው ሲሆን እምነት ደግሞ ይህ መንፈሳዊ ሀይል ይፈፅማል ተብሎ በተከታዮቹ አዕምሮ ሰርፀው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ትክክለኛ በመሆናቸው ኃያልነቱን አምኖ መቀበልን ይጠቁማል፡፡

ወደ ሀገራችን ስንመጣ የመንፈሳዊ አምልኮ እምነት በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ቢሆንም የመንፈሳዊ ውህደት እምልኮ ከሰዎች የዕለት ተዕለት የኑሮ ለውጦች ጋር አብረው እያበቡ ወይም እየከሰሙ የሚሄዱ ናቸው፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው መንፈሳዊ እምነቶች የማህበረሰቡን አኗኗር፣ ባህል፣ ወግና ልማድ በመለወጥ ወይም በተፈጠሩበት ህብረተሰብ የሚኖራቸው ሚና አሉታዊ ይሆንና ይንኮታኮታሉ፣ አስተዋሽ ያጣሉ፤ ወይንም ደግሞ በሀይማኖት ተፅዕኖና በስልጣኔ መስፋፋት ምክንያት እየተተውና እየተረሱ ይመጣሉ፡፡ [4]

---

[4] በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስልጣኔ በተለይም የህክምናና የትምህርት መስፋፋት ሲኖር በመንፈስ የሚያመልኩ ሰዎች እንደሚቀንሱና ለዛር የሚደረግ ከበራም እንደሚጠፋ ከሚከተለው ጥቅስ መረዳት ይቻላል፡፡

የመንፈስ አምልኮ ከበራዎች እምነቱንና አምልኮቱን ለተቀበሉት እንደ ህይወት አንቀሳቃሽ መሳሪያ በመሆን ያገለግላሉ፤ ስነ ልቦናዊ ወይም መንፈሳዊ ንፅህናን፣ የአዕምሮ እርካታን፣ የመዳን ተስፋን፣ ወዘተ የማጎናፀፍ ተግባራዊ አገልግሎት ያበረክታሉ። ፈውስ ፈላጊዎች ሲጎዱና ጥሩ ሁኔታ ላይ በማይሆኑበት ጊዜ ዘመናዊ መድሀኒትን እንደማይመርጡ እና መንፈሶችን ለማስደሰትና ፈውስ ለማግኘት በራሳቸው የከበራ ዳንስ፣መዝሙርና በግን ለመንፈሶች መስዕዋት በማረድ ፈውስ እንደሚያገኙ (Lewis፣1971፣35) ያስረዳሉ።

አውቀውትም ሆነ ሳያውቁት ወይም ካለባቸው ችግር ለመላቀቅ ሲሉ የሚያመልኩባቸው መንፈሳዊ ሀይላት ቢኖሩም የሚደረጉት ከበራዎች በእጅጉ በመጥፋት ላይ ይገኛሉ።

ስለሆነም በመጥፋት ላይ ካሉ ባህሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የመንፈስ አምልኮ ማጥናት አስፈላጊ ነው። ይህ ጥናትም በወረባቦ ወረዳ የመንፈስ ውህደት የሚገለፅበት እና የአምልኮው ስርዓተ ክዋኔ መጠሪያ የሆነውን “ገፈራ”ን የሚመለከት ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የገፈራን ስርዓተ ክዋኔ ለማጥናት ያነሳሱኝ ምክንያቶች አራት ናቸው። እነዚህም፡- በ 2007 ዓ.ም የፎክሎር ኮርሶችን ስወስድ በአካባቢው በገፈራ ስነ-ስርአት ላይ በተሳተፍኩባቸው ጊዜያት የተመለከትኳቸው ክንውኖች ፎክሎራዊ ጉዳዮች እንደሆኑ ተረዳሁ። በመሆኑም በተማርኩት መሰረት የገፈራ ክዋኔ በንድፈ ሀሳብ ተደግፎ መጠናት ይችላል የሚል እምነት አደረብኝ፡፡ ከዚያም ለወረባቦ ወረዳ ማህበረሰብ፣ባህልና ቋንቋ ቅርብ ስለሆንኩ የቋንቋና የባህል ልዩነት ሳያስቸግረኝ መረጃዎችን በማግኘት የተሻለ ስራ መስራት እንድችል ትኩረቴን በገፈራ ላይ አድርጊያለሁ።

ሌላው አነሳሽ ምክንያት ደግሞ በዞኑ ውስጥም ሆነ በወረባቦ ወረዳ ላይ የመንፈስ ውህደትን የሚመለከትም ሆነ በቀጥታ ከ“ገፈራ” ጋር የሚገናኝ ምንም አይነት ጥናታዊ ፅሁፍ አለመኖሩ ነው። ስለዚህ የማህበረሰቡ ባህል ከማስተዋወቅና ከማጥናት ረገድ አንዳች ክፍተት ስለሚኖር ይህን መሙላት አለብኝ የሚል ፍላጎት ስለአደረብኝ በዚህ ርእስ ላይ ለማጥናት ተነሳስቻለሁ።

---

“Socio-economic modernization has led to a decline in interest in zar ceremonies, as today there are not only state medicine and education.” (Arvihurskainen, 2004,222)

የመንፈስ ውህደትን በሚመለከት የተደረጉ ጥናቶችን ስቃኝ በሀገራችን ከመጀመሪያ ዲግሪ ጥናታዊ ፅሁፎች ውጭ በማስተርስም ሆነ በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ የተጠና የለም፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናታዊ ጽሁፎች ላይም አንዳንድ ክፍተቶችን ስላስተዋልኩኝ እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ነው፡፡ ለምሳሌ ከታዩት ክፍተቶች ውስጥ ክዋኔን በቅደም ተከተል ማሳየት አለመቻል፣ የመንፈስ ውህደትን የአንድ ክልል ወይም የተወሰነ ማህበረሰብ ባህል ብቻ ማድረግ፣ የመንፈስ ውህደት የዛር ባለቤትነትን ለወንዶች ወይም ለሴቶች ብቻ መስጠት፣ የቁሳዊ ባህሎቹን ትዕምርት አለመግለፅ የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አብዛኞቹ ጥናቶችም ከመንፈስ መጠሪያዎች (የመንፈስ አይነቶች) ውስጥ ማለትም ዛር፣ ውቃቤ፣ አዶከበሬ፣ አውሊያ… ወዘተ አንዱን ብቻ በመምረጥ ድራማዊ አላባዎቹን እና ቃል ግጥሞቹን መግለፅ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የመንፈስ ውህደቶቹን የመጠሪያ ስም አንድትና ልዩነት የሚገልፁ ናቸው ስለሆነም ክዋኔያቸውና የቃል ግጥሞቹ ይዘት በንድፈ ሀሳብ ተደግፎ አልተጠናም፡፡

ስለዚህ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በስፋትና በጥልቀት ካለመጠናቱ የተነሳ የሁሉም መንፈሶች መገኛና መገለጫ የሆነውን የገፈራ ከበራ በመምረጥ ክዋኔያቸውን ከአውዳቸው አንፃር በንድፈ ሀሳብ በማስደገፍ ለማጥናት ካለኝ ፍላጎት ተነሳ ለማጥናት ተነሳስቻለሁ፡፡

የገፈራ ስርዓተ-ክዋኔ እና ከበራ በደቡብ ወሎ ዞን በወረባቦ ወረዳ በመጥፋት ላይ በመጥፋት ላይ ያለ በመሆኑ ከነአካቴው ከመጥፋቱ በፊት ክዋኔውን ከእነ ባህላዊና ማህበራዊ አውዱ ቀርጾ በሰነድነት (በመዘክርነት) እንዲቀመጥ ለማድረግ ካለኝ ፍላጎት የተነሳም ላጠናው ችያለሁ፡፡ ምክንያቱም ይህ ባህል አንዱ ፎክሎር ዘርፍ ውስጥ የሚካተት በመሆኑ ለፎክሎር ትምህርት መስክ እንደ ግብአት ያገለግላል በሚል ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በወረባቦ ወረዳ የሚካሄደውን የገፈራ ስርዓተ ክዋኔን ምን እንደሚመስል አውዱን ተመስርቶ መተንተን ሲሆን ንዑሳን ዓላማዎቹ ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ምን እንደሚመስል በሁነቶቹ ላይ በመመስረት የክዋኔውን አውድ በቅደም ተከተል ማጥናት፣

- በገፈራ ክዋኔው ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሳዊ ባህሎችን ትርጉም መግለጽ (ለምን ትዕምርት እንደዋሉ መግለፅ) ፣
- ክዋኔው ላይ የሚዜሙ ወይም የሚነገሩ ቃል ግጥሞች እንዴትና ለምን እንደሚቀርቡ ተግባራቸውን በማጤን ማሳየት፣
- የክዋኔው ተሳታፊዎች ለከበራው (ለገፈራ ስርዓቱ) ያላቸውን አመለካከት መግለጽ፣
- የስርአቱ ታዳሚዎች በክዋኔው ላይ መሳተፋቸው የሚያገኙትን ጥቅም መግለፅ፣
- የገፈራ ስርአተ- ክዋኔን ፎክሎራዊ ተግባር ማብራራት እና መሰነድ ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ገፈራ ምንድን ነው?
- የገፈራ ክዋኔ አወቃቀር ምን ይመስላል? ወይም ክዋኔው የምን፣ የምን ሁነቶች ድምር ውጤት ነው?
- ለሁነቶቹ መፈጠርና መከወን ምክንያቶቹ ምን ምን ናቸው?
- በገፈራ ክዋኔ ላይ ተሳታፊዎች እንዴት ይሳተፋሉ?
- የገፈራ ክዋኔ ፋይዳ ምንድን ነው?
- ለገፈራ ስርአት ማህበረሰቡ የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው?

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል፡፡

- የገፈራ ክዋኔ በመጥፋት ላይ ስለሚገኝ ክዋኔውን ከነቃል-ግጥሞቹ በቅደም ተከተል በማሳየትና በመቅረፅ በሰነድነት ያስቀምጣል፡፡
- የከበራው ክዋኔ መጠናት ለፎክሎር ጥናት መስክ አንዳች አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ሰፊ ጥናት ማድረግ ለሚሹ ሰዎች እንደ መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡
- የገፈራ ክዋኔን ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ማወቅ ለሚፈልጉ መረጃ ይሰጣል፡፡
- የአገራችን የባህል ክዋኔዎች ዘርፈ ብዙ መሆናቸውን ከሚያረጋግጡት ከበራዎች ውስጥ አንዱ ገፈራ በመሆኑ ይህን ያረጋግጣል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በደቡብ ወሎ ዞን በወረባቦ ወረዳ በተመረጡ አራት ቀበሌዎች ኗሪ በሆኑ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድም በወረዳው ይህን ከበራ የሚያካሂዱት የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ሲሆን አንድም ደግሞ ከላይ በአካባቢያዊ ዳራ ላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በወረዳው የሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች ከጠቅላላው ህዝብ 1% ቱን ብቻ የያዙ በመሆናቸው እና በተመረጡት ቀበሌዎች ውስጥም የክርስትና እምነት ተከታይ አለመኖሩ ነው፡፡

ከአራቱ የፎክሎር ዘርፎች ማለትም ስነ-ቃል፣ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ሀገረ-ሰባዊ ልማድ እና ቁሳዊ ባህል ውስጥ ደግሞ ሀገረሰባዊ ልማድ ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ከሚካተቱት ደግሞ ሀገረሰባዊ እምነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ከሚጠናው ርዕስ ጉዳይ አንፃርም ከእምነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው የከበራ አይነት በሆነው የገፈራ ስርአት ላይ ያተኩራል፡፡ ፎክሎር እጅግ በጣም ሰፊ ይዘት ያለው ጥናት መስክ በመሆኑ የሚያካትታቸው አራቱ ዘርፎች እንኳን ቢታዩ በብዙ አይነት (Geners) የሚከፋፈሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለብቻቸው ድንበር ከልለው የተቀመጡ ሳይሆኑ አንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ "በመሀከላቸው ግንኙነት፣መስተጋብር እና ተደጋግፎ ያላቸው ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም" (ፈቃደ፣1991፣15)፡፡ በመሆኑም የጥናቱ ዋና ትኩረት የገፈራ ስርዓትን ክዋኔ ማሳየት ነው፡፡ ትንተናው አውዱን መሠረት ያደረገ ስለሆነ በክዋኔው ላይ የሚዜሙ የስነ-ቃል ዘርፍ የሆኑት ቃል ግጥሞች እና ቁሳዊ ባህሎችም ተዳሰዋል፡፡ እንዲሁም የክዋኔው ፋይዳና ፎክሎራዊ ተግባር ተነስተዋል፡፡በቃል ግጥሞቹ ቅርፅ ላይ ግን ትንተና አይደረግም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ሲጠና የጊዜ፣የበጀትና የመረጃ ውስንነት አጋጥሟል፡፡ እነዚህ ችግሮችም ርስበርሳቸው ተያያዙ ናቸው፡፡ የጊዜው ማነስ ማለትም መስክ ወጥቼ ጥናቱን እንዳካሂድ ከትምህርት ክፍላችን የተፈቀደልኝ የጥር ወር መጨረሻ አካባቢ በመሆኑ ከስድስት ቤቶች በላይ የገፈራ ቤቶች ተገኝተው ምልከታው እንዳይካሄድና በስፋት እንዳይጠና አድርጓል፡፡ በተጨማሪም የገፈራ ስርአተ ክዋኔ የሚካሄድባቸው ጊዜያት ጥር፣የካቲትና መጋቢት በመሆናቸው የጥር ወር ስላላቀ በጥር ወር ገፈራ የሚያደርጉትን ሰዎች

ማግኘት አልተቻለም፡፡ እነዚህ ውስንነቶችና አብዛኞቹ ገፈራ አድራጊዎች ለቀረፃ ፍቃደኛ አለመሆናቸውና የከበራው እየጠፋ መምጣት ደግሞ በአንድነት ለመረጃ ውስንነት ዳርገዋል፡፡

## 1.8 የአጠናን ዘዴዎች

### 1.8.1. የመረጃ ምንጮችና መሰብሰቢያ ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች መጽሀፎች፣ መጽሔቶችና ሌሎች ጥናታዊ ጽሁፎች እንደ አስፈላጊነታቸው ተመርጠው ተወስደዋል፡፡ ከቀዳማይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተመርጠዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎች ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት ተመራጭ ሲሆኑ ዘዴዎቹን እንደ አስፈላጊነታቸውና አመቺነታቸው እያፈራረቁ መጠቀም ለመረጃው ግብዓትና ጥራት አስተዋፅኦና ጠቀሜታ እንዳላቸው የመስኩ ምሁራን ገልጸዋል (ፈቃደ 1991፣90-99፣ Goldstein፣1964፣77-104)፡፡ በአንድ አጋጣሚ ላይ ቢያንስ ሁለት አይነት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መጠቀም መረጃዎች እንዳይረሱና እንዳይጠፉ ያደርጋል፡፡

የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መጠቀም ምልዑ መረጃ እንድናገኝ ከማድረጉም በተጨማሪ የመረጃዎቹን ትክክለኛ መልዕክት ሳንረዳ እንዳንቀር ያደርጋል፡፡ በመሆኑም ይህን ጥናት ምልዑ ለማድረግ በዚህ ጥናት እነዚህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እያደጋገፍኩ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ቀጥሎ ሦስቱን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በአጭሩ እገልጻለሁ፡፡

#### 1.8.1.1 ምልከታ

ምልከታ በአይናችን የተመለከትናቸውን ብቻ ሳይሆን በአፍንጫችን ያሸተትናቸው፣ በዕዝነ አዕምሮአችን የተመለከትናቸው፣ በምላሳችን የቀመስናቸውና በመዳፎቻችን የዳሰስናቸው ነገሮችን እንደሚያካትት (Goldstein፣1964፣79) ይገልፃሉ፡፡

> The term 'observation' as used in this context is not limited only to visual aspects of the situation, but also involves a full range of sensual experience including hearing, feeling, smelling and tasting. Whenever these may be appropriate.

በመሆኑም የዚህ የጥናት ዋና ትኩረት የሆነውን "ክዋኔ" ከነአውዱ ለማግኘትና ለማሳየት ምልከታ በዋነኝነት ተግባር ላይ ሆኗል፡፡

ከምልከታ አይነቶችም ሁለቱንም ማለትም ተሳትፏዊ ምልከታ እና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ እንደ አስፈላጊነታቸው ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ እነዚህ ዘዴዎች የተወሰኑ ማህበረሰብን ባህል፣ ልምድ፣ ትውን-ጥበብ ማጥናት ሲታሰብ ጠቃሚ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው፡፡ (ዝኒ ከማሁ 1964, 78-99)

ተሳትፏዊ ምልከታ የባህሉ ባለቤቶች ጉዳዩን ሲያከናውኑ ነፃ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አጥኚዎች በሚያካሄዱት ስርዓተ-ክዋኔዎች ሁሉ እየተሳተፉ የሚፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ይችላሉ፡፡ በአንፃሩ ጉዳዩ በሚፈፀም ጊዜ ሙሉ ክዋኔውን ለመመልከትና ለመቅረፅ አያስችልም፡፡ በዚህ ዘዴ የማይገኙ መረጃዎችን ለመመልከትና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለመያዝ ተሳትፏዊ ያልሆነ (ኢ-ተሳትፏዊ) ምልከታን መጠቀም ይቻላል፡፡ (ፊቃደ፣1991፣17)

እኔም ተሳትፏዊ ምልከታን የገፈራ ክዋኔ በተካሄደባቸው ስድስት ቤቶች ተገኝቼ በቅድመ ክዋኔ ስርዓቱ ላይ በመሳተፍ፣ ምን፣ በማን፣ እንዴት፣ በምን ይከወናል፣ ምን ይባላል፣ ቁሳዊ ባህሎቹ አይነት ቀለም፣ የተሰሩበት ነገር ለምንስ ትዕምርት ይውላሉ፣ ምን ይበላል፣ ምን ይጠጣል ወዘተ የሚሉ ጉዳዮችን በንቁ አዕምሮ በመመልከት ማስታወሻ ይዣለሁ፡፡ ይህን ተሳትፏዊ ምልከታም ሳካሂድ ገፈራው በሚካሄድባቸው ቤቶች በመዋልና በማደር የበሉትን በመብላትና የጠጡትን በመጠጣት እና አንዳንድ ስራዎችን በማገዝ ጭምር አጠቃላይ የቅድመ የክዋኔ ሂደቱን ተመልክቻለሁ፡፡ እንዲሁም በክዋኔው ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ቃል ግጥም በመቀበል፣ በማጨብጨብ፣ ወዘተ ተሳትፏዊ ምልከታ አካሂጃለሁ፡፡

በተጨማሪም ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታን ደግሞ ከቅድመ ክዋኔ ስርዓቱ በኋላ ማለትም በክዋኔው ወቅት ያለውን አጠቃላይ የክዋኔ ሂደት ምን እንደሚመስል ፈቃደኛ ከሆኑት ባለ ገፈራዎች በመቅረፀ ምስል (photograph) ፣ በመቅርፀ ድምፅ (recorder) እና በመቅርፀ ድምፅና ምስል (video) መረጃዎችን ለመያዝ ተጠቅሜበታለሁ፡፡ እንዲሁም ከክዋኔው በኋላ በክዋኔው ወቅት አስደሳች፣ አስደንጋጭ፣ አዲስና አስገራሚ የሆኑብኝን ነገሮች እና አወዛጋቢ የሆኑብኝን ጉዳዮች በማስታወሻ ለመያዝ ይዣለሁ፡፡

#### 1.8.1.2 ቃለ መጠይቅ

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የተጠቀምኩበት ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ይህ ዘዴ ለጥናት የሚረዱኝን መረጃዎች ስለሚጠናው ጉዳይ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች በመጠየቅ መረጃዎችን የሚሰበሰብበት ዘዴ መሆኑን (Goldstein, 1964, 77-78)

"…those methods used by the field worker to obtain data about ideas or events outside the context of the interview itself through questioning person's believed or known to have that information." በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ቃለመጠይቅ ተጠያቂዎቹ ከሚሰጡት ምላሽ በተጨማሪ ከሰውነት እንቅስቃሴያቸውም መረጃ ማግኘት ያስችላል፡፡ ስለሆነም በምልከታ ያልተሟሉ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ለማሟላት ሲባል ይህ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ "The interviewer may also not only be listening to the verbal responses, but other elements of the interview process such as the body language of the interviewee also included." (Gray, 2004, 213) ይላሉ፡፡

ከቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ውስጥ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ በማካሄድ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ እነዚህ የቃለ መጠይቅ ቴክኒኮች እንደ መረጃ ሰጪዎቹ ሁኔታ እና እንደፈለገው የመረጃ አይነት ሁሉም እንደ አመቺነታቸው ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን የጥናቱ ታላሚ አካላት ሳይፈሩና ሳይጨነቁ ተፈጥሯዊ የሆነውን አመለካከት፣ ግንዛቤና እውቀት ለመቃኘት አመቺ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

#### 1.8.1.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

በመስክ ላይ እያለሁ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ያልተሟሉና የተዘነጉ መረጃዎችን ለማሟላት እና ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የተተኳሪ ቡድን ውይት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ከተተኳሪ ቡድን ውይይት በፊት በሁለቱ ዙር የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ከማስታወሻ፣ ከቪዲዮና ከፎቶግራፍ መረጃዎችን በመምረጥና በስርዓት በመሰደር አደራጅቼያለሁ፡፡ የተተኳሪ ቡድን ውይይቱ ያወዛገቡና በቃለ መጠይቅ ያልተመለሱ

ጥያቄዎች የቀረቡበት ሲሆን ከ5-7 ሰዎችን ያሳተፈና በስድስቱም ጎጦች አንድ አንድ ጊዜ ከክዋኔ በኋላ የተካሄደ ነው፡፡

የተተኳሪ ቡድን ውይይት ለመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት የተመረጠበት ምክንያትም ያልተሟሉ መረጃዎችን ማሟላት ከማስቻሉም በተጨማሪ ያልተዳሰሱ ጉዳዮች እንዲታወሱ ይረዳል፣ የመረጃዎቹን ሀቀኝነት ለማረጋገጥና አዲስ መረጃን ስለሚያስገኝ ነው፡፡

### 1.8.2 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

ከላይ ለተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ታላሚ የሚሆኑ መረጃ አቀባዮች ለሚፈለገው መረጃ የበለጠ ቅርብ ናቸው፤ የተሟላ መረጃን ይሰጣሉ የተባሉ መረጃ ሰጪዎች በተለያዩ መንገዶች ተገኝተዋል፡፡ ይኸውም ከዚህ በፊት በማውቀው ላይ በመመስረት፣ በትውውቅ፣ ሰዎችን በመጠየቅ፣ በጥቆማ፣ በመኖሪያ ቤታቸው እና በአጋጣሚ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ገፈራ ይካሄድባቸዋል የተባሉት ቀበሌ 01 (ሀራ)፣ቀበሌ 02(ቡልቡሎ)፣ቀበሌ 05 (ፊቶ) እና ቀበሌ 18 (ቁኖ) ናቸው፡፡ ከፊቶ ቀበሌ ቤሬ እና ቀርሱ ጎጥ፣ከቁኖ ቀበሌ ዋዚ ጎጥ፣ ከሀራ ቀበሌ ቸሪት ጎጥ እና ከቡልቡሎ ቀበሌ ዱሬ ጎጥ ለመረጃ ሰጭነት ተገኝቷል፡፡ ከእነዚህም በቸሪትና ዱሬ ጎጥ አንድ አንድ ገፈራ ቤቶች የተገኙ ሲሆን በሌሎቹ ደግሞ ሁለት ሁለት ገፈራ ቤቶች ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም በድምሩ ስድስት ገፈራ ክዋኔ የሚካሄድባቸው ቤቶች ተመርጠዋል፡፡ ለመረጃ ሰጪነትም ባለ ገፈራዎች፣ ተሳታፊዎች እና በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ በዕድሜ የገፉ ሰዎች፣ጎልማሳዎችና ወጣቶች ተመርጠዋል፡፡ በአጠቃላይ 31 ሰዎች በመረጃ ሰጭነት ተካተዋል፡፡

### 1.8.3 የመረጃ መተንተኛ ስነ ዘዴ

በምልከታ፣ በቃለ መጠየቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተሰበሰቡት መረጃዎች የተተነተኑት አውድ ተኮር ስነ-ዘዴን በመጠቀም በገላጭ የትንታኔ ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ጥናት አይነታዊ ምርምር በመሆኑም ዓላማው ደግሞ የገፈራ ክዋኔን አውድ መሰረት በማድረግ ክዋኔውን በቅደም ተከተል ተንትኖ ማሳየት ስለሆነ ይህ ስነ-ዘዴ ቴክስቱን ከአውዱ ጋር በመተንተን ምልዑ መረጃን ስለሚያስገኝ ነው፡፡ በመሆኑም በቀዳማይ እና በካልአይ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች ጥናቱን ከግብ በሚያደርስ መልኩ በማደራጀት ተንትኜ አቅርቤያለሁ፡፡ ይህን ሳደርግ ገለጻን

(description) ተጠቅሜያለሁ። ይህም ማለት በዋናነት የገፈራ ክዋኔ በሁነት ላይ በመመስረት እየገለጽኩ ወደ ትርጓሜ አምርቻለሁ። በዚህም ዘዴ በመገልገል የክዋኔው የክዋኔውን ቃልግጥሞች፣ቁሳዊ ባህሎች ተግባርና ትርጉም እንዲሁም ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ እና የሚፈጸሙ ተከታታይ ድርጊቶችን ከአውዱ በመነሳት አጥንቻለሁ።

## 1.9 የመስክ ተሞክሮ እና በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

### 1.9.1 የመስክ ተሞክሮ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ መስክ ከመውጣቴ በፊት ከትምህርት ክፍላችን ለወረባቦ ወረዳ የድጋፍ ደብዳቤ በ23/05/08 ዓ.ም አፃፍኩኝ። የጥናቴን ዋና መረጃ ለመሰብሰብ ጉዞ የጀመርኩት ሀሙስ በ26/05/08 ዓ.ም ወደ ደሴ ነበር። ከዚያም ቤተሰቦቼ ጋር በማረፍ በ27/05/08 ዓ.ም ረፋድ ላይ ጉዞየን ወደ ሀይቅ ከተማ አደረኩ። ሀይቅ ከ30 ደቂቃ በኋላ ወዲያው ከሀይቅ 17 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘው የጥናት ቦታየ ወረባቦ ወረዳ ጉዞ ጀመርኩ። ከ 30 ደቂቃ በኋላ የወረዳው ዋና መቀመጫ ከሆነችው ቢስቲማ ከተማ ደረስኩ። ወዲያውም ዘመዶቼ ተቀብለውኝ አንዳንድ መረጃዎችንና ፍቃድ ለማግኘት ወደ ወረዳው አስተዳደር ፅህፈት ቤት ሄድኩ። ፅህፈት ቤቱም ጥናቱን ማካሄድ እንደምችል በቃል በመግለፅ ስለ ወረዳው በቂ መረጃ ወደማገኝበት የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅህፈት ቤት አመለከቱኝ። እዚያም የምፈልገው አጠቃላይ መረጃ በቃልና በፅሁፍ ሰጡኝ። ከዚያም ባገኘሁት መረጃ መሰረት ካሉት 22 ቀበሌዎች ውስጥ ለጥናቴ የሚሆኑኝ በመምረጥና አንዳንድ ሁኔታዎችን ሳመቻች ከዘመዶቼ ጋር ቅዳሜና እሁድን ቆየሁ። የመረጥኳቸው ቀበሌዎችም ቀበሌ 01 (ሀራ)፣ቀበሌ 02(ቡልቡሎ)፣ቀበሌ 05 (ፊቶ) እና ቀበሌ 18 (ቁኖ) ናቸው።

በመረጥኳቸው ቀበሌዎች መሰረትም ዘመዶቼ ከሚያውቋቸው ሰዎች ጋር ስልክ በመደወል አጣርተው በ 05 ቀበሌ (ፊቶ) ልዩ ስፍራው (ጎጡ) ቤሬ ከተባለው ቦታ ሰኞ ማታ ገፈራ እንዳለ ጠቆሙኝ። ከዚያም ለመጀመሪያ የመስክ ምልከታ በ 30/05/08 ዓ.ም ጠዋት በቀበሌው ከሚኖር ሰው ጋር በአደራ ወደ ቦታው ላኩኝ። ለስጦታ(ጀባታ) የሚሆን ስኳር፣ ጫትና ዕጣን ገዝቼ ከአንድ ሰአት የእግር መንገድ በኋላ በቦታው ደረስን። ይህ ሰው የስርአቱ ባለቤቶች ጎረቤት ስለነበር ከሰዎቹ ጋር አስተዋውቆኝ ለሄድኩበት ጉዳይ ጥሩ መረጃ እንዲሰጡኝ ነገራቸው። እኔም የመጣሁበትን ዓላማና መረጃውም

ለትምህርት እንጂ ለሌላ አለመሆኑን በማስረዳት ፍቃደኝነታቸውን ጠየኩኝ፡፡ የያዝኩትን ጀባታም ለገፈራ አድራጊዋ(ባለጉዝጓዟ) ሰጠሁ፣ተመረቅኩም፡፡ ነገር ግን የክዋኔውን ሀድራ በድምፅ እንጂ በምስል መቀረፅ እንደማይፈቅዱና ሌላውን ክዋኔ በምስልም በድምፅም እንድቀርፅ ፈቀዱልኝ፡፡ ምክንያቱም ዛሮች ስለሚቆጡ ሀድራው ይበላሻል ብለው ስለፈሩ ነው፡፡

እኔም በፍቃዳቸው መሰረት የዛኑ ዕለት (ሰኞ) ቀን ቅድመ ዝግጅቱን አንዳንድ ስራዎችን በመስራት ተሳትፏዊ ምልከታ አድርጌ በፎቶ ግራፍ ጭምር መረጃ ሰበሰብኩ፡፡ ማታ ሌሊቱን ሙሉ ደግሞ በተሳትፏዊ ምልከታና በድምፅ ቀረፃ አማካይነት ሙሉ ክዋኔውን ተከታተልኩ፡፡ በሁለተኛው ቀንም እዚያው ቤት በመዋል ያሉትን ሁኔታዎች በሙሉ በመመልከትና ክዋኔው ላይ ጥያቄ የሆኑብኝን አንዳንድ ክንውኖች ቃለመጠይቅ በማድረግ አሳለፍኩ፡፡ እዚያው ቤት አድሬ በሦስተኛው ቀን ማለትም በ02/06/08 ዓ.ም ክዋኔው ጉሪያ ስላልነበረውና ስለተላመድኩኝ ለቀረፃ ፈቀዱልኝ፡፡ የጠረጋውን ቀን ሙሉ ክዋኔ ተሳትፏዊ ምልከታ በማድረግ በመስክ ረዳቴ አጋዥነት በቪዲዮና በምስል ጭምር መረጃዎችን ሰበሰብኩ፡፡

በዚሁ ቀበሌ ቀርሱ በሚባል ጎጥ የምትኖር እዚህ ክዋኔ ቤት ተጠርታ የመጣች ተሳታፊ በዚሁ ቀን (ረቡዕ ማታ) ገፈራ እንደምታደርግ ሰማሁ፡፡ እኔም ፍቃደኝነቷን ጠይቄ ከፎቶ ግራፍና ከቪዲዮ ውጭ በድምፅና በተሳትፏዊ ምልከታ ብቻ መረጃ እንድወስድ ፈቀደችልኝ፡፡ ከዚያም ወደ ምትኖርበት ቀርሱ ጎጥ ቅርብ ስለነበር ከሰአት አብረን ሄድን፡፡ ቅድመ ዝግጅቱ ባለመጠናቀቁ የነበረውን በተሳትፏዊ ምልከታ ተከታትየ ረቡዕ ማታ በ02/06/08 ዓ.ም የነበረውን የሙሉ ሌሊት ክዋኔ በተሳትፏ ምልከታና በድምፅ ቀረፃ ብቻ መረጃየን ሰበሰብኩኝ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሁለተኛውን ቀን መረጃዎችን በቃለመጠይቅና በቡድን ውይይት በማጠናከርና ሁኔታዎች በመከታተል አሳለፍኩ፡፡ የሦስተኛውንም ቀን (04/06/08ዓ.ም) ክዋኔ በተሳትፏዊ ምልከታ አማካይነት መረጃ ሰበሰብኩ፡፡

ሦስተኛውን የመስክ ምልከታ ለማካሄድ በ 05/06/08 ዓ.ም ጉዞየን የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ምልከታ ላደረኩበት ለቤሬና ቀርሱ ጎጥ ወደሚቀርበው ቁኖ በመባል ወደሚጠራው 018 ቀበሌ አደረኩ፡፡ ለ 1፡30 ያህል ከመስክ ረዳቴ ጋር በእግር ከተጓዝን በኋላ ደረስን ፡፡ ከዚያም እንደ አጋጣሚ ሆኖ አብሮን የተማረ ጓደኛችንን ስላገኘን በሱ

በኩል ሁኔታዎች እንዲመቻቹልን አደረግን፡፡ ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋርም አገናኝቶን ለምን እንደመጣሁ ዓላማየንና ምን እንደምፈልግ ነገርኳቸው፡፡ እነሱም በዚሁ ቀበሌ 5 ኪ.ሜ አካባቢ ራቅ ብሎ ወደሚገኘው ዋዚ በመባል የሚጠራ ጎጥ ገፈራ መኖሩን ጠቆሙኝ፡፡ እዚያም የመስክ ረዳቴ የሚያውቃቸው ሰዎች ስለነበሩ እዚያ በማደር ዓላማየን አስረደኋቸው፡፡ በ 07/06/08 ዓ.ም እና በ14/06/08 ዓ.ም ሁለት ገፈራ እንዳለ ጠቆሙኝ፡፡ በማግስቱ እሁድ በ 06/06/08 ዓ.ም ከነዚሁ ሰዎች ጋር በመሆን ወደ ገፈራ አድራጊዎቹ ቤት ፍቃደኝነታቸውን ለመጠየቅ ሄድን፡፡ አስተዋውቀውኝም ዓላማየን ካስረዳኋቸው በኋላ ሁለቱም ገፈራ አድራጊዎች ከማንኛውም አይነት ቀረፃ ውጭ በምልከታ መረጃ ማግኘት ፈቀዱልኝ፡፡ ከዚያም የገፈራው ዕለት ሰኞ 07/06/08 ዓ.ም ጠዋት በመገኘት የጫት ጀባታ ሰጥቼ ከቅድመ ዝግጅቱ እስከ ጠረጋው ቀን ድረስ ያለውን ክንውን በተሳትፏዊ ምልከታ ተከታተልኩ፡፡ በሁለተኛ ቀን ላይ ከቀድሞው ክዋኔ የተለዩ መረጃዎችንና አንዳንድ ጥያቄዎችን በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ማሟላት ችያለሁ፡

በ10/06/08 ዓ.ም ወደ ወረዳው ከተማ ቢስቲማ ለጀባታ ጫት መግዣ ስላነሰኝ ከባንክ ለማውጣት ተመለስኩኝ፡፡ ዘመዶቼ ጋር በማደርም በ13/06/08 ዓ.ም ተመልሼ ወደ ዋዚ ሄድኩ፡፡ በፊት ካደርኩባቸው የመስክ ረዳቴ ዘመዶች ቤት አደርኩ፡፡ ሰኞ በ14/06/08 ዓ.ም ገፈራ ወደሚደረግበት ቤት በመሄድ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ጠረጋ ቀን ያለውን ሙሉ ክዋኔውን በተሳትፏዊ ምልከታ ተከታተልኩ፡፡ የተለዩ መረጃዎችንና አንዳንድ ጥያቄዎችን በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አሟላሁ፡፡

በ16/06/08 ዓ.ም ከሰአት በኋላ ከመስክ ረዳቴ ጋር በመሆን ከ 2፡30 የእግር ጉዞ በኋላ ወደ ቢስቲማ ከተማ ዘመዶቼ ዘንድ ተመለስን፡፡ ዘመዶቼም ለጥናት ከመረጥኳቸው ቀበሌዎች አንዱ ወደሆነው 01 ቀበሌ (ሃራ) ከሚያውቋቸው ሰዎች ጋር ስልክ በመደወል ጉዳየን አስረድተው በአደራ ጭምር እንዲቀበሉን ነገሯቸው፡፡ ከዚያም ሀሙስ በ 17/06/08 ዓ.ም በመኪና ሃራ ሄድን ከ 45 ደቂቃ በኋላ ደርሰን ሰዎቹ ተቀብለውን አደርን፡፡ ስለሄድኩበት ጉዳይ ዘመዶቼም ነግረዋቸው ስለነበር እኔም በተጨማሪ ሳስረዳቸው ገፈራ የሚደረግበትን ቤት አጣርተው ሰኞ ቸሪት በተባለ ጎጥ እንደሚካሄድ ጠቆሙኝ፡፡ በ20/06/08 ዓ.ም እሁድ ጠዋት ብዙም ልዩ ቦታው ቸሪት ወደሚባለው ጎጥ ከተቀበሉኝ ሰዎችና ከመስክ ረዳቴ ጋር ሄድን፡፡ከዚያ በፊት ዓላማየን አስረድቼ

የሄድኩባቸውን ገፈራ ቤቶችና የቀረፅኳቸውንም መረጃዎች በማሳየት እንዲተባበሩኝ ፍቃደኝነታቸውን ጠየኩኝ፡፡ እነርሱም ማንኛውንም ነገር መቅረፅ እንደማልችል ነገር ግን አብሬ በመሳተፍና በማየት ብቻ መረጃውን መውሰድ እንደምችል ገለፁልኝ፡፡

ቦታው ቅርብ ስለነበር የተቀበሉኝ ሰዎች ቤት አድሬ ሰኞ በ 21/06/08 ዓ.ም ጠዋት ከመስክ ረዳቴ ጋር በመሆን ወደ ቸሪት ጎጥ ሄድን፡፡ ከገፈራ ቤቱም እንደደረስን ጫት በጀባታ ለባለጉዝጓዟ ጀባሁ (ሰጠሁ) ፡፡ በተፈቀደልኝ መሰረት ሙሉ ቀን ቅድመ ዝግጅቱን አንዳንድ ስራዎችን በማገዝ ተከታተልኩ፡፡ ከማታ እስከ ንጋት ያለውንም ክዋኔ በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ ሰበሰብኩኝ፡፡ በሁለተኛው ቀን ያለውን ሁኔታ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት መረጃዎቼን እያጠናከርኩኝ እዚያው አሳለፍኩኝ፡፡ የሦስተኛውን ቀንም (የጠረጋውን ክዋኔ) በ23/06/08 ዓ.ም በተሳትፏዊ ምልከታ ተከታተልኩ፡፡

ለስድስተኛው ምልከታየ ከሰአት በኂላ ከዚሁ ቀበሌ (ሀራ) በመኪና ከመስክ ረዳቴ ጋር ለሀይቅ ወደምትቀርበው 02 ቀበሌ ቡልቡሎ ተመለስን፡፡ እዚህ ቀበሌ ከ 30 ደቂቃ በኂላ ደርሰን ከዘመዶቼ ቤት አደርን፡፡ በዘመዶቼ ረዳትነት ገፈራ የሚያደርጉ ሰዎች ቤት መኖሩን ስናጣራ በዚህ ሁለት ሳምንት ውስጥ እንደማላገኝ ነገርግን በሚቀጥለው ወር(መጋቢት) ዱሬ የተባለ ጎጥ ውስጥ አንድ ቤት እንደሚኖር ጠቆሙኝ፡፡ በጥቆማው መሰረት ገፈራ አድራጊዎቹ ቤት ሄደን ዓላማየን አስረድቼና ቀረፃዎቼን አሳይቼ መቼ እንደሚደረግና ለመረጃ እንዲተባበሩኝ ፍቃደኝነታቸውን ጠየኩ፡፡ እነሱም ገና ቀኑን እንዳልወሰኑና በሚያደርጉ ጊዜ ለዘመዶቼ እንደሚነግሯቸውና ከቀረፃ ውጭ የገፈራ ስርአቱን መከታታል እንድችል ፈቀዱልኝ፡፡

አምስቱን የመስክ ምልከታ አጠናቅቄና ስድስተኛውን ተነጋግሬ በ26/06/08 ደሴ ተመልሼ ቤተሰቦቼ ጋር አደርኩ፡፡ ከዚያም ከሁለት ቀን በኂላ ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ ከአማካሪየ ጋር ስለ መስክ ቆይታየ ተነጋገርን፡፡ በመቀጠልም ትንተናየን በመስራት ላይ እያለሁ መጋቢት 12 /2008 ዓ.ም ቡልቡሎ ቀበሌ በ21/07/08 ዘመዶቼ ቀድሜ ነግሬያቸው የነበረው ገፈራ እንደሚደረግ ነገሩኝ፡፡

ስድስተኛውን ምልከታየን ለማካሄድ በ15/07/08 ዓ.ም በድጋሜ ከአዲስ አበባ ወደ ደሴ ሄድኩ፡፡ ከዚያም  ከመስክ ረዳቴ ጋር በ19/07/08 ዓ.ም ለሀይቅ ወደ ምትቀርበው 02

ቀበሌ ቡልቡሎ ደርሰን ከዘመዶች ቤት አደርን፡፡ ገፈራ የሚደረግበት አካባቢ ለነበርንበት አሰለል ጎጥ ቅርብ ስለነበር ማክሰኞ ከመስክ ረዳቴና ከዘመዶቼ ጋር በመሆን ወደ ዱሬ ጎጥ ገፈራ አድራጊዎቹ ቤት በመሄድ በድጋሚ ዓላማየን አስረድቼና ቀረፃዎቼን አሳይቼ እንዲተባበሩኝ ፍቃደኝነታቸውን ጠየኩ፡፡ ነገር ግን ከምልከታ ወጭ ለፎቶም ሆነ ለቪዲዮ ቀረፃ ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ ዘመዶቼ ቤት በማደር በማግስቱ ረቡዕ ጠዋት በ21/07/08 ዓ.ም በገፈራ ቤቱ በመገኘት ጫት ለባለጉዝጓዟ ጀባታ ሰጠሁ፡፡ ከዚያም ከቅድመ ዝግጅቱ ጀምሮ እስከ ጠረጋው ቀን ያለውን ክዋኔ በተሳትፏዊ ምልከታ ተከታተልኩ፡፡ በሁለተኛው ቀንና በ22/07/08 ዓ.ም ከጠረጋው ቀን በኋላ በክዋኔዎቹ ላይ ጥያቄ የሆኑብኝ ጉዳዮችና አንዳንድ ጥያቄዎችን በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት መረጃዎቼን አሟልቻለሁ፡፡

ስድስተኛውን ምልከታ ካጠናቀኩኝ በኋላ ወዲያው ሳልመለስ መረጃዎቼን ለማሟላት በ23/07/08 በዚሁ ቀበሌ አደርኩ፡፡ የመረጃ ትንተና ሳካሂድ ጥያቄ የሆኑብኝን ሀሳቦች ደግሞ ከ24 እስከ 28 ባሉት ቀናት በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት አሟላሁ፡፡ ከዚያም በ29/07/08 ዓ.ም የመስክ ተግባሬን አጠናቅቄ ከወረባቦ ወረዳ ተመለስኩ፡፡

### 1.9.2 በመስክ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

ለጥናቱ በተመረጡት የወረባቦ ወረዳ በስድስት ገፈራ ቤቶች ባካሄድኩት የመስክ ቆይታ መረጃዎችን ለማግኘት ሁኔታዎች ሁሉ አልጋ ባልጋ አልነበሩም፡፡ ይኸውም በቪዲዮና በፎቶ ምስል ክዋኔውን ሙሉ ለሙሉ ለማሳየት እንዳልችል ያደረጉኝ አንዳንድ ችግሮች ነበሩ፡፡ የመጀመሪያውና ዋነኛው ችግር ከላይ በተጠቀሱት የገፈራ አድራጊዎቹ ለቀረፃ ፍቃደኛ አለመሆን ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት የጥናቱ አላማ ለትምህርት ግብአትነት ብቻ መሆኑን በማስረዳት እና ቀረፃ በፈቀዱልኝ የመጀመሪያ ቤት ያደረጉትን ቀረፃ በማሳየት እንዲተባበሩኝ ጠይቃለሁ ነገር ግን ሁለተኛው ቤት ብቻ ለድምፅ ቀረፃው ፍቃደኛ ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ለሁለቱም ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡

ሌላው ደግሞ በወረዳው የገጠር ቀበሌዎች መብራት አለመኖሩ ለጥናቴ መሳካት እንቅፋት ሆኖብኛል፡፡ ይኸውም የገፈራ የመጀመሪያው ቀን ክዋኔ ማታ የሚካሄድ በመሆኑ ጉሪያ ካለበት ሀድራ ውጭ ያሉትን ክዋኔዎች ለቪድዮ ቀረፃ ፍቃደኛ በሆነው ቤት ቀረፃ ለማካሄድ ጨለማው አስቸጋሪ ነበር፡፡ ይህን ችግር መስክ ከመውጣቴ በፊት መብራት አለመኖሩን አውቅ ስለነበር በፀሀይ ብርሀን የሚሰራ ባውዛ ገዝቼ ነበር፡፡ ነገር

ግን ከዋኞቹ በዕድሜ የገፉ ስለነበሩ ብርሀኑ አይናችንን ይጣላናል በማለት እንዲቀነስ ስለተደረገ እንብዛም አይታይም። ይህን ችግር ለማስወገድ የወሰድኩት መፍትሄ እምድጃው ላይ እሳቱን በደንብ እንዲነድ ማድረግ ነበር። ቢሆንም በመቅረጫ መሳሪያው መታየት አልቻለም።

እንዲሁም ክዋኔው ሌሊቱን  መሆኑ የዕንቅልፍ ጊዜየን ስላዛባው ለማንጋት ተቸግሬ ነበር። ይህን ችግር ቡና አብዝቼ በመጠጣትና ጫት በመቃም ልወጣው ችያለሁ። በመሆኑም ሙሉውን ክዋኔ በምልከታ ተከታትያለሁ። በተጨማሪም በመጀመሪያው ጉዞ ወቅት በቡልቡሎ ቀበሌ ያካሄድኩት ቆይታ አለመሳካት ነው። እንዲሁም በየቀበሌዎቹ ላሉት ጎጦች የትራንስፖርት አገልግሎት ባለመኖሩ በእግር ለመሄድ አስቸጋሪ ሆኖብኝ ነበር። ይህንንም ችግር ጉዞየን ጠዋትና ከሰአት በኂላ ማለትም ፀሀይ ቀዝቀዝ ሲል በማድረግ ድካም እንዲቀንስልኝ አድርጊያለሁ።

## 1.10. የጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ[5]

ወረባቦ ወረዳ በምስራቅ አማራ ደቡብ ወሎ ዞን የሚገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ ተነስቶ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ባለው መስመር ከደሴ 47 ኪ.ሜና ከሃይቅ ከተማ በስተምስራቅ በኩል 17 ኪ.ሜ ገባ ብሎ ይገኛል። ወረዳውን በምስራቅ አፋር ክልል(ጭፍራ ወረዳ)፣ በምዕራብ ተሁለደሬ ወረዳ፣ በሰሜን ሀብሩ ወረዳ(ሰሜን ወሎ)፣ በደቡብ ባቲ ወረዳ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ያዋስኑታል። የወረዳው ዋና ከተማ ቢስቲማ ስትሆን ከአዲስ አበባ 447 ከ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ወረዳው የከተማ ሁለት ቀበሌዎችን ማለትም ቢስቲማ እና ቦከክሳ ቀበሌን እና የገጠር 20 ቀበሌዎችን ያካትታል። እነሱም ሀራ(01)፣ ቡልቡሎ(02)፣ደየ(03)፣ዱበታ(04)፣ ፊቶ (05)፣ ጉቢሳ(06)፣ ገደሮ(07)፣ አዳሜ(08)፣ ጎሀ(09)፣ገረባቦ(10)፣ ጭቅሌ(11)፣ጫሊ(12)፣ ቦከክሳ ዙሪያ(13)፣ ገዲዳ(14)፣ አረባቲ(15)፣ኡላኡላ(16)፣ ሀደሬ(17)፣ ቁኖ(18)፣ ገንደባሽ(19)፣ ኤጀርሳ(20) በመባል ይታወቃሉ። የወረዳው የመሬት አቀማመጥ ሁኔታ 24% ሜዳማ፣ 49% ወጣ ገባ ፣ 26%ተራራማ እና 1% %ሸለቆ ነው።

---

[5] ከህዝብ ቁጥሩ ውጭ ሌሎቹ መረጃዎች ከወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ “የወረባቦ ወረዳ አጠቃላይ ገፅታ በ2007 ዓ.ም” ከሚለው ሰነድ የተገኙ ናቸው።

የወረዳው የአየር ንብረት ሁኔታ ደግሞ ቆላ 56 %፣ ወይናደጋ 40 %፣ደጋ 4% ሲሆን ከባህር ጠለል በታች ከፍታው 1000-2800ሜ ነው፡፡ አማካይ የዝናብ መጠን 700-1000 ሚ/ሜ ፣ አመታዊ የሙቀት መጠን 18C ዝቅተኛ እና 35C ከፍተኛ መሆኑ ታውቋል፡፡

የወረዳው ህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታውን ስንመለከት 97% የሚሆኑት በጥምር ግብርና የሚተዳደሩ ሲሆን በተጨማሪ በአነስተኛ የንግድ ስራዎች 5% ፣ በዕደጥበብ 1% ፣ በጉልበት ስራ 3% የሚተዳደሩም አሉ፡፡ ወረዳው የሚታወቅባቸው ምርቶች ውስጥ ጫት፣ ቡና፣ ከፍራፍሬ ዘይቶኒ፣ ብርቱካን፣ ሙዝ ፣ ፓፓያ፣ ማንጎ፣ አቮካዶ እንዲሁም አገዳ እህሎች (በተለይ ሸንኮራ አገዳና ማሽላ) በብዕር እህሎች እና አትክልት ይጠቀሳሉ፡፡ የወረዳው የትምህርት ተቋማት ብዛት መደበኛ ትምህርት ቤት (1-8) 54 ፣ መደበኛ ከፍተኛ ደረጃ ት/ቤት(9-10) አንድ፣ መሰናዶ ት/ቤት(9-12) አንድ አሉ፡፡

በወረዳው የሚገኙ ሌሎች ተቋማት ደግሞ ጤና ጣቢያ 5፣ ጤና ኬላ 20፣ የግል ክልሊክ 9፣ የእንስሳት ህክምና ጣቢያ 9፣ የግል መድሀኒት ቤት 5፣የገበሬዎች ማሰልጠኛ ጣቢያ 20፣ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበር 47 እና ሌሎች ማህበራት 39 ናቸው፡፡

በ2007 ዓ.ም የተካሄደው የወረዳው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ እንደሚያመለክተው ወረዳው በገጠር ወንድ 47,173፣ ሴት 46,631 እንዲሁም በከተማ ወንድ 3,286 ሴት 3,440 ሲሆኑ በአጠቃላይ በወረዳው ወንድ 50,459 ሴት ደግሞ 50,071 ህዝብ ይኖርበታል፡፡ የወረዳው ህዝብ ብዛት 100,530 ነው፡፡፡ የማህበረሰቡ ሀይማኖት 99% እስልምና ሲሆን 1% ክርስትና ነው፡፡ በወረዳው የሚነገሩ ቋንቋዎች 95% አማርኛ እና 5 % ኦሮምኛ ናቸው፡፡ (Federal Democratic Republic of Ethiopia Population Consus Commission, 2010, 3)

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

ይህ ምዕራፍ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስራዎች የተቃኙበትና የንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የቀረበበት ነው፡፡

### 2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ለቺሳ (በ1982 ዓ.ም.) በጨሊያ አውራጃ ስለ ውቃቢ ያለው እምነትና የእምነቱ መገለጫ ግጥሞች "በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ት/ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያነት ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ ስለውቃቢ ምንነት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የጨሊያ አውራጃ ነዋሪዎች ስለውቃቢ ያላቸውን አመለካከትና እምነት ስርዓት የሚገልፅ ሲሆን የእምነቱ መገለጫ በሆኑት የቃል ግጥሞች ላይ ትንተና አድርጓል፡፡ ጥናቱ ግጥሞቹን በመገኛ ቋንቋቸው ማለትም በኦሮምኛ ቋንቋ ሰብስቦ ወደ አማርኛ በመተርጎም ከቅርፅና ከይዘት አንፃር ቃኝቷል፡፡ ጥናቱ ያነሳው ጉዳይ አንድ የመንፈስ አይነት የሆነውን ውቃቤን ቢሆንም የመንፈሱ መገለጫ የሆኑት ቃል ግጥሞች መገኛ ስለሆነው ክዋኔ አያነሳም፡፡ እንዲሁም ስለዛር ምንነትና ተያያዥ ጉዳዮች የሰጠው ማብራሪያ የለም፡፡

መኮንን (1982 ዓ.ም.) "የአቴቴ ፊጨሳ ክዋኔና ስነ-ቃላዊ ግጥሞች በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ" በሚል ያቀረበው ጥናት ደግሞ የአማራና የኦሮሞዎች የመንፈስ አምልኮ ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተሞከረበት ነው፡፡ ትኩረት ያደረገውም "የአቴቴ ፊጨሳ (የሴት ውቃቢ) ብቻ ላይ ነው፡፡ አጥኚው አቴቴ የአንድ ሴት መንፈስ መጠሪያ እንደሆነና መንፈሿም አቴቴ ሀራ፣ አቴቴ ግቢቢ፣ አቴቴ ዱላ፣ አቴቴ ጉራጌ እየተባለች በተለያየ አካባቢ እንደምትጠራ ገልጿል፡፡ ይህ ጥናት አቴቴ የሴት ዛር መጠሪያ መሆኑን ቢስማማበትም ለማሳየት የሚሞክረው የወንድ መንፈስ ውቃቢዎችን ጨምሮ መሆኑን ከትንተናው መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ጥናቱ አንድም ዛርንና ውቃቤን ተተኪ ስሞች አድርጎ የተጠቀመ ሲሆን ለሴት ዛር መጠሪያ ነው ያለውን ስያሜ(አቴቴ) በትንተናው ለወንድ መንፈስም ተገልግሎበታል፡፡ በመሆኑም የሀሳብ መዛነፍ ይታይበታል፡፡

በወልዱ (1991 ዓ.ም.) “የዛር ትያትራዊ ክንውን ሲሚዩቲክስ ትንተና” በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት የውቃቢ፣ የአዶ ከበሬና የዛር ስርዓት ክንውን አንድነትና ልዩነት በመጠኑ የተገለፀበት ነው፡፡ የቀጨኔው “ሻንቆ” ዛር ስርዓተ ክንውን አጠቃላይ ዕይታ በሚል የስርአቱ የፍርድ ክዋኔ ላይ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡በሶስተኛው ምዕራፍ የቀረበው የዛር “ሲዩሚዩቲክ ትንተና” ሲሆን ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ የለውም፡፡ በጥናቱ ላይ ዛርና ውቃቢ የተለያዩ መሆናቸውን ለማሳየት ሞክሯል፡፡

ታደገኝ (1992 ዓ.ም.) በመንዝ (ላሎ ማማ ምድር ወረዳ) የሚገኙ ውቃቢዎች ልዩ ልዩ ገፅታዎችና የፍርድ ክዋኔ “በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት በውቃቤዎች አመጣጥና መጠሪያ ስማቸው ላይ ያተኮረ ትንተና ሰጥቷል፡፡  ውቃቢዎችና የውቃቢ ዓይነቶች በሚል ርዕስ መጤ እና ተወላጅ፣ እስላምና ክርስቲያን በማለት ከመለያ ባህሪያቸው ጋር በአይነቶቻቸው ለማሳየት የሞከረበት ሲሆን የውቃቢ (የዛር) ክዋኔ በሚል ዝርዝር ትያትራዊ ክዋኔ አቅርቧል፡፡ የዚህ ጥናት ከሌሎች ለየት የሚያደርገው ትኩረቱን ያደረገው በክድመት አይነቶችና በፍርድ ክዋኔ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ክዋኔን ማሳየቱ ቢያመሳስለውም የክዋኔው ትንተና ከጥንቆላና ከስነ-ልቦና አቀራረብ አንፃር  የተተነተነ እና ዛርና ውቃቢን ተተኪ ስሞች አድርጎ መጠቀሙ ያለያየዋል፡፡

በየውልሰው (1992 ዓ.ም.) “አዋቂና የጥንቆላ ስራው በደብረ-ማርቆስ አካባቢ” በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ስለአዋቂ ምንነት ስለ ዛር ምልመላና ስለጥንቆላ ስራ የክዋኔ ሂደት የዛር መቀበያ፣ የፍርድ ቀን እና የዛር መሸኛ የተሰኙ ሶስት የክዋኔ ደረጃዎች እንዳሉት ገልጿል፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ግጥሞች የክዋኔውን ሂደት ተከትለው እንደሚዜሙና ዛር ቶሎ እንዲወርድ የሚለምኑ ብሎም የአስጠንቋዮችን ችግር የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን በመግለፅ ጥናቱ ተጠናቅቋል፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ስለ ዛር የክዋኔ ደረጃዎች በሚያትተው ክፍሉ የዛር መቀበያና መሸኛ በሚል ባነሳቸው አንዳንድ ሀሳቦች ብቻ ነው፡፡ ስለጥንቆላ እና ስለዛር ፍርድ የሚያትተው የጥናቱ ዋና ዓላማም ሆነ በርዕሰ ጉዳዩ የተለያየ ነው፡፡

በእንዳልካቸው (1993 ዓ.ም.) “በምዕራብ ሀረጌ (ጨርጨር) አካባቢ የአወሊያ ቤት የልመና ግጥሞች የይዘት ትንተና በሚል የቀረበው ጥናት ደግሞ ዋና ትኩረቱ የአውሊያ ቤት የልመና ግጥሞችን ይዘት መተንተን ነው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር

የሚመሳሰለው የልመና ክዋኔውን በተወሰነ መልኩ ለማሳየት በመሞከሩና የመገልገያ ቁሶችን ትዕምርት ስለሚገልፅ ነው፡፡ ጥናቱ የአውሊያ ቤት የልመና ግጥሞች ይዘት በተለያዩ ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍሎ ተተንትኗል፡፡ የአውሊያ ቤት የልመና ግጥሞች የአውሊያን ጥንካሬ፣ ትሁትነት፣ ፈጥኖ ደራሽነትና ሁሉን አዋቂነት የሚገልፁ መሆናቸው በማጠቃለያ ሀሳብነት በማቅረብ ተጠናቅቋል፡፡ አውሊያና ዛርን እንደ አንድ የመንፈስ መጠሪያ አድርጎ በተተኪነት መጠቀምን እንደክፍተት አይቸዋለሁ፡፡

በተመስገን (1995 ዓ.ም.) “የዛር ትውፊት እና በውስጡ የሚገኙ ቴአትራዊ አላባውያን በራያና ቆቦ አካባቢ” በሚል ርዕስ በትያትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የቀረበው ጥናት “የዛር ትውፊታዊ ክንውን ትያትራዊ (ድራማዊ ይዘት)” የተተነተነበት ነው፡፡ ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ክዋኔን ባሳየበት ክፍል የሚመሳሰል ቢሆንም ዋና ዓላማው “ትያትርን እና የዛር ትውፊታዊ ክዋኔን በማዛመድ በዛር ትውፊታዊ ክዋኔ ውስጥ የሚገኙ ተውኔታዊ አላባዎችን ነቅሶ ማውጣት እና የሁለቱን የዝምድና ባህሪያት መተንተን/መመልከት” በመሆኑ ይለያያል፡፡ ትንተናውም ትኩረቱን ያደረገው የዛር ክዋኔን ከትያትር ጋር በማነፃፀር ተውኔታዊ አላባዎቹን ለይቶ ማሳየት ላይ እንጂ ፎክሎራዊ ገፅታን ማሳየት አይደለም፡፡

“የዛር ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ በወግዲ ወረዳ” በሚል ርዕስ እንድሪስ (1997 ዓ.ም.) የወግዲ ወረዳ የዛር ልዩ ልዩ መጠሪያዎችና አይነቶች በሚል ርዕስ ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ (ህዝበ ቃየ) የመንፈሶቹ የወል መጠሪያ ናቸው ያላቸውን ስያሜዎች በመጥቀስ መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸው ቀርቧል፡፡ ሴት ዛርና ወንድ ዛር፣ ተወላጅና መጤ ዛሮች፣ ክርስቲያንና እስላም ዛሮች በማለት ቃለ መጠይቆች ተጠቅሰው ተብራርተዋል፡፡የዛር መንፈስ መቀበያ ዘፈን ግጥሞችና ክዋኔ፣ የዛር ንግስ ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ፣ የዛር ሽኝት ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ በሚሉ አብይ የጥናቱ ጉዳዮች ያተኮረ ፅሁፍ ትንተና ቀርቦበታል፡፡ ይህ ጥናት ክዋኔን በተወሰነ መልኩም ቢሆን መዳሰሱ ከዚህ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡

በሲሳይ (1999 ዓ.ም.) የቀረበው ጥናት “የቢሾፍቱ ከተማ ዛር ግጥሞች” በሚል ርዕስ የተካሄደ ጥናት ሲሆን ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የዛር ግጥሞችን ከነክዋኔያቸው ማሳየት በሚል ነው፡፡ ይህ ጥናት የስነ-ቃልና ዛር ምንነት እና ታሪካዊ አመጣጥ የተገለፀበት ሲሆን ዛርና ውቃቢን አንድ መጠሪያ አድርጎ የመጠቀም ችግር ይስተዋልበታል፡፡ እንዲሁም ምንም አይነት ክዋኔን የሚያሳይ የፎቶ ማስረጃ አላቀረበም፡

፡ ሌላው በዚህ ጥናት የታየው ክፍተት ትንተናው በቀጥታ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችን ብቻ መሠረት ያደረገ ነው ለምን ይህ እንደሆነ ግን አይገልፅም።

በ Erku (1966 ዓ.ም.) "The Zar cult as an out let to express suppressed feeling and its impact on Ethiopian personality" በሚል ያቀረበው ጥናት የዛር እምነት ምክንያቶች፣ የዛር እምነት ጥቅም፣ የዛር መንፈሳዊ አምልኮ ከህብረተሰቡ ጋር ባለው ውህደትና ጥብቅ ትስስር፣ በሰዎች ሰብዕና ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ ዙሪያ ያተኮረ ነው። በተለይም ዛር የሚመለከው በሴቶች ብቻ እንደሆነ ጠቅሷል። ይህን አስመልክቶ ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ማህበረሰቡ ለሴቶች ያለውን ዝቅተኛ ግምትና ሴቶችም ባላቸው የተገዥነት ስሜት የእምነቱ ተከታዮች ሊሆኑ እንደቻሉ ነው። ጥናቱ ስለ መንፈሱ ክዋኔና ቃል ግጥሞች ያለው ነገር ባለመኖሩ ከዚህ ጥናት ጋር ብዙ አይቀራረብም።

ደረጀ (1988 ዓ.ም.) ባዕድ አምልኮ በሃይማኖት ጥላ ስር በሚል ርዕስ ያዘጋጀው መፅሀፍ "የዛር መንፈስ አሠራር በኢትዮጵያ"፣ "በነፃ የተገኘ ፈውስ" እንዲሁም "የአሩሲዋ እመቤት" የሚሉ ዋና ዋና ምዕራፎች አሉት። መፅሀፉ ስለ ውቃቢ፣ ዛርና አውሊያ ቢያነሳም በእምነቱ ስርዓቶች መካከል ያሉ ተመሳስሎችና ልዩነቶችን አልተመለከተም፣ የተነሱትን የመንፈስ አይነቶች ክዋኔንም አልገለፀም። በዚህ ፈንታ በርካታ መንፈሶች መኖራቸውን "ጠቋር"፣ "ግራኝ"፣ "አዶከበሬ"፣ "ጨሌ" ፣ "አቴቴ" ፣ "ሰልካይ"፣ "ወልይ" እና "አውሊያ" ወዘተ በማለት ጠቁሟል። እዚህ ላይ ሌላው እንደ ክፍተት ያየሁት ጨሌ ተብሎ በተተኪነት የቀረበው መንፈስ ሳይሆን የመንፈስ ማምለኪያ የሆነና በተለያዩ ቀለማት ያጌጠ ስንደድ እንደሆነ ከሰጠው ገለጻ መገንዘብ ይቻላል።

Fuller E.Torry. "The Zar Cult in Ethiopia" በሚል ርዕስ ያቀረቡት አጭር ጥናታዊ ፅሁፍ የውቃቢን፣ የዛርን እና የአወሊያን ምንነት ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ አብራርቷል። ይኸውም ከዛር ጋር የሚመሳሰሉ በተለያዩ ስሞች የሚጠሩ ሌሎች መንፈሶች መኖራቸውን በመጠቆም ከእነዚህም መካከል ውቃቢ፣ አቦ (ዶ) ከብሬ፣ ጥንቆላና አወሊያ ላይ ትንተናው ያተኩራሉ። ከዛር ጋር ያላቸው ግንኙነት እጅግ ውስብስብ መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን ለዚህ በምክንያትንት የጠቀሱት ደግሞ በተለያዩ ቦታዎች በሰፊው

የተለያየ ትርጓሜ ስለሚሰጣቸው መሆኑን ነው፡፡ ለምሳሌ ውቃቢ የዛር ቤተሰብ ነው ይባላል ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

Timkehet *"ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ [Yagarun sardo Bagaru Bare] Zar Spirit possession Among the Amhara And the Role of Music*" በሚል ርዕስ ያቀረበችው አጭር ፅሁፍ ደግሞ ያተኮረው የዛር መንፈስ ክዋኔ ላይ የሚሰሙ ግጥሞች ሙዚቃዊ የኖታ (ምት) ላይ ነው ፡፡ ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስለዛር ምንነትና ክዋኔ ባነሳቸው ነጥቦች ነው፡፡ ጥናቱ የዛር ከበራ አድራጊዎችን ወይም በተለምዶ "የዛር ፈረስ" ተብለው የሚጠሩ ሰዎች በአማራ ክልል የተለያዩ ስያሜዎች ያላቸው መሆኑን ባለዛር፣ ባለውቃቤ፣ ባለቆሌ፣ ባለ አውሊያ የሚሉትን ስሞች በመጥቀስ ያብራራል፡፡ ትንተናውም "ባለዛር" የሚለውን ስያሜ በመጠቀም የተደረገ ነው፡ ፡ ይህ ጥናት በአንድ ሰፊ ክልል ውስጥ ያሉ የተለያዩ የመንፈስ ከበራዎችን በተወሰነ ክልል (በተለይም በጎንደር) ዕይታ ብቻ ሁሉንም ክልሎች ያካተተ ትንተና እና ማጠቃለያም ይሰጣል፡፡ ጥናቱ የተለያዩ መንፈሶችን በአንድ መጠሪያ ተመሳሳይ አድርጎ የመጥራቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘሁትም፡፡

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

ይህ ክፍል ለዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በመሆን የሚያገለግለውን የክዋኔ ንድፈ ሀሳብን /performance theory/ እና ከዚህ ንድፈ ሀሳብ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ፅንሰ ሀሳቦች (concepts) ላይ ማብራሪያ የተሰጠበት ነው፡፡

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በማዕቀፍነት የተመረጠበት ምክንያት የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የገፊራ ስርዓቱን አጠቃላይ ክዋኔ ማሳየት በመሆኑ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዳ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ደግሞ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡

### 2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ

የክዋኔን ንድፈ ሀሳብ አስመልክተው የሚሰጡ ማብራሪያዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተቃኙ ናቸው፡፡ የአንዳንዶቹ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ክዋኔው የተከሰተበትን አጋጣሚና የአከዋወኑን ጥበባዊነት ደረጃ ይመለከታል፡፡ በዚህ አይነቱ አመለካከት የውበት ጉዳይ ግድ የሚለው ነው፡፡ ከክዋኔው ውስጥም ክዋኔው የቀረበበትን ቋንቋ ግልጽነት፣ የንግግሩን ሂደትና የከዋኞቹን ስልት በትኩረት ይመለከታል፡፡ በዚህ ዓይነቱ አተያይ

ጥናቱ መደረግ ያለበት ከባህሉ፣ ከቋንቋው በወጡ ሰዎች ነው፡፡ ስለሆነም ውስጥ አዋቂ አጥኚ ያስፈልገዋል፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ከክዋኔው አስቀድመው የተሰበሰቡ ጥሬ ነገሮች በሙሉ ጥበብ አልባ እንደሆኑ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ማንኛውም ክዋኔ በከዋኙ ብቃት ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ በሚከሰተው እያንዳንዱ ክስተት ላይ ከዋኙ ሁኔታዎችን እየተመለከተ የመለዋወጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ እነዚህ ሁኔታዎችም መቼቱንና ታዳሚውን እየተመለከተ እንዲቀበሉ ትወናውን የማመቻቸት ኃላፊነቱን የሚያመላክቱ ናቸው፡፡ ፎክሎር ትዕምርታዊ እንደመሆኑ፣ ከባህል ጋር እንደመታሰሩ ከተግባር ጋር የተያያዘና የሰውን ባህሪ እንደማሳየቱ መጠን እነዚህን ነጥቦች በትኩረት ማየት እንደሚያስፈልግ (Bauman, 1982, 2) ያስረዳሉ፡፡

የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ የአሜሪካዊያን የፎክሎር እና የነገረ-ሰብ ባለሙያዎች ያደረጉት እንቅስቃሴ ሲሆን የምዕራባዊያንን ሜታፊዚካል አስተሳሰብ በመቃወም የተነሳ ነው፡፡ በዋነኛነት ትርጉምን አንድ ማዕከል በመፍጠር ከእርሱ አንፃር መፈከር እንዲሁም ምንጩን በግለሰብ ደረጃ መወሰንን፣ ተጨባጭ በሚባል ቴክስትና አውድ ላይ መመስረትን በመቃወም በቋንቋና በማህበረሰባዊ ህይወት ላይ በማተኮር ማዕከልን ማፍረስ እና በሌላ አተያይ ትርጉምን መፈከር ላይ ትኩረት አድርጎ መነሳቱን (Bauman እና ሌሎችም፣ 1990፣ 61) ገልጸዋል፡፡

ይህን ንድፈ ሀሳብ ለፎክሎር ባለሙያዎች በማስተዋወቅ ደረጃ መስራት ችሏል በመባል በቀዳሚነት የሚጠቀሱት Richard Bauman ናቸው (Sims እና Stephen፣ 2005፣ 128) ፡፡ አቀራረቡ መሰረት ያደረጋቸው በርካታ እሳቤዎች ሲኖሩ ከእነዚህ መካከልም ፎክሎር ተግባራዊ የሚሆነው በተከሰተበት ጊዜ ባለው ክዋኔ ወይም ተግባቦት እንጂ በቴክስቱ ብቻ መሆን የለበትም፣ ሁሉም ተግባር/ሁነት መመዝገብ ይኖርበታል፤ ምዝገባው አድካሚ ቢሆንም ገላጭ የሆኑ መረጃዎችንም መጨመር ያስፈልጋል የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

> The folklore concepts apply not to a text but to an event in time in which a tradition is performed or communicated. Hence the whole performance or communicative act must be recorded. However, recording "events" often amounted to little more than taking extradirt from around the root wad. (Hufford, 1995, 528)

አቀራረቡ ቃላዊ ጥበብ ላይ ትርጉም ሲሰጥ ቢታይም በክዋኔ ወቅት አገልግሎት ላይ የሚውሉ ቁሶችና ከእነሱ ጋር ያለው ግንኙነት እንዲሁም ባህሪን፣ አመለካከትን እና ድርጊትን ጨምሮ ለመቃኘት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም መንፈሳዊ፣ ቁሳዊ እና ቃላዊ ባህሪያቱንም ጥናቱ ይመለከታቸዋል፡፡ አጥኚውም የተፈፀመውን ተግባርና ተግባቦት መነሻ አድርጎ በሰላና በነቃ መንፈስ ምልከታውን የተለያዩ መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም መከታተል ይጀምራል፡፡ ለሁሉም እኩል ዕድል በመስጠት በዋነኛነት ግቡ የሆነውን ከዘወትራዊ ህይወት ውጭ የሚመጣውን ተፅዕኖ ለማግኘት በሚያስችለው መልኩ ጥያቄውን ይጠይቃል፡፡ በዙሪያው ያሉ ቁሳቁሶች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች እና ምልክቶች ምን ግንኙነት አላቸው? በትርጉም ላይስ የሚያመጡት ለውጥ አለ? ብሎ ለማየት ያስችለዋል፡፡ ወደ አውዱ በማተኮርም ምዕራባዊያን እንደ ተጨባጭና ያልተበረዙ አድርገው የሚወስዱትንና ቴክስት የት ይጀምራል? አውዱስ መቼ ይገባል? ብለው ለሚያነሱት ጥያቄ ለሁለቱም እኩል ዕድል በመስጠት ራሳቸውን የሚገልፁበትን ሌላ ስያሜ በመስጠት ያጠኑበታል፡፡ ለቴክስት (entextualization) ፣ ለአውዱ ደግሞ /contextualization/ የሚል አቻ መጠሪያ በመስጠት ምዕራባውያን ለውጤት ትኩረት ሰጥተው የሰሩበትን መንገድ በመቃወም እና በመተው ሂደቱ ላይ ትኩረት እንዲሰጥበት አድርገዋል፡፡ (Richard Bauman, 1990, 68)

ባህሉን ለመተርጎምም ከዋኝ ተኮር የሆነውን አቀራረብ ብቻ ሳይሆን ተደራሲንም በማካተት ሁለቱንም እንደ አንድ ትርጉም አስገኝ በመጠቀም በሂደቱ ላይ የነበረውን የሁለቱን ግንኙነት መሰረት በማድረግ ጥያቄዎችን ያነሳል፡፡ ሂደቱ ተግባቦታዊ በመሆኑ አጥኚው ትርጉሙን የሚያመጣው ውጫዊም ሆነ ማህበራዊ አውዱ በሚመርጠው ሳይሆን በስምምነቱ ላይ በመመስረት ነው (ዝኒ ከማሁ፣ 1990፣ 62-70) ይላሉ፡፡

ሌላው የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አቅጣጫ ስነ-ሰብዓዊ (Anthropologic) የክዋኔ አጠናን አቅጣጫ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ክዋኔን የሰውን ሁለንተናዊ ባህሪ የመግለጫ መንገድ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ በዚህ አጠናን አቅጣጫ ተጠቃሽ የሆኑት ምሁር (Schechner, 1988) ናቸው፡፡ አንድ ከዋኝ ከሌሎች ከዋኞች ጋር አብሮ የመስራት ችሎታና ፈቃደኝነት ሊኖረው ይገባል፡፡ እንዲሁም ከተመልካቹ፣ ከአድማጩ በአጠቃላይ ከታዳሚው ጋር እነሱን በማሳተፍ መልኩ ቢከወን ተመራጭ ነው፡፡ ከዋኙ ሌሎች ደጋፊዎችን በመያዝ ወይም ለብቻው ታዳሚ ባለበት ወይም በሌለበት ሊከወንም ይችላል፡፡ የክዋኔ ንድፈ

ሀሳብ የአጠናን ሂደት የበለጠ ውጤታማ የሚሆነው ዘዴ በተግባር በአካል በመስኩ ላይ በመገኘት ከተጠኚው ማህበረሰብ እውነተኛ የህይወት ተሞክሮ በመቅዳትና በመተንተን ነው፡፡

በንድፈ ሀሳቡ ላይ የሚነሱት ሀሳቦች የተለያዩ እንደመሆናቸው ከክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ጋር ተያይዘው የሚነሱት የክዋኔ፣ የአውድና የቴክስት ፅንሰ ሀሳቦችም የተለያዩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ለእነዚህ ፅንሰ ሀሳቦች ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

**ክዋኔ**

ክዋኔን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ በይነውታል፡፡ (Bauman, 1992, 14) በራሱ “performance usually suggests an aesthetically marked and heighted mode of communication, formed in a special way and put on display for an audience” በማለት ክዋኔ ለየት ባለ መንገድ የሚቀርብ ጥበባዊ የተግባቦት ስልት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ክዋኔ ውበታዊ የሆነ የድርጊት ባህሪ፣ የንግግር ዘዴ፣ በአካል የሚከወን፣ በጊዜና በቦታ የተገደበ፣ በታወቀ መዋቅር በከዋኞች የሚቀርብ ከመሆኑም በተጨማሪ በተደጋጋሚ የሚፈፀም፣ በግልና በቡድን የሚዋቀር የማንነት ማሳያ እንደሆነ (Kapchan, 1995, 479) አስረድተዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ (Bronner, 1988,53) ክዋኔ የፎክሎርን ፅንሰ ሀሳብ የሚመራ ውበት ያለው ጥበባዊ ድርጊት ነው፡፡ ይኸውም የፎክሎር ጥበባዊ ድርጊት ከዋኝ፣ ቦታ፣ ተመልካች እና የክዋኔውን ሁኔታ የሚይዝ ነው በማለት አብራርተዋል፡፡

በተጨማሪም (Finnegan, 1992, 95) የክዋኔ አይነቶችን የሚከወኑበትን ሁኔታ መሠረት በማድረግ የታቀዱ፣ ያልታቀዱ፣ ሰፊ ክብረ-በዓል ላይ ያሉ፣ ከሌሎች ጋር በሚደረጉ ኢ-መደበኛ ግንኙነቶች የሚፈጠሩ በማለት በአራት ከፍለዋቸዋል፡፡ የታቀዱ ክዋኔዎች ማህበረሰቡ ያዋቀራቸው ሲሆኑ ሰፊ ክብረ-በዓል ላይ ያሉ የክዋኔ አይነቶች ደግሞ ብዙ ህዝብ በሚገኝበት ቦታ የሚካሄዱ ናቸው፡፡ ያልታቀዱ ክዋኔዎች ማህበረሰቡ ሆን ብሎ ያላዋቀራቸው ቢሆኑም ራሳቸውን ግን ለክዋኔው ዝግጁ ያደርጋሉ፡፡ ከሌሎች ጋር በሚደረጉ ኢ-መደበኛ ግንኙነቶች የሚፈጠሩ ክዋኔዎች የታቀዱ ወይም ያልታቀዱ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ከዋኔ ታስቦበትም ሆነ ሳይታሰብበት በማንኛውም አጋጣሚ ከታላላቅ (ታዋቂ) ከሆኑና ከተቀናበሩ ዝግጅቶች ጀምሮ እስከ ኢ-መደበኛ የሆኑ (በአጋጣሚ የሚፈጠሩ) ዝግጅቶች ድረስ የሚከወን መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ስለዚህ ክዋኔ እንደየባህሉ አይነት የተለያየ አቀራረብ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ከዋኔ የሚቀርብበትና የሚተረጎምበት ሁኔታ የተለያየ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው ጉዳይ ፎክሎር ያለ ክዋኔ እንደማይገለጽና ህልውና ሊኖውም እንደማይችል (Finnegan 1977,101, Rappaport, 1992, 95) ያስረዳሉ፡፡

በክዋኔ ተኮር አቀራረብ አንዱን ከዋኔ ለማጥናት/ለመረዳት የተለያዩ ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ነጥቦች ከዋኙ፣ ተደራሲው፣ ለክዋኔው የሚቀርበው ጉዳይ፣ መቸቱ፣ መልዕክቱ፣ የአቀራረብ ቅደም ተከተሉ፣ ደንቡና የአድማጩ ምላሽ ዋነኞቹ ናቸው፡፡

አንድን ክዋኔ ስንመረምር ቃላዊ ለሆኑና ቃላዊ ላልሆኑ ክዋኔዎች፣ ለመሳሪያው ቅንብር ለከዋኞቹ ድምፅና አጨዋወት ስልት፣ ለሚነሳው ርዕሰ ጉዳይ፣ ለፊት ገለፃዎች፣ ለባህላዊ ስምምነቶች፣ ለአካል እንቅስቃሴዎች (ማጨብጨብ፣ በጣት ማፏጨት… ለአልባሳት፣ ለፀጉር አሰራር፣ ለጌጣጌጥ፣ ለሙዚቃ መሳሪያዎች፣ ለሀገርኛ ትዕምርቶች፣ በአጠቃላይ ከከዋኞቹና ከታዳሚዎቹ ለሚመጡ ክዋኔዎች ሁሉ ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ (Bauman, 1992, 44) ያስረዳሉ፡፡ ይህ ደግሞ በቃል ከሚነገሩት ክዋኔዎች በተጨማሪ ቃላዊ ያልሆኑትን ማለትም እንደ ዳንስ ያሉ የሰውነት እንቅስቃሴዎች እና የፊት ገፅታዎች ያሉ ክዋኔዎች ዓላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል፡፡

በመሆኑም አንድን ክዋኔ ስንመረምር የክዋኔው አገላለፅና ጥበባዊ ተግባቦቱ መቼ፣ ከማን ጋር እና እንዴት ተከወነ የሚሉት ጥያቄዎች ይፈጠሩብናል፡፡ ስለዚህ ስለ ቴክስቱ፣ ከቴክስቱና ከአውዱ አንፃር የክዋኔውን ምንነት እና የሚያስገኘውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ከክዋኔ ፅንሰ ሀሳብ ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮች ውስጥ አውድ፣ ከዋኝና ታዳሚ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እነዚህን በዝርዝር እንመልከት፡፡

### አውድ

በርካታ ምሁራን ስለ አውድ የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ አውድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ከክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚነሳ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ አንድን ክዋኔ ስንመረምር አውድን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት፡፡ ይህም በሰዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶችንና ባህላዊ ስምምነቶችን ለመረዳት ያስችላል፡፡ (Finnegan, 1992, 88) በመሆኑም አውድ

በቴክስት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም (Dundes, 1986, 4)

> The structure of performance events is a product of the interplay of numerous situational factors, including physical setting, participant's identities and roles, cultural ground rules for performance, norms of interaction and interpret ation, and the sequence of actions, making up the conventional scenario of the event itself as a cultural scene.

በማለት አውድ የአንድን ክዋኔ አካላዊ መቼት፣ የተሳታፊዎቹ ማንነትና በክዋኔው ውስጥ የሚኖራቸውን ሚና፣ የድርጊት ቅደም ተከተል፣ ክዋኔውን የሚገዙት የተለያዩ ህግጋት እና በከዋኙና በታዳሚዎቹ መካከል ያለውን ተግባቦት አጠቃሎ እንደሚይዝ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ፎክሎራዊ ክስተቶች የብዙ ሁኔታዊ አውድ ውጤቶች መሆናቸውን ነው፡፡

አውድ በከዋኙ፣ በዋናው ጉዳይ ክዋኔና በታዳሚዎች ዙሪያ ያሉትን ጉዳዮች የሚገልጽ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የአንድን ቃል ግጥም ክዋኔ ብንመለከት ለግጥሙ፣ ለገጣሚው እና ለታዳሚዎቹ እንቅስቃሴ፣ ድርጊት፣ ሁኔታ እና ሌሎችም ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡ ፡ አውድ ተኮር ምርምር ሲካሄድ ክዋኔው ከመጀመሩ በፊት ምን እናውቃለን፤ ከክዋኔ በኋላስ ምን አዲስ ነገር ተገኘ፤ ክዋኔው በሚከወንበት ወቅት የሚታዩ አካባቢያዊ ገለፃ እና በክዋኔ ጊዜ በተሳታፊዎቹና በከዋኙ መሀል ያሉ ግንኙነቶች ምን ይመስላሉ? የሚሉትን ነጥቦች ማስተዋል አለብን (Finnegan, 1992, 95) ይላሉ፡፡ ይህን ማድረጋችን ደግሞ የሚከወነውን ቴክስት ከነሙሉ ፍቹ እንድንረዳ ያስችለናል፡፡

(Bauman, 1982, 367) አውዳዊ ትንታኔን ስናደርግ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉዳዮች ብለው ያስቀመጧቸው ስድስት ነጥቦች አሉ፡፡ እነሱም የፍቺ (የትርጉም) አውድ (የሚከወነው ዋና ጉዳይ ምንድነው?)፣ ተቋማዊ አውድ (የት ይወናል?)፣ ተግባቦዊ አውድ (ከሌላ የፎክሎር አይነት ጋር እንዴት ይዛመዳል?)፣ ማህበራዊ መሰረት (ምን አይነት ሰዎችን አካቷል)፣ ግለሰባዊ አውድ (ከግለሰቡ ኑሮ ጋር እንዴ ይስማማሉ?)፣ እና ሁኔታዊ አውድ (ማህበረሰቡ በምን ሁኔታ ውስጥ ነው የሚጠቀምባቸው?) የሚሉ ናቸው፡፡

እነዚህን ክፍልፋዮች ባህላዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ በማለት በሁለት ጎራዎች መድበዋቸዋል፡፡ የኔም ጥናት የትኩረት ነጥብ የሚመሰረተው በእነዚሁ Bauman ባስቀመጣቸው ነጥቦች ላይ በመሆኑ ነጥቦቹን በአጭሩ እንመልከታቸው፡፡

**ባህላዊ አውድ**

ባህላዊ አውድ ማህበረሰቡ ባለው ባህል መሠረት ለአንድ ቴክስት፣ ድርጊት ወይም ሁኔታ የሚሰጠው አውዳዊ ፍቺ ነው፡፡ ይህም ማለት የአንድ ቡድን ግንኙነት መግባቢያ ደንብ ሆኖ የሚያገለግል ነው፡፡ አውድ ለፎክሎሩ ባህሉ የሚሰጠውን ትርጓሜ ይመለከታል፡፡ በዚህ ስርም የትርጉም አውድ፣ ተቋማዊ አውድ እና ተግባቦታዊ አውድን እንደሚይዝ (Bauman 1982:363) ይገልጻሉ፡፡

**የትርጉም አውድ** የፎክሎሩን ባህላዊ ትርጉም ለመረዳትና ለማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም ማለት ባህሉ ፎክሎራዊ ጉዳዩን የሚተረጉምበትን አንፃር ለማወቅ ያስችላል ማለት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በባህሉ ባለቤቶች በምን መልኩ እንደተወከለ፣ እንዴት እንደሚተላለፍና ምን ምን እሴቶች እንደተወከሉበት ይመረምራል፡፡ በፎክሎሩ ውስጥ የሚገኙትን የአከዋወን ስልቶች፣ መንስኤና ውጤት እንዲሁም ትምህርታዊና ዘይቤያዊ አገላለጾች እንዴት እንደተገለጹበት ትኩረት ይሰጣል፡፡ ፎክሎረኞች ባህላዊ ትርጉምን ከባህሉ ባለቤቶች በቀጥታ ቢወስዱ ጥናታቸው የተሻለና ትክክለኛ እንደሚሆን ዝኒ ከማሁ ያስረዳሉ፡፡

**ተቋማዊ አውድ** ፎክሎራዊ ጉዳዩ የት ቦታ ይከወናል? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ሲሆን ጉዳዩ የሚከወንበት ተቋም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ ወይስ ሃይማኖታዊ መሆኑን ከመመርመር ባሻገር ምን አይነት ተቋማዊ ፋይዳ ያበረክታል የሚለውን ይመለከታል፡፡ በዚህ አውድ ፎክሎራዊ ጉዳዩ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ ያለውን አውድ ይመለከታል፡፡ ይህን ሲያደርግ ተቋማቱና ፎክሎራዊ ጉዳዩ በምን እንደሚገናኙ መመርመር፣ ተቋማቱ በየትኛው ባህል ውስጥ እንደሚገኙና እንዴት እንደሚያገለግሉም ማተኮር አስፈላጊ እንደሆነ ዝኒ ከማሁ ያስረዳሉ፡፡

**ተግባቦታዊ አውድ** በክዋኔው ውስጥ በፎክሎራዊ ጉዳዮች መካከል ያለውን ዝምድና ይመለከታል፡፡ ይህም ማለት በአንድ ክብረ በዓል ወቅት ከበዓሉ ጋር ተያይዞ ልብሱ፣ ድግሱ፣ ዘፈኑ፣ ጭፈራው... አብሮ ይመጣል፡፡ ለምሳሌ፡- የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ

የሆነውን የገፈራ ከበራን ስንመለከት ስርዓቱን ራሱን ችሎ ለማጥናት ተያይዘው የሚመጡትን፡ ቃላዊ ግጥሞች ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎችና ቃል ግጥሞቹ ከገፈራው ክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ማጥናት (መዳሰስ) ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

**ማህበራዊ አውድ**

ይህ አውድ ከቤተሰብ አባላት ባልና ሚስት፣ ልጆች ጀምሮ፣ እስከ ቡድናዊ፣ ሃይማኖታዊ ቡድኖች፣ አካባቢያዊና የመሳሰሉትን ተግባቦት የሚያጠቃልል ነው፡፡ ማህበሩ (Folk group) የሚገናኙበት ነው፡፡ በመሆኑም ከዋኙ፣ ተመልካች ወይም ተሳታፊ በጋራ ይገናኙበታል፡፡ ማህበራዊ አውድ ማህበራዊ መሠረት፣ ግለሰባዊ አውድ እና ሁኔታዊ አውድ የተሰኙ ሶስት መልኮች አሉት፡፡ እነዚህን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

**ማህበራዊ መሠረት** የማህበራዊ ግንኙነት አውድ በክዋኔ ላይ ትልቅ ተፅእኖ አለው፡፡ አንድ ፎክሎራዊ ቴክስት የሚከወነው እንደ ማህበረሰቡ የስልጣን ደረጃ የክብር ተዋረድ ሊወሰን ይችላል፡፡ አንድ ቀልድ፣ ታሪክ፣ ሚስጥር ወይም ስነቃል በሚከወንበት ወቅት እንደ ማህበረሰቡ የአመለካከት ሁኔታ ይወሰናል፡፡ እያንዳንዱ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የእድሜና የስልጣን ተዋረድ አለው፡፡ ስለዚህ ይህ አውድ ትኩረቱ ከፎክሎሩ ባለቤቶች ማንነት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን አውድ ያጤናል ማለት ነው፡፡

ክዋኔ በጾታ፣ በእድሜ በቡድን ይለያያል፡፡ ስለዚህ ክዋኔውን ማህበረሰቡ የሚጋራው ቢሆንም ክዋኔው ሁሉንም ማህበረሰብ አይወስንም ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የፎክሎሩን አውድ ለመረዳት የፎክሎሩን ባለቤቶች ማንነት (ፎክ ቡድን) ማወቅ ግድ ይላል፡፡

**ግለሰባዊ አውድ** ግለሰቡ በፎክሎራዊ ጉዳዩ የሚኖረው ሚና፣ ፎክሎሩ ለግለሰቡ የሚሰጠው ፋይዳ፣ ግለሰቡ ለፎክሎሩ የሚሰጠው ትርጉም እንዲሁም ግለሰቡ ከሌሎች ግለሰቦች ጋር በመዋቀር ቡድን የመሰረተበትን አውድ ያጠናል፡፡

**ሁኔታዊ አውድ** አንድ ፎክሎራዊ ጉዳይ የተደራጀ፣ ፍሰታዊና የተለመደ አከዋወን ወይም አውድ ሊኖር ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ድንገተኛ ለውጥ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች የሚከሰቱትም ከፎክሎራዊ ጉዳዩ፣ ካለው ነባራዊ ሁኔታ፣ ለመከወን ከምንጠቀምበት ስልት እና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ፎክሎራዊ የቃልግጥም ቴክስት ለመከወን እንደየ ማህበረሰቡ የአኗኗር ሁኔታ፣ ባህልና አካባቢ ሁኔታ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡

ቴክስቱም ሲከወን በከዋኙና በተሳታፊዎቹ መካከል እንዲሁም በተመልካቹ መካከል ባለው ማህበራዊ አውድ ይወሰናል፡፡

አጥኚው ሁኔታዊ አውድን ለማግኘት ራሱንም ሆነ ቡድኑን መጠየቅ ያለበት እየተከናወነ ያለው የፎክሎር ቅንጣት አሁን ባለው ሁኔታ ውስጥ ምን ማለት ነው? ብሎ በመጠየቅ ለቡድኑ ተግባቦት እንዴት እንደሚውል ማጣራት ላይ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች እንደምንረዳው አንድን ክዋኔ ለመከወን የራሱ የሆነ አውድ እንደሚያስፈልገው ነው፡፡ በአውድ ውስጥ የሚገኙት እንደ ተሳታፊ፣ ከዋኝ፣ መቼት ያሉት ደግሞ ለእያንዳንዱ ክዋኔ የራሳቸው አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

**ከዋኝ**

ክዋኔ አንድ ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ያለውን ነገር የሚገልጽ ነው፡፡ በዚህ ባለው ነገር ላይ በመመርኮዝም የከዋኞቹን ሚና ምን እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከዋኞቹ ያደጉበትን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ በማሳየት በአቀራረቡ ነፍስ ይዘሩበታል፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክተው (Bauman, 1992, 44) “The performer assumes responsibility to an audience for a display of communicative skill and effectiveness of the performer’s accomplishment.” ይህም በክዋኔው ወቅት ከዋኞቹ ክዋኔውን የተሳካ ከማድረግም በተጨማሪ ታዳሚዎችን የማግባባት ኃላፊነት አለባቸው ተብሎ እንደሚታሰብ ይገልጻሉ፡፡

(Finnegan, 1992, 90-91) ከዋኞች ከፍተኛ አድናቆት የተሰጣቸው፣ ከታዳሚው የተለየ ተሳትፎ የሌላቸው እና በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያሉ ናቸው በማለት በሶስት ከፍለዋቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ (Bauman, 1992, 48) ክዋኔ በሚከወንበት ጊዜ ለከዋኞቹ ድርጊት፣ ለሚከውኑበት እቃ እና ለሚያሳዩት ሚና ከተመለከትነው ክዋኔ በመነሳት ትርጉም የምንሰጥበት ነው ይላሉ፡፡ ይህም የሚያመለክተው በክዋኔ ውስጥ ለአጠቃላይ የከዋኞቹ ሁኔታ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

ከዋኞቹ የሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችን የሚከውኗቸው ክዋኔዎች ማንነታቸውን በመግለጽ ረገድ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ (Bronner, 1988, 53)፡፡ ስለሆነም ከዋኞች ለክዋኔ ያላቸው ስሜትና ተሳትፎ እስከምን ድረስ እንደሆነ፤

የሚጠበቅባቸውን ሚና በተገቢው መልኩ እየተወጡ እንደሆነና ክዋኔውን እየከወኑ ወይም ከመከወናቸው በፊት የፈጠራ ችሎታቸው ምን ያህል እንደነበር መጤን አለበት፡፡

አንድ ክዋኔ ሲከወን የታዳሚዎቹ ሁኔታ ቴክስቱ ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ሁሉ የከዋኞቹ ማንነትም በታዳሚዎቹ ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል (Dundes, 1986, 28):: ስለዚህ አንድ የፎክሎር ምርምር ሲደረግ የከዋኞች እድሜ፣ ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ልምድ፣ ብቃትና ተቀባይነት ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

የክዋኔን ዋና ቦታ የሚይዘው ከዋኙ ነው፡፡ ምክንያቱም የከዋኙ ሚና የሌሎችንም ሰዎች ቀልብ ስለሚስብ ነው፡፡ ስለዚህ ቀዳሚው ከዋኙ ሲሆን ሁለተኞቹ ደግሞ ታዳሚዎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተሳታፊዎች ተሳትፎ ላቅ ያለ ሲሆን ተሳታፊዎቹን ከከዋኞቹ መለየት በጣም ያስቸግራል፡፡ ይህም ከከዋኙ ቀጥሎ ትልቁን ቦታ የሚይዘው ተሳታፊው እንደሆነ ያመለክታል፡፡

### ታዳሚ

ከአውድና ከከዋኝ በመቀጠል ክዋኔ ሲነሳ ተያይዞ የሚመጣው ጉዳይ ታዳሚ ነው፡፡ አንድ ክዋኔ ሲከወን በአጋጣሚ ወይም ደግሞ ሆን ተብሎ የሚገኙ ሰዎች ታዳሚዎች ይባላሉ፡ ፡ እነዚህም ሰዎች ክዋኔው ላይ ወይም በቀጣይነት ይሳተፋሉ፤ አልያም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ይቆያሉ፡፡ ክዋኔን ያለ ተሳታፊ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም የተሳታፊዎቹ ሁኔታ በራሱ ክዋኔውን ማስቀጠል ስለሚችል ነው፡፡

አንድ ክዋኔ በሚከወን ጊዜ ክዋኔው ለሚካሄድበት መቼት፣ ለተሳታፊዎቹ ባህሪያትና ምላሽ ትኩረት መስጠት ያሻል፡፡ ይህ ደግሞ አዲስ አቅጣጫን ያስጨብጣል፡፡ በመቼቱና በተሳታፊው መካከል ያለው ግንኙነት እንደ ተሳታፊዎቹ እድሜ፣ ጾታና ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል፡፡ ተሳታፊዎቹ በራሳቸው መንገድ ክዋኔውን ሊረዱት ይገባል፡፡ ከክዋኔ በኋላ ታዳሚው የሚሰጠው ምላሽ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ከሆነ አድናቆቱን አልያም ስሜቱን እየገለጸ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የፎክሎር ጥናት ተመራማሪ ታዳሚዎቹ በክዋኔው ተሳታፊ መሆናቸው፣ ተሳትፎአቸው እንዴት እንደነበርና ወደ ክዋኔው ከመግባታቸው በፊት ከነበራቸው ሁኔታ እንዴት ሊነጠሉና በክዋኔው ሊመሰጡ እንደቻሉ መመርመር አለበት፡፡

(Finnegan, 1992, 91-92) በክዋኔ ጊዜ በከዋኝና በታዳሚ መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነት አለ፡፡ ታዳሚዎች መደበኛ የሆነ ድርሻ የላቸውም፡፡ ስሜታቸው እንዳዘዛቸው ምላሽ ይሰጣሉ፤ የማይሳተፉም አሉ፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን የራሳቸውን ተጽዕኖ ያሳድራሉ፤ በማለት የታዳሚዎች ምላሽ መስጠትም ሆነ አለመስጠት በክዋኔው ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም በክዋኔ ውስጥ ታዳሚዎቹ ለሚያሳዩት ማንኛውም እንቅስቃሴ ትኩረት መስጠት ያሻል፡፡

**ቴክስት**

ቴክስት የሚለው ቃል ከፅሁፋዊ እሳቤው ባሻገር ቁሳዊ ነገሮችን እንደሚያመለክት እና ቃላትን፣ ቁሶችን፣ ሀሳብን እና ባህሪን የሚጠቁም መሆኑን (Sim እና Stephen፣ 2005, 19) ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም ክዋኔ፣ ቃላዊ ትርክቶች እና ሃይማኖታዊ ክብረ-በዓላትም ቴክስት መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ጥናትም በዋናነት ትኩረት የሚደረግባቸው ቴክስቶች “የገፈራ ክዋኔ”፣ በገፈራው ክዋኔ ወቅት የሚባሉ ቃል ግጥሞች፣ “የክዋኔው ተሳታፊዎች የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁስና አልባሳት፣ ምግቦች፣ ድርጊቶች… ናቸው፡፡

**ከበራ**

ስለ ከበራ ምንነት የተለያዩ ምሁራን ተመሳሳይ አንድምታ ያላቸው የተለያዩ ምላሾችን ሰጥተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Sims እና Stephen (2005፣95) ሲገልጹ በማህበረሰቡ ዘንድ ተደጋጋሚ (repeated) ሆኖ የሚከበር፣ የተለመደ ድርጊት የሚስተዋልበትና ዘወትር ከምንከውናቸው ልማዶች የተለየ ዓላማ ያለው መሆኑን ሲገልጹና፤ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ያለውን ቦታ ሲያስረዱን፤ ከበራ አንድ ልዩ ትውፊት አይነት ሆኖ ፎክለሪስቶች ሲያጠኑት ግን የተለያየ ምድብ ውስጥ ያስገቡታል፡፡ ከበራዎች የሚደጋገሙ ቢሆኑም ከልማድ የበለጠ አላማ ያላቸውና የተደራጁ ሲሆኑ አልፎ አልፎ የአንድን ቡድን አባላት ያስተዋውቃሉ፡፡ ብዙዎቹ ከበራዎች በአንድ ላይ ሲሆኑ የተለያዩ የፎክሎር አይነቶችን ይፈጥራሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ ቃላዊ ግጥሞች፣ዜማዎችና እንጉርጉሮዎች ያሉ ቃላዊ ፎክሎሮችን፣ እንደ የአካል እንቅስቃሴ፣ውዝዋዜ ያሉ ልማዳዊ ፎክለሮችን እና እንደ ምግብ፣መፅሀፍት፣ሽልማቶች፣ልብሶች ያሉ ቁሳዊ ፎክሎሮችን እንደሚይዙ ምሁራን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

> A ritual is a particular type of tradition that many folklorists study as a distnict category of folklore. Rituals are repeated, habitual actions, but they are more purpesful than custom, rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore. Verbal, such as chants, recitations, poems or songs, customary such as gestures, dance or movements, and material, such as food, books, awards, clothing. (Sims እና Stephen፣2005፣104)

በሌላ በኩል ደግሞ እንደ Rappaport (1992፣157) አገላለጽ ከበራ ከአብዛኞቹ የመግባቢያ አይነቶች አንዱ ሲሆን ለሌሎች (በቋንቋ ጭምር ለማይገለጹት) ተግባቦቶች መነሻ የሆነ፤ ግልጽ የሆነ ቅርጽ ያለው፤ የተለያዩ ገጽታዎችና ባህሪያት ያሉት ከመሆኑም በላይ እነዚህ ባህሪያቶቹ አነሰም በዛም እርስ በእርስ የተያያዙ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ እያንዳንዱ ማህበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ በዝግጅትና በጉጉት የሚጠብቃቸው ከበራዎች አሉት፡፡ እነዚህ ከበራዎች ደግሞ ወቅታዊ፣ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ በሚል የሚታወቁ ናቸው፡፡ (Sims እና Stephen፣ 2005፣102-105) እንደሚያስረዱት ከበራዎች ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውና እና ከሃይማኖታዊ ይዘት ውጭ መሆናቸውን ይገልጹና አንዳንዶቹ ከበራዎች ደግሞ ሁለቱንም የሚይዙ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አብዛኞቹ ከበራዎች ሲከበሩ በተመሳሳይ ጊዜ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን በአንድ አጠቃላይ ይዘው ይመጣሉ፡፡ ለምሳሌ፡-የዚህ ጥናት ትኩረት አቅጣጫ የሆነውን የገፈራ ስርዓተ ክዋኔን ስንመለከት ከበራውን ራሱን ችሎ ለማጥናት ተያይዘው የሚመጡትን ቃላዊ ግጥሞች፣ ልዩ ልዩ ቁሳዊ ባህሎችና ቃል ግጥሞቹ ክዋኔ ጋር ተያይዞ የሚመጡ እንቅስቃሴዎችን ማጥናት (መዳሰስ) ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ (Sims እና Stephens፣ 2005፣95) እንደሚከተለው ገልጸውታል፡

> Rituals are frequently highly organized and controlled, often meant to indicate or announce membership in a group. Most rituals bring together many types of folklore: verbal, such as chants, recitations, poems or songs; customary, such as gestures, dance or movements; and material, such as food, books, awards, clothing and consumes….

አንድ ፎክለሪስት አውዱን መነሻ በማድረግ በሚያጠናበት ወቅት ይዘትን መግለጽ ባቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉ ቁሳቁሶች፣ ጌጣጌጦች፣ ስዕሎች፣ ምልክቶች እርስ በርስ ምን

ግንኙነት አላቸው? በትርጉሙስ ላይ የሚያመጡት ነገር አለ?" በሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ መመስረት እንዳለበት (Finnegan ፣1992፣86) ገልጸዋል።

ከበራ በተግባር የሚገለፅ አንድ የፎክሎር ዘርፍ ነው። በከበራዎች ላይ እያንዳንዱ የፎክሎር ዘርፍ ሊስተዋል ይችላል። ከበራ በስነ ቃሎች፣ በቁሶችና በተለያዩ ልማዶች ታጅቦ ይከናወናል። ይህ ከበራም ፎክቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች የሚያውቁትና የሚተገብሩት የራሱ ስርዓት እንዳለው (Sims እና Stephen፣2005፣158) ገልጸዋል።

አንድ ህብረተሰብ በህይወቱ ውስጥ ተደጋግመው ለሚደረጉ ከበራዎች መነሻ ምንነት የሚያምንበትን ነገር ወይም ሃይማኖቱን ይጠራል። ከሃይማኖቱ ጋር አጣምሮ ይመለከታቸዋል። ህብረተሰቡ ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ጭንቀቱን፣ ብሶቱን፣ ማንነቱንና ሌሎችንም ለመግለጽ ከበራዎችን እንደ አጋጣሚ ይጠቀማቸዋል። በህይወቱ ውስጥ የሚጠቀምባቸውንና የሚመራባቸውን እሴቶችና ተምሳሌቶችን መግለጫ አድርጎም ይወስዳቸዋል።

## የከበራ ባህሪያት

ከበራዎች በምንም ምክንያት ይከበሩ ክዋኔ አላቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘም የክዋኔና የከበራ ትስስርን በተመለከተ ከበራ ከሌለ ክዋኔ እንደማይኖርና ክዋኔ በራሱ ግልጽ የሆነ መልዕክት ያለው ድርጊት መሆኑ መገለጫው እንደሆነ (Rappaport, 1992, 25) "…There is no performance, there is no ritual, performance it self is an aspect of that which is performed the medium is a part of the message, more precisely, it is a meta message about what ever is encoded in the ritual." በማለት ያስቀምጣሉ። በመሆኑም ከበራ በየትኛውም ህብረተሰብ ይከወን አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ባህሪያት ይስተዋሉበታል (Salmon፣ 2004፣321) ።

1. መዋቅራዊነት፡- ይህ የከበራ ባህሪ የከበራው ክዋኔ ከተጀመረበት አንስቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የሚያልፍባቸውን ደንቦችና አደረጃጀቶች የሚመለከት ነው። የትኛውም ከበራ በምንም ምክንያት ቢከበር የራሱ የሆነ የሚከተለው መዋቅርና ደንብ አለው። እያዳንዱ የከበራ እንቅስቃሴም የከበራው ባለቤት ባበጀውና በሚመራበት ደንብ መሰረት ይመራል።

2. ቅደም ተከተላዊነት፡- ይህ ባህሪ በክዋኔ ወቅት የሚቀርቡ ድርጊቶች ወይም ሁነቶች የሚከወኑበትን ቅደም ተከተል የሚያሳይ ነው፡፡ በከበራ ወቅት ቀድሞ የሚመጣ ቀጥሎ የሚመጣ መጨረሻ የሚመጣ እየተባለ ክዋኔዎች በእለፍ ተቀደም ይቀርባሉ፡፡ በመዋቅር ያሉ ደንቦች የተለመዱ በመሆናቸው ሳይዛነፍ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ይቀርባሉ፡፡
3. ተደጋጋሚነት፡- ይህ ባህሪ የጊዜንና የጉዳዩን ድግግሞሽ የሚያሳይ ነው፡፡ ከበራዎች በሳምንት በወር ወይም በአመት ተደጋግመው ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ከበራ ላይ የሚታዩ ክዋኔዎች ያ ከበራ ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜም ተደጋግመው የሚቀርቡ ናቸው፡፡
4. ታዳሚ፡- ከበራ ለመከበር ወይም ለመከወን ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን የግድ ታዳሚም ያስፈልገዋል፡፡ በመሆኑም በአድማጭና ተመልካች ፊት ይከወናል፡፡
5. ውጤት፡- ይህ ደግሞ ከበራ ለባለቤቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ከበራው ከተከናወነ በኂላ ለከዋኙ ህብረተሰብ ስነ-ልቦናም ሆነ ሌላ የሚሰጠው ፋይዳ ወይም ውጤት ይኖረዋል፡፡
6. ቅዱሳዊነት፡- አብዛኞቹ ከበራዎች በሚያከብራቸው ማህበረሰብ ዘንድ ቅድስናን ወይም ንፁህነትን ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ ማህበረሰብ ከበራዎችን በማድረጉ ከርክሰት እንደሚፀዳ ይሰማዋል፡፡ አንዳንዴም ካለበት ዝቅ ያለ ደረጃ ከፍ ወዳለ ደረጃ የመሸጋገሪያ መገለጫዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡

የገፈራ ክዋኔንም ብንመለከት እነዚህ ባህሪያት ይስተዋሉበታል፡፡ የገፈራ ስነ-ስርዓት የራሱ የሆነ የሚመራበት መዋቅራዊ አካሄድ አለው፡፡ ይህ መዋቅር በክዋኔው የሚሳተፉ ሰዎች ቦታ ከመኖር ይጀምራል፡፡ እያንዳንዱ በገፈራ ክዋኔ ላይ የሚገኝ ሰው እኩል ሚና የለውም፤ ደረጃውም የተለያየ ነው፡፡ በገፈራ ላይ የሚከወኑ ክዋኔዎች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የሚፈሱ ናቸው፡፡ ምናልባትም ያ ቅደም ተከተል ቢዛነፍ ገፈራው ተቀባይነትና ትክክለኛነት አይኖረውም ተብሎ ይታሰባል፡፡ የገፈራ ክዋኔ በሁለት አመት አንድ ጊዜ ተደጋግሞ ይካሄዳል፡፡ ክዋኔው በከዋኝና በታዳሚ ተሳትፎ ጎልቶ የሚወጣ ነው፡፡ የገፈራ ክዋኔው ከተደረገ በኂላ ተሳታፊዎች አንዳች ማህበራዊ ፋይዳ (የጤና፣ የኢኮኖሚ ወዘተ ) ያገኛሉ ተብሎ ይታሰባል፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የገፈራ ምንነት እና የሥርአተ-ክዋኔው ዝግጅት

### 3.1 የገፈራ ምንነት[6]

የመንፈስ ውህደት (በመንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን) ከሚገለፅባቸው ከበራዎች ውስጥ አንዱ ገፈራ መሆኑን በምዕራፍ አንድ ላይ ተቁሜያለሁ፡፡ በጥናቱ ተተኳሪ ማህበረሰብ ዘንድ ገፈራ የዛር መንፈስ የተዋሀዳቸው ሰዎች ስነ-ልቦናዊ ወይም መንፈሳዊ ንፅህና ፣ የአዕምሮ እርካታ ፣ የመዳን ተስፋን ፣ ዕድገትና ብልፅግና ፣ ወዘተ ለማግኘት ሲሉ ለሰፈረባቸው የዛር አይነት የሚያቀርቡት የግብር ድግስ ነው፡፡ የገፈራን ምንነት በተመለከተ በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት ካነጋገርኳቸው  የገፈራ ተሳታፊዎች ውስጥ ወ/ሮ አሚናት አሊ(አበጋሪት) የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> ገፈራ ማለት ባለጉዝጓዟ[7] ድግስ በመደገስ ላይዋ ላይ ያሉት ዛሮች ከሚዜዎቿ ጋር ሆነው በሳቅ በጨዋታ በሀድራ በመጫወት የሚሷረፉበትና የሚደሰቱበት እንዲሁም ቀጣይ እስከ ምትገብርበት አመት ድረስ በሰላም ፣ በአፍያ እኛንም እሷንም እንዲያቆዩን የምንለማመንበት ነው፡፡ በሁለት አመቷም እንደዚሁ ግብራቸውን እንደምትሰጣቸው ቃል የምንገባበት ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣01/06/08ዓ.ም፣ቤሬ)

ስለዚህ ገፈራ ማለት የዛሮች ልዩ ልዩ ግብሮች ተሚልተው የሚቀርቡበት እና ዛር የሰፈረባቸው ሰዎች በሁለት አመት አንድ ጊዜ የሚሞሸሩበት ሲሆን ዛሮች ባለጉዝጓዚቱንና የእሷን ቤተ ዘመድ ከህመም እንዲፈውሱ፣ሀብትና ንብረታቸውን እንዲጠብቁላቸው፣ርዚቅና ሲሳይ (ረድኤትና በረከት) እንዲለግሷቸውና የወደፊት ህይወታቸውን ያማረ እንዲያደርጉላቸው የሚለመኑበት ለዛር የሚደረግ የድግስ አይነት ነው፡፡[8]

---

[6] ገፈራ ሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት "የፈረስና የበቅሎ መኖ " ሲል ፍቹን አስቀምጧል፡፡ በዚህ ጥናት አውድ ግን ገፈራ ከዚህ የተለየ ትርጉም አለው፡፡

[7] ባለ ጉዝጓዝ የምትባለው ገፈራውን ያዘጋጀችው ሴት ናት፡፡ ይህ ስያሜ ሙሽራ፣ባለጨሌና ባለጨፌ በሚሉ ስሞች ሊተካ የሚችል ሲሆን እነዚህ ስያሜዎች ለወንድ ገፈራ አድራጊም ያገለግላሉ፡፡ በአካባቢው ብዙውን ጊዜ ሲገለገሉበት የሰማሁት ባለ ጉዝጓዝ የሚለውን ነው፡፡ በመሆኑም ፅሁፌ አንድ ወጥ የቃል አጠቃቀም እንዲኖረው  ባለ ጉዝጓዝ የሚለውን ስያሜ ተጠቅሜያለሁ፡፡

[8] ከዚህ ተቀራራቢ በሆነ ሁኔታ በዋቄፌና እምነት መንፈሶች የማህበረሰቡን ማንኛውንም  ችግር እንደሚያስወግዱ አተቴ በተለያዩ የኦሮሞ ግዛቶች እየተዘዋወረች ሴቶች በሰላም እንዲወልዱ፣ ጓዳቸው እንዲሞላ፣ጤናቸው እንዲስተካከል ወዘተ ታደርጋለች፡፡ በክዋኔው ወቅትም ዝናብ እንዲዘንብ፣ከብቶች እንዲሰማሩ፣አገሩ ሰላም እንዲሆን እና ሌሎች ብዙ ችግሮች ተጠቅሰው እንዲፈቱ ልመና እንደሚደረግ  (አዲስ፣2005፣70) ገልፃለች፡፡

በመሆኑም ይህን ከበራ ለማድረግ የመጀመሪያውና ዋነኛው መስፈርት በመንፈስ የመሞላት ሂደት ነው፡፡ ስለሆነም የገፈራን ክዋኔ ከማየታችን በፊት የዛር መንፈስ እንዴት ከሰዎች ስነ-ልቦና ጋር ይዋሀዳል ወይም ዛር በሰዎች ላይ እንዴት ይሰፍራል? እና አንድ ሰው በዛር መንፈስ ቁጥጥር ስር ለመሆኑ ማረጋገጫዎቹ ምንድን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል፡፡

### 3.1.1 የዛር አሰፋፈር

አንድ ሰውን በሀይማኖትና በባህል ከተለመደውና ከተዘወተረው ማንነቱ ውጭ በመሆን የተለያዩ ድርጊቶችን እና ባህሪያትን ሲያሳይ ከራሱ በላይ በሆነ ሀይል ቁጥጥር ስር እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

እዚህ ላይ አንድ መሰረታዊና መነሳት የሚገባው ጥያቄ በመንፈስ ለመሞላት መነሻው ምንድን ነው? ወይም የዛር መንፈስ የሚመርጣቸው ሰዎች ምን አይነት ናቸው? የሚል ነው፡፡

አንድ ሰው በዛር መንፈስ ሀይል የሚሞላው በቅድሚያ በዛር መንፈስ ሲመረጥ ነው፡፡ የዛር መንፈሱም የሚመርጣቸውና የሚያርፍባቸው ሰዎች ለዛር መንፈስ የሚመቹ ወይም ተጋላጭ ሆነው ሲገኙ እንደሆነ የገፈራ ተሳታፊዎች ይገልፃሉ፡፡ (የቡድን ውይይት ፣ 02/06/08፣ቤሬ)

ይህን ሀሳብ በግልፅ ለመረዳት ደግሞ የዛር መንፈስ በሰዎች ላይ እንዴት እንደሚያርፍ እና መንፈሱ ሰዎችን ሲመርጥ የሚከተላቸውን መስፈርቶች ማንሳቱ ተገቢ ነው፡፡

በዚህ ጥናት የመስክ ቆይታ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎቹ እንደሚሉት የዛር መንፈስ በሰዎች ላይ የሚሰፍረው በተለያዩ አጋጣሚዎች የመረጣቸውን ሰዎች ሲያጭ ነው፡፡ ለምሳሌ በአካባቢው የነበረ ግብር የሚገበርለት ትልቅ ዛፍ ሲቆረጥ ፣ በጠራራ ፀሀይ አስፈሪና ሸለቋማ ውስጥ ብቻውን እያወራ የሚሄድ ሰው ሲያገኝ ፣ሲቆጣ ለምሳሌ ዛር ክፉ መንፈስ ነው ፣ገፈራ አጉል ባህል ነው በማለት በገፈራ ላይ በሚያጥላሉና በሚያሾፉ ሰዎች ላይ በመቆጣት ይሠፍራል፣ ዛር ያረፈበት ሰው ሲሞት ዛሩ እወደደው ላይ ሊሰፍር ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በገፈራ ክዋኔ ወቅት ዛር ያረፈባት(በት) ሰው ሲያጓራ(ስታጓራ) ከተሳታፊዎች ውስጥ ከባለጉዝጓዟ የበለጠ ያማረች(ረ) ሆኖ ከተገኘች(ኘ) አይቶ እወደደው ላይ ሊያርፍ ይችላል፡ ይህም የሚሆነው ተሳታፊዋ(ው)

በአለባበስ(ደማቅና ቡራቡሬ ቀለም ያላቸው ልብሶች ከለበሱ)፣ በድምፅ ፣ በፀጉር አሰራር ፣ ወዘተ ከባለጉዝጓዚቱ ወይም ከሌሎች ዛር ከሰፈረባቸው ተሳታፊዎች ቀልብ ውስጥ ሲገባ ነው፡፡

ለምሳሌ በፊቶ ቀበሌ ዘሀቡ ይማም ቤት ያነጋገርኳቸው ማሲንቆ ተጫዋች የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> እንደሰዎች ባህሪ ሁሉ የዛርም መጥፎም ጥሩም አለ፡፡ ጥሩው ዛር ሴትዮዋ ግብር ለመስጠት በቀልቧ እያሰበች እያለች ከሆነና መስጠት የማትችል ከሆነ ያቺን ሴት እርጅና ሲመጣ ዛሩ ሊተዋት ይችላል፡፡ ምክንያቱም ዛሩ ግብሩን ማቋረጥ እንዳልፈለገችና አቅም እንዳነሳት ፍላጎት ግን እንዳላትና ማድረግ እንዳልቻለች የቀልቧን ስለሚረዳ ይተዋታል፡፡ በመጨረሻ ሞት ሲመጣም ቢሆን በዘር ሳይሆን በራሱ ምርጫ እወደደው ላይ ከቤተሰብም ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ ሌላ ሰው ላይ ይሰፍራል፡፡ የወንዱም ቢሆን ያው ተመሳሳይ ነው፡፡ ለምሳሌ አቶ ሰይድ አደም አላህ ይራህማቸውና [9]ሲያርፉ የሳቸው ዛር ቤተዘመድ ላይ አልሰፈረም ፤ ማን ላይ እንዳረፈ እስካሁን አልታወቀም፤ በሮ ጠፍቷል ፡፡(ቃ.መ አቶ አደም እንድሪስ(አደም ሂዶ) ፣03/06/08፣ቀርሱ)

በአጠቃላይ ከመረጃ ሰጪዎቹ ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው የዛር መንፈስ በሰዎች ላይ የሚያርፈው በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ በመልክ፣ በአለባበስና አጋጊያጥ፣ በንፅህና እና በድምፅ በመማረክ ነው፡፡ በመሆኑም የዛር መንፈስ አንድም በጥላቻ አንድም በውዴታ(በመውደድ) በሰዎች ላይ ይሰፍራል፡፡ የዛር መንፈስ ከሰዎች ስነ ልቦና ጋር የሚዋሀድበትና የሚተላለፍበትን ምክንያት ሌሎች በውጭ ሀገራት የተሰሩ ጥናቶች ከኔ ጥናት ጋር ተቀራራቢ በሆነ መልኩ ገልፀውታል፡፡ [10]

---

[9] አላህ ይራህማቸው የሚለው ቃል የአረብኛ ቃል ሲሆን አላህ ራህመቱን ይስጣቸው ማለት ሲሆን የአማርኛ ትርጉሙም አላህ ይማራቸው (ይዘንላቸው) ማለት ነው፡፡

[10] "… In Somali land,as in other muslim lands are held to lurk in every dark and empty corner, poised and ready to strike capriciously and with out warning at the un wary passer-by. These malevolent spirits are said to be consumed by envy and agreed, and tobe particularly covetous of luxurious clothing, finery, perfume and dainty foods. They are known generally as zar." (lewis,1966,312) በማለት የዛር መንፈስ አንድም በአጋጣሚ አስፈሪ ቦታዎች ጋር የተገኘ ሰው ላይ በጥላቻ አንድም በአለባበስና በአመጋገብ፣በሽቶ ወዘተ የማረከው ሰው ላይ በውዴታ እንደሚሰፍር ይገልፃሉ፡፡

"Zar may also occasionally be transmitted to aspetator at a zar ceremony. Especially if the spectator has audacity to lough or challenge the authenticity of the possession and the ceremony. Individuals thought pensive dispositions or weak personalities but sometime the opposite is true. The victims could be attractive people or those who have qualities that generate envy." (Al-Adawi, S. እና ሌሎች ፣ 2001፣52) በማለት በዛር ከበራዎች ላይ በሚያሾፉና በሚስቁ ሰዎች ላይ በጥላቻ እና ማራኪ በሆኑ ሰዎች ላይ ዛር ሊሰፍር እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡

በሌሎች ጥናታዊ ፅሁፎች ዛር መንፈስ እርጅናንና ሞትን ተከትሎ በዘር እንደሚተላለፍ ተገልጿል፡[11] ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ተተኳሪ ማህበረሰብ ውስጥ የዛር መንፈስ በውርስም ሆነ በዘር የማይተላለፍ መሆኑን የባህሉ ባለቤቶች ይናገራሉ፡፡

### 3.1.2 የዛር መንፈስ ምልክቶች

የዛር መንፈስ በሰዎች ላይ ካረፈ በኋላ እንዲሚሉለት የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ፡፡ ይሄውም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የሰፈረበትን ሰው የቀድሞ ማንነት ይለውጣል፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በዛር መንፈስ ለመሞላቱ ወይም በዛር ቁጥጥር ስር መሆኑን ለማወቅ የግለሰቡን የቀድሞ ማንነት (ሰብዕና) ከአሁኑ ሰብዕናው ጋር ማነፃፀር አስፈላጊ ነው፡፡ በአብዛኛው የዛር መንፈስ የተዋሀዳቸው ሰዎች የማያቋርጥ ራስ ምታት፣ የምግብ ፍላጎት መቀነስ፣ስራን በአግባቡ መስራት አለመቻል እና ለሎች የህመም ስሜቶች እንደሚታዩባቸው ነጭናጫነት፣ ብቸኝነት፣በሆነው ባልሆነው መቆጣትና መሳቅ፣ የትዳር አጋርን መራቅ፣ ማጓራት፣ መፈከር፣ መዝፈንና ማንጎራጎር የሚታዩባቸው ባህርያት እንደሆኑ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

> Zar spirit possession is typically accompanied by persistent headaches, dezzinness, insomnia, lack of oppetite, loss of sense of time, unable to work, day time sleepiness and diffused pain. In some instance, the possed person may experience eepisodes of shouting, aggressive behaviour with absence words, singing, loghing and weeping with out course, and hitting the head aganistwalls; this occurrence are thought to form the core feature of 'possessive syndrome.' (Pereira፣ እና ሌሎች ፣ 1995፣ 53)

የዛር መንፈስ የተዋሀዳቸው ሰዎች ከሚያሳዩቸው ምልክቶች መካከል በወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ ቤት ከግርዶሽ ውጭ የነበረ ተሳታፊ የሚከተለውን ነግሮኛል፡፡

> ዛር የሰፈረበት ሰው ውስጡ ይሸበራል፣ፍርሀት ፍርሀት ይለዋል፣ ብዙውን ጊዜ ግሳት መብዛትና ይሄነው የማይባል ህመም ያመዋል፡፡ ቢሆንም ምች መታኝ እንጂ ዛር አረፈብኝ አይልም፡፡ እንደባህላችን ዳማከሴውን፣ጤና አዳሙን ያሽታል፡፡ ቀስ በቀስ በህልሙ ያቃዠዋል፣ ድግስ ደግስልኝ ፣ ተለማመነኝ፣ ግብር ስጠኝ፣ ደም አድማልኝ አለበለዚያ አለቅህም ፤ እገድልሀለሁ ይለዋል(ይተያየዋል)፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እንደ አቅሙ ግብር መገበሩን ይጀምራል፡፡ አብዛኞቹ ደግሞ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ከሌላ

[11] (በእንድሪስ ይማም እና በተመስገን ፋንታየ ጥናት ውስጥ ዛር በሁለት አይነት መንገድ ማለትም በዘር (በዛር ፈረስ ሚች ዘመዶች ላይ በሞት ጊዜ) እና ዛር ሲቆጣ በሰዎች ላይ እንደሚሰፍር ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ በእኔ ጥናት ተተኳሪ ማህበረሰብ ዘንድ ዛር በዘር የሚተላለፍና የሚወረስ አይደለም፡፡)

> ሰው ቤት ገፈራና መወከል ሲደረግ ያስጎራቸዋል፡፡ መውሊድና ወዳጃ ቦታ ሄደው ሀድራውን ሲሰሙ አህላቸው ተቀይሮ በድንገት ይጮሀሉ፣ተንሰቅስቀው ያለቅሳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ዛር እንደያዛቸው ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ግብሩን እንደ አቅሙ ያቀርባል፡፡ (ቃ.መ፣አቶ መሀመድ ሀሰን 09/06/08፣ዋዚ)

የዛር መንፈስ በሰዎች ላይ ከሰፈረ በኋላ በተለያዩ የሀድራ አጋጣሚዎች ላይ በድንገት በማስጮኽ፣ በማስጎራት እና አስፈሪ ህልም በማሳየት እንደሚለይ ከቃለ መጠይቁ መረዳት ይቻላል፡፡[12]

ገፈራ አድራጊዎቹ ገፈራ ከማድረጋቸው በፊት በምን ሁኔታላይ እንደነበሩና ገፈራ ለማድረግ የተነሳሱት በምን ምክንያት እንደሆነ እና ገፈራ ለስንት ጊዜ እንዳደረጉ ባነጋገርኳቸው ጊዜ ለብዙ ጊዜ ከማድረጋቸው ተነሳ አንዳንዶቹ እርግጠኛውን ማስታወስ ባይችሉም እንደሚከተለው አጫውተውኛል፡፡

በፊቶ ቀበሌ ያነጋገርኳቸው ወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ከትዳር አጋራቸው ጋር ከተፋቱ ከአምስት አመት በኋላ ባደረባቸው ህመም ምክንያት ገፈራ ማድረግ እንደጀመሩና ለ 20 አመት ያህል ገፈራ እንዳደረጉ ገልፀውልኛል፡፡ ወ/ሮ ዘሀቡ ይማም ደግሞ ከአንድ ሰላሳ አመት በፊት ወዳጃ ቤት እያሉ ሀድራው ላይ እንዳጎሩና ከዚያ በፊት እንደ እራስ ምታት፣ድካምና እንቅልፍ እንቅልፍ ይላቸው እንደነበር በመግለፅ ገፈራ ማድረግ ከጀመሩ 25 አመት ገደማ እንደሚሆናቸው ነግረውኛል፡፡ እንዲሁም በቁኖ ቀበሌ ያነጋገርኳቸው ባለ ጉዝጓዝ ወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ ከአስራ አምስት አመት በፊት ገፈራ ቤት በመሳተፍ ላይ እያሉ ዛራቸው እንደተነሳና እንዳጎሩ ከተነገራቸው በኋላ ለአስር አመት ገፈራ እንዳደረጉ ገልፀውልኛል፡፡ በዚሁ ቀበሌ ያነጋገርኳቸው ወ/ሮ ከድጃ ሁሴን ደግሞ በመውሊድ ሀድራ ላይ ይጮኹ እንደነበርና ብዙ አስፈሪ ህልሞችን ያዩና ያቀባዥራቸው እንደነበር በመግለፅ ከ30 አመት በፊት ገፈራ ማድረግ እንደጀመሩ ነግረውኛል፡፡ በተጨማሪም በሀራ ቀበሌ ያነጋገርኳቸው ባለ ጉዝጓዝ ወ/ሮ መይረማ እንድሪስ ትክክለኛ ጊዜውን ባያውቁትም ገፈራ ማድረግ ከጀመሩ ከ20 አመት እንደሚበልጣቸው እና ይሄ ነው የማይባል ህመም ያማቸው እደነበርና ሀኪም ጋር

---

[12]( Arvihurskainen, 2004,43-44)የዛር መንፈስ የሰፈረባቸው ሰዎች የድቤ ምት ዜማ ባላባቸው ከበራዎች ላይ ፣ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ድቤ ሲሰሙ እንደሚዳንሱ እና አስፈሪ ህልሞችን እንደሚያዩ የዛር መንፈስ መጋራት ምልክቶችን "Dancing in healing rituals with drum beating፣Dancing when hearing debes beat፣Terrifying dreams፣Excessive power" በማለት ጠቅሰው አብራርተዋቸዋል፡፡

ቢሄዱም የሚሰጧቸው መድሀኒት ሊያሽራቸው እንዳልቻለ አጫውተውኛል፡፡ የቡልቡሎ ቀበሌ ኗሪ የሆኑት ባለ ጉዝጓዝ ወ/ሮ አንሻ አሊ ደግሞ ለስንት አመት እንዳካሄዱ ባያውቁትም ከአርባ አመት በፊት የልብ ድካም ህመም ይሰማቸው እንደነበረና ገፈራ ማድረግ ከጀመሩ በኂላ እንደተዋቸው ገልፀውልኛል፡፡

በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ምልክቶችን በማሳየትና በማስፈራራት የታረቀኝ (የልመና ) ድግስ (ገፈራ) ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዛር መንፈስ የተያዙ ሰዎች እንደአቅመዘቸው መጠነኛ ድግስ ያደርጋሉ፡፡ ይህ የዛር መንፈስን አምኖ በመቀበል ሰላም ፣ ጤና ፣ ብልፅግና ፣ስነ-ልቦናዊ እርካታና ደስታን ለማግኘት በመሻት ለዛር የሚደረግ አነስተኛ “ የታረቀኝ ” ወይም “ የልመና ” ድግስ “ ገፈራ ” በመባል ይታወቃል፡፡

የገፈራን የድግስ ሁኔታ በተመለከተ ካነጋገርኳቸው ገፈራ አድራጊዎች(ባለ ጉዝጓዞች) መካከል ወ/ሮ አረጋሽ አህመድ እንዲህ ብለውኛል፡፡

> ገፈራ በአቅም የሚደረግ ግብር ነው፤ ማጋፈር ነው ምክንያቱም ቁጥቦቹ እንዲታረቁን በአቅማችን ቆሎውንም፣ ዳቦውንም፣ ጠላውንም፣ ቡቅሪውንም ፣ ኑጉንም ፣ ቅቤውንም ፣ ፍንዱንም፣አመንካከውን ሁሉንም አስፈላጊ ነገር የምናቀርብበትና የምናስደስትበት ነው፡፡ ጭሳጭሱን አጭሰን በሙገሳ እያነሳን እንዲታረቁን ፣ የቸገረንን እንዲሞሉልን የምንለምንበት አነስ ያለ ድግስ ነው እንጂ ላለዉማ በሰፊው መወከሉን አርዶ መወከል ነው የሚያደርገው፡፡ (ቃ.መ፣ 01/06/08፣ቤሬ)

የገፈራ ክዋኔ አላማ በሰዎች ላይ በሽታን ፣ መጥፎ የባህሪ ለውጥን፣ሰላም ማጣትን፣ ወዘተ ከሚያስከትለው መንፈስ ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት በማድረግና መንፈሱ የሚያስፈልገውን በተደጋጋሚ ግብር በማሟላት የአዕምሮ ህመምን (አደጋ ይደርስብኛል ብሎ በመፍራት ከሚመጣው የጭንቀት በሽታ) መፈወስ ነው፤እፎይታ ማግኘት ነው፡፡[13]

የዛር መንፈስን የሚያምኑ ማህበረሰቦች ለዛር ካላቸው ከፍተኛ እምነት፣ክብርና ፍራቻ የተነሳ ግብሩን ያቀርባሉ ፤ የመንፈስ እርካታንም ያገኛሉ፡፡ የጥናቱ ተተኳሪ ማህበረሰብ ለዛር መንፈስ ያላቸው አመለካከት አወንታዊ መሆኑን ባካሄድኩት የመስክ ቆይታ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ለአብነት ከወ/ሮ ከድጃ ሁሴን ቤት የተገኘውን የሚከተለው ንግግር መውሰድ ይቻላል፡፡

---

[13] Jhon Kennedy ዛር ድግስ ዓላማ በሽታን ከሚያስከትሉ መንፈሶች በመጠበቅ የአዕምሮ ህመምን በፈወስ እንደሆነ “The purpose of the zar ceremony is to cure mental illness through contact with the possessing spirits, which causes maladies. (1967፣ 190)” በማለት ገልጸዋል፡፡

ዛሮች ከሰው ልጆች ጋር አብረው የሚኖሩ ፤ የሰዎችን ችግር የሚፈቱ ፤ ጤና፣ ሰላም፣ ርዚቅ የሚሰጡ ፤ ልጅን፣ ንብረትን ፤ አጠቃላይ ቤተሰብን ፤ ጀማዐውን የሚጠብቁ ፤ ካሻቸውም የማጥፋት ሀይል ያላቸው ናቸው ፤ ነገርግን ለማንኛውም ሰው አይታዩም (አይገለጡም) ። (ቃ.መ ፤ አቶ አህመድ አሊ፣ 15/06/08፣ ዋዚ)

ቢሆንም በመስክ ቆይታየ እንደተረዳሁት የዛር እምነት ቀድሞ(ከበፊቱ) በማህበረሰቡ ዘንድ የታወቀና ስር የሰደደ በመሆኑ "የዛር አሰፋፈር" ማለትም ዛር አረፈባት(በት) የሚለው ጉዳይ ስነ-ልቦናዊ ነው የሚል እምነት አለኝ። ይህን ለማለት ያስቻለኝም በአንድ ሰው ስነ- ልቦና ውስጥ የሰረፀ ፍርሀትና ጭንቀት በኂላ ለሚተገብረው ድርጊት ወሳኝነት አለው።

በገፈራ ክዋኔ ወቅት ገፈራ አድራጊዎችም ሆኑ የሚሳተፉ ተሳታፊዎች የዛር መንፈስ መኖሩን አምነው የተቀበሉ በመሆናቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች ማለትም ከላይ በተጠቀሱት የዛር አሰፋፈር ምክንያቶች፣ በክዋኔው ወቅት ዛር የሰፈረባቸው ሰዎች አተኩረው ሲመለከቷቸው፣በተለያዩ ድርጊቶች ሲደነግጡ፣ ወዘተ ሳቢያ "ዛር ይሰፍርብናል" የሚል እምነት በውስጣቸው ይሰርፃል። ስለሆነም በውስጣቸው ይህን እሆናለሁ ብለው ስለሚያስቡ በሚተኙበት ጊዜ በህልማቸው እስከ መተያየት፤መባነን ሁሉ ሊደርሱ ይችላሉ። በተጨማሪም በመውሊድና በወዳጃ ቦታ፣በገፈራ ቤት ሲሄዱ መጮሀቸው የዛር ፅንሰ ሀሳብ በውስጣቸው በመኖሩ ነው። ስለሆነም አሿራፊዎችን በማማከር ገፈራ በማድረግ የዛር ግብር ያቀርባሉ። ስለዚህ "ባለ ጉዝጓዝ ፤ ባለጨፌ፣ ሙሽራ ፤ ባለጨሌ " በመባል ይጠራሉ፤ከሚባሉት ጎራም ይመደባሉ።

የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ከላይ እንደተገለፀው ለዛር ግብር ሲባል የሚደረግ አነስተኛ ድግስ ሲሆን የራሱ የሆነ የአከዋወን ሂደቶች አሉት። ሂደቶቹም የዛር መንፈስ በሰዎች ላይ ካረፈበት ጊዜ ጀምሮ መንፈሱ የሰፈረባቸው ሰዎች መከተል እና ማሟላት ካለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እስከ ዛር ሸኝት ያሉትን ሁኔታዎች ያካትታል። የገፈራ ክዋኔ ሂደቶች መንፈሱ የሰፈረባቸው ሰዎች ወደ መጥፎ እንዳያስገባቸው ወይም ችግር እንዳያደርስባቸው ሲሉ ለሰፈረባቸው መንፈስ እምነታቸውን የሚገልፁባቸው፣ ችግር ብሶታቸውን የሚያዋዩባቸው፣ ጤና ሰላማቸውን የሚለምኑባቸው፣ ለመንፈሱ አንሰው መገዛታቸውን የሚያሳዩባቸው፣ በሚቀጥለው ጊዜም ግብሩን አሟልተው እንደሚለማመኗቸው እና እንደሚያከብሯቸው ቃል የሚገቡባቸው ሂደቶች ናቸው።

ነገር ግን የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ከቅድመ ሁኔታዎች ውጭ በዋናነት የሦስት ተከታታይ ቀናት ክዋኔ ነው። የገፈራ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት፣ ሀድራ እና ጠረጋ በሚሉ ሦስት ሂደቶች የተከፈለ ነው። እነዚህን ሂደቶች በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ለመተንተን ሞክሬያለሁ።

### 3.1.3. የገፈራ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት

የገፈራ ስነ-ስርአት ቅድመ ዝግጅት የዛር መንፈሶች በአንድ ሰው ላይ ከሰፈሩበት ጊዜ ጀምሮ የእምነቱ ተከታዮችና ተሳታፊዎች ማሟላት የሚገባቸውን ተግባራት የሚያጠቃልል ነው። ይኸውም መንፈሱን አምኖ ከመቀበል ጀምሮ ግብሩን የመገበር ፍላጎት እንዳለ ሆኖ ግብሩ የሚቀርብበት ቀን መለየት፣ ልመና ፣የምግብና መጠጥ አይነቶች ዝግጅት፣ የቁሳቁስና አልባሳት ዝግጅት፣ የስፍራ ዝግጅትና መሰናዶን ማሟላት ናቸው።

#### 3.1.3.1. የገፈራ መከወኛ ጊዜን መለየት

ስለዚህ የገፈራ ክዋኔ ቅድመ ዝግጅት የዛር መንፈሱ መስፈሩን ከማረጋገጥና አምኖ ከመቀበል ይጀምራል። የእምነቱ ተከታዮች ከተረዱና አምነው ከተቀበሉ በኋላ ግብሩን ለመስጠት ለሚደረገው ድግስ ወቅት፣ ዕለትና ሰአት ይመርጣሉ። እንዲሁም የዛር መንፈሱ እንዲሟሉለት የሚፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ለማሟላት ለራሳቸው ከአሷራፊ ጋር በመሆን አጫጭሰው ቃል ይገባሉ። የዛር መንፈስ የሚለመንባቸውና ግብር የሚሰጥባቸው ጊዜያት እንደየ ማህበረሰቡ ይለያያሉ። በወረባቦ ወረዳ ማህበረሰብ ለገፈራ ክዋኔ የተመረጡት አጋጣሚዎች ጥር፣ የካቲት እና መጋቢት ወራት ሲሆኑ የተለዩ የመከወኛ ዕለታት ደግሞ ሰኞ ማታ ለማክሰኞ፣ ረቡዕ ማታ ለሀሙስ እና አርብ ማታ ለቅዳሜ መሆኑን አረጋግጫለሁ። ይህም በሁለት አመት አንድ ጊዜ የሚካሄድ ከበራ ነው። በሌሎች ጥናቶች ለዛር የሚደረጉ ዝግጅቶች ከእነዚህ አጋጣሚዎች በተለየ መሆኑን ባካሄድኩት ቅኝት ተረድቻለሁ።[14]

[14] በጊዜ ሰሌዳ(calander) ላይ ከተገለፁ ትልልቅ በአላት ውጭ እንደሚደረግ (እንዳልካቸው፣1993፣ 35 እና እንድሪስ፣1997፣25) ፣ በዘመን መለወጫ፣በመውሊድ፣በጥምቀት፣በቡሄ እና በመስቀል በአላት ጊዜ የዛር ዝግጅት እንደሚካሄድ (ተመስገን፣1995፣24 እና ሲሳይ፣1999፣30) ገልፀዋል። የተለየ የመከወኛ ዕለታት ማክሰኞና ሀሙስ እንደሆኑ በእንዳልካቸው ጥናት ተጠቁሟል።

ገፈራ ከወራትና ከዕለታት ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ባደረኩት ቃለ መጠይቅም እንደተረዳሁት ይህ ወቅት የተለያዩ ሰብሎች ተሰብስቦ የሚገባበት በመሆኑ ለሚካሄደው ልመና አመቺ በመሆኑና ዛሮች አዲስ ምርት የሚወዱ በመሆናቸው ነው፡፡ ለአብነት ባለጉዝጓዝ ወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> በጥር፣በየካቲትና በመጋቢት አዝመራው ሁሉ የሚሰበሰብበት፣ ሁሉ በእጀ ሁሉ በደጄ የሚሆንበት ሰአት ስለሆነ ሁሉም የጥራጥሬም ሆነ ለሎች ምርቶች እንደልብ የሚገኙት በዚህ ወቅት በመሆኑ ስንለምንም በሁሉም ቃየ አዲስ ምርት ስለማይጠፋ ሳይሰስቱ ከቡናውም፣ ከሽምብራውም ከገብሱም፣ከኑጉም፣ ሁሉ አናጣም፡፡ ያው እንደነገርኩሽ ወቅቱ ለማንኛውም ባለ ሀጃ አመቺ ስለሆነና አዝመራ ተሰብስቦ የገባበት በመሆኑ ሰው ሁሉ ብዙ ስራ ስለማይኖረው በገፈራው እለት ድካም ሳይኖረው በንቃት ይሳተፋል፡፡ ማታ ማታ የምናደርግበት ምክንያት ደግሞ ሁሉም ሰው የነፍሱን ሃጃ አጠናቆ ወደየቤቱ የሚገባበትና የሚያርፍበት በመሆኑ ቀልቡን ሰብስቦ ዱዓ እንዲያደርግ አመቺ ሰአት ስለሆነ ነው፡፡ (ቃ.መ፣08/06/08፣ዋዚ)

እንዲሁም ለገፈራ ክዋኔ የተመረጡት ዕለታት ደግሞ ከኢድ አልፈጥር፣ከአረፋና መውሊድ በአላት ውጭ ምንም አይነት ክብረ በዓል ቢኖር ገፈራ ይደረግባቸዋል፡፡ ሌሎቹ ቀናት ያልተመረጡበት ምክንያት በእስልምና ሀይማኖት ሰኞ ረቢአል አወል (ነብዩ መሀመድ(ሱ.ዐ.ወ)) የተወለዱበት[15] ስለሆነ ቀድሞ ያለው ሌሊት ማለትም እሁድ ለሰኞ ለዱአ ስለሚቀመጡ ገፈራ አይደረግም፡፡ ረቡዕ (አብዱየ ጂላሊ)፣ሀሙስ (ኸሚስ) ለአርብ ጁምአ እና ቅዳሜ (ከድር) በመባል የሚጠሩ ሲሆኑ በእነዚህ ዕለታት የአካባቢው ነዋሪዎች በየቤታቸውና በየመስጂዱ ዱአ ያደርጋሉ፡፡ ስለሆነም ዕሁድ ማታ ለሰኞ፣ ማክሰኞ ማታ ለረቡዕ እና ሀሙስ ማታ ለአርብ፣ቅዳሜ ማታ ለእሁድ ገፈራ አይደረግም፡ እንዲሁም በእስልምና ሀይማኖት በፆም ወርነቱ የሚታወቀው የረመዳን ወር በሚገባበት ማንኛውም ወር ገፈራ አይደረግም፡፡ ምክንያቱም ፆም በመሆኑ የሁለተኛውንና የሦስተኛውን ቀን ክዋኔ ያለ ምግብና መጠጥ ማካሄድ ስለማይቻል ነው፡፡ እዚህ ላይ አንዳንድ ተወያዮች በረመዳን ወር ዛርም ሆነ ጅን ስለሚታሰር ዛር አይቀሰቀስም፤እሺ አይልም በማለት ገልፀውልኛል፡፡ (ከቡድን ውይይት፣ 02/06/08 ቤሬ እና 09/06/08 ዋዚ)

ሆኖም የሀይማኖቱ መመሪያ የሆነው ቅዱስ ቁርአን ላይ የረመዳን ፆም ግዴታ እንደሆነ እና የታመመ ወይም ሩቅ መንገድ ተጓዥ የሆነ ሰው ብቻ ለዛን ጊዜ ብቻ የተፈቀደለት

---

[15] ረውደቱል አንዋር (1981፣5) ላይ ተገልጿል፡፡

ሲሆን ከረመዳን በኋላ ያልፆመባቸውን የረመዳን ቀናት ቆጥሮ መፆም እንዳለበት እንደሚከተለው ተደንግጓል፡፡[16]

> "እናንተ ያመናችሁ ሆይ ፆም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ህዝቦች) ላይ እንደተደነገገ በናንተ ላይ ተደነገገ፡፡ ልትጠነቀቁ ይከጀላልና የተወሰኑ ቀኖች (ፁሙ) ከናንተ ውስጥ በሽተኛ ወይንም በጉዞ ላይ ያለ የሆነ ሰው ከሌሎች ቀኖች የተወሰነውን መፆም አለበት…." (አል-በቀራ፣183-184)

ስለዚህ የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ሚያካሂዱ ሰዎችና ተሳታፊዎች ሁሉም የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ይህን የሀይማኖቱን ቀኖና መጣስ የለባቸውም፡፡ በመሆኑም በረመዳን ወር ገፈራ አያካሂዱም፡፡

የወረበቦ ወረዳ ለዛር መንፈስ የሚደረገው ገፈራም ከጥር ፣ የካቲት እና መጋቢት ሲሆኑ ምርት የሚገባባቸውና ፀሀያማ ወራት ናቸው፡፡[17]

### 3.1.3.2. ለገፈራ የሚደረግ የልመና ስነ-ስርአት

የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ዝግጅቶች ውስጥ የመጀመሪያው የሆነው የተለመደው የጊዜ ምርጫ መለየት ከተጠናቀቀ በኋላ የሚቀጥለው ቅድመ ዝግጅት ደግሞ ገፈራ አድራጊዎች በተናጠል የሚያካሂዱት የጥራጥሬና የርጥብ ቡና ልመና ስርአት ነው፡፡ ይህ የልመና አይነት የሚከወነው ከገፈራው ዕለት ከመድረሱ አስራ አምስት ቀን በፊት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያትም ለምግብና መጠጥ ዝግጅት ረዘም ያለ ጊዜ ስለሚያስፈልግ ነው፡፡

ለገፈራ የሚደረግ ልመና ሦስት ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ይኸውም የመጀመሪያው ልመና የሚካሄደው በአካባቢው አጠራር ከአሚን ቤት (ተጋብተው ካልተፋቱ ወይም ከመጀመሪያ

---

[16] በኩዌት የተካሄደው ጥናትም በረመዳን ወር ጅኖች ስለሚታሰሩ የዛር ከበራ እንደማይደረግና ሁሉም ሰው ወሩን በፆምና በዱአ በዱአ (በፆሎት) የሚያሳልፍ እንደሆነ "…is a ceremony which takes place in the hijri month of Shaban, which preceeds the month of 'Ramadan, as was explained elsewhere in this thesis, the jinn are believed to be imprisoned as a result of the religious practice of the people which is manifested in fasting during the day for the whole month, extra prayers during the night and also feeding poor people who might not be attended to during the year."(Ashkanani,1988,289)

[17] በተመሳሳይ መልኩ እንደ ኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር ለዛር ድግስ ምቹ የሚሆኑት ፀሀያማ ወራት እንደሆኑና እነዚህ ወራት ዝናብ የማይታይባቸውና የመሬት ገፅታ ደረቅ በመሆኑ ተመራጭ አጋጣሚ መሆናቸውን (Messing፣1958 ፣121) ይገልጻሉ፡፡ "In the Abyssinian calander, the most active period for zar activity is the 9…month dry seasons, beginning when the spirits escape from confinement of cold rains and the landscape blossoms forth. The major zar celebration occurs just before the "little rains."

የትዳር አጋራቸው ጋር በመኖር ላይ ከሚገኙ ሰዎች ቤት) ነው፡፡ የሚለመንባቸው አሚኖች ብዛት እንደ አካባቢው ሁኔታ ከሦስት እስከ አምስት ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛው እና ሦስተኛው ልመና ደግሞ በተለያዩ ቀናት የሚደረግ ሲሆን ከማንኛውም ሰው ቤት የሚካሄድ ነው፡፡ ሶስቱም ልመና ሲካሄድ በተከታታይ ቀናት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ማለትም በባለጉዝጓዞቹ ምርጫ የሚወሰን ነው፡፡ ነገር ግን ባለጉዝጓዞቹ ሀብታም ከሆኑ ሁለተኛውንና ሦስተኛውን ልመና ላያካሂዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያውን ልመና የማካሄድ ግዴታ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም ለዛሮቹ መተናነሳቸውን ማሳየት ስላለባቸው ነው፡፡ (ቃ.መ፣ከሁሉም ገፈራ አድራጊዎች በየሁለተኛው ቀን )

መጀመሪያው ልመና ካልተፋቱ ሰዎች (ከአሚኖች) ቤት የሆነበት ምክንያት እነዚህ ሰዎች በሰላምና በፍቅር ሳይለያዩ የሚኖሩ በመሆናቸው ዛሮቹ ከእነሱ የተገኘ ነገር ስለሚያስደስታቸው እንደሆነ (ቡድን ውይይት፣02/06/08፣ቤሬ፣04/06/08፣ቀርሱ፣ 09/06/08፣ዋዚ፣ 16 እና 23/07/08፣ዱሬ) ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ የልመና ሂደቱም የራሱ የሆነ ስርአት አለው፤ማለትም እንደ ባህሉ ከዋኞቹ ሊከተሏቸው የሚገቡ ደንቦችና ስርአቶች አሉት፡፡

### የገፈራ ልመና ደንቦችና ስርአቶች

- አለባበስ፡- ሴቶች ካላቸው ነጭ ቀሚስ ከነጭ ጉፍታ ጋር በመልበስ በቀኝ እጅ ጃን ጥላ ዘርግተው መያዝና ፀጉርን በሻሽ መሸፈን አለባቸው፡፡ ከሌላቸው ግን ነጭ ላይለብሱ ይችላሉ፡፡
- ካላቸው ቅቤ ሊቀቡና ሊኳኳሉ ይችላሉ፡፡
- ለእህል መያዥ የሚሆን አቅማዳ ወይም ማዳበሪያ በግራ ትካሻቸው አንግተው መያዝ፣
- ርጥብ ቅጠል፣ናትራ(አሩቲ)ና ርጥብ ሰርዶ (ጠጄ) ሳር ጃንጥላውን በያዙበት እጃቸው መያዝ
- በልመና ጊዜ ድምፅን ሳያሰሙ (በዝምታ) ከሚለምኑበት ቤት ደጅ (ቀየ) መልስ እስኪሰጣቸው ድረስ መቆም
- የሚሰድባቸውና የሚዘልፋቸው ሰው ቢያጋጥማቸው እንኳ ምንም አይነት ምላሽ አለመስጠት

- ልመናው የሚካሄደው ፀሀይ ሙሉ በሙሉ ከወጣች በኋላ እስከ ረፋድ አምስት ሰአት ድረስ መሆን አለበት
- ካላዩዋቸው እህ፣እህ (እኽ፣እኽ) በማለት ብቻ- እንዲሰሟቸው ማድረግ፡

ወንዶች ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ቅቤ ተቀብተውና ተኳኩለው የሚቀልጠው ቅቤ አይናቸው እንዳይገባ ሻሽ ግንባራቸው ላይ ያስራሉ፡፡ አለባበሳቸውም ነጭ ልብስ ካላቸው ነጭ ከሌለ ሌላ ልብስ ለብሰው ጋቢ በማጣጣል ቀጠንና ረዘም ያለ ዱላ (ቆቲ) በቀኝ እጃቸው በመያዝ አርጥብ ቅጠሉን፣ በአንዱ የፈለጉት ጆሯቸው ላይ አሩቲ ያደርጋሉ፡፡ ጃንጥላውን ዘርግተው በግራ እጃቸው እንዲሁም አቅማዳውን በግራ ትካሻቸው አግተው በመያዝ ይሄዳሉ፡፡ ከላይ ሴቶች ያሚኗቸዋል የተባሉትንም ሌሎች ስርአቶች ያሚላሉ፡፡

እነዚህን ስርአቶች አክብረው ለገፈራ ልመና የሚያደርጉበት ምክንያት ባለጉዝጓዞች ለሰፈረባቸው የዛር መንፈስ ሲሉ ከሌሎች ሰዎች አንሰው በመታየት ፣ በተለያዩ ሰዎች በመገልመጥ በሚደርስባቸው ማንኛውም በደል በመተውና በመተናነስ ዛሩን ለማስደሰትና የሚወደውን በማድረግ ተለማምኗቸውን ሙሉ ለማድረግ ነው፡፡

በዚህ ሁኔታ ሦስቱም ልመና ሲካሄድ በባለጉዝጓዞቹ ቤት በቤተሰብ፣ በቤተዘመድ ወይም በጎረቤቶች አማካኝነት ለእያንዳንዱ ልመና የሚደረግ አነስተኛ ዝግጅት አለ፡፡ ይኸውም ቤት ውስጥ ጉዝጓዝ ተጎዝጉዞ እንደኑሮ ደረጃቸው ዳቦ፣ቂጣ፣ፈንድሻ፣እንጀራ፣ ቡና እና ቆሎ በማዘጋጀት ጎረቤቶች ይጠራሉ፡፡ ባለጉዝጓዞቹ ከልመና  መልስ ምንም አይነት ድምፅ ሳያሰሙ ወደቤት ይገባሉ፤ ሰላምታ መስጠት ካስፈለጋቸውም ከአንገታቸው ብቻ ጎንበስ በማለት ይሰጡና ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያም መነጋገር ይችላሉ፡፡ ምግብ ከተበላ በኋላ ቡና ይቆላል፣ የቡና ቁርስ ዳቦ ወይም ቆሎ ቀርቦ አቦል ቡና ይቀርባል፡፡ ቡናው የሚቀዳዉ በባለ ጉዝጓዝ ሲሆን ሌሎች ስራዎች የሚሰሩት በልጅ፣በሚስት፣በባል፣ በምራት ወይም በቅርብ ዘመድ ወይም በጎረቤት ነው፡፡ እነዚህም ካዳሚ በመባል ይጠራሉ፡፡ የመጀመሪያ ቡና(አወል ቡን) ከተጠጣ በኋላ በባል ወይም በመጀመሪያ ወንድ ልጅ ጫት ጀባ ይባላል፡፡  እነዚህ ከሌሉ በሁለተኛ ወንድ ልጅ ወይም በቅርብ ዘመድ ሊሆን ይችላል፡፡ ምርቃት በሚችል ሰው ምርቃት ከተሰጠ በኋላ ቡናው ይቀዳል፤ ከቀኝ ወደ ግራ በካዳሚ አማካኝነት ታድሎ ይጠጣል፡፡

### 3.1.3.3 በብቅል ውሀ የሚደረግ ትጥበት

ተለምኖ ከተገኘው ገብስ ወይም በልመናው ገብስ ካልተገኘ የተገኘውን የማሽላ ወይም ሌላ የእህል ዘር የተወሰነውን በመሸጥ በብሩ ገብስ በመግዛት ይተካል፡፡ ከዚያም የተወሰነ ገብስ ብቅል ከተበቀለ በኋላ በትልቅ የብረት ድስት ወይም በሌላ ሰፋ ባለ ዕቃ በውሀ በማንፈቅፈቅ ሲጠል ለገላ መታጠቢያ እስኪበቃ ድረስ ውሀ በመበረዝ በብቅሉ ውሀ ገላቸውን ይታጠባሉ፡፡ይህን የሚያደርጉበት ምክንያትም የዛሮቹን ፍላጎት ለማሟላት እንደሆነ ባለጉዝጓዝ ወ/ሮ አረጋሽ አህመድ "ከአሚን በተለመነው የገብስ ውሀ መታጠባችንን ቁጥቦቹ ስለሚወዱት ነው" ብለውኛል፡፡(ቃ.መ፣01/06/08፣ቤሬ)

በብቅል ውሀ ከታጠቡ በኋላ ባህሉን ጠንቅቀዉ ከሚያውቁት ውስጥ በሚሞሸሩበት ቀን ማለትም በገፈራው ዕለት አሿራፊ የሚሆን ሰው ማለትም በቋሚነት ቅቤ በመቀባት ፣ ጨሌ በመንከርና በማጥለቅ ወዘተ የሚያገለግል ሰው ከጎረቤቶች ጋር ገፈራው ዕለት መቼ እንደሚሆን እና ጨሌው መቼ እንደሚነከር ይነጋገራሉ፡፡ ከዚያም ከአንድ ሳምንት ቀደም ተብሎ የሚያስፈልጓቸውን ሰዎች ማለትም አበጋሪቱን፣አሿራፊቱንና ሌሎች ተሳታፊዎችን ይነግራሉ፡፡ በአብዛኛው ገፈራ የሚደረገው ከልመናው አስራምስት ቀን በኋላ ሲሆን የዕለት ምርጫው ደግሞ ከላይ በገፈራ አጋጣሚ ላይ ከተጠቀሱት ዕለታት መከከል እንደ ባለጉዝጓዞቹ ፍላጎት ይወሰናል፡፡

### 3.1.3.4 የገፈራ አጠቃላይ የመጠጥ ፣ የምግብና እና የቁሳቁስ ዝግጅት

የገፍራ ክዋኔ ሁለተኛው ቅድመ ዝግጅት የሆነው ልመና ከላይ በተገለፀው ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ ለገፈራ ስርዓቱ የሚውሉ የምግብና መጠጥ እንዲሁም የቁሳቁስ ዝግጅት ነው፡፡ ለእነዚህ ዝግጅቶች ግብአት የሚሆኑት በዋናነት ከልመናው የተገኙት የእህል አይነቶች ናቸው፡፡ ሆኖም የተለመነው እህል ለድግሱ የማይበቃ(የሚያንስ) ከሆነ ሌላ እህል ሊጨመርበት ይችላል፡፡ ነገር ግን ከልመና የተገኘውን እህል ለሌላ ጉዳይ ( አገልግሎት) ለምሳሌ ለዕለት ጉርስ ማዋል አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ለዛሮች ተብሎ ስለተለመነ ለሌላ ጉዳይ ከዋለ ይቆጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ሁሉም ባለጉዝጓዞች ገልፀውልኛል ፡፡

### ለገፈራ ክዋኔ የሚውሉ መጠጦች ዝግጅት

ለገፈራ ክዋኔ የሚውሉ መጠጦች ቡቅሪ (ቀሪቦ) እና ጠላ  በዋናነት የማይቀሩ ሲሆኑ የባለጉዝጓዞቹ ዛር በገፈራው ቀን አረቂ የሚጠይቅ መሆኑ ከታወቀ ተገዝቶ ይቀመጣል። ይህም በገፈራው ዕለት ዛሩ አረቂ አምጡ በሚልበት ሰአት የሚሰጥ እንጂ ለተሳታፊዎች የሚዘጋጅ አይደለም። ጠላና ቡቅሪው ግን ሁሉም ተሳታፊ እንደየፍላጎታቸው የሚጠጣቸው ናቸው። ጠላ የሚዘጋጀው ከገፈራው ከ13-15ቀን ቀደም ብሎ ሲሆን ቡቅሪው ደግሞ ከ4-5 ቀን ቀደም ብሎ ይዘጋጃል። በዝግጅቱ የሚሳተፉት ሴቶች ሲሆኑ ከባለ ጉዝጓዧ በተጨማሪ የሚሳተፉት ለመስራት ፍላጎት ያላቸው ሴቶች እና ባለሙያ የሆኑ መሆን አለባቸው። እነሱም የባለጉዝጓዧ ቤተዘመዶች ወይም ጎረቤቶች ናቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት ምልከታ ያካሄድኩባቸው ባለጉዝጓዞች እንደነገሩኝ ሴት ዛሮች ቡቅሪ ወንድ ዛሮች ደግሞ ጠላ ስለሚፈልጉ ነው። ለምሳሌ ወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ሦስቱንም አይነት መጠጥ እንደሚያቀርቡና መጠኑም አነስተኛ እንደሆነ እንደሚከተለው ነግረውኛል፡

> ገፈራ ስናደርግ ጠላ እና ቡቅሪ እናዘጋጃለን። አረቂ ግን ይገዛል እንጂ አይዘጋጅ፤ ጠላና ቡቅሪ ግን የማያዘጋጅ የለም ።ምክንያቱም ቁጥቢቱ ቡቅሪ ካልቀረበ፣ ወንዘኛው ደግሞ ጠላ ካልቀረበ አይታረቁንም፣ አይለመኑንም፣ምን ያደርግልሻል ኧረ ጭራሹንም ቢለመኑ አይገቡም። ከተቆጡ ደግሞ ችግርና በሽታ ያመጣሉ። ሁሉም በገፈራው ቀን የመጡት ሰዎችም ማታ ሀድራ ላይ አድረው በጠላና ቡቅሪ ጠዋት ላይ ጉሮሯቸውን ያርሳሉ።አረቂ ግን እንደየዛሩ አይነት ይለያያል። አንዳንዱ ወንድ ዛር አረቂ ይፈልጋል ስለዚህ ሁልጊዜ በግብሩ ቀን አረቂ አምጡ የሚል ከሆነ ከአንድ አስከ ሁለት ስኒ የሚሆን አረቂ ማቅረብ ግድ ነው። እኔ አሁን በየሁለት አመቱ አንድ ስኒ አረቂ እገዛ ነበር አሁን ግን በገበያ ቀን ስላጣሁኝ አልገዛሁም። ያው እንዳየሽው አረቂ ጠይቆ ምትክ የሚሆን 50 ብር በማባበል ለምነው ሰጥተውታል። ይሄ ብር አረቂ ባይገዛበትም ጨምሬ ዶሮ እገዛለታለሁ። በኋላም ተሸጦ ብሩ ለገፈራ ይውላል። (ቃ.መ፣02/06/08፣ ቤሬ ጎጥ)

ሌሎቹ ባለጉዝጓዞች ግን አረቂ እንደማያቀርቡ ነግረውኛል ፤ በምልከታም ማረጋገጥ ችያለሁ። የጠላና ቡቅሪ መጠጦች ከተዘጋጁ በኋላ በተለያዩ ማሰሮዎች ተሞልተውና በጨርቅ ታስረው እስከ ገፈራው ቀን ድረስ ይቀመጣሉ። ይህም በአካባቢው አጠራር “ ሚጁ ” በመባል ይታወቃል። የእነዚህ መጠጦች ድፍድፍም ሆነ ገፈታ ከገፈራው ቀን ውጭ አይቀመስም ። ይህ የሆነበት ምክንያትም የዛር መንፈሱ እንዳይቆጣና የመንፈሱ ግብር ከቀኑ ውጭ ከተቀመሰ በመቆጣት በሽታ ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው። በዚህ ዙሪያ ያነጋገርኳቸው ባለጉዝጓዝ ወ/ሮ ከድጃ ሁሴን  የሚከተለውን ነግረውኛል።

ጠላውንም ሆነ ቡቅሪውን ስናዘጋጅ ድፍድፉን እንኳ አንቀምስም ፤ እንዲሁ በነሱ ይብቃኝ ነው፣ እናንተው አሳምሩት፣ የጣፈጠ አድርጉልን ብለን ተለማምነን ነው ውሀ የምንሞላው፡፡ መድረሱንም ለማረጋገጥ ገፈታ አንቀምስም፡፡ እነሱም አያሳፍሩንም ያው ያማረ የጣፈጠ ያደርጉታል፡፡ ሚጁ ከተቀመሰማ ምኑን ሚጁ ሆነ ሚጁ ማለት እኮ ያልተነካካ ማለት ነው፡፡ ለገፈራ የሚዘጋጅ ጠላም ሆነ ቡቅሪ መነካካት የለበትም፣ ከተነካካ፣ ከተቀመሰ ቁጥቢቱ ትቆጣለች ወንዘኛው ይጣላናል፣ ለጠጣው ሰውም ፈውስ ሳይሆን በሽታ ነው የሚሆነው፡፡ (ቃ.መ፣15/06/08፣ዋዚ ጎጥ)

## ለገፈራ ክዋኔ የሚውሉ ምግቦች ዝግጅት

ለገፈራ የሚዘጋጁት የምግብ አይነቶች እንጀራ ፣ ድፎ ዳቦ ፣የምስር ወጥ ፣ የሽንብራ እና የገብስ ቆሎ፣ የተለጠለጠ ኑግ ፣ የማሽላ ወይም የበቆሎ ፈንድሻ፣ ፣የሩዝ ወይም የአጃ ቅንጬ፣ ፣የፀጉር ቅቤ፣ጫት፣ቡና እና ሻይ ናቸው፡፡ በምልከታ እንዳረጋገጥኩት የወ/ሮ ዘሀቡ ይማምና የወ/ሮ መይረማ እንድሪስ ገፈራ ላይ የተዘጋጀው የአጃ ቅንጬ ሲሆን እንዲሁም ለፈንድሻ በሚሆነው በቆሎ ፈንድሻ ተዘጋጅቷል፡፡ በሌሎቹ ገፈራ ቤቶች ግን የሩዝ ቅንጬ ነው፡፡ እነዚህ የምግብ አይነቶች የሚዘጋጁት ከገፈራው ቀን አንድቀን ቀደም ብሎ ወይም ገፈራው ማታ ሊካሄድ ቀን ላይ ነው፡፡ በስራው የሚሳተፉት ፍቃደኛ የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ በምግብ ስራው ላይ ሴቶች ሲሳተፉ ወንዶች ደግሞ በማገዶ እንጨት ማዘጋጀት ላይ ይሳተፋሉ፡፡

ምግቦቹ የሚዘጋጁት አንድም ባለጨፌዎቹ ከለመኑትና ከራሳቸው ባቀረቡት እህል ሲሆን አንድም ደግሞ ሌሎች ሰዎች ከሚያመጡት ጀባታ ነው፡፡ ጀባታ ማለት አንድሰው ማንኛውንም አይነት ድግስ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሌሎች ሰዎች ለዚያ ድግስ ማስኬጃነት እና ባለድግሱን ሰው ለማገዝ ሲሉ የሚሰጡጥ የእህል፣የገንዘብ ፣ወዘተ ስጦታ ነው፡፡

ስለሆነም ለዛር ግብር በሚደረግ ድግስ ላይም ከተለያዩ ሰዎች ጀባታ ለባለጉዝጓዝ ይሰጣል፡፡ ከሚሰጡት ጀባታዎች ውስጥ ርጥብ ቡና ፣ ጫት፣ ድፎ ዳቦ ፣ እንጀራ ፣ ስኳር ፣ ማሽላ እና ጭሳጭስ እንደሚገኙበት በሁሉም ገፈራ ቤቶች ባካሄድኩት ምልከታየ አረጋግጫለሁ፡፡ ለገፈራ የሚሰጡት እነዚህ ጀባታዎች ለሰጭዎቹ ምን ፋይዳ እንደሚያስገኙላቸው ካነጋገርኳቸው ጀባታ ሰጭዎች ውስጥ ርጥብ ቡና ለወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ሲሰጡ ያገኘኋቸው አቶ መኮነን አህመድ የሚከተለውን ነግረውኛል፡

ለገፈራ ፣ለመውሊድ፣ለወዳጃ፣ ለሰርግ እና ለሌሎችም ድግሶች ጀባታ ይሰጣል፡፡ ይህን የምናደርገው አጅር ለማግኘትና በጥቂቱም ቢሆን ደጋሾቹን ለማገዝ ነው፡፡ አሁን እኔ ለአረጋሽ ያመጣሁት ርጥብ ቡን ማገዣ ነው፣ዛሮቹም ከቀሽሩ ቡን ይልቅ ያልደረቀውንና ያልተፈለፈለውን ድፍን ቡን ይወዳሉ፡፡ ይህ ነው ከሰማ ምጣድ ላይ

ደርቆ ፣ ተቆልቶና ተወቅጦ ለገፈራ የሚዘጋጀው፡፡ ከቡና በተጨማሪ ጫት፣ ጭሳ ጭስጭስና ሌላም ጀባታ ይሰጣል፡፡ (ቃ.መ፣30/05/08፣ቤሬ ጎጥ)

ለጀባታ የሚሆነው ቡና በአብዛኛው በገበያ ላይ የምናገኘው የተፈለፈለ(ቀሽር) ሳይሆን ከዚያው ከእርሻቸው የተለቀመ ርጥብና ያልተፈለፈለ ድፍን ቡና ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ድግሱ ከሚደረግላቸው ዛሮች ፍላጎት ጋር የተያያዘ መሆኑን ከቃለመጠይቁ መረዳት ይቻላል፡፡በተጨማሪም ይህን ጉዳይ ከገፈራ የመከወኛ አጋጣሚ ጋር ማያያዝ ይቻላል፡፡ ይኸውም ከላይ በቅድመ ዝግጅቱ ላይ እንደተጠቀሰው ገፈራ የሚከወነው አዲስ ምርት የሚገኝበት የመኸር ወቅት ነው፡፡ ስለዚህ የገፈራ የመከወኛ አጋጣሚ ለዛሮቹ ፍላጎት መሟላትና ለምግብና መጠጥ ዝግጅትም ወሳኝነት አለው፡፡

ሆኖም የጥናቱ ተተኳሪ ማህበረሰቦች ጀባታ የመስጠት ባህላቸው እና በተለያዩ የስራ ድርሻዎች ላይ መሳተፋቸው ርስበርስ የመተጋገዝ ፣የመተሳሰብና የመረዳዳት ባህል እንዲያዳብሩ ከማገዙም በላይ አንድነታቸውን ያጠናክራል ማለት ይችላል፡፡

### ጫት በገፈራ ጊዜ ያለው ትርጉምና ማህበረሰቡ ለጫት ያለው አመለካከት

ጫት በገፈራ ጊዜ ያለዉ ትርጉም ከፍተኛ ነዉ፡፡እንዲያዉም ያለ ጫት የሚደረግ ገፈራ የለም፡፡ ነገር ግን ጫት የማይወድና ህመም ያለበት ተሳታፊ ላይቅም ይችላል፡ ይህ ደግሞ ሊሆን የቻለበት ምክንያት በማህበረሰቡ ዕምነት የሚወደደው የገነት ቅጠል ነው ተብሎ ስለሚታመንና የመድሃኒትነት ጠባይም እንዳለዉ ስለሚታመንበት ነዉ፡፡ ጫት ነክሶ ዱአ ያደረገ ልመናው ይሰምርለታል፣ ምስጋናዉ ይደርስለታል፡፡ ለምሳሌ ቡዳ ለበላው ሰው ጫቱን በውሀ አፍልተው በስኳር ሲያጠጡት ይድናል፣ ለበሽተኛ በሚደረግ ወዳጃ ላይ የወዳጃው ታዳሚዎች የቃሙትን ጫት በዉሃ እየተቀላቀለ ለበሽተኛው እየተፉበት ኣላህን ቢለማምኑለትና መድሃኒት ቢያደርጉለት ከበሽታው ሊፈወስ እንደምችል የባህሉ ባለቤቶች ነግረውኛል፡፡ በአጠቃላይ በማህበረሰቡ እምነት ላይ በመመስረት የጫትን ሚና ስንመለከት በአንድ በኩል ለተለያዩ አላማዎች ዱአ ለማድረግ የጎላ ትርጉምና ትኩረት ሲሰጠው በሌላ በኩል መድሃኒቱ የታመነበት ለሰው ልጅ ብርታትና ጥንካሬ ይሰጣል እየተባለ የሚነገርለት ቅጠል ነው፡፡ ይኸውም የዱአ ተሳታፊዎች እንቅልፍ እንዳይዛቸውና እንዲነቃቁ ያግዛቸዋል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ ጫትና ቡና በዱአ ላይ የማይቀሩ ናቸው፡፡ ለገፊራ ብቻ ሳይሆን ለወዳጃ፣ለመውሊድ በሚደረግ ዱአም ጫት ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ገፊራም ዱአ ከሚደረግባቸው ስነ-ስርአቶች ውስጥ አንዱ በመሆኑ ዱአው የሚካሄደው ጫት እየተቃመና ቡና እየተጠጣ ነው፡፡



ምስል 3. በገፊራ ክዋኔ ላይ የቀረበ ርጥብ ቡና እና ጫት (ምልከታ፣30/05/08፣ቤሬ)

### 3.2.1.5 ለገፊራ ክዋኔ የሚያስፈልጉ ቁሳቁስና አልባሳት ዝግጅት

ለገፋራ ክዋኔ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ለክዋኔው ድባብ ከፍተኛ ድምቀት በመስጠት አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ከባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ውስጥ ድቤና ማሲንቆ ለዚህ ክዋኔ ይውላሉ፡፡ ድቤው የሚሰራው ከፍየል ቆዳ እና ከላይ ክፍት ከሆነ ቆሪ ሲሆን ቆዳዉ ከቆሪው ላይ በደንብ እንዲጣበቅ ርጥቡን ይሰፋል፣ከዚያም ሲደርቅ ለአገልግሎት ይውላል፡፡ ማሲንቆው ደግሞ ከፍየል ቆዳ፣ ከፈረስ ጭራና ከእንጨት ነው፡፡

የእነዚህ መሳሪያዎች ተመራጭነት ድምፃቸው ዛሮችን ቶሎ ለመጥራት፣ ለማስደሰት፣ ለማስጎራት ይረዳሉ፡፡ ዛሮች የማሲንቆና የድቤ መሳሪያዎች ድምፅ ከሌለ ሲለመኑ አይገቡም ፣ ተሳታፊን ያነቃቃሉ ተብሎ ስለሚታሰብ መሆኑ የባህሉ ባሌቤቶች ይገልፃሉ፡፡ (ቃ.መ፣አብዱ ረያን 03/06/08 ቀርሱ፣ በላይነሽ አህመድ 08/06/08 ዋዚ፣ ሚፍታህ መሀመድ 22/06/08 ቸሪት እና አደም አወል 23/07/08 ዱሬ)

በተጨማሪም በምልከታ ለመረዳት እንደሞከርኩት ድቤና ማሲንቆ በገፊራ ክዋኔ ላይ የዛር መንፈሱን ለማወደስና ተሳታፊዎችን በማነቃቃት አውዱን ለማድመቅ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ በመሆኑም ድቤው ከመመታቱ በፊት ጥሩ ድምፅ እንዲሰጥ ቀን ፀሀይ

ማታ እሳት የሚንቃቃ ሲሆን የሚመታው በጨርቅ በተጠቀለለ አንድ አነስተኛ እንጨት እና በአንድ እጅ ነው፡፡ ይኸውም በቀኝ እጅ የድቤ መምቻውን በመያዝ ከግራ እጅ ምት ጋር እያቀናጁ ይመታል፡፡



ምስል4.አሗራፊ አብዱ ረያን ድቤ እየመታ



ምስል 4.አደም እንድሪስ ማሲንቆ እየተጫወተ

የማሲንቆው ከዋኞች የመሳሪያዎቹ የግል ባሌቤቶች ሲሆኑ ድቤው ግን የጋራ ንብረት በመሆኑ በአሗራፊ ይመታል፡፡ ሁለቱም ግን በሙያው የተካኑ መሆን አለባቸው፡፡ ማለትም ገፊራ ለዛሮች የሚደረግ ድግስ እንደመሆኑ የሙዚቃ መሳሪያዎቹ አመታት ለዛሮቹ ከሚዜሙት ግጥሞች ጋር አብሮ የሚሄድን ምት ጠንቅቀው የሚያውቁ፣ ማንኛው የሙዚቃ መሳሪያ ለማንኛው የዛር አይነት እንደሚያስፈልግ የሚያውቁ እና በገፊራ ክዋኔ ልምድ ያላቸው መሆን ይጠበቅበቸዋል ፡፡ በተጨማሪም ማሲንቆ ተጨዋቹ አሗራፊዋን የአፍ እንቅስቃሴና የድምፀት ቅየራ በቅፅበት በመረዳት(በመናበብ) ምቱን መቀያየር የሚችል መሆን አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ የክዋኔው ሂደት ስለሚስተጓጎል የዛር መንፈሶች አይቀሰቀሱም፤ ተሳታፊዎችም ይፈዛሉ፡፡ ክዋኔ ደግሞ ንቁ ተሳታፊዎችን እንጂ ፍዝ ተሳታፊዎችን አይፈልግም፡፡ በሀራና ቡልቡሎ ቀበሌ ገፊራ ጊዜ ማሲንቆ በመጫወት የሚታወቁት አቶ አሊ ሰይድ የሚከተለውን አጫውተውኛል፡፡

> *እኔ ማሲንቆ በገፈራ ላይ በሰርግ ላይም እጫወታለሁ፡፡ አጨዋወቴ ግን ይለያያል፤ በሰርግ ጊዜ የምጫወተውን ማሲቆን በገፈራ ላይ አልመጫወተውም፡፡ ገፈራ የራሱ የሆነ ስርአት አለው ስለዚህ አሿራፊዎቹን ተከትየ ከሚያዜሙት ግጥም አይነት ጋር አጨዋወቴን አስተካክላለሁ፡፡ለምሳሌ መጀመሪያ ላይ ከእርቅበይ እስከ ነገያነገያ[18] ሲባል እኔ አልመታም ምክንያቱም ዛሮቹ ገና አልገቡም፡፡ ድቤው ግን ይመታል፡፡ ከገቡ በኋላም ቢሆን ማሲንቆ ለሚፈልጉት ብቻ ነው የምመታው ፤ ቁጥቢቱ ስትሆን እመታለሁ እንዲሁም አንዳንድ ኪነተኛ ዛሮች ማሲንቆ ይወዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ሁለቱንም የሚፈልጉ አሉ፡፡ ይሄን ደግሞ ራሳቸው በሚያሳዩት ድርጊት መለየት እችላለሁ፡፡ ባለጉዝጓዞቹም ሆኑ ሌሎች ዛራቸው የተቀሰቀሰ ሰዎች ሲያጎሩ ወደ ማሲንቆው መጥተው ጎንበስ በማለት ያጎራሉ የዚህ ጊዜ ዜማውን ተከትየ እጫወታለሁ፡፡ ወደ ድቤው ከሄዱ ግን አልጫወትም፡፡ አጉርተው ሲበቃቸው ደግሞ ማሲንቆየን ጎንበስ በማለት ስመዉ ወይም ወደ እኔ በማጎንበስ አመስግነው ይቀመጣሉ፡፡ (ቃ.መ ፣ 22/06/08፣ ቸሪት ጎጥ)*

ስለዚህ በገፈራ ክዋኔ ማሲንቆና ድቤ ለክዋኔው ድባብ ድምቀት ከመስጠት በተጨማሪ ድግሱ ከሚደረግላቸው የዛር መንፈሶች ጋር በእጅጉ የሚቆራኙ መሆናቸውን ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ቁሳቁሶች ምርጫ ለክዋኔው ምሉዕነት ወሳኝነት አለው፡፡ የድቤ ምት የተለመደ የዛር መለያ ዘዴ እንደሆነና በከበራ ላይ የዛር መንፈሱ በአንድ ሰው ላይ ሲያርፍ የሚወደውን የሙዚቃ ቃና መስማት እንደሚፈልግና ዛር ታማሚዋ በሙዚቃ ቃናው መዳነስና የማታውቀውን ዜማ ማዜም ከጀመረች በዛር መያዟ እንደሚታወቅ በታንዛንያ የተካሄደው ጥናት ይገልፃል፡፡[19]

ከእነዚህ የሙዚቃ መሳሪያዎች በተጨማሪ በቁሳቁስ ዝግጅት ጊዜ የሚያስፈልጉት አልባሳትና ጌጣጌጥ ናቸው፡፡ አልባሳትና ጌጣጌጦቹ በዋናነት የሚዘጋጁት ለባለ ጉዝጓዟ ሲሆን ወጬ መሸፈን ያለበትም በራሷ ብቻ ነው፡፡ ማለትም በተውሶ ልብስና ጌጥ መዋብ አይፈቀድም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ድግሱ የሚደረግላቸው ዛሮች ባለጉዝጓዟ በራሷ አቅም(ባላት) አጊጣና አሽብርቃ ማየትን ስለሚፈልጉ እንደሆነ የባህሉ ባሌቤቶች ይገልፃሉ፡፡

---

[18] እርቅ በይ እርቅ በይ የሚባለው ለሴቷ ዛር ሲሆን ትርጉሙም ታረቂ (ተስማሚ) ማለት ነው፡፡ ነገያ ነገያ የሚለው ቃል ደግሞ ኦሮምኛ ሲሆን ሰላም ማለት ነው፡፡ ሀድራው ሰላም እንዲሆንና በሰላም እንዲጠናቀቅ የሚመኙበት ቃል ግጥም ነው፡፡

[19] Drum beating was the most common means of identifying spirit intrusion. It is thought that the spirit, who has entered the person, will reveal it self when hearing its favourite rhythm. If the patient starts to dance in the rhythm of the drum beat, and possibly to sing a song supposedly unknown to her, it is conceived as an almost sure proof of spirit intervention. (Arvihurskainen, 2004, 43-44)

ከአልባሳት ውስጥ የሚዘጋጁት ባለጉዝጓ፟ዟ የምትለብሰው ነጭ የሀር (ጥበብ) ቀሚስ፣ ጉፍታ፣ ነጭ ሻሽ ፣ የውስጥ ሱሪ እና በገፈራው ዕለት ቅቤ ስትቀባ የሚለበስ ነጭ ሻሽና ጥቁር ሻሽ በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ነጭ ልብስ ከሌላት ሌላ ንፁህ ልብስ ይዘጋጃል፡፡

ለወንድ ባለጉዝጓዝ ነጭ የሀገር ልብስ፣ነጠላ (ኩታ)፣ጥምጣም ፣ቅቤ ሲቀባ የሚታሰር ጥቁር እና ነጭ ሻሽ ከጌጣጌጥ ጨሌና ሙስበሀ እንደሚያስፈልግ የባህሉ ተሳታፊዎች ይገልፃሉ፡፡

ከጌጣጌጥ ውስጥ ደግሞ ዋናውና አይቀሬው የተለያዩ ለዛር መግለጫ የሚያገለግሉ ቀለማትን የያዘ ጨሌ ሲሆን ባለጉዝጓዟ አንገቷ ላይ የምትለብሰው ጌጥ ነው፡፡ የጨሌው (ስንድድ) ቀለማት አምስት ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የሚወክሉት የዛር መንፈስ አላቸው፡፡ ይኸውም ቀይ የቀየ በላ፣ ነጭ የነጨ በላ፣ አረንጓዴ ጭረቸኛ ፣ ደማቅ ሰሚያዊ የጥቁረ በላ ፣ ዥንጉርጉሩ ዘባንያ በመባል የሚጠሩትን ዛሮች ትዕምርትነት ያመለክታሉ(ይወክላሉ)፡፡ እነዚህ ቀለማት ከያዙት ስንድዶች መጨረሻ የሚገኘውና ሁሉንም አይነት ቀለም የያዘው ደግሞ ተፉሰስ በመባል የሚጠራ ሲሆን የሚወክለው የዛር መንፈስ የለውም፡፡ ይህ ተፉሰስ ስንድድ ያልተሰካባቸው ትርፍ ክሮች ያሉት ሲሆን ባለጉዝጓዞቹ ለማስዋብ የፈለጉትን አይነት ስንድድና ሙስበሀ(ዶቃ) የሚደረድሩበት ነው፡፡

በተጨማሪም ባለጉዝጓዟ የምታጌጥባቸው እንደ አምባር ፣ የጆሮ ጌጥ ፣ ቀለበት ፣ ሙስበሀ (ዶቃ)፣ወዘተ ካሉ ይዘጋጃሉ፡፡ ከአልባሳትና ጌጣጌጥ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ቅድመ ዝግጅት የገፈራ አድራጊዋ መዋብ ነው፡፡ ባለጉዝጓዟ (ሙሽራዋ) ፀጉር ሹርባ መስራት በምትችል ሴት ከገፈራው ቀን አንድ ቀን ቀደም ብሎ ፀጉሯን ሹርባ ትሰራለች፣ እጅና እግሯን ሂና እና ቡሽርጥ (ድንች የሚመስል ለምግብነት የማያገለግል ስራስር ሆኖ እጅና እግርን የሚያቀላ የስራስር አይነት) ትሞቃለች፡፡ ጠዋት 12፡00-1፡00 ባለው ሰአት ውስጥ ገላዋን ትታጠባለች፡፡



ምስል 6. ጨሌ



ምስል 7. ሙስበሀ



ምስል 8. አንባር

በተጨማሪም በገፈራ የቁሳቁስ ዝግጅት ጊዜ አብሮ የሚነሳው በገፈራው ቀን የሚጨስ ጭሳጭስ ዝግጅት ነው። ለገፈራ ክዋኔ የሚያስፈልጉ ጭሳጭሶች ገውሌ ፣ ስንቡልና ከርቤ ፣ቀንጦጢስ (ምጥን የወሎ ጭስ)፣ ወገርትና ጉማ ፣አደስ፣ ቀጠናዮ ፣ናትራ(ነጭ አሽኩቲ)፣ ጥቁር አሽኩቲ ፣ጀዌና አደን አድሩስ ፣ ሚስክ ፣ ምስርች ፣ ነድ (ሰንደል) ፣ ዕጣን እና ወይራ ናቸው።




ምስል 8. ጫሳጭስ



እነዚህ ጭሳጭስ ለገፈራ ክዋኔ እንደ ሌሎቹ ቁሳቁሶች ሁሉ የግድ አስፈላጊ መሆናቸውን የባህሉ ባሌቤቶች ገልጸዋል። ይኸውም እነዚህ በገፈራ ቤቱ ውስጥ በአንድ ላይ ተደርገው ሲጨሱ ዛር ጥሩ ሽታ ይወዳል ተብሎ ስለሚታመን የዛር መንፈስን ቶሎ ለመጥራትና ለመቀስቀስ ፣ተቀይጠው የሚፈጥሩት ሽታ ቤቱን በጥሩ መዐዛ ከማወዱም በላይ ለተሳታፊዎች ደስታን ይሰጣል ተብሎ ይታመናል። ከእነዚህ

ጭሳጭሶች መካከል አንዱ እንኳን ከጎደለ በተለይም ስንቡልና ከርቤ የተባሉት ካልተጨሱ የዛር መንፈሱ እንደማይነሳና እንደማያጓራ ይገልፃሉ፡፡ (ቃ.መ፣ ካዳሚዎች ሀድያ አደም 01/06/08፣ ቤሬ፣ ወ/ሮ ዚነት መኮነን 03/06/08 ቀርሱ፣ ወ/ሮ ሰሚራ አህመድ፣ 08/06/08 እና ሀያት እንድሪስ 15/06/08 ዋዚ፣ወ/ሮ ሶፊያ አሊ 22/06/08 ቸሪት እና ወርቅነሽ አህመድ 22/06/08)

እነዚህ ጭሳጭሶች አውዱን በጥሩ መዐዛ በማወድ እንደሚያደምቁትና የዛር መንፈሶችንም በቶሎ እንደሚቀሰቅሱ በምልከታ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ዕጣኖች የሚጨሱባቸው ጋቻዎች ፣ የቡና ማፍሊያ ጀበናዎች ፣ የሻይ ማፍሊያ በራድ ወይም ትልቅ ጀበና ፣ ስኒና ረከቦት ፣ የቅቤ ማቅለጫ የማይቀልጥ ሰሀን፣ የጨሌ መንከሪያ ጎድጎድ ያለ ሰሀን፣ የቅቤ ማስቀመጫ ሦስት ትንንሽ ስኒዎች፣ ከቅል የተሰራች ትንሽ የቁኒ (ከደረቅ አደስ ቅጠል ተፈጭቶ የሚዘጋጅ የቅቤ ሽታ ማጣፈጫ) መያዣ ቁኒ ቀዳዳ ፣ ሰፌድ ፣ ዳንቡይ (ቆሪ) ፣ወንፊት፣ አቦሬ(ከቅል የተሰራ የጠላና ቡቅሪ መጠጫ) ፣ኩባያ እና ጃንጥላ ይዘጋጃሉ፡፡

በመሆኑም በቅድመ ዝግጅት ወቅት የምግብና የመጠጥ፣የቁሳቁስ (የአልባሳትና ጌጣጌጥ፣የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የጭሳጭስ) ዝግጅት ለከበራው ድባብ ድምቀትና ምሉዕነት ወሳኝነት አላቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በገፈራ ከበራ ላይ የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎችን (ድቤ፣ ማሲንቆ፣ጨሌ፣ጭሳጭስ፣ጉዝጓዝና ቅቤ) ከግልጋሎታቸው ወጣ ብለን ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳይ ጋር አያይዘን ስንመረምር ቁሶቹ የሚከተሉትን ሶስት ባህሪያት ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡

የመጀመሪያው የተፈጥሮአዊና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡[20] በዚህም መሰረት በማንኛውም አውድ ውስጥ ሆነን ድቤን፣ ማሲንቆን፣ጨሌን፣ ጭሳጭስን፣ጉዝጓዝን እና ቅቤን በአንድ ላይ ስናስብ በቀጥታ የሚመጣብን ለዛር መንፈስ የሚደረግ ድግስ እና ክዋኔ ነው፡፡ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ደግሞ ለዛር

[20] ይህን ሐሳብ በተመለከተም (Prown፣1982፣4) “The most obvious cultural beliefs associated with material objects has to do with value”. ብዙ ጊዜ ቁሶች የተለየ እሴት ባለቤት ሆነው ይገኛሉ፡፡ ይህንን እሴት አንድም በተፈጥሮ ወይም ሰው ራሱ ይጭንባቸዋል፡፡ በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከሚደረጉ ድግሶች ውስጥ አንዱ መሆኑን ከላይ በምንነቱ ላይ ተብራርቷል፡፡ እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች እንደፈለግን በየትም ቦታ እንደፈለግን የማናገኛቸው መሆኑ የበለጠ እሴት ወይም ዋጋ እንድንሰጣቸው ያደርገናል፡፡ ይህ በተፈጥሮ እንደልብ ያለመገኘት ጉዳይ የቁሳዊ ባህሎቹን እሴት ቀጣይ ያደርገዋል፡፡

ሁለተኛው ደግሞ ታሪክ ነቃሽነት (Surviving Historical Events) ፡- ድቤ፣ ማሲንቆን፣ጨሌን፣ጉዝጓዝንና ቅቤን በአንድ ላይ ተመልክተን (አጥንተን) በረጅም ዘመን ስለተፈጸመ ባህላዊ ድርጊት የሚነግሩን ቁም ነገር አላቸው፡፡ ምክንያቱም ቁሳዊ ባህሎቹ በአንድ በተወሰነ አካባቢና የጊዜ ገደብ ውስጥ መጠነኛ የሆነ ለውጥ በማሳየት ረጅም እድሜ ይቆያሉና ፡፡ በዚህም መሰረት እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ስለአለፈው ወይም ስላልኖርንበት ዘመን የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ታሪክ ለማወቅ እድል ይሰጡናል፤ ዋቢ ምስክሮቻችንም ናቸው፡፡[21] በመሆኑም እነዚህ ቁሳ ቁሶች በታሪክም ሆነ በቁሳዊ ባህል የጥናት መስክ ስለ ገፈራና ሌሎች ለዛር መንፈስ የሚደረጉ ክበራዎችን ሁለንተናዊ ባህልና ታሪክ ለማወቅ የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

ሶስተኛው የበለጠ ተወካይነት (More Representativeness) የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ላይ የሚከወኑ ቃላዊ ግጥሞችን ለማጀብ፣ የዛር መንፈሶችን ለመጥራት እና አውዱን ለማድመቅ ከሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎች በጽሁፍ ከተገኘ መረጃ የበለጠ ተወካይነት አላቸው፡፡ ይህም ማለት ድቤ ፣ማሲንቆ፣ጉዝጓዝና ቅቤ በአብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል የተማረውም ሆነ ያልተማረው ደሀውም ሆነ ሀብታሙ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖረው ህዝብ ይገለገልባቸዋል፡፡ ድቤና ማሲንቆ ጨዋታን(ጭፈራን) ሲወክሉ ለተጠቃሚው የሚሠጡትን የመንፈስ እርካታ ይወክላሉ፡፡ ጨሌ ግን የዛር መንፈስን ይወክላል፡፡ ይህም ሲባል በአብዛኛው በዛር ድግስ ቦታዎች የሚነበቡት ወይም በቃል የሚባሉት ቃል ግጥሞች ከቦታ ቦታ ሲለያዩ እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ግን በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው ማለት ነው፡፡

---

[21] ይህንን ሀሳብ በተመለከተ (Prown፣1982፡3). የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል፡፡
"Objects created in the past are the only historical occurrences that continue to exist the present. They provide an opportunity by which we encounter the past at first hand; we have direct sensory experience of surviving historical events."

### 3.1.3.5 የስፍራ መሰናዶ

የዛር ድግስ የሚደረግበት ቤት ገፈራው በሚደረግበት ቀን ከሰአት በኋላ ለስራው ፍላጎት ባላቸው ሰዎች  አማካይነት ይዘጋጃል፡፡ ይኸዉም የቤቱ ዉስጥና ዉጭ በዉሃ ተርከፍክፎ ይጠረግና ርጥብ ሳር ወይም የባህርዛፍ ቅጠል ይጎዘጎዛል፡፡ ቤቱ ክፍል ክፍል ከሌለው በመጋረጃ ለሁለት ይከፈላል፡፡ አላማዉም ዋና የገፈራ ተሳታፊዎችን ከሌሎቹ  ተሳታፊዎች እንዳይቀላቀሉ ሲባል ነው፡፡ የተሳታፊዎች ቦታዎች በመጋረጃ ከተከፋፈሉ በኋላ የጥጥም ሆነ የስቦንጅ አልያም የሳር ፍራሽ ዙሪያቸውን ይነጠፍባቸዋል፡፡ ፍራሽ ከሌለ ደግሞ ሸራ ወይም ሌላ ምንጣፍ ይነጠፋል፡፡ ከወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት የተነጠፈው ጥቁር ሸራ ከዚያ ላይ የሰሌን ምንጣፍ እና ዙሪያውን ሦስት የስፖንጅ ፍራሽ ሲሆን ከወ/ሮ አንሻ አሊ ቤት ደግሞ ቀይ የሸራ ምንጣፍ ላይ አንድ የሳርና አንድ የጥጥ ፍራሽ ነው፡፡ በሌሎቹ ገፈራ ቤቶች ባለ ጉዝጓዚቱ ከተቀመጠችበት የሳር ፍራሽ ውጭ ሌላው በሻራ ብቻ የተነጠፈ ነው፡፡

በገፈራ ቤቱ የመግቢያ በር ላይ እርጥብ አረንጎዴ ቅጠል በቀኝም በግራም ይሰካል፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያትም በቤቱ ዱአ መኖሩን ለማሳወቅና ያላወቀ ሰው ወደቤት ሲገባ ያልተገባ ድምፅ( ረብሻ) እንዳያሰማ እንደሆነ የባህሉ ባለቤቶች ይገልፃሉ፡፡ እነሱ እንደሚሉት በባህላቸው መሰረት በወዳጃና ሌሎች ዱአ በሚደረግባቸው አጋጣሚዎች ቤቱ በር ላይ ለምልክት ርጥብ ቅጠል ይሰካል፡፡ ከዚያም አካባቢው ጥሩ መዐዛ እንዲኖረው በቤቱ ውስጥና ውጭ ለገፈራው ክዋኔ ሲባል በተዘጋጁት ጋቻዎች ላይ ጭስ ይጨሳል፡፡

**በገፈራ ወቅት ከተሳታፊ የሚጠበቁ ደንቦችና ስርዓቶች**

የገፈራ ተሳታፊዎች ከባለ ጉዝጓዧ በተጨማሪ በዋናነት ወንድና ሴት አሏራፊ፣አበጋርና ማሲንቆ ተጨዋች ሲሆኑ ሌሎች በባለ ጉዝጓዧ የተጠሩ የአካባቢው ሰዎች ናቸው፡፡ አሏራፊ ማለት ቀጥተኛ ትርጉሙ አስታራቂ ሲሆን የዛር መንፈስ የሰፈረባቸውን ሰዎች ከዛር መንፈሱ ጋር እንዲስማሙ የማድረግ ሚና ያለውን ሰው የሚገልፅ ነው፡፡ በተጨማሪም በወንድም በሴትም ገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ላይ ባለጉዝጓዧን ቅቤ በመቀባት፣ ጨሌ በመንከር፣ቃል ግጥሞችን በመምራት፣የተጋጩ ዛሮችን በዛር አፍ አነጋግሮ በማስታረቅ እና ሌሎች ዋና ዋና ተግባራትን ለሚፈፅም ሰው የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ በአንድ ገፈራ ላይ የሚሳተፉ አሏራፊዎች አንድ ወንድና አንድ ሴት ሲሆኑ በዋናነት

የአሿራፊነቱን ሚና የምትይዘው ሴቷ ናት፡፡ የወንዱ አሿራፊ ሚና ሴቷ አሿራፊ ሌሎች ተግባራትን በምትከውንበት ጊዜና አንዳንድ ዛሮች በወንድ ድምፅ የሚዜም ቃል ግጥም ሲፈልጉ በማዜም ማሿራፍ እና አሿራፊዋ ድካም ሲሰማት ማገዝ ነው፡፡

አሿራፊዎች በአካባቢው በሙያቸው የታወቁ ሲሆኑ የአሿራፊነቱን ሙያ ያገኙት በልምድ ወይም በዘር ውርስ ሳይሆን በሰፈረባቸው ዛር መንፈስ ችሎታ የተወሰነ ነው፡፡ ማለትም የሰፈረባቸው ዛር በቋንቋ፣በአጎራር፣በጭፈራ ወዘተ ከሌሎች የተሻለ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ ይህን ችሎታውንም በገፈራ ክዋኔ ላይ በማሳየት አስታራቂነቱን እንደሚይዝ ሲናገር ዛር ያረፈባት ሴት በአሿራፊነት ትመረጣለች፡፡ የተመረጠችው አሿራፊ ስትሞት በእሷ ላይ የነበረው የዛር መንፈስ በችሎታው በሚወደው ሌላ የዛር መንፈስ ይተካል፡፡ ይህም የሚታወቀው በገፈራ ክዋኔ ላይ ዛሩ በሰፈረበት ሰው ላይ ሆኖ ስልጣን እንደተሰጠው ሲገልፅ ነው፡፡ ከዚያ በኂላ ይህ ዛር የሰፈረባት ሴት የአሿራፊነት ሚና ትይዛለች፡፡

አበጋር ማለት የመሪነት ወይም የአለቃነት ሚናን የሚጫወት ሰው መጠሪያ ነው፡፡ አበጋሮች በክዋኔዉ ላይ መራቂና አንዳንድ ስራዎችን አዛዥ በመሆን ሚና አላቸው፡፡ በአንድ ገፈራ ቤት አንድ አበጋር ብቻ ይሳተፋል፡፡ በሴት ገፈራ ላይ ሴት አበጋር ስትሆን በወንድ ገፈራ ላይ ደግሞ ወንድ ወይም ሴት ሊሆን እንደሚችል ተሳታፊዎች ገልጸዋል፡

ከላይ የተብራሩት ዝግጅቶች ከተጠናቀቁ በኂላ ከምሽቱ 12፡00 ሰአት ጀምሮ የገፈራ ተሳታፊዎች ከየቤታቸው ወደ ገፈራው ቤት ይመጣሉ፡፡ በገፈራ ላይ የሚሳተፍ ማንኛዉም ግለሰብ ሊወጣቸው የሚገባው ግዴታዎችና ስነ-ስርዓቶች አሉ፡፡ እነዚህን ደንቦችና ስነስርዓቶች ማንኛዉም ለአቅመ አዳም የደረሰ የማህበረሰቡ አባል የሚያውቃቸው ናቸው፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ማንኛዉም በገፈራ ላይ የሚታደም ግለሰብ ሃሳቡና ስሜቱ በሙሉ ወደ ገፈራው ዱአው ሆኖ በከፍተኛ ተመስጦና ትዕግስት ሀድራውን መከታተል አለበት፡፡
- ሁሉም ሰው ሙሉ ውዱኡ አድርጎ መምጣት አለበት፡፡ ማለትም በእስልምና ሀይማኖት የተለመደውን የእጅ፣የአፍና የአፍንጫ፣የፊት፣የክርን፣የፀጉር እና የእግር ትጥበት አከናውኖ መገኘት አለበት ፡፡ ይህን የሚያደርጉት ለሁለት

ዓላማ ሲባል ነው ። አንደኛው ዛሮች ልመናችንን የሚቀበሉን ከዉስጥም ሆነ ከላይ ንፁህ ሆነን ስንገኝ ነው ብለው ስለሚያምኑ ሲሆን ሌላው ደግሞ ክዋኔው በቡድን ስለሆነ እያንዳንዱ ሰው ንፁህ ሆኖ መቅረብ ስላለበት ነው፡ ፡ ምክንያቱም በሙቀት ሳቢያ መጥፎ ጠረን ሊፈጠር ይችላል በማለት ነው።

- ወደ ገፈራው በሚመጣበት ወቅት ግለሰቡ ከማንኛዉም ነጃሳ (ቆሻሻ) ከሚባሉ ነገሮች የራቀ መሆን ኣለበት። አንድ ሰው ተነጅሷል (ጦሀራ ወይም ንፁህ አይደለም) የሚባለው ግለሰቡን ዉሻ ከነካው፣ ራሱን ከቆሻሻ አካባቢ ሳይጠብቅ፣ሽንትቤት ሄዶ ካልታጠበ፣ ከሴት ተገናኝቶ ከመኝታ ሲነሳ ገላውን ካልታጠበ፣ወዘተ ከሆነ ነው።
- በገፈራ ወቅት ተሳታፊዎች በልባቸው ተንኮል ማሰብ የለባቸውም።
- በዋናው ግርዶሽ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው መቀመጥ የለባቸዉም፡ ፡ ወንድ በሴት ሊማረክ ሲለሚችል ጎን ለጎን ከተቀመጡ ቀልቡ ወደሷ እየሄደ የገፈራ ዱአ ላይ መሆናቸዉን ሊዘነጉ ይችላሉ።
- የተጣሉና ለክፉ የተሳሰቡ ሰዎች ካሉ በደንቡ መሰረት ራሳቸዉን እንዲያጋልጡና ይቅር እንዲባባሉ ይደረጋል። ይቅር ተባባዮቹ ይህን ለማድረግ ለገፈራው ያላቸው እምነት ይገፋፋቸዋል።
- ማንኛዉም ግለሰብ ጫማዉን ከግርዶሽ ዉጭ ማውለቅ አለበት። ምክንያቱም ጫማው ቆሻሻ ሊኖረው ሲለሚችል ከዉጭ አውልቆ ወደመሰሎቹ መቀላቀል አለበት፡
- የገፈራው ክዋኔ ሀድራ ከተጀመረ በኋላ መንጫጫት፣ ወጣ ገባ ማለትና ሌላ ነገር መስራት የተከለከለ ነው።
- በግል መጠቃቀስ ፣ መሰዳደብና የግል ጉዳይ መወያየት የተከለከለ ነው። ሁሉም ሰው ሀድራውን በተመስጦ መከታተልና መሳተፍ አለበት።

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ደንቦችና ስነ-ስርዓቶች ማንኛዉም የማህበረሰቡ አባል ቀድሞ አውቆና ተረድቶ መምጣት ይኖርበታል። ምክንያቱም ወደ ገፈራ ቤቱ ከገባ በኋላ እነዚህን ደንቦችና ስነስርዓቶች ለማስከበርና ለመቆጣጠር ዘብ የሚቆም የለም። በመሆኑም ሁሉም ባላቸው እምነት ተገፋፍተው አስፈላጊ ለሆኑና ሊወጡት ለሚገባቸው ግዴታ ሁሉ ተገዥ ከመሆን ወደኋላ አይሉም።

## ምዕራፍ አራት

## የገፈራ ክዋኔ ሀድራና ቃል ግጥሞች ምንነትና ክዋኔ

### 4.1. የሀድራ ምንነት

ሀድራ የተወሰነ መዋቅር ያለው ቅደም ተከተላዊነት የሚታይበትና የተለያዩ ትርጉም አዘል ሁነቶች ድምር ውጤት ነው፡፡ የገፈራ ሀድራ የዛር ተለማምኖ፣የቡና ስነስርዓት፣ የጉሪያ (ማጉራት)፣የራት ስነ-ስርዓት፣ የጫት ጀባታ፣ ዱአ፣ የእርፎ መረባ ምርቃት እና የጨሌ ነከራ ሂደት በአንድነት የሚፈጥሩት የከበራው የሞቀ (የደራው) ክፍል ነው፡፡ ይህም ከማታ 2፡30 እስከ ንጋቱ 12፡00 ሰአት ባለው ጊዜ የሚካሄድ ከበራ ነው፡፡ እነዚህ ሁነቶች የራሳቸውን ቅደም ተከተል ይዘው የሚከወኑ ሲሆን እንደሁኔታው በቃል ግጥም ዜማ (በዘፈን መልክ) እና በእንጉርጉሮ ስልት ይከናወናሉ፡፡ [22]

ጉሪያ[23] የሚባለው ደግሞ ዛር ያረፈባቸው ሰዎች በሀድራው ላይ ዛሩ ሲነሳ የሚያሳዩት አሀይ፣አሀይ ወይም እስስ፣አስስ የሚል ድምፅ ወይም ንግግር ያለው ውዝዋዜ ነው፡፡ ይኸውም በዛሩ ሀይል ባለ ጉዝጓዞቹ ወገባቸውን በመያዝ፣አንገታቸውን በማወዛወዝ ወዘተ ቁመው ወይም ተንበርክከው ከድምፅ ጋር የሚያደርጉት ውዝዋዜ ነው፡፡ በገፈራ ክዋኔ ላይ እንደተመለከትኩት ሁለት አይነት አጎራር አለ፡፡ እነዚህም ፊታቸውን በጉፍታቸው በመሸፈን እና ሳይሸፈኑ ማጉራት ናቸው፡፡ ተሸፍነው የሚያጎሩበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ባደረኩት ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይትም እንደተረዳሁት ዛሩ በራሱ እንዲሸፈኑ ስለሚያደርጋቸው እንጂ የተለየ ምክንያት የለውም፡፡

### 4.2. የገፈራ ቃል ግጥሞች አደራረስ፣ተስተላልፎና ክዋኔ

የዛር መንፈስ ማወደሻ ቃል ግጥሞች ተፈጥሯዊ አጋጣሚያቸው የዛር ግብር አሰጣጥ ከበራዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ አጋጣሚዎች መካከል ደግሞ አንዱ የገፈራ ከበራ መሆኑን

[22] ለዛር የሚደረግ ዝግጅት በሰአታት ተከፋፍለው የሚከወኑ መዝሙር(ዘፈን)፣ዳንስ፣የድቤ ምት፣ራስን መሳት፣ ለዛር መንፈስ የሚሰጥ ስጦታ እና መብላት መጠጣት ክንውኖች እንዳሉት (Nicole M. & Dana J., 2011, 242) "The Zar Cermony entails prolonged singing, Dancing, Drumming and Trance-like states Gift Offerings to the spirits and patient, and eating and drinking. All of this can take place over the courses of hours or days." በማለት ያስረዳሉ፡፡

[23] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርመር የአማርኛ መዝገበ ቃላት ጉሪያ ለሚለው ስም ግስ የሆነውን "አጉራ"ን በመውሰድ "ተደጋጋሚ ጩኸት አሰማ (ዛር የሰፈረበት ሰው)" በማለት ይፈታዋል፡፡(1993፣342)

ከላይ ተብራርቷል፡፡ በገፈራ ክዋኔ ወቅት ለተለያዩ የዛር መንፈሶች የቃል ግጥሞች ይፈጠራሉ፣ይዜማሉ፤ይደረደራሉ፡፡ አደራረሳቸው እንደየ ሀድራው አይነት በግልም በቡድንም ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ የዛር ግጥሞች ያለ አጋጣሚዎቻቸው ማለትም ያለተገቢ ቦታዎቻቸው እና ያለ ትክክለኛ አጋጣሚያቸው አይዜሙም ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ያለአጋጣሚዎቻቸው የዛር ግጥሞችን በሚያዜሙ ሰዎች ላይ ዛሮች ይቆጣሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ የዛር ቃል ግጥሞች እንደሌሎች ቃል ግጥሞች ሁሉ የመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው የተወሰኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም የዛር ዘፈን ቃል ግጥሞች የሚተላለፉት በቃል በመከወን ቢሆንም ሁሉም ሰው የሚያውቃቸውና በየቦታው የሚዘፈኑና የሚደረደሩ ባለመሆናቸው በስርጭታቸው (ተስተላልፏቸው) ደረጃቸው ወሰነ ሰፊ አይደሉም ፡፡

በመሆኑም በመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ወቅት ይዜማሉ፡፡የዚህ ጥናት ተተኳሪ ርዕሰ ጉዳይ በሆነው የገፈራ ክዋኔ ወቅት የዛር ቃል ግጥሞች የሚዜሙት በቅድመ ዝግጅት ጊዜ ሳይሆን በክዋኔው ሀድራ ላይና በጠረጋ (በሽኝት) ጊዜ ነው፡፡ እነዚህ ቃል ግጥሞች በአሷራፊ የሚመሩ ቢሆኑም ክዋኔያቸው የተለያየ ነው፡፡ በመሆኑም በሚከወኑበት የክዋኔ ሂደት (በሀድራው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) አንፃር በድቤ፣በማሲንቆና በጭብጨባ ታጅበው የሚዜሙ፣ በእንጉርጉሮ የሚዜሙ እና በዝግታ ንግግር(መነባንብ) የሚባሉ ናቸው፡፡ በሙዚቃ መሳሪያና በጭብጨባ የሚዜሙት የበለጠ አሳታፊ ሲሆኑ በእንጉርጉሮ የሚዜሙት ደግሞ ተሳታፊዎች አሜን በማለትና ሰውነታቸውን ከቀኝ ወደግራ ከግራ ወደቀኝ በዝግታ በማወዛወዝ ብቻ የሚሳተፉባቸው ናቸው፡፡ በንግግር አይነት የሚባሉት ደግሞ በአሷራፊ ብቻ የሚባሉ በመሆናቸው አሳታፊ አይደሉም፡፡ ከዚህ በመቀጠል ከቅድመ ዝግጅት በኋላ በሦስቱ የገፈራ ክዋኔ ቀናት የሚካሄዱ ሁነቶችን እንደሚከተለው በመተንተን አሳያለሁ፡፡

## 4.3 የገፈራ የመጀመሪያ ቀን ክዋኔ

### 4.3.1. የገፈራ ክዋኔ አጀማመር ስነ-ስርዓት

የገፈራ ተሳታፊዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ካሟሉ በኋላ ወደገፈራው ቤት እንደየ አመጣጣቸው ቅደም ተከተል ጫማቸውን እያወለቁ ይገባሉ፡፡ ይኸውም በምልከታና በቃለመጠይቅ እንዳረጋገጥኩት ለገፈራ ተሳታፊዎች የተለየ የአገባብ ህግና

ደንብ የለም፡፡ ነገር ግን እንደየ አመጣጣቸው ከገቡ በኂላ ወደ ግርዶሹ የሚገቡ ተሳታፊዎች አቀማመጣቸው የተለያየ ነው፡፡ይኸውም ባለጉዝጓዟ ለሁሉም አማካኝ በሆነ ቦታ ላይ የምትቀመጥ ሲሆን አሷራፊዋ ደግሞ ከባለጉዝጓዟ በስተቀኝ በኩል ትቀመጣለች፡፡ እንዲሁም አበጋሪት የቤቱ ምሶሶ አጠገብ ትቀመጣለች፡፡ ይህ እንደየ ቤቱ አሰራር ይወሰናል፤ የቤቱ አሰራር ምሶሶው መሀል ላይ የቆመ ከሆነ የአሷራፊዋ ቦታ ግልፅ ሲሆን ይህ ካልሆነ ግን ለቤቱ ምሶሶ ነው የተባለው ቦታ ላይ ትቀመጣለች፡፡ ምክንያቱም አበጋሪቱ ምርቃን በመስጠት ደጋፊና መሪ ስለሆነች እንደ ቤቱ ምሰሶ ትቆጠራለች፡፡ ማለትም ምሰሶ የቤት ዋና መሰረት እንደመሆኑ ምርቃትም ለገፊራው ዱአ ከፍተኛውን ሚና ስለሚይዝ ነው፡፡ ለዚህም እንደ ቃል ግጥሞቹ ሁሉ ምርቃቱም በየ ክዋኔው ላይ አለ፡፡

በምልከታየ እንደተከታተልኩት በወ/ሮ ዘሀቡ ይማም እና በወ/ሮ ከድጃ ሁሴን ቤት ምሰሶው መሀል ቋሚ ሲሆን በሌሎቹ ገፊራ ቤቶች ደግሞ ምሶሶው በግልፅ ስለማይታይ በግምት ቤቱ ምሶሶ ነው የተባለው ቦታ ለአበጋሯዋ መቀመጫ ተሰጥቷል፡፡ ሌሎች በግርዶሹ ውስጥ የሚገኙ ተሳታፊዎች ግን እንደፈለጉ ባገኙበት ይቀመጣሉ፡፡ ከግርዶሹ ውጭ ያሉ ተሳታፊዎችም የተለየና የተደነገገ አቀማመጥ የላቸውም፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች ገብተው ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኂላ በግርዶሹ ክፍል በር በቀኝ በኩል የተቀመጠች ተሳታፊ በእነሱ አጠራር "በረኛ" ወይም የመጀመሪያ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ ምክንያቱም ለማንኛውም ለሚታደል ነገር ከቀኝ ወደ ግራ ለመስጠት አመቺ እንዲሆን ነው፡፡ ከቀኝ ወደ ግራ የሚታደለውም ዱአው ያማረ (ቀኝ) እንዲሆን እንደሆነ የባህሉ ባለቤቶች ይገልፃሉ፡፡

ወንዱ አሷራፊ እና ማሲንቆ ተጫዋቹም ሀድራው ሳይሞቅና የአበጋሯን ፍቃድ ሳያገኙ ወደግርዶሹ አይገቡም፡፡ ከገቡም በኂላ ከሴት ተሳታፊዎች መሀል ሳይገቡ ዳር ላይ ጎን ለጎን ይቀመጣሉ፡፡ የወንዱ አሷራፊ ሚና በዋናነት ማሷራፍ ሳይሆን ሴቷን አሷራፊ ለማገዝ እና አንዳንድ ዛሮች የወንድ ድምፅ ስለሚወዱ ለማዜም ነው፡፡ (ቡድን ውይይት፣ 02/06/08 ቤሬ፣04/06/08 ቀርሱ፣09/06/08 ዋዚ፣16/06/08 ዋዚ፣23/06/08 ቸሪት እና 23/07/08 ዱሬ)

### 4.3.2. የገፈራ ክዋኔ ሀድራ አጀማመር

በክዋኔው አጀማመር ላይ እንደተገለፀው ሁሉም ተሳታፊዎች በተዘጋጀላቸው ክፍል ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ማታ 2:30 አካባቢ የባለጉዝጓዟ ጫሌ እና ሦስት ትንንሽ ስኒዎች ቅቤ ተሞልተው ይቀርባሉ፡፡ ከቅቤው ላይ ናትራ፣ የሀደስ ቅጠል ከነእንጨቱ እና ቀጠናዮ ይሰካሉ፡፡ ይህ የሚደረግበት ምክንያት ጥሩ ሽታ ስላላቸው ቅቤው ጥሩ ሽታ እንዲኖረው ነው፡፡ በመቀጠል ሰፌድ፣ወንፊትና ዳንቡይ (ቆሪ) ይቀርባሉ፡፡እነዚህ ካልተገኙ በሌላ ዕቃ ሊተኩ ይችላሉ፡፡ በወ/ሮ አንሻ አሊ ቤት ወንፊቱ በጎድጓዳ ሳህን እንዲሁም በወ/ሮ መይረማ እንድሪስ ቤት ሰፌዱ በትሪ መተካታቸውን ተመልክቻለሁ፡፡

ከዚያም ባለጉዝጓዟዋ እግሯን ዘርግታ እንድትቀመጥ ከተደረገች በኋላ አሏራፊዋ እነዚህን የተዘጋጁት ነገሮች ሁሉ በሰፌድ አድርጋ ባለጉዝጓዟ ጭን ላይ ታስቀምጣለች፡፡ ከዚህ በኋላ የዛር መንፈሶች ጥሪ (የዛር ተለማምኖ) በዜማ እና በእንጉርጉሮ ይጀመራል፡፡

#### 4.3.2.1. ለዛር መንፈስ የሚደረግ ተለማምኖ

ሁሉም ነገር ከተሰናዳ በኋላ የመጀመሪያው ቃል ግጥም በተለማምኖ ይጀምራል፡፡ ተለማምኖውም ወደጉሪያው (ጭፈራው) ከመገባቱ በፊት የዛር መንፈስ እንዲወርድ የግቡልን ሽምገላ የሚደረግበት የሀድራው መንደርደሪያ ሁነት ነው፡፡ ልመናው መጀመሪያ የሚደረገው ቁጥቢቱ ለተባለችው ሴት ዛር ሲሆን የተለማምኖው ግጥም የሚያተኩረው የግቢልንና ተለመኝን እና ተደሰችልን ጥሪ ላይ ነው፡፡ በቅድሚያ የሴት ዛር የሚለመንበት ምክንያትም የሁሉም ዛሮች መሪ ናት ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይኸውም በገፈራው ቤት ውስጥ የተሰበሰበው ሰው ሁሉ እሷን ለማስደሰት እንደተገኘ በመግለፅ ገብታ እንድትደሰት ፣ ባለጉዝጓዟንም ገፈራዋን እንድትቀበላት ፣ አጠቃላይ ህይወቷን እንድታሳምርላት የግብዣ ጥሪ የሚደረግበት ተለማምኖ ነው፡፡ ተለማምኖውም በእንጉርጉሮ መልክ እንደሚከተለው በአሏራፊዋ ቃል ግጥም መሪነት ይካሄዳል፡፡

አሏራፊዋ "እልል እልል" በማለት ትጀምራለች፡፡ ተሳታፊዎችም እሷን ተከትለው "እልል እልል" ይላሉ፡፡ ከዚያም አሏራፊዋ ከባለጉዝጓዟ ጭን ላይ ከተቀመጡት ቅቤዎች "እልል እልል" በማለት ባለጉዝጓዟን መቀባት ትጀምራለች፡፡ በምትቀባበት ጊዜ የሚከተለውን ተለማምኖ ድምጿን ቀነስ አድርጋ ትላለች፡፡

**እልልልል...**

እልልልል...፣
አቤት ለበይክ ብያለሁ እናቴዋ፣
ወርቂዋ ልመናዋን ልትቀበያት፣
አዎ እናቴዋ ቀየዋን ልጠቢቂላት፣
ልጆቿን ልጠብቂላት፣
አቤት ብያለሁ ወርቂዋ፣
ለማኝ ሳታጪ ለመንኩሽ፣
በሚዜ ይሁንብሽ፣ በዱበርቲ ይሁንብሽ፣
በሴት በወንዱ ይሁንብሽ እናቴዋ፣
ሙሉ ጤና ልትሰጭልኝ፣
የጤሰውን ቤት ልታደምቂልኝ፣
አቤት ብያለሁ አቤት በይኝ እናቴዋ፣
መጀን ብየ ነው እናቴዋ፣
ሊላህ ብያለሁ ወርቂዋ፣ .......[24]
አሜን

በልመናው ጊዜ የዛር መንፈሷ የተጓደለባት ነገር ካለ ትናገራለች፤እንዲመጣላት ትጠይቃለች፡፡ እኔም ተለማምኖ ሲደረግ የዛር መንፈሷ የጎደለውን በመናገር ካልተሟላልኝ አልነሳም ሲሉ በምልከታ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ለምሳሌ በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት በተደረገው ገፈራ ላይ ዛሯ ስትለመን አልነሳ ብላ አስቸግራ ከቆየች በኋላ ከጭሳጭስ ውስጥ "አደስና ምስርች የለኝም" በማለት የጎደለባትን ተናግራለች፡፡ ወዲያውም በካዳሚዎች አማካኝነት ተፈልጎ ቀርቦላት ልትነሳ ችላለች፡፡ ይህንም በባለጉዝጓዟዋ ረጅም ሳቅና ውዝዋዜ የታከለበት ጉሪያ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከዚያም አሷራፊዋ አበጋሪቱን "በሉ ይመርቁ" በማለት ተለማምኖዋን ማጠናቀቋን ትነግራለች፡፡ አበጋሯዋም ትመርቃለች፡፡

| **አበጋር** | **ተሳታፊ** |
|---|---|
| እርፎ መረባ (2 ጊዜ) | መረባ (2 ጊዜ) |
| እንግዲህ እኒህ ወርቆች | መረባ |
| ይችን አይተው፣ቀማምሰው ይታረቂት | መረባ ( በየሀረጉ መጨረሻ) |
| ቁጥቢቱ መጀን ፣ወንዘኛው መጀን | ›› |
| በእርቅ ይግቡላት | መረባ |
| ልጆቿን ተብቀው፣ርዚቋን ሰጥተው | መረባ( በየሀረጉ መጨረሻ) |

[24] ሊላህ የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን ለአላህ ስል ይቅር ብያለሁ(ይቅርታ) ማለት ነው፡፡ በዚህ አውድ አሷራፊዋ ዛሪቱ ተለማምኖዋን እንድትሰማትና ባለጉዝጓዟን ገፈራዋን እድትቀበላት ያስከፋቻት ነገር ካለ ይቅርታ እየጠየቀችላት ነው፡፡

ጤና ትሁንልን፣ቁጥቢቱ በእርቅ ትግባላት መረባ (በየዐ.ነገሩ መጨረሻ)
ደስ ይበላት፣በእኒሁ በልጆቿ ይለመኑላት ››
አላህ ያቆያት መረባ
ይሁን በይ እርፎ ይሁን(ረዘም ባለድምፅ)
እርፎ መረባ (2 ጊዜ) መረባ (2 ጊዜ)
ቀኑም ሌቱም ግጥሟ ይሁን መረባ
እናቶቿ መጀን፣ እህቶቿ መጀን መረባ(በየሀረጉ መጨረሻ)
አላህ ያሽራት፣መሻሪያዋ ይሁን መረባ(በየዐ.ነገሩ መጨረሻ)
መከበሪያዋ ይሁን፣ጤና ማግኛዋ ይሁን ››
ይሄ ቀየ እንግዲህ፣መውሊድ ማውጫዋ ይሁን መረባ(በሀረጉና በዐ.ነገሩ መጨረሻ)
ቁጥቡ መጀን፣ወንዘኛው መጀን መረባ(በየ ሀረጉ መጨረሻ)
ይሁን በይ እርፎ ይሁን ( ድምፃቸውን ረዘም በማድረግ)
እርፎ መረባ (2 ጊዜ) መረባ (2 ጊዜ)
አላህ ያቆያት፣ልጆቿ ጋር ደህና ትሁን መረባ(በየ አ.ነገሩ መጨረሻ)
የላይቷ ላይ፣በእርቅ ይግቡላት፣ ይለመኑ መረባ(በሀረጉና በዐ. ነገሮቹ መጨረሻ)
ቁጥቢቱ መጀን፣እናቶቿ መጀን፣እህቶቿ መጀን መረባ(በየሀረጉ መጨረሻ)
መሻሪያዋ ይሁን፣ልጆቿን የሚጠብቅ ይሁን፣ደህና ይሁኑላት መረባ(በየዐ.ነገሩ መጨረሻ)
ልጆቿ ጋር ሰፊ ጤና፣ረጅም ሀያት አላህ ይስጣት መረባ
ይሁን በይ እርፎ ይሁን (ድምፃቸውን ረዘም በማድረግ)

ምርቃቱ በዚህ ሁኔታ ከተመረቀ በኋላ አሏራፊዋ ድቤዋን መምታት ትጀምራለች፡ ድቤዋን እየመታችም ቁጥቢቱ የተባለችውን ዛር በማወደስ ታረቂያት፣ነይ ግቢ፣ ተደሰች በማለት ታዜማለች፡፡ ይህ ቃል ግጥም እርቅ የሚጠየቅበት ብቻ ሳይሆን ቁጥቢቱ የተሰኘችውን ዛር አለባበስና አጋጊያጥ በማንሳት የሚወደስበት ነው፡፡ ተሳታፊዎችም ግጥም በመቀበልና በማጨብጨብ ሀድራውን ያደምቁታል፡፡ ባለጉዝጓዟም ማጉራት ትጀምራለች፡፡ በምታጎራበት ጊዜ ከጭኗ ላይ የተቀመጠው እንዳይፈስ ሰፌዱ ይነሳላታል፡፡ በዚህ ጊዜ የሚዜመው ቃልግጥም እርቅ በይ እርቅበይ የተሰኘው ሲሆን እንደሚከተለው ይባላል፡፡

**አሏራፊ** **ተሳታፊዎች**

እርቅበይ እርቅበይ፣ (2 ጊዜ) እርቅበይ እርቅበይ፣ (2 ጊዜ)
እርቅበይ እርቅበይ፣ (2 ጊዜ) እርቅበይ እርቅበይ፣ (2ጊዜ)
እርቅበይ እርቅበይ፣ እርቅበይ
እርቅበይ እርቅበይ፣ እርቅበይ፣
አርቅበይ ቁጥቤዋ፣ እርቅበይ፣
ባለጉዝጓዚቱ፣ እርቅበይ፣
አንቺ ባለጨፌ፣ እርቅበይ፣
አንቺ ባለጥልፍ ቀሚስ፣ እርቅ በይ፣

| | |
|---|---|
| ባለላስታ ቅቤ፣ | እርቅበይ |
| እርቅበይ እርቅበይ፣ (2 ጊዜ) | እርቅበይ እርቅበይ፣(2ጊዜ) |
| አንቺባለ አንባር፣ | እርቅበይ፣ |
| ባለ ገፈታይቱ፣ | እርቅበይ፣ |
| እርቅበይ እርቅበይ፣ | እርቅበይ፣ |
| እርቅበይ እርቅበይ፣.. | እርቅበይ፣ |
| አዝማች | |

ይህ የቃል ግጥም ለተወሰነ ጊዜ ዛሯ እስከምትነሳ በዚህ መልኩ ይባላል፡፡ ዛሯ ስትነሳ በድንገት ባለጉዝጓዟ የቀድሞ ባህሪዋ ተለውጦ ወገቧን በመያዝ ፣ አንገቷን ወደላይ ወደታች፣ከቀኝ ወደግራ፣ከግራ ወደቀኝ በማወዛወዝ ታጎራለች፡፡ በምታጎራበት ጊዜ አይኗን ጨፍና እሽም እሽም፣ አኸይ አኸይ ፣ ዋይ ዋይ ፣ ወዘተ በማለት ከወዲያ ወዲህ እየተንቀሳቀሰች ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለች አሏራፊዋ እርቅበይ የተሰኘውን ግጥም ስትጨርስ ወዲያው ዛሪቱ ከሰው የተለየ ሩቅ ቦታ መኖሯን በመጥቀስና በማሞገስ አገሯ ወዲያ ነው የሚለውን ቃል ግጥም እንደሚከተለው ከተሳታፊዎች ጋር ማዜም ትጀምራለች፡፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፣ ማን ነው፡፡ (4ጊዜ) | አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፣(4 ጊዜ) |
| አገሯ አገሯ ወዲያእንዲያ አረቦቹ ገንዳ፡፡ (2 ጊዜ) | አገሯ አገሯ ወዲያእንዲያ አረቦቹ ገንዳ፡፡ |
| አገሯ ወዲያ ነው፣ (2 ጊዜ) | ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፡፡ (2 ጊዜ) |
| አንቺ ባለ ጨሌ፣ አንቺባለላስታ፣አንቺ ባለአልቦ፣ | ሂጂ ያለብኝ ማነው፡፡ |
| አገሯ አገሯ ወዲያነው ሂጂ ያለብኝ ማነው፣ (4ጊዜ) | አገሯ አገሯ ወዲያ፣ ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፡፡ |

ይህ የቃል ግጥም በድቤ እና በጭብጨባ ታግዞ በተደጋጋሚ እየተባለ ባለጉዝጓዟ ጉሪያዋን ትቀጥላለች፡፡ ከዚያም አሏራፊዋ እናቴዋ ወርቂዋ ሌቱን ሙሉ ሀድራሽን እናጠግብሻለን ፤ አሁን ተኮበሪ(ቁጭ በይ) ትላታለች፡፡ አልጠግብ ብላ አልቀመጥ ካለች በዛር አፍ አሏራፊዋ ድቤ እየመታችና ተሳታፊዎች እያጨበጨቡ ለተወሰነ ደቂቃ ታስጨፍራታለች፡፡ አሁንም አልቀመጥ ብላ እምቢ ካለች በዛር አፍ በዜማ ሳይሆን በንግግር መልክ እንድትቀመጥ ትለምናታለች፡፡ እሷም ጎንበስ በማለት አመስግናና ድቤውን ስማ ትቀመጣለች፡፡ እግሯን ዘርግታ ትቀመጣለች፡፡

### 4.3.3. የጨሌ ነከራ ሂደት

ስታጎራ ከጭኗ ላይ አሏራፊዋ አውርዳው የነበረው የስኒ ቅቤ፣ወንፊትና ዳንቡይ (ትንሽ ቆሪ) የያዘው ሰፌድ ተመልሶ ከጭኗ ላይ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በአሏራፊዋ አማካይነት ቅቤው በብረት ሳህን ወይም በሸክላ ድስት የከሰል ምድጃ ላይ ወይም ጋቻ ላይ

ይቀለጣል፡፡ ከቀለጠ በኋላ ጭኗ ላይ ካለው ቆሪ ላይ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በሌላ ተሳታፊ ወይም በወንዱ አሷራፊ ድቤ እየተመታና በጭብጨባ እልል እልል እልል እየተባለ ከባለጉዝጓዟ አንገት ላይ ጨሌዋ ይወጣና ከቆሪው ቅቤ ውስጥ ይነከራል፡፡ ጨሌው እንደተነከረ አሷራፊዋ እልል እልል እልል ስትል ሁሉም ተሳታፊዎች እያጨበጨቡ እልል እልል እልል ይላሉ፡፡ አሷራፊዋ ጨሌውን ከተነከረበት ቅቤ በማውጣት እልል እልል እልል እያለች የጨሌውን በግምት ¼ በሁለት እጆቿ በመያዝ የባለጉዝጓዟን ግንባር ሦስት ጊዜ በማስነካት መልሳ አንገቷ ላይ ታጠልቅላታለች፡፡ ተሳታፊዎችም አሷራፊዋን ተከትለው በማጨብጨብ እልል እልል እልል ይላሉ፡፡ ጨሌ ግንባር የሚነካበት ምክንያት ግብር ነው ተቀባበል እያሉ መዘየር ሲሆን ሦስት ጊዜ የሆነበት ምክንያት ደግሞ አንድ ጊዜ ብቻ ከሆነ ላያቸው ላይ ያሉት ዛሮች ይቆጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ በሰላምታ እንደመለማመን መሆኑን የባህሉ ባለቤቶች ያስረዳሉ፡፡

ከዚያም ካልቀለጠው ቅቤ ከጋለው ሳህን ወይም ሸክላ ላይ ቆንጠር ተደርጎ ይቀለጣል፡፡ ሲቀልጥ ቆሪው ላይ ይገለበጣል፡፡ በመቀጠል ድቤ እየተመታና እልል እልል እልል እየተባለ አሷራፊዋ መልሳ ጨሌውን ከባለጉዝጓዟ አንገት ላይ አውጥታ ከቀለጠው ቅቤ ውስጥ ትነክራለች፡፡ አሷራፊዋ ጨሌውን ከተነከረበት ቅቤ በማውጣት እልል እልል እልል እያለች የጨሌውን ¼ በመያዝ ሦስት ጊዜ ግንባሯን አስነክታ አንገቷ ላይ ታጠልቅላታለች፡፡

ይህ ሂደት ሦስት ጊዜ በተከታታይ በድቤ ፣ በጭብጨባና በእልልታ ታጅቦ ይከናወናል፡፡ አሷራፊዋ በዚህ ሂደት ሦስት ጊዜ ጨሌውን ቅቤ ከነከረች በኋላ ሰፌዱን ከባለጉዝጓዟ ጭን ላይ ሳታነሳ ቁጭ ትላለች፡፡ ከዚያም ድቤ እየመታች እልል በሉ እስቲ እልል በሉ በማለት ታዜማለች፡፡ ተሳታፊዎቹም እሷን በመቀበል በጭብጨባ እልል በሉ እስቲ እልል በሉ በማለት እንደሚከተለው ያዜማሉ፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊ** |
| --- | --- |
| እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣ | እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣ |
| እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣ (2 ጊዜ) | እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣ (2ጊዜ) |
| እልል በሉ ዛሬ ነው አሉ፣ | እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣ |

ይህ ቃል ግጥም በድቤና በጭብጨባ ታግዞ በተደጋጋሚ ከተዜመ በኋላ አሷራፊዋ ጥቁር ሻሽ እና ነጭ ሻሽ እንዲያመጡ ካዳሚዎችን ታዛለች፡፡ ከዚያም ባለጉዝጓዟ ጭን ላይ

በቆሪ የተቀመጠውን የቀለጠ ቅቤ ለባለጉዝጓዟ ፀጉር ላይ እልል እልል እልል በማለት ታፈስላታለች፡፡ ቅቤው እንዳይፈስም በጥቁሩ ሻሽ ታስርላታለች፡፡ ከዚያም ነጩን ሻሽ ከጥቁሩ ላይ ደርባ ታስርላታለች፡፡ ሁሉም ተሳታፊ እልል እልል እልል ይላል፡፡ በመቀጠል አሷራፊዋ መጀመሪያ ትንንሽ ስኒዎቹ ላይ የተሰኩትን ናትራ እና ነጭ አሩቲ ታነሳና ከባለጉዝጓዟ ሁለት ጆሮዎች ስር (በፀጉሯና በጆሮዋ መካከል) ትሰካላታለች፡፡ ከዚህ በኋላ የሚካሄደው የተሳታፊዎች ጨሌ ነከራ ሂደት ነው፡፡

ባለጉዝጓዟ ጨሌዋ ቅቤ ከተነከረና ፀጉሯን ቅቤ ከተቀባች በኋላ አሷራፊዋ ሌሎቹ ተሳታፊዎች "ጨሌ ካላቸው አምጡ ቅቤ ይነከርላችሁ" ትላለች፡፡ ጨሌ ያላቸው ተሳታፊዎች እያወለቁ ይሰጣሉ፡፡ የቀለጠ ቅቤ እንዲነከርላቸው የማይፈልጉ ባለጨሌዎች ደግሞ "አይ እኛ ቃሉውን (ያልቀለጠውን) ቅቤ ነው የምንፈልገው" በማለት ይናገራሉ፡፡ ጨሌያቸውን የሰጡት ቅቤ ይነከርላቸዋል፡፡ ያልሰጡት ደግሞ ካልቀለጠው ቅቤ እየተቆነጠረ ይሰጣቸውና ራሳቸው አውልቀው ወይም እዛው አንገታቸው ላይ እያለ ይቀቡታል (ይለቀልቁታል)፡፡ የቀለጠ ቅቤ የተነከረላቸው በአሷራፊዋ አማካይነት እልል እልል እልል በማለት የተነከሩትን ጨሌዎች በየተራ እያወጣች  በማሳየት የባለዚህ ትላለች፡፡ የጨሌዉ ባለቤት የሆነች ተሳታፊ ከተቀመጠችበት ተነስታ እስክስእስክ በማለት እንደችሎታዋ እስክስታ ትላለች፡፡ ተሳታፊዎች እልል እልል እልል እያሉ አሷራፊዋ ለሙሽራዋ እንዳደረገችው የጨሌውን ¼ በመያዝ ባለጨሌዋን ግንባሯን ሦስት ገዜ በማስነካት አንገቷ ላይ ታጠልቅላታለች፡፡ በዚህ ሁኔታ የሁሉም ባለጨሌዎች ጨሌ ይጠለቅላቸዋል፡፡ አሷራፊዋ ቅደም ተከተላዊ በሆነ አካሄድ የጨሌ ነከራውን ሂደት ካጠናቀቀች በኋላ ካዳሚዎችን የእጅ ውሀ እና ሳሙና ወይም አጃክስ  እንዲያመጡ አዛ እጇን ያስታጥቧታል፡፡ የታጠበችበትን ካዳሚዎች ውጭ ወስደው ይደፋሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የሚካሄደው የቅንጬና የቡና ስነ-ስርአት ነው፡፡

### 4.3.4 የቅንጬ (አመንካኮ) እና የቡና ስነ-ስርአት

በገፈራ ቀን  ለተሳታፊዎች የሚቀርቡ ምግቦች የራሳቸው የሆነ የአቀራረብ ቅደም ተከተል አላቸው፡፡ በመጀመሪያ የሚቀርበው ከሩዝ ወይም ከአጃ የተዘጋጀው ቅንጬ ወይም በአካባቢው አጠራር አመንካኮ ሲሆን ይህም የራሱ አቀራረብ ስርአት አለው፡፡ ይኸውም አበጋሯ ቅንጬ የያዘው ድስት ፣ጭልፋ አንድ አነስ ያለ ሳህን እና በዛ ያሉ ሰፋፊ ትሪዎች ወይም ሳህኖች እንዲቀርቡ ካዳሚዎችን ታዛለች፡፡ እነዚህ ነገሮች ከቀረቡ

በኋላ አሏራፊዋ ቢስሚላሂ ረህማን ረሂም( በአላህ ስም እጅግ ሩህሩህና አዛኝ በሆነው) በማለት ከቅንጨው አንድ ጊዜ በጭልፋ ጨልፋ ትንሹ ሳህን ላይ ታደርጋለች፡፡ ይህን የሳህን ቅንጨ ከባለጉዝጓዟ ጭን ላይ ከተቀመጠው ሰፌድ ላይ ታስቀምጣለች፡፡ ባለጉዝጓዟም ከሳህኑ ቅንጨ እየቆነጠረች ትበላለች፡፡ ባለጉዝጓዟ ቅንጨውን ከቀመሰች በኋላ አሏራፊዋ ለሌሎች ተሳታፊዎች በትሪ በትሪ እያደረገች ለአምስት ለአምስት ወይም ለሶስት ለሶስት እንዲበቃ በማድረግ መድባ ለካዳሚዎች እንዲያድሉ ትሰጣለች፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች ቅንጨውን በቡድን በቡድን ሆነው ይበላሉ፡፡ ባለጉዝጓዟ ጥቂት ሲቀራት (1-2 ጉርሻ) ወይም ያስተረፈችው ቅንጨ እዚያው ከነሳህኑ ሰፌዱ ላይ ይቀራል፡፡ ቅንጨው በዚህ አይነት ከተበላ በኋላ አበጋሯ "እንግዲህ ሁሉም ሰው ተሏረፈ አይደል አወል ቡን አፍሉ" በማለት ካዳሚዎችን ታዛለች፡፡ ካዳሚዎችም መርሀባ በማለት ስኒ በረከቦት ፣ ቀደም ብሎ ከተዘጋጀው ያልተፈጨ ቡና ፣ የባለጉዝጓዟ ጀበና፣ ስኳር ጭሳጭስ እና የቡና መቁሊያ ያቀርባሉ፡፡ ከዚያም ራህመት( እሳት) በገል ተጭሮ ጋቻው ላይ ይደረጋል ፤ ጭስ ይጨሳል፡፡ ለቡና ስነ ስርአአቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከተሰናዱ በኋላ በአንዷ ካዳሚ አማካኝነት ቡናው ይቆላል፤አጋም ሲመስል (የዶሮ አይን ሲመስል) በማውጣት ከሙሽራዋ በመጀመር ከቀኝ ወደ ግራ በማዞር ግርዶሹ ውስጥ ላሉት ተሳታፊዎች ሁሉ ታሽታለች፡፡ ቡናው ተወቅጦ ከተፈላ በኋላ ካዳሚዋ "ቡን ጀባ" በማለት አወል ቡናውን አፍልታ መጨረሷን በማብሰር ለአሏራፊዋ ቦታውን ትለቃለች፡፡ አሏራፊዋም ከተቀመጠችበት በመነሳት ከወገቧ ጎንበስ በማለት ጀበናውን በሁለት እጆቿ በተቀመጠችበት ይዛ "አወል ጀባ አወል ጀባ" ስትል አበገሯ እንደሚከተለው በማለት ምርቃኗን ትመርቃለች፡፡ አሏራፊዋ ጀበናውን ለቃ አሜን በማለት ፤ ተሳታፊዎችም ሁለት እጆቻቸውን ዘርግተው ወደታች በማንቀሳቀስ መረባ እያሉ ምርቃቱን እንዲሰምር ይመኛሉ፡፡ ባለ ጉዝጓዟም አሜን በማለት ምርቃቱን ትቀበላለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ባለጉዝጓዝና አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|---|
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| እርፎ መረባ | " | " |
| ጤናሽን አላህ ይስጥሽ | " | " |
| የላይትሽ ላይ በእርቅ ይግቡልሽ | " | " |
| ይሄ ቀየ እንግዲህ መውሊድ ማውጫ ይሁን | " | " |
| ................................ | " | " |

እርዚቁን ይዞ ጤናውን ይዞ ” ”
ዕድሜውን ይዞ ወንዘኛው ይታረቅሽ ….. ” ”
የሴቱ እመቤት የወንዱ ጌታ ” ”
ሽኾቹ መጀን ቁጥቡ መጀን ” ”
በእርቅ ይግቡልሽ ” ”
…………………….. ” ”
ይሁን በይ እርፎ አሜን ይሁን

ምርቃቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አሏራፊዋ የአበጋሯን እጅ ስማ ትቀመጣለች፡፡[25] ይህን የምታደርገውም ምርቃቱን በደስታ መቀበሏንና እንዲሳካ ምኞቷ መሆኑን እና ለአበጋሪቱ ያላትን ክብር ለመግለፅ ነው፡፡ ከዚያም ጭስ ቆንጠር አድርጋ ጋቻው ላይ ካረገች በኋላ ሁለት ስኒ ቡና ብቻ በመቅዳት ለባለጉዝጓዟ እግሯን ዘርግታ በተቀመጠችበት ትሰጣለች፡ ፡ እሷም በሁለት እጆቿ (አንዱን በቀኝ እጇ አንዱን በግራ እጇ) ትይዛለች፡፡ ከዚያም መጀመሪያ "ፉት ፉት" በማለት ትቀምስና ከቻለች ሁለቱንም ስኒ ቡና ትጠጣለች፡፡ ካልቻለች ግን አንዱን ጠጥታ ትመልሳለች፡፡ በመቀጠል አሏራፊዋ ስኳር የሚፈልግና የማይፈልገውን ተሳታፊ ጠይቃ በመለየት ቡናውን ከቀኝ ወደ ግራ ትቀዳለች፡፡ በካዳሚወቹ አማካኝነት ከበረኛይቱ በመጀመር ወደግራ ለሁሉም ተሳታፊዎች እንዳዳረሰ ይሰጣል፡፡ ከዚያም ሁለተኛ(ቶና)ና ሦስተኛ(በረካ) ቡናው ተፈልቶ በአሏራፊዋ ቀጂነት ይጠጣል፡፡ ቡናው ተጠጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ስኒዎቹና ጀበናው ታጥቦ እጣቢው በማስታጠቢያ ወይም በሌላ ሰፊ ዕቃ እንዳይደፋ ካዳሚዎች ወደጓዳ ወስደው ያስቀምጣሉ፡፡ይህ ዕጥጣቢ የገፈራው ሦስተኛ ቀን ድረስ ይቀመጣል፡፡ የቡናው ስነ-ስርአት በዚህ መልኩ ከተጠናቀቀ በኋላ የዛር መንፈስ የሹመት ስነ-ስርአት ይካሄዳል፡፡

### 4.3.5. የዛር መንፈስ ሹመት ስነ-ስርአት

የሹመት ሰነ ስርአቱ የሚደረገው ቁጥቢቱ ለተባለችው የሴት ዛር ሲሆን ሌሎች የዛር መንፈሶች እንዲገቡ ዕድል የሚፈጠርበትና ወደ ዋናው የሀድራ ስነ ስርአት መሸጋገሪያ ክዋኔ ነው፡፡ እሷ ቀድማ የተሸመችበት ምክንያት የሁሉም ዛሮች መሪ በመሆኗ እሷ ካልተሾመች ሌሎች ዛሮች መግባት ስለማይችሉ እንደሆነ የባህሉ ባለቤቶች ያስረዳሉ፡፡ (ቃ.መ፣ባለ ጉዝጓዝ ወ/ሮ መይረማ እንድሪስ፣፣2/06/08፣ቸሪት እና ሀድያ ሲራጅ፣ 27/07/08፣ዱሬ) ይህ ክዋኔ ትርጉም ባለው ቅደም ተከተላዊ ሂደት የተሞላ ሲሆን

[25] የአበጋሯን እጅ ስሞ የመቀመጡ ክዋኔ በሁሉም ምርቃቶች መጨረሻ ላይ የሚካሄድ ሲሆን በወሎ ባህል ምርቃት ከተሰጠ በኋላ የመራቂን እጅ መሳም በምርቃት ስነ-ስርአት የተለመደ ድርጊት ነው፡፡

በክዋኔው ላይ ከፍተኛውን ሚና የምትጫወተው አሷራፊዋ ናት፡፡ የክዋኔው ቅደም ተከተል እንደሚከተለው ነው፡፡

በመጀመሪያ አበጋሯ ካዳሚዎችን ቄና እንዲያመጡ ታዛለች፡፡ ቄናውን ተቀብላ ከባለጉዝጓዟ በቀኝ በኩል ታስቀምጥና ባለጉዝጓዟ ጭን ላይ ያለውን ጨሌ የተነከረበትን ቆሪ፣ ቅቤ የተቀለጠበትን ጎድጓዳ ሳህን፣ቅቤ ይዘው የነበሩትን ትንንሽ ስኒዎች እና ቅንጨ የያዘውን ሳህን የያዘውን ሰፌድ ታነሳለች፡፡ ከዚያም ከባለጉዝጓዟ ራስ በላይ ቀረብ አድርጋ ሦስት ጊዜ የሚከተለውን ተለማምኖ በንግግር በማለት ታዞራለች፡፡

እንዳትወቅሺ እንዳትነቅሺ እነሆልሽ፣
እናቴዋ ወርቄዋ ለማኝ ላታጨ ለመንኩሽ፣
በሚዜ ይሁንብሽ፣በዱበርቲ ይሁንብሽ፣
ግብርሽ እነሆልሽ፣
ተቀበያት እንዳትወቅሽ፣
..............................

ይህ ድርጊት ድግሷን የዛር መንፈሷ እንድትቀበላት ሲባል የሚደረግ ተለማምኖ ሲሆን አሷራፊዋ የተለያየ ቋንቋ የምትችል ከሆነ በምትችለው ቋንቋ ሁሉ የምትለው ነው፡፡ ካዳሚዎች ዳቦ፣ኑግ ፣ ፈንድሻ እና ሽምብራ  እንዲያመጡ ይደረግና አሷራፊዋ ሦስት ሙልሙል ዳቦ፣ኑግ፣ ሽምብራ እና ፈንድሻ ቄናው ላይ ታደርጋለች፡፡ ከዚያም ሰፌዱን ቄናው ላይ ይከደንና ነጭ ኩታ(ነጠላ) ወይም ጋቢ ይሸፈናል፡፡ ይህን ቅደም ተከተላዊ ክንውን ካጠናቀቀች በኋላ አሷራፊዋ “ይሄው እንግዲህ ተሾመች እልል እልል እልል” በማለት ታበስራለች፡፡ ተሳታፊዋችም “እልል እልል እልል” በማለት የሹመት ብስራቱን ያስተጋባሉ፡፡ የገፈራው ሦስተኛ ቀን ድረስ እንደተሸፈነ ይቀመጣል፡፡

በስነ-ስርአቱ ላይ እንደሚታየው ባለጉዝጓዟ ከጨሌ ነከራ እስከ ሹመት ስነ-ስርአቱ ድረስ ሰፌዱንና ሰፌዱ ላይ ያሉትን ነገሮች ጭኗ ላይ ተሸክማ ቆይታለች፡፡ ይህ የሆነበትን ምክንያት የባህሉ ከዋኞች ሴቷ ዛር የሹመት ስነስርአቱን መቀበሏን ለማረጋገጥ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ መቀበሏን የሚያረጋግጡትም ባለ ጉዝጓዟ ሀድራው እርቅ በይ እርቅ በይ በሚለው ቃል ግጥም ሲጀመር ተነስታ በማጉራቷ(በመጨፈሯ)ና የሹመት ክንውኑ ሲካሄድ ምንም የእንቢኝታ( ፍቃደኛ አለመሆን) እንቅስቃሴም ሆነ ድምፅ ባለማሰማቷ ነው፡፡ ከሹመት ስነስርአቱ በኋላ ጭኗ ላይ ያለው ሰፌድ ወርዶላታል ፤ የደገሰችው ድግስም ቀርቦላት አድርሳለች፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኋላ በነፃነት መጨፈር(ማጉራት)

የምትችልበት መንገድ ተጠርጎላታል፡፡ በዚህ ክዋኔ ላይ ቁጥቢቱ የተባለችው ዛር ተሷርፋለች ፤ተደስታለች ማለትም ዛሪቱ ተለምናለች ፣ጨሌው ተነክሯል፣አወል ቡናው ከተጠጣ በኋላ የዳቦና የጥራጥሬ ድግሱ ተሰጥቷታል( ተሹማ ተቀምጣለች)፡፡

ስለዚህ ሹመት የሚባለው ቁጥቢቱ የተባለችው ከሁሉም የዛር አይነቶች በፊት ቀድማ የምትገኝ መሆኗ እና የበላይነቷ የሚረጋገጥበት የክዋኔ ሂደት ነው፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ከወንድ ዛር ይልቅ የሴት ዛር(ቁጥቢቱ) መሪነትንና የበላይነትን እንዲሁም ማህበረሰቡ ለሴት ዛር ያለው ክብር ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ ምክንያቱም እሷ ከተቆጣች ለበሽታ አጋልጣ ትሰጣለችም ተብሎ ሲለሚታመን ነው፡፡ ይህ የዛር መንፈስ ሹመት ከተጠናቀቀ በኋላ የራት ስነ ስርአቱ ይቀጥላል፡፡

## 4.3.6. የራት ስነ-ስርአት ፣ የጫት ጀባታ፣ዱአ እና የሙዳ ስነ-ስርአት

የራት ስነ ስርአቱን ለመጀመር ካዳሚዎች ግርዶሹ ውስጥ ያሉትን ተሳታፊዎች እጅ ያስታጥባሉ፡፡ አበጋሯ "በሉ ማድ(ምግብ) ይቅረብ" ስትል በባለጉዝጓዟ ልጅ፣ምራት፣ ወይም ሰራተኛ እና በካዳሚ አማካይነት እንጀራ በምስር ወጥ ለአምስት ለአምስት ወይም ለሦስት ለሦስት የሚጠጣ ውሀ ጋር ይቀርባል፡፡ ሁሉም ተሳታፊ ምግቡን ከበሉ በኋላ በካዳሚዎች ማድ ይነሳል ፤ እጅም ያስታጥባሉ፡፡ ራት ከተበላ በኋላ የገፈራ ተሳታፊዎች (የቡድኑ) የጋራ መገልገያ በሆነው ትልቅ ጀበና በቅድመ ዝግጅት ጊዜ ከተዘጋጀው የተፈጨ ቡና ለሁለተኛ ጊዜ አወል ቡን በካዳሚ ይፈላል፡፡ ከዚህ ጀምሮ የሚፈላው ቡና እና ሻይ የሚቀዳው በአሷራፊዋ ሳይሆን በካዳሚ ነው፡፡ ካዳሚዋ "አወል ጀባ አወል ጀባ" በማለት ጀበናውን ጎንበስ ብላ እንደመያዝ ታደርጋለች፡፡ አበጋሯም ምርቃን ትሰጣለች፡፡ ካዳሚዋም ጀበናውን ለቃ፣ተሳታፊዎችም ምርቃኑን ይቀበላሉ፡

የቡና ቁርስ የሚሆን ዳቦ በካዳሚ ይቀርባል፡፡ በአሷራፊቱ ወይም በአበጋሪቱ ዳቦው ቢስሚላሂ ረህማን ረሂም ተብሎ ከተቆረሰ በኋላ ካዳሚዎች ከበረኛይቱ በመጀመር ለሁሉም ተሳታፊ ያዳርሳሉ፡፡ ከዚያም እንደ መጀመሪያው የአወል ቡና ስነስርአት አወሉ( የመጀመሪያው ቡና) ከተጠጣ በኋላ በባለጉዝጓዚቱ የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ወይም በባል ጫት ይጀባል (ይቀርባል)፡፡ እነዚህ ሁለቱ ከሌሉ በሌላ ቅርብ ወንድ ዘመድ ጫቱ ይቀርባል፡፡ ጫቱ የሚጀባው ለአበጋሯ ሲሆን ጀቢው ጫቱን እንደታሰረ በሁለት እጆቹ ይዞ ከወገቡ ጎንበስ በማለት "ጫት ጀባ ቀንበጥ ጀባ" ይላል፡፡ አበጋሯም "መርሀባ"

በማለት ምርቃቷን በ “እርፎ መረባ” ትጀምራለች፡፡ ባለጉዝጓዟ እና ጫት የጀባው ሰው በቁሙ ከወገቡ ጎንበስ ብሎ አሜን አሜን በማለት ምርቃቱን ሲቀበሉ ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ “መረባ” በማለት አወንታ(የይሁንታ) ቃል ያሰማሉ፡፡ የእርፎ መረባ ምርቃቱ በአንድ ይሁን ፣በሁለት ይሁን ፣በሦስት ይሁን እየተባለ ሦስት ጊዜ ይመረቃል፡፡ ለአብነት በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት የተካሄደው ገፈራ ክዋኔ ላይ ጫት የጀባው የመጀመሪያ ወንድ ልጇ የሆነው መሀመድ አሊ ሲሆን ፋጡማ ሰይድ ቤት ደግሞ ባልተቤቷ የሆኑት ሀሰን አህመድ ናቸው፡፡ በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት የነበረው ክዋኔ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| **አበጋሪት** | **ጫት ጀቢውና ባለጉዝጓዟ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|---|
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| የዛሬው ቀን ላንተም ግጥም | አሜን | |
| ለእናትህም ግጥም አላህ ያድርገው | አሜን | መረባ |
| በአውራጫው አላህ ያሽርህ | ” | ” |
| ጤና ጀባ እናትህም ደህና ትሁንልህ.... | ” | ” |
| የብር ቤት ፣የጤና ቤት፣ያማረ ቤት ይሁን | ” | ” |
| ሸኾቹ መጀን፣ቁጥቡ መጀን፣ደጋጎቹ መጀን | ” | ” |
| በልግ ከመኸር ይግጠምህ.......... | ” | ” |
| ይሁን በይ እርፎ | አሜን | ይሁን |
| በሁለት ይሁን ማግኛህ ዛሬ ይሁን | አሜን | ይሁን |
| ......................................... | | |
| የራበውን አጉርስበት፣የጠማውን አጠጣበት | | |
| የታረዘውን አልብስበት አላህ ያቆይህ......... | | |
| ይሁን በይ እርፎ | አሜን | ይሁን |
| በሦስት ይሁን ማግኛህ ዛሬ ይሁን | ” | ” |
| ሁሉም ግጥምህ ይሁን........... | ” | ” |
| ይሁን በይ እርፎ | አሜን | ይሁን |

ጫት የጀባው ተመራቂ የአበጋሯን እጅ ስሞ ይቀመጣል፡፡ ምርቃቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ወንዱ አሏራፊ እና ማሲንቆ ተጫዋቹ ወደ ግርዶሹ እንዲገቡ አበጋሯ ትፈቅዳለች፡፡ ከዚያም ነገያ ነገያ የተሰኘው ቃል ግጥም በድቤ በጭብጨባ ታግዞ እንደሚከተለው ይዜማል፡፡ ይህ ቃል ግጥም ሀድራው አማን(ሰላም) ይሁን በማለት በዜማ ዱአ የሚያደርጉበት ነው፡፡ ይህንንም ነገያ የሚለው የኦሮምኛ ቃል ሰላም ከሚለው ፍቺ እንረዳለን፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊ** |
|---|---|
| ነገያ ነገያ፣ (2 ጊዜ) | ነገይ ነገያ (2 ጊዜ) |
| ነገያ አለሚቱ፣ | ” |
| ነገያ ቁጥቢቱ፣ | ” |
| አዝማች | |
| ነገያ በይላት ፣ | ” |
| ነገያ አሁን ነው፣…………….. | ” |
| ነገይ ነገያ፣ (2 ጊዜ) | ” |
| ነገያ ወንዘኛው፣ | ” |
| ነገያ ነገያ ፣ | ” |
| ነገያ ሦስት ነው | ” |
| በአራተኛውማ ጠቅልሎ መሄድ ነው፡፡ | ” |
| ነገያነገያ፣ | |
| ይሁን      አሜን | ይሁን |

ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ያህል ይህ ቃል ግጥም ከተዜመ በኂላ አበጋሯ ትመርቃለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ተሳታፊ** |
|---|---|
| እርፎ መረባ | መረባ |
| እርፎ መረባ | መረባ |
| አላህ ያሽራችሁ፣ደስ ይበላችሁ | ” |
| ቁጥቡ መጀን ወንዘኛው መጀን | ” |
| ሁሉም ይታረቃችሁ | ” |
| በላስታው ሻሩ | ” |
| አላህ ያሽራች | ” |
| አብራቸሁ ሻሩ | ” |
| እሷም ደህና ትሁንልን | ” |
| ልጆቿም ደህና ይሁኑልን | ” |
| አማን አላህ ያድርገን | ” |
| ይሄ ቀየ ይሻር | ” |
| ……………………………… | |
| ይሄ ሀድራ እንግዲህ ያማረ ይሁን | ” |
| የገባንበት ሰቀላ የተቀመጥንበት ነጠላ ግጥም ያድርገን | ” |
| ….ይሁን በይ እርፎ | ይሁን |

ከምርቃት በኂላ ነገያ ነገያ የሚለው ቃልግጥም በድጋሜ እየተዜመ ሳለ አበጋሪቱ የጫቱን እስር(ቋጠሮ) ትፈታና ሦስት ጊዜ ቆንጥራ ለባለጉዝጓዟ ትሰጣታለች ፤ እሷ በርሀባ በማለት ትቀበላለች፡፡ ከዚያም ሁለቱን ቁንጥር ለራሷ አስቀርታ አንዱን ቁንጥር

ለባሏ ትሰጣለች። ባል ከሌላት ደግሞ ለወንድ ልጇ ትሰጣለች ፤ ይህ ካልሆነ ደግሞ ጫቱን ለጀባው ቅርብ ዘመዷ ትሰጣለች።

አበጋሪቱ በነገያ ነገያ ግጥም ታጅባ ጫት ማደሏን ትቀጥላለች። ከሙሽራዋ ቀጥላ ለበረኛይቱ ቆንጥራ ትሰጣለች ፤ በረኛይቱም ከተቀመጠችበት በመቆም ትቀበላለች። በዚህ ሁኔታ ከቀኝ ወደ ግራ ለሁሉም ተሳታፊ ጫቱን ታዳርሳለች። ጫቱ እየተቃመ የነገያ ነገያ ዜማው ይቀጥላል። በአጠቃላይ ሦስት ጊዜ "ነገያ ነገያ" የሚዜም ሲሆን ከእያንዳንዱ ዜማ በኋላ አበጋሯ ምርቃን ትሰጣለች። የዛር መንፈስ በዚህ ዜማ ከተነሳ ባለጉዝጓዟ ተነስታ ታጎራለች። በዚህ ዜማ ሙሽራዋም ሌሎችም ዛር ያለባቸው ሰዎች ለተወሰነ ጊዜ ካጎሩ በኋላ ሲቀመጡ አበጋሯ "ከላይም ከታችም ያላችሁ እሳት የፈጃችሁ ፣ ስትመጡ እሾህ የወጋችሁ ካላችሁ አውፉ በሉን፣ አውፍ እንባባል እና እንቃም፣ አላህ ያሸራቸው ፀጥ ብለን እንቃም ፣ ዱአ እናድርግ።" በማለት በተለያዩ ጉዳዮች የተጣሉ ካሉ በቀልባቸው ይቅር እንዲሉ በመንገር ለተሳታፊዎቹ ሁሉ የዱአ ሰአት መሆኑን ታሳውቃለች። ይህ ዱአ በቡድን ሚካሄድ ሳይሆን በየግል በዝምታ(በተመስጦ) የሚካሄድ ነው። ዱአው ለተወሰነ ደቂቃ (ከ5-10 ደቂቃ) ከተደረገ በኋላ አበጋሯ ሴት ዛሯ ከባለ ጉዝጓዟ ላይ በሽታን፣ችግርን፣መጥፎ ነገርን ወዘተ እንድታስወግድላት ከሌላው ምርቃት በተለየ "አንሺ" የሚል የማስወገጃ (ማባረሪያ) ቃል ያለውን ምርቃት እንደሚከተለው ትመርቃለች።

| **አበጋሪት** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እረፎ መረባ (2 ጊዜ) | መረባ (2 ጊዜ) |
| መጥፎ ነገርን ያዥላት | መረባ |
| በላን አንሺላት | አንሺ |
| እንግዲህ ዛሬ ከማጀቷ አውጭላት | አንሺ |
| ጫት ቅሜም አላምጬም | አንሺ |
| እንግዲህ ሞኝ ነገርን አባሪላት | አንሺ |
| እዚያው ጣይላት | አንሺ |
| .................. | ........... |
| አንሺ እፍ አንሺ እፍ | አንሺ እፍ አንሺ እፍ (በእጃቸው ምልክት በማሳየት) |

የባለጉዝጓዟን ህመምና ችግሮች ሴቷ ዛር እንድታነሳላት የሚያደርጉበት ምርቃት መዝጊያው "አንሺ እፍ አንሺ እፍ" የሚል ሲሆን በሽታና ችግሮቿ ይነሱ(ይወገዱ)

ማለትን ያመለክታል፡፡ይህ ምርቃት እንደተጠናቀቀ "አማን አውለን አማን አውለን" የሚለው ቃል ግጥም በድቤ እና ጭብጨባ በሚከተለው ስልት ይዜማል፡፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| አማን አውለን አማን አውለን፣ | አማን አውለን አማን አውለን፣ |
| አሚን አማን አውለን፣ | አሚን አማን አውለን፣ |
| አማን አውለን አማን አውለን፣ | አማን አውለን አማን አውለን፣ |
| አሚን አማን አውለን፡፡ | አሚን አማን አውለን፡፡ |
| አዝማች | |

ይህ ቃል ግጥም ከሁለት እስከ ሦስት ደቂቃ የሚዜም ሲሆን በሰላምና በጤና የገፈራ ስርአቱን እንዲያካሂዱ ልዕለ ተፈጥሯዊ ሀይልን የሚማፀኑበት ነው፡፡ በቃል ግጥሙ ላይ ተደጋግሞ የሚሰማው "አማን አውለን" የሚለው ዜማ ሲሆን አማን የሚለው ቃል ሰላም ማለት ነው፡፡ እዚህ ላይ የገፈራ ክዋኔው የሚካሄደው ሌሊቱን ሙሉ ሆኖ ሳለ እንዴትና ለምን አውለን ይባላል የሚል ጥያቄ ማንሳቱ የማይቀር ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የገፈራ ተሳታፊዎች እንደሚገልፁት የረፍትና የዕንቅልፍ ጊዜያቸውን መስዕዋት አድርገው ምሽቱን እንደቀን ቆጥረው ክዋኔውን ስለሚያካሂዱ ወቅቱ ለተርታው ህዝብ ምሽት ቢሆንም ለእነሱ ግን ቀን (ብርሀን) ነው፡፡ ስለዚህ እንደማምሻ ሳይሆን እንደውሎ የሚቆጥሩት ነው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ሉባባ ሁሴን፣01/06/08ዓ.ም)

ይህ የልመና ቃል ግጥም እየተዜመ ሳለ ምንም አይነት ጉሪያ የለም ምክንያቱም ተለማምኖው ለዛሩ የሚደረገው ለዛር መንፈስ ሳይሆን ለፈጣሪያቸው(አሏህ) በመሆኑ ነው፡፡ ቃል ግጥሙ ሲያልቅ አበጋሯ እንደሚከተለው ትመርቃለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እርፎ መረባ | መረባ |
| እርፎ መረባ | መረባ |
| እንግዲህ ዛሬ አላህ ያሽርልን | መረባ |
| ጤናውም ክብረቱም እርዚቁም እዚሁ ቤት ይሁን | መረባ |
| ……….ይሁን በይ እርፎ | ይሁን |

በሴት ሰሀቦች( በእስልምና ሀይማኖት ታሪክ የሚታወቁ ታላላቅ ሰዎች) ስም በመጥራትና በማወደስ ሴት ዛሯ ወደ ሀድራው እንድትገባ ዕድል የሚሰጥና የሚፈቅድ ቃል ግጥም ያለ ድቤ መዜም ይጀምራል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች እንደተባሉ ድቤ እየተመታና እየተጨበጨበ ቃል ግጥሙም ተሳታፊዎቹ አሏራፊዋ የምትለውን እየተቀበሉ እንደሚከተለው ይከወናል፡፡

**አሏራፊ** **ተሳታፊዎች**

ግቡ ግቡ አሚናት (2 ጊዜ) ግቡ ግቡ አሚናት (2 ጊዜ)
የሰይዳችን እናት ግቡ ግቡ አሚናት የሰይዳችን እናት ግቡ ግቡ አሚናት
ግቡ ግቡ መይረሙ (2 ጊዜ) ግቡ ግቡ መይረሙ (2 ጊዜ)
አላህ ሊያሽረን ከህመሙ ግቡ ግቡ መይረሙ አላህ ሊያሽረን ከህመሙ ግቡ ግቡ መይረሙ
ግቡ ግቡ ፋጢማ (2 ጊዜ) ግቡ ግቡ ፋጢማ (2 ጊዜ)
የአውገረዶቹ ኢማማ ግቡ ግቡ ፋጢማ የአውገረዶቹ ኢማማ ግቡ ግቡ ፋጢማ
ግቡግቡ ሀዋየ (2 ጊዜ) ግቡግቡ ሀዋየ (2 ጊዜ)
ዱአችን ይሁን የለየ ግቡግቡ ሀዋየ................

በዚህ ግጥም ጊዜ ጊዜ ሀድራው በጣም የሚደምቅበትና የተለያዩ የዛር መንፈስ አይነቶች ወደ ሀድራው የሚቀላቀሉበት በመሆኑ አውዱ ይበልጥ ይደምቃል፡፡ ቃል ግጥሙ በድቤና በጭብጨባ ታግዞ በደመቀ ሁኔታ ከተዜመ በኂላ ሁለተኛው ቡና (ቶና) በካዳሚ ይቀርባል፡፡ አበጋሯ እንደሚከተለው ምርቃት ትሰጣለች ካዳሚዋም ምርቃቱ ሲያልቅ ትቀዳለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እርፎ መረባ | መረባ |
| እርፎ መረባ | መረባ |
| ቁጥቡ መጀን ወንዘኛው መጀን… | መረባ |
| ዕድሜ ጀባ ጤና ጀባ | መረባ |
| ክፉ አይንካህ ደግ አይለፍህ……… | መረባ |
| ይሁን በይ አርፎ | ይሁን |

ቶናው ተጠጥቶ ሲጠናቀቅ አማንየ አማኔው ነብየ በማለት የሚዜመው ቃል ግጥም ይጀመራል፡፡ ይህ ቃል ግጥም ደግሞ በእስልምና ሀይማኖት በመልዕክተኛነት (በነብይነት) የሚታወቁትንና ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸውን መሀመድ(ሰ.ዐ.ወ)ን የሚያነሳ ነው፡፡ በግጥሙ ውስጥ አማንየ የሚለውን ቃል ተከትለው ተደጋግሞ የሚመጡት ስሞች ነብይ እና ሰይዲና መሀመድ ናቸው፡፡ ሰይዲ የነብዩ መሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) ሌላው ስማቸው ሲሆንነብይ የሚለው ደግሞ የመልዕክተኝነታቸው መጠሪያ ስያሜ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ቃል ግጥም ጫት ቅመው ወደ ሞቀ ሀድራ ከመግባታቸው በፊት ከላይ ፈጣሪያቸውን አላህን ሰላም አድርገን ብለው እንደጠየቁበት ቃል ግጥም ሁሉ ነብዩ(ሰ.ዐ.ወ)ን ሰላም አድርጉን በማለት በሙገሳ የሚለምኑበት እና ታሪካቸውንም የሚያነሱበት ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ቃል ግጥም ላይም የዛር መንፈሶች ጥሪና ሙገሳ

ባለመኖሩ ምንም አይነት ጉሪያ(ማጓራት) አይታይም፡፡ ቃል ግጥሙ በድቤና በጭጭብጨባ ታግዞ እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| አሷራፊ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| አማንየ አማኔው ነብየ፣ (2 ጊዜ) | አማንየ አማኔው ነብየ፣ |
| አማኔው አማኔው አማኔው ነብየ፣ (2 ጊዜ) | አማንየ አማኔው ነብየ፣ |
| አማኔው አማኔው አማኔው ሰይዲ፣ | አማንየ አማኔው ነብየ፣ |
| አማኔው አማኔው አማኔው መሀመድ፣ | አማንየ አማኔው ነብየ፣ |
| ሄደች ግመሊቱ…………………….. | |

ይህ ቃል ግጥም ለተወሰነ ጊዜ (ከ4-5 ደቂቃ) ሲዜም ከቆየ በኂላ ያቆሙና ካዳሚዋ ሦስተኛና የመጨረሻውን ቡና (በረካ) ያቀርባሉ አበጋሯ እንደሚከተለው ትመርቅና ካዳሚዋ ትቀዳለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እርፎ መረባ | መረባ |
| እርፎ መረባ | መረባ |
| እንግዲህ ዛሬ ጨርሶ ትሻር | መረባ |
| ጤና ጀባ፣ዕድሜም ጀባ፣እርዚቅም ጀባ፣ደግ ከራማ ጀባ | ” |
| ይሄ ቃየ እንግዲህ ያማረ ቤት ይሁን | ” |
| ልጆቿም ደህና ይሁኑ | ” |
| ይሄ ቃየ እንግዲህ ለራበው ማጉረሻ፣ለታረዘው ማልበሻ ይሁን | ” |
| ………………………… | |
| ይሁን በይ እርፎ | ይሁን |

በረካው ተጠጥቶ እንዳለቀ ባለጉዝጓዧ እግሯን ዘርግታ በተቀመጠችበት በአጉሎ ቅጠል ተጠቀልሎ በፌስታል የታሰረ ቃሉ(ያልቀለጠ) ቅቤ ፌስታሉን ፈትታ በመግለጥ በሁለት እጇ ይዛ ለአበጋሯ ከነፌስታሉ “ሙዳ ጀባ” ትላለች፡፡ አበጋሯም “መረሀባ” ብላ ከተቀበለች በኂላ እንደሚከተለው ሙሽራዋን መርቃ ለሚጁ ሴት እንድታድል ትሰጣለች፡ ፡ ሚጁ ማለት የመጀመሪያ ባሏን ያልፈታች፤ ከመጀመሪያ ባሏ ጋር በመኖር ላይ ያለች ሴት ናት፡፡

| **አበጋሪት** | **ባለ ጉዝጓዝ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|---|
| እርፎ በረባ | አሜን | መረባ |
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| በዚሁ በሙዳው አላህ ያሸርሽ | ” | ” |
| በጥንድ ውለጂ | ” | ” |

ሽኾቹ መጀን፣ቁጥቡ መጀን ” ”
ይታረቁሽ በእርቅ ይግቡልሽ ” ”
ፍሬው የአንቺ ይሁን ” ”
እርዚቅሽ ብዙ ይሁን ከራማሽ ጥሩ ይሁን ” ”
……………………………………..
ይሁን በይ እርፎ አሜን ይሁን

አበጋሯ በዚህ መልኩ ከመረቀች በኋላ “ሙዳ ጀባ” በማለት ለፈለገችው የመጀመሪያ ባሏን ላልፈታች ሴት “ሚጁ ጀባ” እንቺ አንቺ እደይ ብላ በሁለት እጇ ትሰጣታለች፡፡ ሚጁዋም መርሀባ በማለት ተቀብላ ለአበጋሪቱ ሦስት ጊዜ ቆንጥራ ትሰጣታለች፡፡ ከዚያም ግርዶሹ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በአይኗ ቆጥራ ቅቤውን ለባለጉዝጓዟ አስቀርታ እዚያው ፌስታሉ ላይ ቆንጥራ በመመጠን በቁጥራቸው ልክ ትመድባለች፡፡ መድባ ስትጨርስ ጫቱ እተቃመ ፤ቂምሀ እንደተቀመጡ (ዱዓ እያደረጉ) ከበረኛይቱ ጀምራ ከቀኝ ወደግራ ሁሉንም በእጇ ታድላለች፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች ከተቀመጡበት በመቆም በእጃቸው ወይም እንድትቀባቸው ፀጉራቸውን ገለጥ በማድረግ ይቀበላሉ፡፡ ለሁሉም ካዳረሰች በኋላ አዳረሰልኝ በማለት ተሳታፊዎችን ትጠይቃለች ፤ ሁሉም በአንድ ላይ አዎ ይላሉ፡፡ ሚጁዋ ለአበጋሯ ብቻ ሦስት ቁንጥር ለሌሎቹ ተሳታፊዎች አንድ አንድ ቁንጥር ቅቤ የሰጠችበት ምክንያት አበጋሯ ከሌሎቹ በበለጠ በአካባቢው የተከበረች መሆኗን ለማሳየት እንደሆነ የባህሉ ባለቤቶች ይገልፃሉ፡፡

ከዚያም እንደቆመች ያደለችበትን ፌስታል እና ለባለ ጉዝጓዟ ያስቀረችውን ቅቤ ይዛ በማሳየት አሜን አሜን አሜን ትላለች፡፡ ከዚያም ከበረኛይቱ ጀምራ ከቀኝ ወደ ግራ የያዘችውን በማዞር አሜን አሜን አሜን እያለች ታሳያለች ከዚያ ሁሉም በየፊታቸው ይዛ ስትመጣ እስስ እስስ ፣ኡስስ ኡስስ፣አላህ ያሸራት፣አላህ ያሸራት እስስ እስስ ይላሉ፡፡ ይህንም ማለት ሁሉም ይስማማሽ ይቀበሉሽ፣ፈውስ አግኚ ማለት እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ይገልፃሉ፡፡ (ከቡድን ውይይት ፣ 23 /07/08፣ ዱሬ)

ሁሉም ግርዶሹ ውስጥ ያሉ ተሳታፊዎች ይህን ድርጊት ካከናወኑ በኋላ የቀረውን ቅቤ ባለጉዝጓዟ አናት ላይ ታደርግላታለች፡፡ ከካዳሚዎቹ አንዷ ለእጇ ዉሀና ሳሙና በማምጣት ታስታጥባታለች፤እጣቢውንም ወደ ውጭ ትደፋለች፡፡ ሚጁዋ ቅቤ እደላውን እንደጨረሰች እጇን ታጥባ ወደ ቂምሀው(ዱዓው) ትቀላቀላለች፤ ጫት መቃሟን ትጀምራለች፡፡

ከዚህ በኋላ ሀድራው በአሙማ በአሙማ ቃል ግጥም እንደገና ይጀምራል፡፡ ሀድራውን የምትጀምረው አሷራፊቱ ስትሆን ድቤውን እየመታች አሙማ አሙማ ስትል ተሳታፊዎችም በጭብጨባ አሙማ አሙማ በማለት ይቀበሏታል፡፡ ባለ ጉዝጓዟም ተነስታ ማጉራት ትጀምራለች፣ሌሎችም ዛር የሰፈረባቸው ተሳታፊዎች እየተነሱ ያጎራሉ፡፡ ሀድራዉ እንደገና ይደራል፤አውዱም ይደምቃል፡፡ የቀል ግጥሙ ክዋኔ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| አሙማ አሙማ (4 ጊዜ) | አሙማ አሙማ (4 ጊዜ) |
| አሙማ አሙማ ለሙዳው | ›› |
| አሙማ አሙማ ቅጥቢቱ አዝማች | ›› |
| ባለዝጓዚቱ አሙማ አሙማ | ›› |
| አሙማ በይላት… | ›› |

በዚህ ቃል ግጥም ላይ አሙማ መፍጠን (ቶሎ መምጣት) ማለት ሲሆን ሴቷን ዛር በፍጥነት(አምመሽ) በባለ ጉዝጓዟ ላይ ነይ በማለት በሙገሳ የሚጠሩበት ቃል ግጥም ነው፡፡ አሷራፊዋ ይህን ቃል ግጥም ከመራች በኋላ ድቤውን ለወንዱ አሷራፊ በመስጠት የአሷራፊነቱን ሚና ለወንዱ ትሰጣለች፡፡ እዚህ ላይ ባለጉዝጓዟ ተነስታ ካላጎራች ወንዱ አሷራፊ ድቤውን እየመታ እሷ እርቅበይ እርቅበይ የተሰኘውን ቃል ግጥም ታዜማለች፡፡ ተሳታፊዎች በጭብጨባ እየተቀበሉ፣አሷራፊውም ግጥም እየተቀበለና ድቤውን እየመታ ያዜማል፡፡ ይህ ቃል ግጥም ብዙም ሳይቆይ አሙማ አሙማ በሚለው ቃል ግጥም ሲቀየር ባለጉዝጓዟ ተነስታ ታጎራለች፡፡ እምቢ ብሎ የዛር መንፈሱ ካልተነሳና ካላጎራች አሚን አሚን አሚን እየተባለ  በደመቀ ሀድራ ይዜማል፡፡ በዚህ ቃል ግጥም ያልተቆጣች ዛር ከሆነች ትነሳለች፤ ማለትም የማትነሳው ግጥሙን ያልፈለገች ከሆነ ነው፡፡  (ከቃ.መ፣አበጋሪት ወ/ሮ አሚናት አሊ 01/06/08፣ቤሬ)

በምልከታም ማረጋገጥ እንደቻልኩት በወ/ሮ አረጋሽ ቤት በተካሄደው የገፈራ ክዋኔ ላይ የዛር መንፈሱ በአሙማ አሙማ እና በእርቅበይ እርቅበይ አልነሳ ብላ በአሚን አሚን ልትነሳ ችላለች፡፡ በሌሎቹ የገፈራ ክዋኔዎች ላይ ግን አላጋጠመኝም፡፡ የቃልግጥሙ አካሄድ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| አሏራፊ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| አሜን አሜን አሜን፣ (8 ጊዜ) | አሜን አሜን አሜን፣ (8 ጊዜ) |
| አሜን እማማየ፣ | አሜን አሜን አሜን፣ |
| አሜን አሜን አሜን፣ | አሜን አሜን አሜን፣ |
| አንቺ ባለሙዳ፣ | አሜን አሜን አሜን፣ |
| .............................. | አሜን አሜን አሜን፣ |
| እልልልል | እልልልል |

በዚህ ቃል ግጥም ዛሩ ይነሳና ባለጉዝጓዧ ተነስታ ታጎራለች፡፡ ሌሎችም ተሳታፊዎች ተነስተው ያጎራሉ፡፡ ቃል ግጥሙ ለተወሰነ ጊዜ ከተዜመ በኋላ እልል እልል ተብሎ ይቋጫል፡፡ በመቀጠል የአወል ቡና ስነ-ስርአት ይጀመራል፡፡ ይህ ቡና በክዋኔ ሂደት ውስጥ ከሚፈሉት ሌሎች የቡና ስርአቶች የተለየ ነው፡፡ ይኸውም የቡና ስርአቱ ሁለተኛ(ቶና) እና ሦስተኛ(በረካ) ቡና የለውም፡፡ እንዲሁም ከምርቃን በተጨማሪ ቡናው የሚቀዳው በሌሎቹ የቡና ስርአቶች ላይ የማይዜም ቃል ግጥም ከተዜመለት በኋላ ነው፡ ፡ አወል ቡናው በካዳሚዎች ይቀርባል ፤ ካዳሚዋ አወል ጀባ አወል ጀባ በማለት አቦል ቡና መቅረቡን ታሳውቃለች፡፡ አበገሯ እንደሚከተለው ባለጉዝጓዧንና ቤተሰቦቿን ትመርቃለች፡፡

| አበጋሪት | ባለጉዝጓዝ | ተሳታፊዎች |
|---|---|---|
| እርፎ መረባ | አሜን | ይሁን |
| እርፎ መረባ | አሜን | ይሁን |
| የዛሬው ቀን ግጥማቸው ይሁን | ” | ” |
| ወንዘኛው መጀን ፣ይሄ ቀየ መጀን | ” | ” |
| እህቶቿ መጀን፣ወንድሞቿ መጀን | ” | ” |
| አላህ ያሸራት…………….. | ” | ” |
| ይቺ ቁጥብ እንግዲህ ቀማምሳ የምታኮብር ትሁን … | | ” |
| ይሁን በይ እርፎ | አሜን | ይሁን |

ቡናው ከመቀዳቱ በፊት ድቤ፣ማሲንቆና ጭብጨባ ሳይኖር አወሉ ነቢ የሚለው ቃል ግጥም በዜማ ብቻ በሴቷ አሏራፊ መሪነት እንደሚከተለው ይባላል፡፡

| አሏራፊ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| አወሉ ነቢ፣ | አወሉ ነቢ |
| አወሉ ነቢ፣ | አወሉ ነቢ |
| አወሉ ሹሙ፣ | አወሉ ነቢ |

አወሉ ጌታው
አወሉ ነቢየ ኸረ አወሉ ጌታው፣ አወሉ ነቢ
አወሉ ነቢየ ኸረ አወሉ ሹሙ፣...... "
ነቢ እለዋለው፣ ....... "
ወዲያ ማዶ ሂዶ አነሳው መደዱን "
አረግዋ አህመድ ቤት ያውቁታል መንገዱን፡፡... "
አዝማች
.............................. አወሉ ነቢ( ረዘም ባለ ድምፅ)

ይህ ቃል ግጥም የአወሉን(የመጀመሪያውን) ቡና መድረስ በማብሰር ወንዶቹን ዛሮች የሚያነሳ ነው፡፡ ከዚህ ቃል ግጥም በኋላ አሷራፊዋ ቡናው አይበቃ እንደሆነ አቦሉ ይሙላ ጥቂት መርቁ ስትል አበጋሯ የሚከተለውን ትመርቃለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ባለ ጉዝጓዝ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|---|
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| አወሉ ሞላ | አሜን | መረባ |
| የሞላ ጤና እዚህ ቤት ይሁን | አሜን | መረባ |
| የሞላ ዱኒያ እዚህ ቤት ይሁን | " | " |
| ሰፊ ማድ እዚህ ቤት ይሁን | " | " |
| ልጆቿ ጋር ግጥም አላህ ያድርጋት | " | " |
| ................................... | | |
| ይሁን በይ እቴ | አሜን | ይሁን |

ቡናው በካዳሚዋ ተቀድቶ ሁሉም ተሳታፊ ይጠጣል፡፡ ሴቷ ዛር በዚህ መልኩ ከገባች በኋላ ቀጥሎ ወንዱ ዛር እንዲገባ የተለያዩ የሙገሳ ቃል ግጥሞች ይዜሙለታል፡፡ በመጀመሪያ እንዲገባ የሚጠራው በአካባቢው አለ ተብሎ በሰፊው የሚታወቀውና የተለመደው ወንዘኛው የተባለው ዛር ነው፡፡ ቁጥብ ማለት በአካባቢው ሰዎች አገላለፅ በቅርብ በዚያ አካባቢ አዘውትሮ የሚገኝ ሁሉን ማድረግ የሚችል ጠባቂ መንፈስ ነው፡፡ ሴቷም ሆነ ወንዱ ዛር በዚህ ቃል የሚጠሩት ይጠራሉ፡፡

በመሆኑም ይህን ዛር አርሂብ ወንዘኛው እያሉ እንደሚከተለው በማወደስ ሲጠሩትና ሲጋብዙት ወደ ሀድራው ይገባል፡፡ ይህ ቃል ግጥም የሀድራ ግብዣ የሚሰጥ መሆኑን አርሂብ ከሚለው ቃል መረዳት ይቻላል፡፡ ባለጉዝጓዟም ማጉራት ትጀምራለች፤በዚህም መግባቱ ይታወቃል፡፡ ቃል ግጥሙም እንሚከተለው በሴቷ አሷራፊ መሪነት ይዜማል፡፡

| አዟራፊ | ተሳታፊዎች |
| --- | --- |
| አርሂብ ወንዘኛው (4 ጊዜ) | አርሂብ ወንዘኛው (4 ጊዜ) |
| አስኪ ልነሳና አዝግሜ ልሩጠው | አርሂብ ወንዘኛው |
| አገኘው እንደሆን … | አርሂብ ወንዘኛው |
| እሱ የሚሄደው ጎራ ለጎራ ነው | ” |
| ጎራ ለጎራ ነው እሱ የሚሄደው | ” |
| ወገርትና ወይራ አጭሱ የሚለው… | ” |

ይህ ቃል ግጥም በድቤና በጭብጨባ ታግዞ ሲዜም ባለጉዝጓዟ ተነስታ ታጎራለች፡፡ በዚህም ወንዘኛው መግባቱ ስለሚታወቅ ማሲንቆ ይመታል፡፡ በማሲንቆ፣በድቤና በጭብጨባ ሲዜም ሀድራው ይሞቃል፡፡ ሀድራው በድካም ወይም በሌላ ምክንያት ከቀዘቀዘ ሙሽራዋ ማጉራቷን ታቆማለች፡፡ በዚህ ጊዜ ድቤው ብቻ ከቀድሞው በተለየ አመታት ለተወሰነ (1-2 ደቂቃ) ከተመታ በኋላ እንዲነሳ አወልያው መርሀባ በለን እየተባለ ይዜምለታል፡፡ የቃል ግጥሙ ትርጉምም እሺ በለን፣ተነሳና ጨፍርልን ማለት ነው፡፡ ይህ አጋጣሚ የተከሰተው በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ፣ በወ/ሮ ፋጡማ ኢብራሂምና በወ/ሮ አሚናት አሊ ቤት ሲሆን በሌሎቹ ቤት ግን አልተከሰተም፡፡ ቃል ግጥሙም እንደሚከተለው ሲዜም ከጥቂት ቆይታ በኋላ ዛሩ ተቀስቅሶ ባለጉዝጓዟ ተነስታ ልታጎራ ችላለች፡፡

| አዟራፊ | ተሳታፊዎች |
| --- | --- |
| አውሊያው መረሀባ በለን | አውሊያው መረሀባ በለን |
| አውሊያው መረሀባ በለን | አውሊያው መረሀባ በለን |
| አዝማች | |

ዛሩ ተነስቶ ባለጉዝጓዝ ስታጎራ ሀድራው ቃል ግጥሙን በመደገገም ይደምቃል፡፡ በዚህ ቃል ግጥም ባለጉዝጓዟ ሲበቃት ሀውሴው አሞራ መናኘ ቶሎ ና በሉልኝ በማለት የሚከተለው ቃል ግጥም እንዲቀየር ታደርጋለች፡፡ ማሲንቆ ተጫዋቹም የማሲንቆውን አመታት በመቀየር ጥቂት ከመታ በኋላ አዟራፊዋ የማሲንቆውን ምት ተከትላ ወዲያው ቃል ግጥሙን መምራት ትጀምራለች፡፡

| አዟራፊ | ተሳታፊ |
| --- | --- |
| ሀውሴው አሞራ መናኘ ቶሎ ና (4 ጊዜ) | ሀውሴው አሞራ (4 ጊዜ) |
| ሀውሴው አሞራ የወደዱት ጋራ | ሀውሴው አሞራ |
| ሀውሴው አሞራ ገዳዩ ናና | ገዳዩ ናና |
| ሀውሴው አሞራ መናኘ ናና | መናኘ ናና |
| አዝማች | |

ይህ ቃል ግጥም ተለምኖ ወደ ሀድራው የገባዉ የዛር መንፈስ ከሀዋሳ አካባቢ የመጣ በረኸኛ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ዛሩ ጨፍሮ ሲበቃው ሀድራው በማሲንቆ፣ በድቤና በጭብጭባ ብቻ ለተወሰነ ደቂቃ (2-3 ደቂቃ) ይቆይና በድጋሜ ዛሩ ሲነሳ እንደምን ውልሀል እየተባለ ደህንነትን በመጠየቅ ሰላምታ የሚሰጥ ቃል ግጥም እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| **አሷረፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እንደምን ውልሀል (4 ጊዜ) | ውልሀል ወይ (4 ጊዜ) |
| ውልሀል ይለሉ ውልሀል ወይ | ውልሀል ወይ |
| አዝማች | |

ከዚህ ቃል ግጥም ጀምሮ የተለያዩ ቃል ግጥሞች በድቤ፣በማሲንቆ እና በጭብጨባ ስለሚዜሙ ሀድራው በጣም ይደምቃል፡፡ ከሚዜሙት ቃል ግጥሞች ውስጥ አብዛኞቹ በዛር አፍ በአሷራፊዋ መሪነት የሚባሉ ሲሆኑ ከአማርኛ ቃል ግጥሞቹ ውስጥ አዘዞ ነው ቤቷ ፣ እሰየው እሰየው ነብይ ፣አሜን አሜን፣...የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

አዘዞ ነው ቤቷ የሚለው ቃል ግጥም ለሴቷ ዛር (ለቁጥቢቱ) የሚባል ሲሆን ተክለ ሰውነቷን፣አለባበስና አጋጊያጧ በማንሳት የሚያሞግሱበት ነው፡፡ እንዲሁም ከሩቅ ሀገር የመጣች መሆኗን በሰሜን ጎንደር የሚገኘውን አገር (አዘዞ) በመጥቀስ ይገልፃሉ፡፡ ይህንንም በድቤ፣በማሲንቆና በጭብጨባ በመታገዝ እንደሚከተለው ያዜማሉ፡፡ ባለጉዝጓዚቱና ቃል ግጥሙ የተስማማቸው የዛር መንፈስ ያረፈባቸው ተሳተፊዎችም በመነሳት ያጎራሉ፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| አዘዞ ነው ቤቷ አዘዞ ነው ቤቷ | አዘዞ ነው ቤቷ |
| አዘዞ ነው ቤቷ ያምረው አንገቷ | አዘዞ ነው ቤቷ |
| አዘዞ ነው ቤቷ ባለብር አንባሯ | አዘዞ ነው ቤቷ |
| አዘዞ ነው ቤቷ ያምራል ቀለበቷ | ” |
| አዘዞ ነው ቤቷ ባለጉዝጓዚቱ | ” |
| አዘዞ ነው ቤቷ ይቺ ባለሙዳ | ” |
| አዘዞ ነው ቤቷ የኔ መድሀኒቴ | ” |
| እየው እየው መላ (2 ጊዜ)... | ” |
| አዝማች | |

ከዚህ በኋላ የሚጀምረው ኧረ ምነው ኧረ ምነው የተሰኘው ቃል ግጥም ነው፡፡ ይህ ቃል ግጥም በእንጉርጉሮ የሚዜም ሲሆን ጭብጨባ፣በድቤና ማሲንቆ የለውም፡፡ ቃል ግጥሙ የሚዜመው ለወንዱ ዛር ሲሆን ሴቷ ዛር ተሏርፋ (ጭፈራውን ጠግባ) ስትቀመጥ እሱ ደግሞ እንዲነሳ እና ባለጉዝጓዚቱንና ሌሎቹን እንዲያስጎራ የሚለምኑበት ነው፡፡ ይህንም በተቀመጡበት ከወገባቸው በላይ በዝግታ ወደቀኝና ወደግራ በመወዛወዝ እንደሚከተለው ያዜማሉ፡፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
| --- | --- |
| ኧረም ነው ኧረ ምነው | አሜን(ረዘም ባለ ድምፅ) |
| አሜን አሜን አሜን አሜን | አሜን |
| ኧረ ምነው እኔ ኧረ ምነው እኔ (4 ጊዜ) … | አሜን (4 ጊዜ) |
| አዝማች | |
| ምንጊዜ መጣና አንቺየ ምንግዜ ደረሰ | አሜን |
| አሜን አሜን አሜን | አሜን |
| በጠዋት ጥመድና በጊዜ ፍታቸው | ” |
| የሰው አገሮች በሮች(በሬዎች) እራትም የላቸው | ” |
| እስከ መቼ ድረስ አንቺየዋ እክክ ብየው | ” |
| በጊዜ ሄደ አሉ ሳልሰበስበው… | ” |
| አሜን አሜን አሜን | ” |
| እወዲያ በር ሆኖ የሚያዳምጠው | ” |
| ወንዘኛው አውልያው ቁጥቡ እንደምን ነው | ” |
| አሰላም አለይኩም እስኪ እንበለው | ” |
| አሜን አሜን አሜን | ” |
| አዝማች | |
| ………………………… | ” |

የዛር መንፈሱ ተነስቶ ሲያጎራ የእንጉርጉሮው ቃል ግጥም እሰየው እሰየው ነቢ በሚል ቃል ግጥም ይተካል፡፡ ቃል ግጥሙ በጭብጨባ፣ በድቤና በማሲንቆ የታጀበ ሲሆን የነብዩ መሀመድ(ሰ.ዐ.ወ)ን ስም ከዛር መንፈሱ ጋር የሚያነሳ ነው፡፡ ይህ ሆነበት ምክንያትም የዛር መንፈሶች የነብያትን የደጋግ ሰዎችን ስም ሲያነሱላቸው ይወዳሉ ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ተሳታፊዎቹ ይገልፃሉ፡፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
| --- | --- |
| እሰየው እሰየው ነቢ (2 ጊዜ) | እሰይ ነቢ |
| እሰይ ነቢ ነቢ | እሰይ ነቢ |
| እሰየው ነቢየ (4 ጊዜ) | ” |
| እሰየው ነቢየ የጦይባው ሙሽራ | ” |

ላነሳሳው እንጂ እንደምን ልረፍ (2 ጊዜ) ”
እላይ እታች ብየ እከተላለሁ ”
የላይ ቤሬ ቁጥብ አዳኙ እንዴት ነሁ… ”
አዝማች

በቃል ግጥሙ ውስጥ የጦይባው ሙሽራ በመባል የተጠራው ነብዩ መሀመድ(ሰ.ዐ.ወ) ሲሆን በእስልምና ሀይማኖት ተሪክ እንደሚታወቀው ነብዩ በሳዑዲ አረብያ ሀገር መዲና (ጦይባ) በመባል ምትጠራው ከተማ የተወለዱና የከተማዋም ገዥም ነበሩ፡፡ በመሆኑም በቃል ግጥሙ ውስጥ ሙሽራ የሚለው ቃል በሀገሪቱ የተከበሩ ነቢይ መሆናቸውን የገለፁበት ቃል እንጂ ለዛር መንፈሱ የተሰጠ መጠሪያ አይደለም፡፡ ከዚህ በመቀጠል የመጡት ሦስት ተከታታይ ስንኞች ግን ለዛር መንፈሱ የተገጠሙ ናቸው፡፡ ይኸውም የዛር መንፈሱን ያለ መሰልቸት በሙገሳ ማንሳትና የሚፈልገውን ማድረግ እንደሚገባ “የላይ ቤሬ ቁጥብ አዳኙ እንዴት ነሁ” በማለት ደህንነቱን የጠየቁበት ነው፡፡ ቁጥብ እና አዳኙ የሚሉት የዛር መንፈሱ መጠሪያ ስሞች ሲሆኑ ቤሬ የሚለው ደግሞ ገፈራ የተደረገበት የፊቶ ቀበሌ አንድ ጎጥ ስም ነው፡፡ በመሆኑም ዛር የሰፈረባቸው ሰዎች ቤሬ ለሚገኘው የዛር መንፈስ ችግራቸውን ሁሉ በመንገር መፍትሄ እንደሚያገኙም በቃል ግጥሙ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| … አንድ ፈረስ ነበር እንደኔ የከፋው | እሰይ ነቢ |
| የሆዴን ባዋየው ለሁሉም ካልተፋው | እሰይ ነቢ |
| እዚያው ቤሬ ወርዶ በመንታው በመንታው | እሰይ ነቢ |
| እሰይ ነቢ ነቢ እሰየው ነቢየ … | እሰይ ነቢ… |

ቤሬ የተባለው ጎጥ መልክዓ ምድራዊ ሁኔታው ረግረጋማና ለምለም እንደሆነና ይህ አካባቢም ሆነ የወረባቦ ወረዳ በአጠቃላይ የትልልቅ ሰዎች (ሸኾች) መገኛ በመሆኑ መጥፎ(ተንኮል) ለመስራት እንደሚያስፈራ በቃል ግጥሙ ያሳውቃሉ፡፡ አያይዘውም የገፈራ ስነ-ስርአት በሚደረግበት ቤት በዚያ አካባቢ ያሉ አንዳንድ ሰዎች ባህሉን በማጥላላትና በሀይማኖት ተፅዕኖ ምክንያት እንደማይገኙና ከሌላ ሩቅ አካባቢ ግን ዱአ ለማድረግ የሚመጡ እንዳሉ የገፈራን ሀድራ ጥቅም በትርጎ ተምሳሌትነት እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

| አሷራፊ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| … ኸረ ቤሬ በሬ ቤሬ ረግረጉ | እሰይ ነቢ |
| እንኳን ስፍራውና ያስፈራል አገሩ | እሰይ ነቢ |
| እሰየው እሰየው ነቢ (2 ጊዜ) | እሰይ ነቢ |
| ቤሬ ላይ ያለው ትርጎው አፍርቶ | እሰይ ነቢ |
| የሩቁ ይበላል የቅርቡ ተኝቶ ….. | እሰይ ነቢ |

በእነዚህ ቃል ግጥሞች ሀድራው መሞቁንና ሙሉ በሙሉ መግባቱንም የሚከተለውን ቃል ግጥም 4-5 ደቂቃ ያህል በድቤ፣በማሲንቆና በጭብቸባ በመደጋገም እያዜሙ ይገልፃሉ፡፡ ዘው አለ የሚለው ቃልም ሀድራው በጉሪያ አውዱን እንዳደመቀውና እንደገባ ይገልፃል፡፡

| አሷራፊ | ተሳተፊዎች |
|---|---|
| ዘው አለ ሀድራው ዘው አለ | ዘው አለ ሀድራው ዘው አለ |
| ዘው አለ ሀድራው ዘው አለ | ዘው አለ ሀድራው ዘው አለ |

ሀድራው ሲደራ በአውዱ ላይ የሚያጎሩት ተሳታፊዎች ከአራትና ከአምስት ያላነሱ ሲሆኑ በቃል ግጥም ምርጫና በተለያዩ አለመስማማቶች ለምሳሌ ከልባቸው ይቅር ሳይባባሉ ቂም (ጎሚ ሆነው) ወደ ሀድራው የገቡ ዛር የሰፈረባቸው ሰዎች ከሆኑ በጥል የሚፈጠር የዛር እርስበርስ ግጭት (መሰዳደብ) ይኖራል፡፡ ይህ ግጭትም በአሷራፊ አማካይነት በዛር አፍ በማነጋገርና የተጣሉትን ዛሮች የሚፈልጉትን አይነት ቃል ግጥም በየተራ እንደሚባልላቸው በመንገር ይፈታል፡፡ የሀድራው መሪዎች በየተራ ወንዱና ሴቷ አሷራፊዎች ናቸው፡፡ ለሰአታት ጭፈራው ከደራ በኋላ አሷራፊዋ በዛር አፍ እንዲቀመጡ ትለምናቸዋለች፤ እነሱም ጎንበስ በማለት አመስግነው እና ድቤ ወይም ማሲንቆ ስመው ይቀመጣሉ፡፡

ከዚህ የሞቀ ሀድራ በኋላ በካዳሚዋ ሻይ በጀበና በማቅረብ ማር ጀባ ማርጀባ ስትል አጭር ምርቃት አበጋሯ ትመርቃለች፡፡

| አበጋር | ባለ ጉዝጓዝ | ተሳታፊዎች |
|---|---|---|
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| እርፎ መረባ | አሜን | መረባ |
| ማር ይሁን ቀለብሽ | አሜን | መረባ |
| ጤና ጀባ፣ እርዚቅ ጀባ፣ ዕድሜም ጀባ | አሜን | መረባ |
| ልጆቿ ጋር በደስታ ትኑር | ” | ” |
| ማሩም ከጓሮ ይቆረጥ | ” | ” |

| | | |
|---|---|---|
| ሆ ብላ ትምጣ | ” | ” |
| ቁጥቡ መጀን ወንዘኛው መጀን ከጓሮ ይቁረጡ | ” | ” |
| እሷም ትሻር | ” | ” |
| …………………. | | |
| ይሄ ቤት እንግዲህ በማሩ ይሻር | ” | ” |
| ይሁን በይ እርፎ | አሜን | ይሁን |

ምርቃቱ እንዳለቀ ሻይው ሳይቀዳ በፊት በወንዱ አሷራፊ መሪነት ማሯ ፈላላት እተባለ በድቤና በጭብጨባ ለተወሰነ ጊዜ (4-5 ደቂቃ) በተደጋጋሚ እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| አሷራፊ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| እልል በሉላት ማሯ ፈላላት | ማሯ ፈላላት |
| እልል በሉላት | ማሯ ፈላላት |
| እልል በሉላት ማሯ ፈላላት | ማሯ ፈላላት |
| አዝማች | |

ከዚያም በካዳሚዋ ሻይው ተቀድቶ ሁሉም ተሳታፊ ይጠጣል፡፡ ከሻይ መስተንግዶ በኂላ ሀድራው ከሁለት እስከ ሦስት ደቂቃ በድቤ፣ማሲንቆና ጭብጨባ ብቻ(ያለቃል ግጥም) ለሚጀመረው ቃል ግጥም እንደመንደርደሪያ ይቆያል፡፡ ከዚያም ወንዱ ዛር ወደ ሀድራው እንዲገባ በሴቷ አሷራፊ ጀማሪነት እንደሚከተለው በድቤና በጭብጨባ ቃል ግጥም ይጋበዛል፡፡

| አሷራፊ | ተሳታፊዎች |
|---|---|
| ናማ ናማ ናማ ናማ (4 ጊዜ) | ናማ ናማ ናማ |
| ኧረ ናማ ናማ (2 ጊዜ) | ናማ ናማ ናማ |
| ወደ ሀድራው ና ግባማ | ” |
| ናልኝ ናልኝ ናልኝ | ” |
| ና ወደ እኔ ግባማ | ” |
| ምን የድርግልሀል የቆንጆ ጎደሎ | ” |
| ናማ ናማ ናማ ናማ…………. | ” |
| አዝማች | |

ቃል ግጥሙ በሴቷ አሷራፊ ሲመራ ዛሩ ካልተነሳ ወንዱ አሷረፊ በመቀበል እንደሚከተለው ይመራል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ዛሮች የወንድ ድምፅ ይወዳሉ ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ተሳታፊቹ ይገልፃሉ፡፡ “እኔ የማሷርፈው ላያቸው ላይ ያለው ጋዝ በሴቷ አሷራፊ ዜማ አልነሳ ሲል ነው፡፡ ለምሳሌ ያው ማታ እንዳየሽው በእሷ አልነሳ ብሎ ናማ ናማ ናማ እያልኩ ሳዜምለት ነው ተነሳው፡፡” (ቃ.መ፣አሷራፊ አብዱ ረያን፣

01/06/08፣ቤሬ) ይህ አጋጣሚ የተከሰተው በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት ሲሆን በሌሎቹ ገፈራ ቤቶች ግን አላጋጠመኝም።

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| ናማ ናማ ናማ ናማ (4 ጊዜ) | ናማ ናማ ናማ |
| ናማ ናማ ናማ ወደ እኔ ግባማ | ናማ ናማ ናማ |
| ናማ ናማ ናማ ሀይለኛ ሲመጣ የለው መመለሻ | ” |
| ናማ ናማ ናማ … | ” |
| አዝማች | |

የዛር መንፈሱ ለማጉራት ሲነሳ የወንድ ዛር ውዳሴ ቃል ግጥም በሴቷ አሏራፊ ይጀመራል። ቃል ግጥሙም እንደምነው ነብይ(ነቢ) የሚል ሲሆን ነብዩ መሀመድን(ሰ.ዐ.ወ) የሚያነሳ ነው። እንዲሁም የዛር መንፈሱን ዉበት፣አለባበስና አጨፋፈር በማድነቅ በማሲንቆ፣ በድቤና በጭብጨባ የሚዜም ነው። የቃል ግጥሙ አካሄድ እንደሚከተለው ነው።

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እንደምነው ነቢ (4ጊዜ) | እንደምነው ነቢ (4 ጊዜ) |
| እንዴት ነህ ልበለው | ” |
| የጦይባው ሙሽራ የጦይባው ሽሪፍ | ” |
| እንደምን ነው ነቢ (2 ጊዜ) | ” |
| ጥርሱን ጉራማይሌ የተወቀረው | ” |
| ባለቡራቡሬ በሳቅ ተጫዋቹ | ” |
| አዳኙ እንዴት ነው… | ” |

ከዚያም ጉሪያው ሲነሳ ይህ ቃል ግጥም ሀድራው ኑር አለበት በተሰኘው ቃል ግጥም ይተካል። ኑር የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን ብርሀን ማለት ነው በመሆኑም ይህ ቃል ግጥም ደግሞ የሀድራውን መድመቅ የሚገልፅ ነው። በተጨማሪም ገፈራው የሚካሄድበት ጎጥ (አካባቢ) ልጆችና የዛር መንፈሱን በመጥቀስ ያወድሳሉ። እንዲሁም በገፈራ ሀድራ የታመመ ሁሉ ፈውስ እንደሚያገኝ የሚገልፅ ነው። ቃል ግጥሙ በድቤና በጭብጨባ ታግዞ በደመቀ ድባብ እንደሚከተለው ይዜማል።

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| ሀድራው ኑር አለበት (2 ጊዜ) | ሀድራው ኑር አለበት (2 ጊዜ) |
| የላይ ቤሬ ልጆች ቆንጆ ሲውልበት | ” |
| ሀድራው ኑር አለበት (2 ጊዜ) | ” |
| የዚህ ሀገር በሬ ጠይሙ ጠይሙ | ” |

የእርጎ ፍርፋሪ የሚመስለው ጢሙ…　　　　　"
የሀድራ ጭብጦ ይዟል በቀኝ እጁ　　　　　"
አለ ወጣ ገባ ሊሰጥ ለወዳጁ　　　　　"
ኧረ ቤሬ ቤሬ በሬ አሻረችው　　　　　"
የታመመውን ሁሉ ሻር እያደረገችው…　　　　　"
አዝማች

ለአብነት ከተጠቀሰው ከዚህ ቃል ግጥም ላይ የቤሬ አካባቢ ልጆች ቆንጆዎችና በገፈራ ክዋኔ ላይ ባላቸው የነቃ ተሳትፎ ሀድራ አድማቂዎች መሆናቸው ተገልጿል፡፡ እንዲሁም የዛር መንፈሱ ጢሙ የሽበተ መሆኑን ከእርጎ ንጣት ጋር በማነፃፀር የሚነግር ሲሆን የዛሩን በዕድሜ የገፋ መሆን (አንጋፋነት) የሚገልፅ ነው፡፡ ይህም ማለት የዛር መንፈሱ በአካባቢው ጥንት ጀምሮ የነበረና ግብር ሲገበርለት የኖረ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲሁም የዛር መንፈሱ እንደ ሰው ልጅ ሁሉ ያረጃል ማለት ሳይሆን የተከበረና ግርማሞገስ ያለው መሆኑን የሚገልፅ ነው፡፡

በዚህ ቃል ግጥም ወንዱ ዛር ጨፍሮ በበቃኝ ድቤውን ስሞ ሲቀመጥ ሴቷ አሏራፊ የቁጥቢቱ ሀድራ ይጀመር ትላለች፡፡ የሴቷ ዛር ሀድራ የሚጀመረው ወደ ሀድራው እንትገባ በሚጋብዝና ከበረሀ የመጣች መሆኗን በሚገልፅ ቃል ግጥም ነው፡፡ ይህም ለአንድ ደቂቃ የድቤ ምት ብቻ እንደመንደርደሪያ ይቆይና ወንዱ አሏራፊ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ(እህቱ) የሚለው ቃል ግጥም መምራት ይጀምራል፡፡ ከዚያም ቃል ግጥሙ ጥቂት በእሱ ከተመራ በኋላ የመሪነት ሚናውን ሴቷ አሏራፊ ትረከባለች፡፡ በሴቷ አሏራፊ መሪነትም ቃል ግጥሙ በድቤና በጭብጨባ እንደሚከተለው ይዜማል፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊ** |
|---|---|
| የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ | የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይእቱ ነይ እቱ |
| የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ | የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ |

ይህ ቃል ግጥም ብዙም ሳይቆይ ተመሳሳይ ይዘት ባለው ነይ ነይ በረኸኘት የተሰኘው ቃል ግጥም በወንዱ አሏራፊ ይጀመራል፡፡ ተሳታፊዎችና ሴቷ አሏራፊ በጭብጨባና ግጥም እየተቀበሉ አሏራፊው ድቤውን በመምታትና ግጥሙን በመምራት ሀድራውን ያደምቃሉ፡፡ ሀድራው ሲሞቅ ባለ ጉዝጓዟ ተነስታ ታጎራለች ፤ቃል ግጥሙም ይበልጥ በደመቀ ሁኔታ አሏራፊው በዜማም በእንጉርጉሮም መልክ እየቀያየረ ይዜማል፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎች ዛር ያለባቸው ተሳታፊዎች (ከ 3 እና 4 ያላነሱ) በመነሳት ከሙሽራዋ ጋር

ያጎራሉ፡፡ አንዳንዶቹ በዛር አፍ እተናገሩ ፣ እርስ በርስም እየተሰዳደቡ ሀድራውን ያደምቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሀድራውም የተለያዩ ዛሮች ስለሚነሱ ማሲንቆ መጨዋት ይጀምራል፡፡ ቃል ግጥሙም እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| ነይ ነይ በረሽኝት (4ጊዜ) | ነይ ነይ በረሽኝት (4ጊዜ) |
| ነይ ነይ በረሽኝት (4ጊዜ) | ነይ ነይ በረሽኝት (4ጊዜ) |

ጉሪያው (ጭፈራው) በድቤ፣በማሲንቆ እና በጭብጨባ ታጅቦ ይቀጥላል፡፡ ሙሽረዋ በዚህ ቃል ግጥም አጉርታ ሲበቃት ማሲንቆ ስማ ስትቀመጥ ቃልግጥሙ በወንዱ አሷራፊ ለሙና ለሙና በሚል ቃልግጥም ይተካል፡፡ ለሙና ውበትን ለማድነቅ የሚጠቀሙበት ቃል ነው፡፡ ሲሆን ቃል ግጥሙ ሴቷንና ወንዱን ዛር የሚያሞግስ ሲሆን ውበታቸውን የሚያደንቅ ይዘት አለው፡፡ ይህ ቃል ግጥም በተመሳሳይ ድባብ እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| ለሙና ለሙና | አሀይ ለሙና |
| ለሙና ለሙና ሸጋው ናና | አሀይ ለሙና |
| ለሙና ለሙና አንቺየዋ | አሀይ ለሙና |
| ለሙና ለሙና ለሙና ታምራለች | አሀይ ለሙና |
| አዝማች | |
| በመኪናው መንገድ በኮረሪማው | ” |
| አንቺን ተከትየ ይብላኝ አሞራው ለሙንየ | ” |
| ለሙና ለሙና ለሙንየ… | ” |
| አዝማች | |

ለተወሰነ ጊዜ በዚህ ቃል ግጥም ከተጎራ በኋላ ሀድራውን ጠግባ ስትቀመጥ ቃል ግጥሙ በሴቷ አሷራፊ መሪነት በወለል በይ ወለል በይ ይተካል፡፡ ቃል ግጥሙ ሴቷን ዛር የሚያሞግስ ሲሆን በድጋሜ ወደሀድራው እንድትቀላቀል የሚጋብዝ ነው፡፡ ይህ ቃል ግጥም ደግሞ በድቤና በጭብጨባ እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊ** |
|---|---|
| ወለል በይ ወለል በይ (2 ጊዜ) | ወለል በይ ወለል በይ (2 ጊዜ) |
| ወለል በይ አንቺየ ወለል በይ ወለል በይ | ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ |
| ባለ ጉዝጓዚቱ ወለል በይ ወለል በይ | ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ |
| አንቺ ባለ ጨፌ ወለል በይ ወለል በይ | ወለል በይ ወለል በይ(2 ጊዜ) |
| ወለል በይ አንቺየ ከነ አባወራሽ… | ……………………… |
| አዝማች | |

ይህ ቃል ግጥም ለተወሰነ ጊዜ ከተባለ በኋላ ሀድራው በድቤና በማሲንቆ ብቻ ይደምቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ባለጉዝጓዚቱ ተነስታ ታጎራለች፤ሌሎችም ዛር የሰፈረባቸው ተሳታፊዎች ወደ ሀድራው ይቀላቀላሉ፡፡ በአረጋሽ አህመድ ቤት ባለመስማማት የሚፈጠር የዛሮች የርስ በርስ ግጭት ተከስቷል፡፡ ይህ ግጭት የተፈጠረው በአዷራፊዋ ዛር እና በሌላ ተሳታፊ ዛር መካከል ነበር፡፡ ከተፈጡት የአለመግባባት ንግግሮች ውስጥ ለአብነት " ...ኦሮሞ እኛኑ ነው የሚወጋው፣ እኛኑ ነው የሚያመው በሮ አይሄድም.. " (ምልከታ፣አዷራፊዋ፣30/05/08፣ቤሬ የተሰማ) እና "ሰው ታሞ መተኛ የለውም አቦ ......" ( ምልከታ፣ዝኒከማሁ፣.ከሌላ ተሳታፊ የተሰማ) ንግግሮችን መውሰድ ይቻላል፡፡

ከንግግራቸው መረዳት እንደሚቻለው ግጭቱ በኦሮሞ ዛር እና በአማራ ዛር መካከል የተፈጠረ ነው፡፡ በዛር አፍ ሲሰዳደቡና ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋላ አዷራፊዋ በሰጠችው የዛር አፍ ቃል ግጥም ግጭቱ ሊበርድ ችሏል፡፡ ይህንንም ምንም እንኳን የዛር አፉን ቃል ግጥም በግልፅ መስማት ባይቻልም በመጨረሻ በአማርኛ ይኸውም፡- "አምሮ ቢተኩስ ብለን ነበር ፣ ሄደ በረረ........"( ምልከታ፣ዝኒ ከማሁ አዷራፊዋ የተሰማ) በማለት ከተናገረችው መረዳት ይቻላል፡፡

ሌላው በዚህ ጊዜ የሰው ልጅ በእውኑ ሊያደርገው የማይችለውን ድርጊት በገፈራው ክዋኔ ላይ ሲደርጉ ተመልክቻለሁ፡፡ ይኸውም በፋጡማ ኢብራሂም ቤት የተከሰተ ሲሆን ዛር ካረፈባቸው ተሳታፊዎች ውስጥ አንዷ ተሳታፊ "እየው እኛ እንዲህ ነን እያለች" ከምድጃው ውስጥ ፍም ከሰል እሳት በማንሳት አንዱን ፍም ከሰል አፏ ውስጥ አስገብታ ካቆየች በኋላ የተፋችው ሲሆን ሌላውን በእጇቿ እስኪጠፋ ድረስ ይዛለች፡፡ ይህን ድርጊት የተፈፀመው "ዛሯ ቃል ግጥሙ ስላልተስማማውና ሶብር (ታገስ) ባለጉዝጓዟን አጥግበን ስንጨርስ የምትፈልገው ይባልልሀል ሲባል ለምን በሚል ሏዩዋ ላይ ያለው ዛር ተቆጥቶ ነው፡፡" በማለት አዷራፊ ወ/ሮ አንሻ ሰይድ ገልፀውልኛል፡፡ (ቃ.መ 08/06/08፣ዋዚ)

ከዚህ ድርጊቷ መረዳት የሚቻለው የዛር መንፈስ የሰፈረባቸው ሰዎች ዛሩ ሲነሳ ከራሳቸው በላይ በሆነ ሀይል ቁጥጥር ስር እንደሚሆኑና ከተለመደውና ከተዘወተረው

ማንነታቸው ውጭ የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን እና ባህሪያትን ሊያሳዩ እንደሚችሉ ነው፡፡ [26]

"በወለል በይ ወለል በይ" ቃል ግጥም ባለ ጉዝጓዚቱ ወደ ሀድራው መግባቷ ሲረጋገጥ ቃል ግጥሙ አሙማ አሙማ የተሰኘው ቃል ግጥም በድጋሜ ይዜማል፡፡ እነዚህን ቃል ግጥሞች በማፈራረቅ እያዜሙ ሀድራው ይደራል፡፡ እዚህ ላይ ሙሽራዋ ሁሉንም ከወደደችው በሁሉም ታጎራለች ካልወደደችው ሲቀየር እየተነሳች ታጎራለች ፤ሌሎቹም አጉሪዎች በሚወዱት ተነስተው ያጎራሉ፡፡ አጉሪዎቹ በዛር አፍ ሲነጋገሩ ሴቷ አሏራፊ በዛር አፍ ቃል ግጥም ትሰጣለች፡፡ ቃል ግጥሞቹ እንደየ ሁኔታው በተለያየ የድቤ አመታት ስልትና በማሲንቆ እንዲሁም በጭብጨባ ታግዘው ይዜማሉ፤ ጉሪያውም በደመቀ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡

በዚህ አይነት የቁጥቢቱ(የሴቷ ዛር) ሀድራ እስክትጠግብ ከተስናገደች በኋላ አሏራፊዋ የወንዱ ተሏርፋለች ሀድራ ይጀመር ትላለች፡፡ ወንዱ አሏራፊ አረብ ሶማሌ አንተ አረብ ሶማሌ በማለት ቃል ግጥሙን ይቀይራል፡፡ ሌሎቹ ተሳታፊዎች አረብ ሱማሌ በማለት በጭብጨባ ይቀበላሉ፡፡ የግጥሙ ክዋኔ ክዋኔው የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| **አሏራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
| --- | --- |
| አንተ አረብ ሱማሌ | አረብ ሱማሌ |
| አንተ አረብ ሱማሌ | አረብ ሱማሌ |
| ........................ | |

ባለ ጉዝጓዟ ከወደደችው ጉሪያው(ጭፈራው) እንደደራ ይቀጥላል፡፡ ይህን ቃል ግጥም ካልፈለገች የፈለገችውን በሉልኝ በማለት ትናገራለች፡፡ ለምሳሌ በአረጋሽ አህመድ ቤት ክዋኔ ላይ ጎጃምን ጥራልኝ በማለት ባለ ጉዝጓዟ ቃል ግጥሙ እንዲቀየር አድርጋለች፡፡ አሏራፊውም የድቤ አመታቱን ወዲያው በመቀየር እይው ጎጃምን እው ጎጃምን አረመመዱን የሚለውን ቃል ግጥም ማዜም ጀምሯል፡፡ ማሲንቆ ተጫዋቹም አጨዋወቱን ቀይሯል፤ተሳታፊዎቹም በጭብጨባ እይው ጎጃምን በማለት ግጥም በመቀበል አዚመዋል፡፡ ባለጉዝጓዟም በደስታ ረጅም ሳቅ ሳቅ ስቃ ጉሪያዋን ትቀጥላች፡፡

---

[26] ተመስገን ፋንታየ ያቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ዛሮች ሲቀጡ በአፍንጫቸው ደም እንደሚፈስ፣ በእሳት ላይ እንደሚራመዱ፣ራሳቸውን ከወለል ጋር እንደሚያጋጩ እና ከቤት ወጥተው ዛፍ ላይ እንደሚጠለጠሉ ተገልጿል፡፡ (1995፣27)

ይህ ዜማ የቀሰቀሳቸው ሌሎች ሁለት ተሳታፊዎችም በመነሳት አጉርተዋል፡፡ ግጥሙ በመቀየሩም ሀድራው እንደገና ሊደምቅ ችሏል፡፡ ክዋኔውም እንደሚከተለው ነው፡፡ (ምልከታ፣ቀርሱ፣02/06/08)

| **አሿራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እየው ጎጃምን እየው ጎጃምን | እይዉ ጎጃምን |
| እየው ጎጃምን እየው ጎጃምን አረማመዱን | እይው ጎጃምን |
| አዝማች | |

ይህ ቃል ግጥም ለተወሰነ ደቂቃ ከተዜመ በኋላ ባለጉዝጓዟ ጎንበስ በማለት አመስግና እና ድቤውን ስማ ተቀመጠች፡፡ሌላ አንዷት እያጎራች የነበረች ተሳታፊም በተመሳሳይ ሁኔታ አመስግና እግሯን ዘርግታ በጀርባዋ ተንጋላ እንደመተኛት አለች፡፡ ሦስተኛዋ ተሳታፊ ግን ለተወሰነ ደቂቃ በግጥሙ ዜማ ማጉራቷን ቀጠለች፤ሲበቃት እሷም በተመሳሳይ አመስግና ተቀመጠች፡፡ ከዚያም አሿራፊው ቃል ግጥሙንና የድቤ አመታቱን በመቀየር አሊ ሰላም ሰላም አሊሰላም የሚለውን ቃል ግጥም ማዜም ጀመረ፡፡ ሌሎች ተሳታፊዎችም በጭብጨባና በድቤ አሊ ሰላም በማለት እየተቀበሉት ሲያዜሙ ሙሽራዋ ጥቂት እንደማፋሽግ አደረገችና(አዛጋችና) ተነስታ ጉሪያዋን ቀጠለች፤ ሌላ አንዷት ተሳታፊም ከጉሪያው ተቀላቀለች፡፡ ሀድራውም በሚከተለው መልኩ ደመቀ፡፡ (ምልከታ፣ዋዜ፣ ከሁለቱም ቤት የተገኘ)

| **አሿራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| አሊ ሰላም ሰላም አሊ ሰላም | አሊ ሰላም |
| አሊሰላም ሰላም አሊ ሰላም | አሊ ሰላም |
| አሊ ነው አሊ ነው | አሊ ሰላም |
| አዝማች | |

በወ/ሮ ዘሀቡ ይማም ቤት በተካሄደው ክዋኔ ላይ ደግሞ አንተ አረብ ሶማሌ ከተዜመ በኋላ ሙሽራዋ አሊሰላም የሚለው ቃል ግጥም እንዲቀየር አዛለች ፡፡ ባለችው መሰረትም አሊ ሰላም ሰላም አሊ ሰላም በማለት ከተዜመ በኋላ እየው ጎጃምን እየው ጎጃምን በሚል ዜማ ጉሪያው ቀጥሏል፡፡ በወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ እና ከድጃ ሁሴን ገፈራ ቤት ግን ሦስቱ ቃል ግጥሞች በቅደም ተከተል (እየው ጎጃምን እና አሊ ሰላም ሰላም ) የሙሽራይቱን የበቃኝ ሁኔታ(እረፍት) ተከትለው ተከናውነዋል፡፡ ከሁሉም የገፈራ ቤቶች

በተለየ ደግሞ ወ/ሮ ዘሀቡ ይማም ቤት የተካሄደው ክዋኔ እዚህ ሀድራ ላይ የተለየ ክስተት ታይቶበታል፡፡ ይኸውም እይው ጎዳምን በሚለው ቃል ግጥም ሙሽራዋ ስታጎራ ቆይታ በበቃኝ እረፍት ከወሰደች በኋላ አሊ ሰላም ሰላም ሲባል ልትነሳ አልፈለገችም፡፡ ከክዋኔ በኋላ ስለ ሁኔታው ያነጋገርኳቸው አሷራፊ ወ/ሮ ሉባባ ሁሴን እንደሚሉት በዚህ ጊዜ ሙሽራዋ ያልተነሳችው ከግርዶሽ ውጭ ባሉ ወጣት ተሳታፊዎች ሹክሹክታና ሳቅ በመሰማቱ ዛሩ ተቆትቶ ነው፡፡ ( ቃለ መጠይቅ፣24/07/08፣ቀርሱ)

በመሆኑም በወቅቱ ድቤ በመምታት ላይ የነበረችው አሷራፊ ድቤውን መምታቷን አቁማ በእንጉርጉሮ ልመና ጀመረች፡፡ ተሳታፊ አሷራፊዋ ያው ግባ ያው ግባ ስትል ሁሉም ተሳታፊ አሚን በማለት ልመናውን አስተጋብተዋል፡፡ የልመናው እንጉርጉሮው የተካሄደው ጫት መቃሙ (ቂምሀው) ሳይቋረጥ አብዛኛው ተሳታፊ ከወገቡ በላይ ወደቀኝና ወደግራ በዝግታ በመወዛወዝ ነው፡፡ የክዋኔው ድባብ ጭብጨባ፣ድቤና ማሲንቆ ስላልነበረው አውዱ የቀዘቀዘና የተረጋጋ ነበር፡፡ የቃል ግጥሙ አካሄድ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ (ምልከታ፣02/06/08፣ቀርሱ)

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| ያውግባ ያው ግባ ያው ግባ | አሜን |
| እውው እውው እውው ያው ግባ | አሜን |
| በቻህንም አይደል በመሊካ ጀባ | ” |
| አንቱው መጀን አንቱ መጀን እውው | ” |
| አዳኙ ግባ አዳኙ ግባ እህ እህ | ” |
| አማን አውለን አማን አውለን | ” |
| አሁን ይመጣሉ ሀድራው እሞቀው ላይ | ” |
| ያው ግባ ያው ግባ ሰይዴዋ…… | ” |

በዚህ የልመና ዘዴ (በእንጉርጉሮው) ለተወሰነ ደቂቃ ከተለመነ በኋላ የዛር መንፈሱ ጮክ ብሎ አዛጋ ወዲያውም አሷራፊዋ ዛሩ የመቀስቀሱን ምልክት ስታይና ስትሰማ አሊ ሰላም ሰላም አሊ ሰላም የሚለውን ቃል ግጥም በድቤ ጀመረች፡፡ ከላይ በተገለፀው መልኩም ተሳታፊዎች እየተቀበሉ ሀድራው ሲደምቅ ባለ ጉዝጓዟም ተነስታ ማጉራቷን ቀጠለች ፤ አውዱም ወደነበረበት የሞቀ ሀድራ ተመለሰ፡፡ ከዚያም ወንዱን ዛር የሚያሞግስ ቃል ግጥም በሴቷ አሷራፊ ተጀመረ፡፡ ቃል ግጥሙ አባ ሙና ሙና ወናፈኛው የተሰኘ ሲሆን

ወደሀድራው ቀድሞ የገባውን ዛር የሚያወድስ ነው፡፡ ወናፈኛ[27] ማለት በዚህ አውድ የዛር መንፈሱ ከሌሎቹ በተሻለ ፈጣንና የሰፈረባቸውን ሰዎች እንደፈለገ የሚያስጨፍር መሆኑን ይገልፃል፡፡ ቃል ግጥሙ በድቤ፣በማሲንቆና በጭብጨባ እንደሚከተለው ይዜማል፡፡

| አሿራፊ | ተሳታፊዎች |
| --- | --- |
| አባ ሙና ሙና ወናፈኛው | አባ ሙና ሙና ወናፈኛው |
| አንተ አውሊያ አሁን የመጣሀው | " |
| እንደፈለክ አድርገህ የምትነዳው | " |
| የሀድራውን ለዛ የምታሳምረው | " |
| ................................ | |

አራተኛው ቃል ግጥም(አባ ሙናሙና ወናፈኛው) እንዳበቃ በሁሉም ገፈራ ቤቶች የበቃን እረፍት ተከትሎ የቀጠለው እደምን መጣኸው በረሀውን የሚለው ቃልግጥም ነው፡፡ እዚህ ቃል ግጥም ላይ ክዋኔ ላይ ድቤውን የሚመታው ወንዱ አሿራፊ ነው፡፡ አሿራፊዋ በተመሳሳይ የድቤ አመታት ስልት እንዴት መጣሀው በረሀውን የሚለውን ዜማ ስትጀምር ተሳታፊዎቹ በጭብጨባ በረሀውን በማለት ይቀበላሉ፡፡ ባለ ጉዝጓዟም ተነስታ ጉሪያዋን ትቀጥላለች፡፡ የቃል ግጥሙ ሀድራ በማሲንቆና በድቤ ምት በሚከተለው አካሄድ ተደጋግሞ ይከወናል፡፡

| አሿራፊ | ተሳታፊዎች |
| --- | --- |
| እንዴት መጣሀው በረሀውን | እንዴት መጣሀው በረሀውን |
| እንደምን ችለኸው ዉሀ ጥሙን | እንደምን ችለኸው ውሀ ጥሙን |
| እንዴት መጣሀው | በረሀውን |
| እንዴት ችለኸው | ውሀ ጥሙን |
| አዝማች | |

ይህ ቃል ግጥም ከሌሎቹ ቃል ግጥሞች የሚለየው ቀጥሎ ለሚመጣው ክዋኔ ወሳኝነት ስላለው ነው፡፡ ይኸውም በቃል ግጥሙ ውስጥ ተደጋግሞ የሚመጣው "በረሀ" የሚለው ቃል ለተተኪው ክዋኔ መፈጠር አይነተኛ ሚና ይጫወታል ማለት ይቻላል፡፡ በረሀን ስናስብ አብሮ የሚመጡ እንደ ውሀ ጥም፣ድካም፣ እረፍት የመፈለግ ወዘተ ያሉ

---

[23] የኢትዮጵ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር አማርኛ መዝገበ ቃላት(1993፣411) ወናፍ ማለት ጨበጥ ለቀቅ ሲያደርጉት ወደ ውስጥ እየሳበ መልሶ በሚያስወጣው የአየር ግፊት የእጅ ባለሙያዎች ብረታ ብረት ለማጋል የሚጠቀሙበትን ከሰል የሚያፎሙበት የአየር ማስገቢያና ማስወጫ ጠባብ ቧንቧ የተገጠመበት ስልቻ በማለት ይፈታዋል፡፡

ክስተቶችና ሁኔታዎች አሉ፡፡ የእነዚህን ክስተቶችና ሁኔታዎች ችግርን ደግሞ ለማስወገድና እፎይታ ለማግኘት አንዳች መፍትሄ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለዚህ የበረሀ ጉዞ የሚሆን ስንቅ መያዝ አለበት፡፡ በቃል ግጥሙ ውስጥ እንደምንሰማው ደግሞ ይህን ተከትሎ ተደጋግሞ የሚመጣው "እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ" የሚል ዜማ ነው፡፡ ስለሆነም መፍትሄው ወዲያው ችግሩን ተከትሎ ይፈታል ማለት ነው፡፡

ይህን የበረሀ ጉዞ ችግርና መፍትሄውን በክዋኔው ላይ እናያለን ማለት ይቻላል፡፡ ይኸውም ክዋኔው ለብዙ ሰአታት በሀድራ ላይ ሲቀይ ባለጉዝንዟም ሆነች ተሳታፊዎች የድካም ስሜት መሰማታቸውና ረፍት መሻታቸው የማይቀር ነው፡፡ ስለሆነም ለዚህ ችግራቸው ደግሞ መፍትሄ ማበጀት የግድ ስለሚሆን እንደምን መጣኸው በረሀውን የሚለውን ቃል ግጥም ያመጣሉ፡፡ ከላይ በበረሀው ጉዙ ተምሳሌትነት ለመግለፅ እንደተሞከረው ቃል ግጥሙ ውስጥ ተደጋግመው የሚመጡት ቃላትና ሀረጋት መፍትሄ ያበጃሉ፡፡ ለረጅም ጊዜ ያለማቋረጥ በጉሪያ ላይ የነበረው የዛር መንፈስም በዚህ ቃል ግጥም አማካኝነት ድካሙን የሚያያበርድበትን ግብሩን ፍለጋ ይሄዳል፡፡ ስለሆነም ክዋኔው እንደሚከተለው ይቀጥላል፡፡

| **አሿራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| ጎጃም ወረደ በበረሀ | እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ |
| ጎጃም ወረደ በበረሀ | እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ |
| ፋሲል ወረደ በበረሀ | እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ |
| ፋሲል ወረደ በበረሀ | እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ |

በቃል ግጥሙ ላይ እንደምንሰማው ከዋኞቹ ለዛር መንፈሱ ጠጅ ለራሳቸው ደግሞ ውሀ እንደሚያስፈልጋቸው ይገልፃሉ፡፡ በታሪክ እንደሚታወቀው በሀገራችን ኢትዮጵያ ጠጅ የነገስታትን የተከበሩ ሰዎች መጠጥ ነው፡፡ በመሆኑም ከዋኞቹ ለዛር መንፈሱ ካላቸው ክብር የተነሳ ጠጅ እንደሚያስፈልገው ሲገልፁ በክብር ከእሱ እንደሚያንሱ ለማሳወቅ ደግሞ ው እንደሚያስፈልጋቸው ገልፀዋል፡፡

ይህን ቃል ግጥም በዜማ፣በጭብጨባ፣በድቤና በማሲንቆ በተደጋጋሚ ሲያዜሙ ባለ ጉዝንዝ እያጎራች (አይኗን እንደጨፈነች) ወደ ጓዳ ታመራለች ፡፡ ከዚያም ወደ ተዘጋጀው ጠላና ቡቅሪ ማለትም ወደ ታሰሩት ጋኖች (ሚጁዎቹ) ትሄዳለች፡፡ እዚህ ቃል ግጥም ክዋኔ ላይ ድቤውን የሚመታው ወንዱ አሿራፊ ነው፡፡ ምክንያቱም ሴቷ አሿራፊ

ሙሽራይቱን ተከትላ ሌላ የምትከውነው አለ፡፡ በመምታት ላይ የነበረችው ሴቷ አሏራፊ ከሆነች ድቤውን ለወንዱ አሏራፊ ትሰጣለች፡፡ ለምሳሌ በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ ቤት ክዋኔውን በድቤ በመምራት ላይ የነበረችው አሏራፊ ድቤውን ለወንዱ ሰጥታለች፡፡ ባለ ጉዝጓዟ ወደ ጋኖቹ (ሚጄዎቹ) ስትሄድ አሏራፊቱ እና ሦስት ተሳታፊዎች እስክስ እስክስ እስክስ አስክስ በማለት ወገባቸውን ይዘው እንደመወዛወዝ እያሉ ከኋላ ተከትለዋት ይሄዳሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ቃል ግጥሙ   ቁጥቤ መጥታለች ገፈራ ብላ
                                ቁጥቤ መጥታለች ግብር ልትበላ…

በሚል ቃል ግጥም ይተካል፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው ቃል ግጥም ዓላማው የዛር መንፈሶቹን የግብር ድግስ(ገፈራ) የመስጠቱን ክዋኔ ለመፍጠር ስለነበር ነው፡፡ አሏራፊው ድቤውን እየመታ ይህን ቃል ግጥም ሲል ተሳታፊዎችም “ግብር ልትበላ” ፣”ገፈራ ብላ” በማለት በጭብጨባ ይቀበላሉ፡፡ በሁሉም ገፈራ ቤቶች እንደተመለከትኩት ባለጉዝጓዟ እያጎራች ከጋኖቹ(ሚጄዎቹ) ስትደርስ ማጉራቷን አቁማ ሄድ መጣ ሄድ መጣ (ወደጋኖቹ ሄዳ እንደመመለስ) እና የማለትና እንደመሳል አይነት ሁኔታዎችን ታሳያለች፡
:

እነዚህ ጠላና ቡቅሪ የያዙ ጋኖች እንደ ከመጀመሪያ የትዳር አጋሯ ጋር ያልተፋታች አንዲት ሴት ከሚሰጣት ስያሜ[28] ጋር በተመሳሳይ ሚጄ ተብለው ይጠራሉ፡፡ በተመሳሳይ ስያሜ የሚጠሩበት ምክንያትም ሁለቱም ያልተነካኩ በመሆናቸው ነው፡፡ ማለትም በአንድ በኩል ያቺ ሴት ሁለተኛ ወንድ ያላገባች በመሆኗ ሌላ ወንድ አልነካትም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ጋኖች ሲጠነሰሱ ጀምረው ውሀ ሲሞሉም ሆነ ከዚያ በኋላ እስከ እዚህ ሰአት ድረስ አልተነኩም፤አልተቀመሱም፡፡ በመሆኑም ሚጄ የሚለው ስያሜ አንድም ከአንድ ወንድ(ከባሏ) ውጭ ላልሄደች ሴት አንድም ደግሞ ድፍድፉ ሳይቀመስና ሳይነካካ ለተጠመቀ ጠላና ቡቅሪ ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው በቅድመዝግጅት ጊዜ የሚካሄደው ልመና ስርአት በመጀመሪያ የሚካሄደውና ግዴታ

[28] በማታው ክዋኔ አበጋሯ ከሙሽራይቱ “ሙዳ ጀባ” ተብላ ተሰጠችውን ያልቀለጠ(ላስታ) ቅቤ ተሳታፊዎቹን እንድትቀባና እንድታድል የሰጠችው “ሚጄ ጀባ” በማለት ለሚጄ ሴት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

የሆነው ከአሚኖች(ከሦስት አሚን)[29] ቤት የሚደረገው ልመና ነው፡፡ ስለዚህ በአካባቢው ባህል መሰረት አለመነካካት ተመራጭና ተወዳጅ መሆኑን ማሳያ ቃል ነው የሚል ትርጓሜ መስጠት ይቻላል፡፡

የመሄድና የመመለስ ሁኔታ ካሳየች ወንዱ ዛር(ወንዘኛው) መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ሁኔታ ስታሳይ አኗራፊዋ በንግግር "ተው እንጂ ጌታዋ ተቀባበለን፣መረሀባ በላት፣ ግብርህን ተቀበላት" በማለት ዛሩን በማባበል ልመና ትጀምራለች፡፡ የመሳል አይነት(እኽ እኽ እኽ) ካለች ደግሞ ሴቷ ዛር(ቁጥቢቱ) መሆኗ ይታወቃል፡፡ እሷንም እማምየ ስቀሽ ተንከትክተሽ ተቀበይ እንጂ  በማለት ታባብላለች፡፡

በሁሉም ቤት ሙሽሮቹ እነዚህን ምልክቶችን በሴቷ ዛር ምልክት በማስቀደም እንደሚያሳዩ በምልከታም ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ሙሽራዋ እነዚህን ምልክቶች ስታሳይ አኗራፊዋ አባብላ ወደጋኖቹ(ሚጁዎቹ) እንድትጠጋ ታደርጋለች፡፡ አኗራፊቱ እና የተከተሏት ተሳታፊዎች "እስክስ እስክስ እስክስ እስክስ" በማለት ያጅቧታል፡፡አኗራፊዋ "እርቅ በይ ማምየ" ስትላት ባለ ጉዝጓዟ ያለምንም ማመንታት ታጅባ መጀመሪያ ወደ ቡቅሪው ጋን(ሚጁ) ቀርባ ትቆማለች፡፡  ከዚያም አኗራፊዋ እዚያው ቁማ ወደሞቀው ሀድራ ጮኽ ብላ "ሚጁ ጀባ አለች" በማለት ትነግራለች፡፡አበጋሯም መረሀባ በማለት ምርቃኗን በሚከተለው ሂደት ትሰጣለች ሁሉም ተሳታፊዎች በያሉበት መረባ በማለት ምርቃቱን ሲያፀድቁ ባለ ጉዝጓዟም ከቆመችበት ሆና "አሚን አሚን" በማለት ምርቃኑን ትቀበላለች፡፡

| **አበጋሪት** | **ባለጉዝጓዝ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|---|
| እርፎ በረባ (2 ጊዜ) | አሜን | መረባ |
| እንግዲህ ዛሬ በሻሪያዋ ይሁን | " | " |
| ልጆቿ ጋር መክበሪያዋ ይሁን | " | " |
| ግጥሟ ይሁን… | " | " |
| ይሁን በይ እርፎ | አሜን | ይሁን |

ምርቃቱ ሲጠናቀቅ ባለ ጉዝጓዟ ጋኖቹን(ሚጁዎቹን ከቡቅሪው በመጀመር ትከፍታለች፡፡ ከዚያም አኗራፊቱ በአቦሬ(ፎሌ) በመጥለቅ ሌሎች ሁለት ኩባያዎች ላይ ከቡቅሪውም

[29] ሁለት ያልተፋቱ የመጀመሪያ ባለ ትዳሮች(ባልና ሚስት) አሚን ተብለው ሲጠሩ ከአንድ በላይ የሆኑ(በብዙ ቁጥር) ሲጠሩ ደግሞ አሚኖች ይባላሉ፡፡ ሚስቲቱ ብቻዋን ደግሞ ሚጁ ተብላ ትተራለች፡፡

ከጠላውም በመሙላት ለባለ ጉዝጓዟ አንዱን በአንድ እጇ አንዱን በሌላ እጇ ታሲዛታለች፡፡ አያያዙ የትኛው በቀኝ የትኛው በግራ መሆን አለበት ለሚለው ያነጋገርኳቸው ሁሉም አሷራፊዎች ምንም አይነት ደንብ እንደሌለውና እንደ አሷራፊዋ አሰጣጥ እንደሚወሰን ገልጸውልኛል፡፡ (ቃ.መ፣ወ/ሮ አረጋሽ አህመድ 01/06/08 ቤሬ፣ ወ/ሮ ዘሀቡ ይማም 03/06/08 ቀርሱ፣ ወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ 08/06/08 ዋዚ፣ወ/ሮ ከድጃ ሁሴን 15/06/08 ዋዚ፣ወ/ሮ መይረማ እንድሪስ 22/06/08 ቸሪት እና ወ/ሮ አንሻ አሊ 22/07/08 ዱሬ)

ባለ ጉዝጓዟ ጠላና ቡቅሪውን እንደያዘች አበጋሯ ካዳሚዎቹን ጃንጥላ ፣ቁራሽ ዳቦ፣ የተለጠለጠ ኑግ፣የገብስ፣የስንዴ እና የሽንብራ ቆሎ እንዲያመጡ ታደርጋለች፡፡ ከዚያም ጃንጥላውን ዘርግታ ለባለ ጉዝጓዟ በአንገቷና በቀኝ ትካሻዋ መሀል ታሲዛታለች፤ሌላውን ባለ ጉዝጓዟን ከተከተከተሏት ተሳታፊዎች ውስጥ አንዷ ትይዛለች፡፡ ክዋኔው ማታ የሚከወን ቢሆንም ጃንጥላ በሰአቱ ዝናብ ዘነበም አልዘነበም የመያዙ ድርጊት አይቀሬ ነው፡፡ ማለትም የገፊራው ዕለት ብርሀን ለጨለማ ስፍራውን የለቀቀበት፤ፀሀይ በጨረቃ የተተካችበት መሆኑ እርግጥ ነው ስለዚህ በጨለማ ጥላ ይዘረጋል እንዴ የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ነገርግን ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ባለ ጉዝጓዟ በክዋኔው ላይ እንደሙሽራ ስለምትቆጠር ነው፡፡ ባለ ጉዝጓዟ በትካሻዋና በአንገቷ ጥላው እንደተዘረጋ በእጇ ጠላና ቡቅሪውን ይዛ አብረዋት ያሉት ተሳታፊዎች፣አሷራፊዋና ኑግ ፣ዳቦ፣ ፈንድሻና ቆሎ የያዘችው ተሳታፊ አጅበዋት ወደውጭ ይወጣሉ፡፡ ከዚያም ወደ ጓሮ ወይም ለመድፋት በሚመች ስፍራ ቆመው ሙሽራዋ ጠላና ቡቅሪውን ትቀምሳለች ፡፡ የማትወደው ወይም የማትጠጣው ካለ ካሽተተች በኋላ አሷራፊቱ ትቀበላትና ሁለቱንም ትደፋለች፤በመቀጠል ከተሳታፊዋም ቆሎ፣ኑግና ዳቦውን ተቀብላ እዚያው ቦታ ላይ ታፈሳለች፡፡

እነዚህ ነገሮች የሚደፉበት ምክንያት ደግሞ ገፊራው (የዛር ድግሱ) የተደረገው ለዛር መንፈሶቹ ስለሆነ ገፊታውንም ሆነ ሌሎቹን ድግሶች ማንም ሰው ሳይቀምስ (ሳይሷረፉ) በፊት ዛሮቹ መቅመስ አለባቸው አለበለዚያ ዛሮች ስለሚቆጡ ድግሱን ለቀመሰ ሁሉ በሽታ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ የባህሉ ባለቤቶች ይገልፃሉ፡፡ (ከቡድን ውይይት፣ 26/07/08፣ዱሬ)

ሌሎቹ ቤቱ ውስጥ የቀሩት ተሳታፊዎች በደማቅ እንጉርጉሮ “አሚን አሚን” እያሉ የዛር መንፈሶችን ያወድሳሉ፡፡ የውዳሴ ግጥሙ የሚመራው ግጥም በአሷራፊው እና ግጥም መድረስ በሚችሉ ተሳታፊዎች ሲሆን ግጥም ሰጪው ግጥሙን አሚን አሚን በማለት ሲሰጥ ሌሎቹ ተሳታፊዎችም “አሚን አሚን” እያሉ ያጎራጉራሉ፡፡ የዚህ እንጉርጉሮ ሀድራ በጣም የደመቀ(የደራ) በመሆኑ ዛር የሰፈረባቸው ተሳታፊዎች እየተነሱ ያጎራሉ፡፡ ይህ ሀድራ ባለ ጉዝጓዟ እስክትመለስ ድረስ እንደሚከተለው ይቀጥላል፡፡

| **ግጥም አውጭ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| አሚን አሚን አሚን | አሜን (ረዘም ባለ ድምፅ) |
| እንደው አሜን አሜን፣ኸረ ምነው ኸረ ምነው | አሜን (ረዘም ባለ ድምፅ) |
| ኸረ መጀን ኸረ መጀን፣ኸረ ማሬዋ ኸረ ማሬዋ | ” |
| እንኳን በሾህና ቢታጠር በብረት | ” |
| አሰላማላይኩም … | ” |
| የዱበርቲ ድቤ የሚያዳምጠው | ” |
| አሰላም አለይኩም ብሎ የገባው | ” |
| ወረንሰላም አላ ብየ ልበለው … | ” |

ገፈራውን ድግሱ ለተደረገላቸው የዛር መንፈሶች ካደረሱ በኋላ ሙሽራይቱ ከፊት አጃቢዎቿ ከኋላ ተከትለዋት ይመለሳሉ፡፡ ከቤቱ በር ሲደርሱም እስክስታ እንደማለት ያህል እተወዛወዙ “እልል እልል እልል ፣እስክስ እስክስ እስክስ” እያሉ ይገባሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቤት ውስጥ የነበረው ተሳታፊ በጭብጨባ በድቤና በማሲንቆ እየቀናው መጣ ደስ እያለው (2 ጊዜ) በማለት በአሷራፊው መሪነት በመደጋገም እንደሚከተለው ያዜማሉ፡፡

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እየቀናው መጣ ደስ እያለው | እየቀናው መጣ ደስ እያለው |
| እየቀናው መጣ ደስ እያለው | ደስ እያለው |

ይህ ቃል ግጥም ደግሞ የዛር መንፈሱ የተደረገለትን ገፈራ እንዳገኘ እንደተሷረፈና እንደተሳካለት ፤በዚህም ደስተኛ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡ ሀድራው በዚህ ቃል ግጥም ይደምቃል ፤ ባለ ጉዝጓዟ አጃቢዎቿ እሞቀው ሀድራ ይቀላቀላሉ፡፡ ከዚያም ባለ ጉዝጓዟ ታጎራለች ፤ሀድራው እስኪበቃት ድረስ ይቀጥላል፡፡ ባለ ጉዝጓዟ ሀድራውን ጠግባ ስትቀመጥ ካዳሚዎች ገፈራውን እስኪያቀራርቡ ድረስ ሀድራው በድቤና በማሲንቆ ተመሳሳይ(አብሮ ተጓዥ) ምት ተሳታፊዎች ይተካል፡፡

ካዳሚዎች ድፎ ዳቦ (ሙጌራ) ፣ፈንድሻ፣ኑግ፣የሽንብራ ፣የስንዴና የገብስ ቆሎ ባለ ጉዝጓዟ ፊት ያቀርባሉ፡፡ አሷራፊዋ ባለ ጉዝጓዟን ቀኝ እጅሽን ከዳቦው መሃል ላይ ዘርጊልኝ ትላታለች፡፡ ባለ ጉዝጓዟ እጇን( እንደ ዳቦው መጠን ከክንዷ በመጀመር እስከ ጣቷ ጫፍ) ከዳቦው መሃል ላይ ስትዘረጋ አሷራፊዋ የባለ ጉዝጓዟን እጅ ሳታነሳ ዳቦውን ቢስሚላሂ ረህማን ረሂም በማለት ለሁለት እጥፍ በማድረግ ትቆርሳለች፡፡ ከዚያም ዳቦው አሷራፊዋ ቆራርሳ መጀመሪያ ለባለ ጉዝጓዟ አንድ ቁራሽ ዳቦ እና ከቀረበው ቆሎ ሁሉ እና ከተወቀጠው ኑግ እየቆነጠረች በሰሀን አድርጋ ትሰጣለች፡፡ በመቀጠል አሷራፊዋ ቆሎውን ፈንሻውንና ኑጉን አቀላቅላ ሦስት ጊዜ በእፍኝ በእፍኟ እየዘገነች ማታ በጨርቅ ተሸፍኖ ከተቀመጠው ቄና(ተሽመች ከተባለችው) ላይ ትጨምራለች፡፡ ዳቦውንና ቆሎና ኑግ ካዳሚዎቹ ለሁሉም ተሳታፊ እንዲሰጡ ታዝና በካዳሚዎቹ አማካኝነትም ከበረኛዋ በመጀመር ከቀኝ ወደ ግራ ለሁሉም ተሳታፊ ይዳረሳል፡፡

ከዚያም ጠላና ቡቅሪ በሁለት አቦሬ (ፎሌ) በአመቅዳት ለሙሽረዋ አንዱን በቀኝ እጇ አንዱን በግራ እጇ ትሰጣታለች፡፡ ባለ ጉዝጓዟም የምትወደውን ትጠጣለች የማትወደውን አሽታ ትተዋለች፡፡ ለሌሎቹ ተሳታፊዎችም በካዳሚዎቹ አማካይነት በአቦሬ(ፎሌ) ከሚፈልጉት እየተቀዳ ይሰጣል፤ይጠጣሉ፡፡ በምልከታ እንዳረጋገጥኩት አብዘሀኞቹ ተሳታፊዎች የሚጠጡት ቡቅሪ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድም የእስልምና ሀይማኖትን ቀኖና ላለመጣስ አንድም ደግሞ ከራሳቸው ምርጫ የተነሳ ነው፡፡

በመቀጠል አቦል ቡና በካዳሚዎች ይፈላል፤ ካዳሚዋ "አወል ጀባ አወል ጀባ" ስትል አበጋሪቷ "መረሀባ" በማለት ምርቃን ትሰጣለች፡፡ ባለ ጉዝጓዟና ተሳታፊዎች እንደተለመደው ምርቃኑን ይቀበላሉ፡፡

| **አበጋሪት** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|
| እርፎ መረባ (2 ጊዜ) | መረባ (2 ጊዜ) |
| ከእንግዲህ በላይ ቁጥቡ መጀን | መረባ |
| በሽታ አይንካት | " |
| ይሄ ቀየ እንግዲህ መውሊድማውጫዋ ይሁን | " |
| ይሄ ቀየ እንግዲህ ሰደቃ መሰደቂያ ያድርገው | " |
| ሁሉም ይስማማት | " |
| ቁጥቢቱ ትታረቃት | " |
| ወንዘኛው ይታረቃት | " |
| ሁሉም ይታረቋት | " |
| ይሁን በይ እርፎ | ይሁን |

አሷራፊዋ ቡናውን ቀድታ ካዳሚዎች መጀመሪያ ለባለ ጉዝጓዟ ከተሰጠች በኋላ ለሁሉም ተሳታፊ ይዳረሳል፡፡ ሁሉም ተሳታፊ የቀረበላቸውን ገፈራ ከበሉና ከጠጡ በኋላ ለባለ ጉዝጓዟ ከተቀመጠችበት ጥግ ከተሸፈነው ቁና (ከተሸመችው) ጋር እስከ ሦስት ቀን የምትቀመጥበት ማለትም የምትሞሸርበት ግርዶሽ ይሰራላታል፡፡ ከዚህ በኋላ ባለ ጉዝጓዟ ከዚህ ግርዶሽ ለመፀዳዳት ካልሆነ በቀር አትወጣም፡፡ ከዚህ ክዋኔ በኋላ ወቅቱ ስለሚነጋ የገፈራው ሁለተኛ ቀን ይጀመራል፡፡ የመጀመሪያው የገፈራ ክዋኔ ቀን የሚጠናቀቀው ሊነጋጋ ሲል ከ11፡30-12፡00 ሰአት ባለው ጊዜ ውስጥ በሆን እንዳለበት የባህሉ ባለቤቶች ይገልፃሉ፡፡ በምልከታ እንዳረጋገጥኩትም በወ/ሮ አረጋሽ አህመድ፣ በወ/ሮ ዘሀቡ ይማም እና በወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ ቤት የተካሄደው ገፈራ 11፡50 ሰአት ላይ የተጠናቀቀ ሲሆን በወ/ሮ ከድጃ ሁሴን እና ወ/ሮ መይረማ እንድሪስ 11፡30 ፣በወ/ሮ አንሻ አሊ ደግሞ 11፡40 ላይ ተጠናቋል፡፡

## 4.4. የገፈራ ሁለተኛ ቀን ክዋኔ

ከማታ 2፤30 ጀምሮ እስከ ጠዋት 12፡00 ሰአት ድረስ በሀድራና በተለያዩ ክዋኔዎች የገፈራ ስርአቱ ከተካሄደ በኋላ ጨሌ የተነከረላቸው ተሳታፊዎች (ሚዜዎች) ፣ አበጋሯ፣አሷራፊዋ እና ቁርስ በልተው እዚያው መዋል የፈለጉ ተሳታፊዎች ሲቀሩ አብዘሀኛዎቹ ተሳታፊዎች "በይ ይግጠምሽ ፣በሰላም ያገናኘን" በማለት ወደየቤታቸው ይሄዳል፡፡ አንዳዶች እንቅልፍ ያስቸገራቸው ተሳታፊዎች መተኛት ከፈለጉ እዚያው ይተኛሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ቤት ለቀሩት ተሳታፊዎች በባለ ጉዝጓዟ ቤተሰቦችና በቀሩት ካዳሚዎች አማካይነት ቁርስ ሻይ፣ዳቦ እና እንጀራ ጠላና ቡቅሪም ለፈለገ ይቀርባል፡፡ ለባለ ጉዝጓዟም በተሞሸረችበት ግርዶሽ ውስጥ ቁርስ ይሰጣታል፡፡

ቁርስ ከተበላ በኋላ ሚዜዎቹ፣አበጋሯ እና አሷራፊዋ የጠረጋው ቀን (በነገታው) 2፡30-3፡30 ሰአት መገናኘት እንዳለባቸው ይነጋገራሉ፡፡ ቤቱ እንዳይጠረግና ማታ የተቀመጠው እጥጣቢ እንዳይደፋ ለባለ ጉዝጓዟ ቤተሰቦች ነግረው ባለ ጉዝጓዟንም በይ እቴዋ ከግርዶሽ እንዳትወጪ በማለት አሳስበው፣ "አንቺንም ይግጠምሽ፤ሁላችንንም በሰላም ያገናኘን ፤ አሰላም አለይኩም" በማለት ይሰናበታሉ፡፡ ባለ ጉዝጓዟም በገፈራዋ ስለተገኙላትና ስለተሳተፉ ምስጋና በማቅረብ " በረካ ሁኑልኝ ሀጃችሁን አላህ ይክፈላችሁ፣ብድር መላሽ

ያድርገኝ" በማለት መርቃ እና በሰላም ያገናኘን" ብላ ትሰናበታለች፡፡ የገፈራው ቤት እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ሳይጠረግ ፤ ባለ ጉዝንዟም ከግርዶሿ ሳትወጣ ይቆያል፡፡

ባለጉዝንዟ መፀዳዳት ሲያስፈልጋት የምትወጣው ከቤተሰቦቿ አንድ ሰው ተከትሏት በጃንጥላ ከፀሀይ ተጠልላ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ያነጋገርኳቸው ተሳታፊዎች እንደሚሉት የገፈራ ቤቱ የማይጠረገው የዛር መንፈሶቹ ስላልተሸኙ ሲሆን ሁሉም ነገር የሚጠረገውና የሚደፋው በሦስተኛው ቀን የዛር መንፈሶቹ ሲሸኙ ነው፡፡ ይህ የሆነበትም ምክንያት ዛሮች ከፈሰሰው ድግስ (ጠላ፣ቡቅሪ፣ ቡና እና ሻይ፣ከቆሎውም ወዘተ) እና ከጫቱም ሽርጥ (ጫቱ ተቅሞ ከሚጣለው የጫት እንጨትና ቅጠል) ስለሚቃመሱ ከተጠረገ እንደተሸኙ ስለሚቆጠር በመቆጣት ጉዳት ያመጣሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ (ቃ.መ ፣ አቶ አደም አወል 24/07/08፣ዱሬ እና ወ/ሮ ሶፊያ አሊ 23/06/08፣ቸሪት)

በገፈራው ሁለተኛ ቀን ጊዜ የሀድራ ክዋኔ የለም፡፡ ምክንያቱም ሌሊቱን ሙሉ በሀድራ ላይ ስለቆዩ ማረፍ ያስፈልጋቸዋል፣እንዲሁም ሁሉም በየቤታቸው የራሳቸው ሀጃ (ጉዳይ) ስላለ የራሳቸውን ስራ ይሰራሉ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣መሀመድ አሊ፣01/06/08፣ቤሬ) ስለዚህ በዚህ ቀን ጎረቤት ቤተ ዘመድ እና አንዳንድ ተሳታፊዎች በመምጣት ባለ ጉዝንዟን ያጫውታሉ፣ይበላሉ፣ይጠጣሉ እንጂ ክዋኔ የለም፡፡

## 4.5 የገፈራ ሦስተኛ ቀን (የጠረጋ ቀን) ክዋኔና ቃል ግጥሞች

የገፈራ ሦስተኛ ቀን ክዋኔ ለዛር መንፈሶች ሽኝት የሚደረግበትና በድጋሚ ከሁለት አመት በኋላ ግብር እንደሚሰጡ ቃል የሚገባባት ስነ-ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ክዋኔ ላይ የሚሳተፉት በዋናነት በመጀመሪያው ቀን የማታ ክዋኔ ላይ ጨሌ ያስነከሩ ተሳታፊዎች ፣ አሏራፊዋ ፣ ማሲንቆ ተጨዋቹ እና አበጋሯ ናቸው፡፡ አንዳንድ የባለጉዝንዟ ዘመዶችና ጎረቤቶችም ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ክዋኔው የሚጀመረው ከጠዋቱ 3፡00-4፡00 ባለው ጊዜ ሲሆን ዋናዋና ተሳታፊዎች ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ እነዚህ ተሳታፊዎች መገኘታቸው እንደተረጋገጠ በኋላ መጀመሪያ ግርዶሹን ፈትተው የገፈራ ቤቱን ይጠርጋሉ፡፡ ከዚያም በአሏራፊዋ እና በአበጋሯ አማካይነት ባለ ጉዝንዟ ገላዋን ታጥባ ሌላ ልብስ ትለብሳለች፡፡ የፅዳት ስራዉ ከተጠናቀቀ በኋላ አሏራፊዋ ጠላና ቡቅሪ በኩባያ በመቅዳት ለባለ ጉዝንዟ በሁለት እጇ ታሲዛታለች፡፡ እሷም ይህን ይዛ ፣የቤቱን ጥራጊ በከሌ ፣በማዳበሪያ ወይም በጨርቅ ፣ የገፈራ

የመጀመሪያ ቀኑን የስኒና የጀበና ዕጥጣቢ ፣ የቀለጠ ቅቤ ዝቃጭ ከነስህኑ፣ በቁና ላይ የተቀመጠውን(የተሾመችወን) በቁና ፣ባለ ጉዝጓዟ ለብሳው የነበረው ነጭ ሻሽ እና ለጨሌ ማጠቢያ የሚሆን ውሀ በጆግ ጨሌ የተነከረላቸው ተሳታፊዎች እና አሷራፊዋ እያንዳንዳቸው በመያዝ የገፈራው መጀመሪያ ቀን ማታ ጠላ፣ቡቅሪ፣ቆሎና ዳቦ የደፉበት ንፁህ(ጡሀራ) ቦታ ወስደው ይደፋሉ።

በጠረጋው ቀን የቆሻሻው መጠረግ ዓላማ የዛር መንፈሶቹን ተለማምነው በመሸኘት በባለ ጉዝጓዟ ቤት የነበረውን በሽታና ችግር እንዲያስወግዱላቸው ማድረግ ነው። በመሆኑም የጠረጋው ቀን ትርጓሜ በቤቱ ውስጥ ቀድሞ የነበረውን ችግር በማባረር አዲስና ጥሩ መንፈስን( እርካታን) ማግኘት እና ከበሽታዎች መፅዳት ነው።

እነዚህ ጥራጊዎች ሁሉ የሚደፉት በአሷራፊዋ አማካይነት ሲሆን እያንዳንዱን ስትደፋ አለሞቼ ወርቆቼ እንግዲህ ሸኘናችሁ ፣ እሷንም ታረቋት፣ቤተሰቦቿን ጠብቁላት ወዘተ በማለት እና በዛር አፍ የዛር መንፈሶችን በመለማመን ነው። እንዲሁም በዚህ ጊዜ ሌሎች ተሳታፊዎች ምንም አይነት ድምፅ (ወሬ) ማሰማት የለባቸውም። ምክንያቱም ዛሮቹን ሲቀበሉ እንደተደሰቱት ሲሸኙ ደግሞ መከፋታቸውን ለመግለፅ እንዲሁም ጫጫታ ካለ ዛሮቹ ይቆጣሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው።

> ያው እንዳየሽው ነው ጋዞቹ እንዳይቆጡብን ስልሁላችንም ዝም ማለት አለብን፣ስቀው እንደገቡ ስቀው፣ተደስተው እንዲሄዱ ነው የምንሻውይህ የገፈራ አደብ ነው። በአደብ ተለማምነን ነው መሸኘት ያለብ። (ቃለ መጠይቅ፣23/06/08፣አሷራፊ ሀሊማ ኡመር፣ቸሪት)

በዚህ ድባብ በሁሉም ገፈራ ቤቶች እንደተመለከትኩት አሷራፊዋ እያንዳንዱን ጥራጊ በቅደም ተከተል ትደፋለች። ይኸውም መጀመሪያ የቤቱ የሳር ጥራጊና የጫት ኧርጥ ጥራጊ በመቀጠል ከዚህ ጥራጊ ላይ የቅቤው ዝቃጭ፣የቁናው(ወንፊቱ) ቆሎና ዳቦ፣ የስኒና የጀበና ዕጣቢ፣ ነጩ ሻሽ ውሀ ፈሰስ ፈሰስ ይደረግበታል፣ቀረቡት ሁሉ ዕቃዎች ይታጠባሉ። ጥራጊዎች በዚህ ቅድም ተከተል ከተወገዱ በኋላ ሷራፊዋ ሙሽራዋ ይዛ የቆመችውን ጠላና ቡቅሪ በየተራ እየተቀበለች ሦስት ሦስት ጊዜ ከአንገቷ በላይ በማዞር ሦስት ዙር አሽትታት ጥራጊው ላይ ትደፋለች። የአንዱን ከጨረሰች በኋላ ሌላውንም በተመሳሳይ ሁኔታ ትከውናለች። ከዚያም የጨሌ አጠባ

ስነ-ሰርአት ይካሄዳል፡፡ ይኸውም የቀለጠ ቅቤ ይዞ በነበረው ጎድጓዳ ሳህን ላይ ንፁህ ውሀና ሳሙና ወይም ኦሞ ይደረጋል ሁሉም ጨሌያቸውን ከአንገታቸው በማውጣት ሳህኑ ውስጥ ያስገባሉ፡፡ አሷራፊዋ ጨሌዎቹን እያጠበች ከሙሽራዋ በመጀመር ትመልሳለች፡፡ የጨሌ አመላለሱም የጨሌውን ¼ በሁለት እጇ በመያዝ ግንባራቸውን ሦስት ጊዜ በማስነካት አንገታቸው ላይ ካጠለቀች በኋላ ወደጉያቸው(በልብሳቸው ውስጥ) ታስገባለች፡፡ ከዚያም ፀጉራቸው ላይ ውሀ "የዘምዘም ውሀ[30] ያድርገው" እያለች በእጇ ታፈስላቸዋለች፡፡ ይህን የሚሉበትን ምክንያት አሷራፊ አንሻ ሰይድ እንደሚከተለው ነግረውኛል፡፡

> አላህ ለአጀቡ የኸለቀው የዘምዘም ውሀ ማንኛውንም አይነት በሽታ የሚፈውስ መድሀኒት ስለሆነ የዘምዘም ውሀ ያርገው እያልኩ የማፈስላቸው ይሄን እኛ የምንጠቀመውን ውሀ አላህ በፍቃዱ የዘምዘም ውሀ እንዲያደርገውና ከበሽታቸው እንዲላቀቁ ፣ እንዲሽሩ ሲባል ነው ፡፡ (ቃ.መ፣15/06/08፣ዋዚ)

በዚህ ሁኔታ አሷራፊዋ ሚናዋን ከተወጣች በኋላ የራሷን ጨሌ ደግሞ አበጋሪቱ በተመሳሳይ ሁኔታ ታጠልቅላታለች፣ውሀም ታፈስላታለች፡፡ ጨሌ ከተመለሰ በኋላ ወደቤት ይመለሳሉ፤ ወደ ቤት ሲገቡም እልል እልል እልል በማለት ቤት ውስጥ ላሉት ተሳታፊዎች የውጪን ሽኝት ክዋኔ መጨረሳቸውን ያበስራሉ፡፡ ቤት ውስጥ ያሉትም በተመሳሳይ እልልታ ይቀበሏቸዋል፡፡ ከዚያም ባለ ጉዝጓዟ፣አሷራፊዋና አበጋሯ በነባር ቦታቸው ላይ ሲቀመጡ ሌሎቹ ባገኙት ባዶ ቦታ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ከዚያም ቡና በካዳሚ አማካይነት ይፈላና አሷራፊዋ ጀበናውን እንደመያዝ አድርጋ "አወል ጀባ አወል ጀባ" ትላለች፡፡ ወዲያውም አበጋሯ መረሀባ በማለት ምርቃን ትሰጣለች፡፡ ምርቃቱ እንደሚከተለው ከተካሄደ በኋላ ዳቦ ይቀርብና በአሷራፊዋ ወይም በአበጋሯ ተቆራርሶ በካዳሚዎች ይታደላል፡፡ ቡቅሪና ጠላ ለሚፈልግም ይቀርባል፡፡ ከዚያም ቡናው በካዳሚዋ ተቀድቶ በካዳሚ ለሁሉም ይዳረሳል፡፡

| **አበጋሪት** | **ባለ ጉዝጓዝ** | **ተሳታፊዎች** |
|---|---|---|
| እርፎ መረባ (2 ጊዜ) | አሜን | መረባ |
| እንግዲህ በሽታ አይንካት | " | " |
| ቁጭ ብላ ትብላ | " | " |
| ዕድሜዋ ረጅም ይሁን | " | " |

---

[30] የዘምዘም ውሀ በእስልምና ሀይማኖት የታወቀ ሀይማኖታዊና ባህላዊ በሽታ መፈወሻ ነው፡፡ ይህ ውሀ በሳዑዲ አረብያ መካ ከተማ የሚገኝ ተፈጥሯዊ ውሀ ሲሆን ከሞት በስተቀር ማንኛውንም በሽታ ማዳን ይችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ከእንግዲህ በላይ ቁጥቡ መጀን ” ”
ሁሉም ይታረቋት… ” ”
ይሁን በይ እርፎ አሜን ይሁን

ቡናው እስከ ሦስተኛው ከአበጋሯ በተጨማሪ ምርቃት መስጠት የሚፈልጉ ተሳታፊዎች እየመረቁ ከተጠጣ በኂላ ቅቤ መቀባት ስርአት ይካሄዳል፡፡ ቅቤው ቃሉ(ያልቀለጠ) ሲሆን ሁሉንም ተሳታፊዎች የምትቀባው አሏራፊዋ ናት፡፡ የአቀባብ ስርአቱ የሚጀመረው ከባለ ጉዝጓዟ ሲሆን በእልልታ ታጅቦ ይከናወናል፡፡ ሁሉም ተሳታፊዎች “እልል እልል እልል” እያሉ አሏራፊዋም ይህንኑ እያለች ባለ ጉዝጓዟን ከፀጉሯ በመጀመር እጅና እግሯን ጭምር ትቀባለች፡፡ በመቀጠል የራሷን ፀጉር ቀብታ ከበረኛይቱ ጀምራ ከቀኝ ወደግራ ሁሉንም ተሳታፊ እናት እናታቸው ላይ ትቀባለች፡፡እንዲሁም በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ለሁሉም ሽቶ ትቀባለች፡፡



ምስል 9. አሏራፊዋ ባለጉዝጓዟንና ተሳታፊዎችን ቅቤና ሽቶ ስትቀባ[31]

በዚህ ሁኔታ የቅቤ መቀባቱ ክንውን ከተጠናቀቀ በኂላ የዛር ሽኝት ቃል ግጥም በጭብጨባ፣በማሲንቆና በድቤ ታግዞ ይዜማል፡፡ ቃል ግጥሙ የሚጀመረው በማሲንቆና በድቤ ምት ሲሆን ከጥቂት ቆይታ በኂላ አሏራፊዋ እንሂድ ይላሉ እንሂደው በሰፊው መንገድ በጎዳናው በማለት ትጀምራለች፡፡

---

[31] የመጀመሪያው ምስል አሏራፊዋ ባለ ጉዝጓዟን ፣ሁለተኛው ደግሞ ሌላ ተሳታፊን ቅቤ ስትቀባ ሲሆን ሦስተኛው ምስል አበጋሯን ሽቶ ስትቀባ የሚያሳዩ ናቸው፡፡(ምልከታ፣30/05/08፣ቤሬ)

| **አሷራፊ** | **ተሳታፊዎች** |
| --- | --- |
| እንሂድ ይላሉ እንሂደው | እንሂድ ይላሉ እንሂደው |
| በሰፊው መንገድ በጎዳናው | በሲፊው መንገድ በጎዳናው |
| ቁጥቤ ዋድ እንነጋገር | ዋድ እንነጋገር |
| የቤትሽን ነገር፣የልጅሽን ነገር | ዋድ እንነጋገር |
| ................................ | .................. |

አዝማች

ይህ ቃል ግጥም ሁሉም  የዛር መንፈሶች መሸኘታቸውን(መሄዳቸውን) የሚገልፅ ሲሆን አደራን የያዘ ነው፡፡ ማለትም ዛሮቹ ባለ ጉዝጓዟን ከማንኛውም መጥፎ ነገር እንዲጠብቋት ለዛሮቹ አደራ የሚሰጥበት ጭምር ነው፡፡

ከዚህ ቃል ግጥም በኋላ በካዳሚ ሻይ ተፈልቶ ይቀርባል፡፡ አሷራፊዋ እንደሚከተለው የክዋኔውን መዝጊያ ምርቃት ከመረቀች በኋላ ቡናውን የቀዳችው ተሳተፊ ትቀዳና ሁሉም ሰው ይጠጣል፡፡

| **አበጋዟ** | **ሻይ ቀጂ ሚዜና ባለ ጉዝጓዝ** | **ተሳታፊዎች** |
| --- | --- | --- |
| እርፎ መረባ | አሚን | መረባ |
| እርፎ በረባ | አሚን | መረባ |
| በሙዳው ለመናቸው | አሚን | መረባ |
| በማሩ ለመናቸው | ” | ” |
| በዱበርቲ ለመናቸው | ” | ” |
| በልተው ጠጥተው | ” | ” |
| እሰፊው አገር… | ” | ” |
| ይስማማት | ” | ” |
| ይታረቃት | ” | ” |
| አሷም ደህና ትሁን | ” | ” |
| ልጆቿም ደህና ይሁኑ | ” | ” |
| ይሁን በይ እቴ | አሜን | ይሁን |

ሻይው ተቀድቶ ሁሉም ሰው ከጠጣ በኋላ ከላይ የተጠቀሰው የሸኙት ቃል ግጥም በድጋሜ ተደጋግሞ ይዜማል፡፡ከዚያም አሷፊዋ በሁለቱንም እጇ ወደፊት በማንቀሳቀስ የመሄድ (የሸኙት) ምልክት እያሳየች በንግግር(ያለዜማ) “ይሂዱ ይሂዱ ሰፊ ነው መንገዱ ይሂዱ ይሂዱ እለመለመው ሳር፣ይሂዱ ይሂዱ እጠራው ውሀ” ስትል ሁሉም ተሳታፊ እጃቸውን እንደ እሷ በማድረግ ይሂዱ ይሂዱ ይሂዱ ይላሉ፡፡ በመቀጠል በድጋሜ ቃል ግጥሙን በማዜም በውዝዋዜ ጭምር እስኪበቃቸው

ይጨፍራሉ። በመጨረሻም የተዘጋጀውን ድግስ ሁሉ በልተውና ጠጥተው ተሰነባብተው ወደየ ቤታቸው ይሄዳሉ። አንዳንድ ጎረቤት የሆኑና መቆየት የፈለጉ ተሳታፊዎች ወዲያው ላይሄዱ ይችላሉ።

## 4.6. የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የሚሰጠው ፋይዳ

ገፈራ ከላይ በትንተናው ለማብራራት እንደተሞከረው ለዛር የሚደረግ ድግስ ሲሆን የራሱ የሆነ መለያ ስርአት አለው። ይህ ስርአተ ክዋኔ ለከዋኞቹ ከሚሰጣቸው ፋይዳዎች ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

- የተወዛገቡ ሰዎች ችግራቸውን በመፍታት በጤነኛ አዕምሮ ተረጋግተውና ተስማምተው ከማህበረሰቡ ጋር ተቀላቅለው እና ሰላማዊ ትስስር ፈጥረው በስርአቱ ውስጥ እንዲኖሩ ያስችላቸዋል።
- ብቸኝነትን በማስቀረት ግለሰቦችንና የማህበረሰቡን የርስበርስ ግንኙነት ያጠናክራል።
- የርስበርስ ትስስራቸው ስለሚጠነክር የማህበረሰቡ መዋቅር እንዳይፈርስ ይረዳል።
- ስነልቦናዊ ህመማቸው ፈውስ ያስገኝላቸዋል።
- ለተወሰነው የማህበረሰብ ክፍል መገለጫ የሚሆኑ ቃል ግጥሞች ፣ ከበራዎች እንዲኖራቸው ያደርጋል።
- የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ሳይረሳ በማህበረሰቡ ውስጥ በቃልና በተግባር ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ያደርጋል።

## 4.7. የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ፎክሎራዊ ተግባራት

ፎክሎር በርካታ ተግባሮች ያሉት ሲሆን ይህንንም በማስመልከት Bascom (1954፣ 279—298) የፎክሎርን ተግባር የመትከልና የማጠናከር፣ የመግለጥ፣ የማስተማር እና ማህበረሰብን የመቆጣጠር ተግባራት እንዳሉት “escape”፣ “validation” ፣ “education” እና “social control” በማለት በአራት ይከፍላቸዋል። ከዚህም በመነሳት የገፈራን ስርአተ-ክዋኔ ተግባራት እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል።

### 4.7.1. የመትከልና የማጠናከር ተግባር

- በገፈራ ክዋኔ ላይ ለመሳተፍ በመጡ ወጣቶችና ህፃናት ላይ ባህሉን በማስረፅ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ ስለሚያደርግ የመትከልና የማጠናከር ተግባር አለው፡
- በተጨማሪም ለስርአቱ ሲባል የሚተገብሯቸው ደንብና ስርአቶች ሠናይ ምግባራትን ያጠናክራሉ፡፡
- ለክዋኔው ግብአት የሚደረገው የጀባታ(ስጦታ) ባህል እና በስራ መተጋገዝ የማህበረሰቡን የመረዳዳትና የመተባበር ባህል ያጠናክራል፡፡

### 4.7.2 የማምለጥ ተግባር

- ክዋኔው በድቤና በማሲንቆ የታጀቡ ቃል ግጥሞች እና እንጉርጉሮዎች ስላሉት ተሳታፊዎች ከአሰልችው የህይወት ውጣ ውረድ በማምለጥ ዘና ይሉበታል፣ስነ-ልቦናዊ እርካታ ያገኙበታል፡፡[32] ስለሆነም የገፈራ ክዋኔ የማምለጥ(ማምለጫ) ተግባር አለው፡፡
- ገፈራ አድራጊዎቹ ዛር አርፎብኛል በሚል ጭንቀት ከሚመጣ ህመም በክዋኔው ላይ ያለምንም ይሉኝታ በመጨፈር ከጭንቀታቸው አምልጠው እፎይታን ያገኛሉ፡፡

---

[32] ይህንን ሀሳብ በተመለከተ Prown፣ (1982፡3). የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል፡፡
Objects created in the past are the only historical occurrences that continue to exist the present. They provide an opportunity by which we encounter the past at first hand; we havedirect sensory experience of surviving historical events.

## ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በወረባቦ ወረዳ የሚካሄደውን የገፊራ ስርአተ ክዋኔን መተንተንን ትኩረት አድርጎ የተካሄደ ነው፡፡ ስለሆነም ክዋኔውን በሁነቶች ቅደም ተከተል መሰረት በመከፋፈልና በመመርመር ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በክዋኔው ላይ የሚዜሙና የሚነገሩ ቃል ግጥሞች እንዴትና ለምን እንደሚቀርቡ ተግባራቸውን ለማሳየት፣ ለክዋኔው ምሉዕነት አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ ባህሎች አገልግሎታቸውንና ትርጉማቸውን እንዲሁም ማህበረሰቡ ለገፊራ ባህል ያለውን አመለካከት ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

የጥናቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስና የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ በሁለት ዙር የመስክ ቆይታ ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅን እና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ መረጃዎቹም በተፈጥሯዊ መቼት የተገኙ ሲሆን ፍቃደኛ ከሆኑ መረጃ አቀባዮች በምስል፣ በምስልና በድምፅ እና በድምፅ ብቻ ተቀርፀዋል፡፡ በሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችን በክዋኔ ንድፈ ሀሳብ በመታገዝ በገላጭ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ በገፊራ ክዋኔ ላይ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ገፊራ የመንፈስ ውህደት (በመንፈስ ቁጥጥር ስር መሆን ) ከሚገለፅባቸው ከበራዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን የዛር መንፈስ የተዋሀዳቸው ሰዎች ስነ-ልቦናዊ ወይም መንፈሳዊ ንፅህና ፣ የአዕምሮ እርካታ ፣ የመዳን ተስፋን ፣ ዕድገትና ብልፅግና ፣ ወዘተ ለመጎናፀፍ ሲሉ ለሰፈረባቸው የዛር አይነት የሚያቀርቡት የግብር ድግስ ስነ-ስርአት ነው፡፡ የገፊራ ክዋኔ አላማ በሰዎች ላይ በሽታን ፣ መጥፎ የባህሪ ለውጥን ፣ ሰላም ማጣትን፣ ወዘተ ከሚያስከትለው መንፈስ ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት በማድረግና መንፈሱ የሚያስፈልገውን በተደጋጋሚ ግብር በማሟላት የአዕምሮ ህመምን (አደጋ ይደርስብኛል ብሎ በመፍራት ከሚመጣው የጭንቀት በሽታ) መፈወስ ነው፤ እፎይታ ማግኘት ነው፡፡

የገፊራ ስርአተ ክዋኔ በልዩ ልዩ ቅድመ ዝግጅቶች የሚጀምር ሲሆን የሦስት ተከታታይ ቀናት ክዋኔ ነው፡፡ ቅድመ ዝግጅቱ የገፊራ አድራጊዎች የልመና ስርአት፣ የብቅል ውሀ ትጥበት፣የቀን ቆረጣ እና ክዋኔው ስርአቱን በጠበቀ መልኩ እንዲካሄድ የሚያስችሉ የምግብና የመጠጥ ዝግጅት፣ የቁሳቁስና አልባሳት አቅርቦት እና የቦታ መሰናዶን

የሚያካትት ነው፡፡ ገፈራ አድራጊዎች የሚሰማሩባቸው ልመናዎች ሁለት አይነት ሲሆኑ መተናነሳቸውን ለዛር መንፈስ የሚያሳዩባቸው ናቸው፡፡ እነዚህም ከአሚኖች(ከመጀመሪያ የትዳር አጋራቸው ጋር ያልተፋቱና በመኖር ላይ ከሚገኙ ሰዎች) የሚደረግ ልመና እና ከማንኛውም ሰው ቤት የሚደረግ ልመና ናቸው፡፡ በብቅል ውሀ የሚደረገው ትጥበት ደግሞ የዛር መንፈሶችን ለማስደሰትና ራሳቸውን ለማፅዳት ሲባል የሚደረግ ነው፡፡ ገፈራ የሚካሄድባቸው ወራት ጥር፣ የካቲትና መጋቢት ሲሆኑ ዕለታት ደግሞ ሰኞ ማታ ለማክሰኞ፣ ረቡዕ ማታ ለሀሙስ እና አርብ ማታ ለቅዳሜ ነው፡፡ በሌሎች ዕለታት የማይካሄደው ተሳታፊዎቹ የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው የሚያከብሯቸው በዓላት ስላሉ ሲሆን በተመረጡት ዕለታት የሚውል ኢስላማዊ ክብረ በዓልና ካለ በዚያ ቀን ገፈራ አይደረግም፡፡ የተጠቀሱት ወራት የተመረጡት አዝመራ ተሰብስቦ የሚገባባቸውና አብዛኛው ሰው ረፍት የሚያገኝባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ተመራጭነት የኖራቸው ድግስ ለማድረግና ተሳታፊ ለማግኘት አመቺ አጋጣሚዎች ስለሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ወራት በእስልምና ሀይማኖት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የረመዳን ፆም ከገባ ገፈራ አይደረግም፡፡

በገፈራ ክዋኔ ላይ የተስተዋሉት ሁነቶች በዋናነት የዛር ተለማምኖ፣የቡና ስነ-ስርአት፣ ጉሪያ(ማጉራት)፣ የራት ስነ-ስርአት፣የጫት ጀባታ፣ዱአ፣ ምርቃት እና የጨሌ ነከራ ሂደት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁነቶች በአሷራፊ (በዛር አስታራቂ) መሪነት በሚዜሙ ቃል ግጥሞችና በአበጋር አለቃነትና ምርቃት ሰጪነት እንዲሁም በተሳታፊ ምርቃት ተቀባይነት ይከወናሉ፡፡ የእነዚህ አጠቃላይ መጠሪያ ሀድራ ሲሆን የክዋኔውን አጠቃላይ ድባብ የሚያመለክት ነው፡፡ ቃል ግጥሞቹ በሚከወኑበት የክዋኔ ሂደት (በሀድራው ላይ በሚቀርቡበት መንገድ) አንፃር በድቤ፣ በመሲንቆና በጭብጨባ የሚዜሙ፣ የአሷራፊ እጉርጉሮዎች፣ የአሷራፊ የተለማምኖ ንግግሮች(መነባንቦች) እንደሚባሉ መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ሁነቶቹ ርስበርስ የተቆራኙና ተከታታይነት ያላቸው ሲሆኑ ተሳታፊዎቹም ይህንን አውቀው ይፈፅሟቸዋል፡፡

የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ በቅድመ ዝግጅት እንደሚጀምር ሁሉ የራሱ የማጠቃለያ ስርአት አለው፡፡ ይኸውም የገፈራ ሦስተኛው ቀን ሲሆን የጠረጋ ቀን በመባል የሚጠራ ነው፡፡ ይህ የጠረጋ ቀን የክዋኔው ማጠቃለያ ሲሆን ገፈራ የተደረገላቸው የዛር መንፈሶች የሚሸኙበትን ክዋኔ የሚያካትት የሽኘት ስነስርአት ነው፡፡ የሽኘት ስነ-ስርአቱ በቤት

ጠረጋ የሚጀምር ሲሆን የዛር መንፈሶች በቃል ግጥም የሚሸኙበት፣ ከሁለት አመት በኋላ ግብር እንደሚሰጣቸው ቃል የሚገባበት እና ባለጉዝጓዟ በአዲስና በተረጋጋ መንፈስ ወደ ማህበረሰቡ የምትቀላቀልበት ነው፡፡ ስለሆነም የስርአተ-ክዋኔው ማጠቃለያ ቀን ሲሆን የከበራው ዓላማ አካላዊና ህሊናዊ መፅዳትን (ፅዱነትን) ማግኘት እንደሆነ ያመላክታል፡፡

ከገፈራ ክዋኔ ጋር በተገናኘ የቃላዊ ግጥሞቹን ክዋኔ ለማጀብ፣ ሀድራውን ለማድመቅና የዛር መንፈሶችን ለመጥራት የሚያገለግሉ ድቤና ማሲንቆ እና ክዋኔው ላይ አይቀሬ የሆነው ጨሌና የዛር መንፈሶችን ለመጥራት የሚያስፈልጉና አውዱን በጥሩ መአዛ የሚያውዱ ጭሳጭሶች አስፈላጊ ቁሳዊ ባህሎች መሆናቸው ተገልጿል፡፡ እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች በክዋኔው ሂደት ካላቸው ሚና አንጻር፤ ከግልጋሎታቸው በተጨማሪ ማህበራዊና ባህላዊ ጉዳይ ጋር አያይዘን ስንመረምራቸው ሶስት ባህሪያትን ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡ እነሱም የመጀመሪያው የተፈጥሮአዊና የተለጣፊ እሴት ባለቤትነት ፣ ታሪክ ነቃሽነት ፣ የበለጠ ወካይነት ባህሪ ይዘው ተገኝተዋል፡፡

የገፈራ ስርአተ ክዋኔ ስነ-ልቦናዊ ህመምን በመፈወስ ፣ የርስበርስ ትስስርን በማጎልበት ፣በወጣቱ ትውልድ ላይ ባህሉን በማስረፅ ባህሉ ቀጣይነት እንዲኖረዉ በማድረግ ለባህሉ አራማጆች ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ አሉት፡፡

ባህሉን በማስረፅ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ፣ ሰናይ ስነ-ምግባራት ፣ የመረዳዳትና የመተባበር ባህል በማጠናከር የየመትከልና የማጠናከር ተግባር አለው፡፡ ተሳታፊዎች ከአሰልችው የህይወት ውጣ ውረድ በማምለጥ ዘና ይሉበታል፣ስነ-ልቦናዊ እርካታ በማስገኘት እና ገፈራ አድራጊዎቹ ዛር አርፎብኛል በሚል ጭንቀት ከሚመጣ ህመም በክዋኔው ላይ ያለምንም ይሉኝታ በመጨፈር ከጭንቀታቸው አምልጠው እፎይታን ያገኛሉ፡፡ ስለሆነም የማምለጫ(የማምለጥ) ተግባር አለው፡፡ ስለዚህ የገፈራ ስርአተ-ክዋኔ ማህበራዊ፣ባህላዊ እና ፎክሎራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡

ቢሆንም ይህ ባህል አጉል ባህል በሚል አመለካከት፣ በስልጣኔና በሀይማኖት ተፅዕኖ ምክንያት በመጥፋት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ባህሉ የሚሰጠውን ፋይዳ ተረድቶ ክዋኔው ከቁሳዊ ባህሎቹና ቃል ግጥሞቹ ጋር ለቀጣይ ትውልድ ሊተላለፍ የሚችልበትን መንገድ ቢያመቻች የተሸለ ነው፡፡

ከገፈራ በተጨማሪ በማህበረሰቡ ውስጥ ለዛር የሚደረጉ ስነ-ስርአቶች ውስጥ ሰፊ የሆነውና በጨሌዎቹ ቀለማት ቁጥር ልክ ለዛር ግብር እርድ የሚካሄድበት መወከል የተባለ ስነ-ስርአት መኖሩን በመስክ ቆይታየ አረጋግጫለሁ። ስለሆነም ይህን ስነ-ስርአት ከገፈራ ስነ-ስርአት ጋር በንፅፅር ወይም ራሱን ችሎ በሰፊው መጠናት እንደሚችል ጥቆማ መስጠት እፈልጋለሁ።

የማህበረሰቡ የመረዳዳት ባህል የሆነው የጀባታ(ስጦታ) በማህበረሰቡ የተለያዩ ክበራዎች ለምሳሌ፡-በወዳጃ፣በመወከል፣በመውሊድ፣በሰርግ፣በፋጢማ ቆሪ (የቅድመ ወሊድ ስነ-ስርአት) ላይ የሚካሄድና እንደየክበራው ዓላማውም የተለያየ መሆኑን የማህበረሰቡ አባል በመሆኔ እና በመስክ ቆይታየ መረዳት ችያለሁ። በመሆኑም ይህ ባህል በሰፊው ሊጠና ይችላል የሚል እምነት አለኝ።

## ዋቢ ፅሁፎች


ለቺሳ አሰፋ። "በጨሊያ አውራጃ ስለውቃቢ ያለው እምነትና የእምነት መገለጫ ግጥሞች"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982 ዓ.ም.

መኮንን ለገሰ። "የአቴቴ ፈጨሳ ክንዋኔና ሥነ-ቃላዊ ግጥሞች በተጉለት ቡልጋ አውራጃ"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982 ዓ.ም.፡

ሰይድ መሀመድ ሳዲቅ እና መሀመድ ሳኒ ሀቢብ። *ቅዱስ ቁርኣን*፡ አዲስ አበባ፣ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣2ኛ እትም ፣ትርጉም፣1997ዓ.ም.

ሰፋል ረህማን አል-ሙባረክ። *ረውደቱል አንዋር*። አዲስ አበባ፣ሂላል ሊሚትድ ማተሚያ ቤት፣1ኛ እትም፣1981 ዓ.ም.

ሲሳይ አራጋው። "የቢሾፍቱ ከተማ የዛር ግጥሞች"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999 ዓ.ም.።

ተመስገን ፋንታዬ። "የዛር ትውፊትና በውስጡ የሚገኙ ትያትራዊ አላባዊያን በራያና ቆቦ አካባቢ"። ትያትርና ጥበባት ትምህርት ክፍል ለአርትስ ባችለር ድግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1995 ዓ.ም.።

ታደገኝ መርን። "በመንዝ ላሎ ማማ ምድር ወረዳ የሚገኙ ውቃቤዎች ልዩ ልዩ ገፅታዎች"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣1992 ዓ.ም. ።

አዲስ ይትባረክ። "የእምነት ውህደት በዝቋላ አቦ ክብረ-በአል"። የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣የድህረ ምረቃ መርሀ ግብር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣2005 ዓ.ም.

እንዳልካቸው አካሉ። "በምዕራብ ሀረርጌ (ጨርጨር) አካባቢ የአወሊያ ቤት የልመና ግጥሞች ይዘት ትንተና"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣

ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993 ዓ.ም።

እንድሪስ ይማም። "የዛር ዘፈን ግጥሞች ክዋኔ በወግዲ ወረዳ"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1997 ዓ.ም.

ወልዱ ይንገሱ። "የዛር ትያትራዊ ክንውን ሲምዩቲክ ጥናት"። የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1991 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል። *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣የካቲት 1993 ዓ.ም.

የውልሰው ላለት። "አዋቂና የጥንቆላ ስራው በደብረ ማርቆስ አካባቢ"። የዲግሪ መመረቂያ ፅሁፍ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1992 ዓ.ም።

ደረጀ አበበ። *ባዕድ አምልኮ በሃይማኖት ጥላ ሥር*፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት ፣አዲስ አበባ 1988 ዓ.ም.

ፈቃደ አዘዘ። የስነ-ቃል መምሪያ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1991ዓ.ም.

Al-Adawi, Samir H., Martin, Rodger G., Al-Salmi, Ahmed, and Ghassani, Harith. "Zar group distress & healing." *Mental Health, Religion and Culture.* Department of Behavioural Sciences & Psychiatry, Collage of Medicine, Sultan Qaboos University, Oman, 2001, 4 (1), 47-61.

Arvihurskainen. "Special Epidemiological Spirit Possession, Among the Massai Tanzania". *Invasion of Spirit Possession*, Nordic Jornal of African studies 14, University of Helsinki Finland, Issue 2004.

Ashkanani Zubaydah Ali M.H. “Middle-Age Women in Kuwait: Victims of Change.” Durham Thesis, Durham University. Available at Durham E. Thesis on line. http:etheses.dur.ac.uk(1695), 1988.

Bauman, Richard, “Methods Cultural Context of Meaning”, in *A Handbook of_American Folklore.* Dorson, Richard, M. (ed), Bloomington: Indiana University Press 1982.

Bauman, Richard, and Briggs L, Charles. “Poetics and Performance as Critical Perspectives on Language and Social life”: *Annual Review of Anthropology.* New York: Vassur College, 1990. Vol. 19

Bauman, Richard. ed. *Folklore Cultural Performances, and Popular Entertainment.* New York Oxford University Press, 1992.

___________. *Folklore Geners*. Texas University of Texax, 1976.

Bronner, Simon J. *Arts, Performance, and Praxis*: The Rhetoric of Contemporary Folklore studies Western Folklore, 1988, Vol, 47, No. 2. pp. 75-101.

Cohen Emma “What is spirit possession? *Defining, Comparing, and Explaining Two possession Forms*. University of Oxford, UK. ETHNOS, march 2008 Vol. 73 I, (pp.xx-xx)”

Cohen, Emma and Justin Barrett. (in press a) *When Minds Migrate: Conceptualizing Spirit Possession* Journal of Cognition and Culture. University of Oxford, UK. ETHNOS, march 2008 Vol. 73 I, (pp.xx-xx)”

.________________ “Conceptualizing Spirit Possession: Ethnographic and Experimental Evidence.” America Anthropological Association ETHOS, 2008, Vol 36, Issue 2, pp. 246-267.

Denneths, Goldstein, and Henderson, Hapminsh. “A Guid for field workers in Folklore”. *The American Folklore Society*. Pensilvaniya 1964.

Dundes, Alen. *Interpreting folklore*, New York: university of Chicago, University Press, 1986.

Erku yimer. “The Zar Cult as an out let to express suppressed feeling and its impact on Ethiopian personality”. AddisAbaba, 1966.

Federal Democratic Repuplic of Ethiopia Population Census Commission, *The 2007 Population And Housing Census of Ethiopia*, Result For Amhara Region, Addis Abeba, August 2010.Part 1, Table 1.

Finnegan, Ruth. *Oral Poetry its Nature, Singificance and Social Context.* London and New York: Cambridge University Press, 1977.

.__________*Oral Traditions and the Verbal Arts: A Gide to Reasearch Practices,* New York: Routledge, Inc, 1992.

Goldstein, Kenneth. *A Guide For field workers in Folklore*. London: Folklore Associates, Inc., 1964.

Rappaport, Roy A. *Folklore, Cultural Performances, and Popular 90 Ertainments*, Ed. Richard Bauman, (249-260). New York, Oxford University Press. 1992

Gray E, David, *Doing Research in the Real World.* London, Sage publication, Thousand. Oaks New Delhi, 2004.

Hufford Marry. “Common Ground: Key words for the study of expressive culture”. *The journal of American folklore*, 1995, Vol. 108, No. 430.

___________ "Context: Key Words for the Study of expressive Culture". *The Journal of American folkore*: Autumn American folklore society, 1995: 528-549.

Kapchan, A. Deborah. Performance. *The Journal of American folklore*. New York 1995: Vol. 108, No. 430.

Kennedy, J. "Nubian Zar Cermonies as Psychotherapy", Human Organization (2), Winter, 1967 NO.4.

Lewis I. M, *Zar in context: The past, The present and Future of an African Healing Cult.* In I.M. Lewis, A.Al-safi and S. Hurrez, eds. *Women's Medicine: The zar Bori Cult in Africa and Beyond.* Edinburgh: Edinburgh university press, 1991, pp. 1-16.

___________ *Spirit Possession and Desprivation Cult*. Man, New series, 1966, Vol, 1, No. 3, pp.307-329.

Martha C. Sims Martine Stephens. *Living folklore, An introduction to the study of_people and their traditions* Ohio Wesleyan university, Utah state university press/Logan, Utah. 2005.

Messing, S.D, "Group Therapy and Social Status in the Zar Cult of Ethiopia." *American Anthropologist*, new Series vol. 60, No. 6:1, 1958. pp. /120-126/.

Nicole M. Monteiro, and Diana J. Wall. "African Dance as Healing Modality Through out the Diaspora: The use of Ritual and movement to work Through Travma." *The Journal of Pan African studies*, 2011, vol. 4. No. 6. pp. 234-252.

Pereira, S., Bhui, K. ,& Dein, S. *Making Sense of Possession States Psychopathology and differential-diagonosis.* British Journal of Hospital Medicine, 1995, Vol 53, 582-362.

Prown J. D. *Mind in M*atter*: An Introduction to Material Culture Theory and Method Source*: Winterthur Portfolio, The University of Chicago Press, (Spring, 1982), Vol. 17, No. 1, pp. 1-19

Rappaport, Roy A. *Folklore, Cultural Performances, and Popular 90 Ertainments*, Ed. Richard Bauman, New York, Oxford University Press, 1992, pp. 249-260.

Richard Schechner. *Performance Theory*, New York, Routledge,1988.

Smith, M. *Baba of Karo*. Faber & Faber, London, 1954.

Timkehet Teffera, "ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ (YAGARUN SARDO BAGARU BARE) Zar Sprit Possession Among the Amhara and the role of Music," paper presented on the 9th International symposium music in societys Sarajevo, 2014, pp. 20-26.

Torrey, E. Fuller, The Zar Cult in Ethiopia. *International Journal of Social Psychiatry*, 13, 1967. pp. 216-223.

William R. Bascom. *Four Functions of Folklore*. Journal of American Folklore, Royal Anthropological Institiute of Great Britian & Ireland, 1954, vol.67, no.266, pp. 277-298.

http://en Wikipedia. Org/wiki*/Spirit Possession*.

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | ቀበሌ | ጎጥ | መተዳደሪያ | ሚና |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወ/ሮ ዘይነባ አደም | ሴ | 68 | ቡልቡሎ | ዱሬ | ግብርና | አበጋር |
| 2. | ሀያት እንድሪስ | ሴ | 26 | ቁኖ | ዋዚ | ስራ የለም | ካዳሚ |
| 3. | ሀድያ አደም | ሴ | 30 | ፊቶ | ቤሬ | ስራ የለም | ካዳሚ |
| 4. | መሀመድ አሊ | ወ | 28 | ፊቶ | ቤሬ | ተማሪ | ልጅ ጨት ጀቢና ካዳሚ |
| 5. | ሚፍታህ መሀመድ | ወ | 20 | ሀራ | ቸሪት | ተማሪ | ተሳታፊ |
| 6. | ወ/ሮ ሰሚራ አህመድ | ሴ | 35 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | ካዳሚ |
| 7. | ወ/ሮ ሶፍያ አሊ | ሴ | 35 | ሀራ | ቸሪት | ግብርና | ካዳሚ |
| 8. | በላይነሽ አህመድ | ሴ | 25 | ሀራ | ዋዚ | ተማሪ | ተሳታፊ |
| 9. | አቶ መሀመድ ሀሰን | ወ | 45 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | የአካባቢው ነዋሪ |
| 10. | አቶ መኮነን አህመድ | ወ | 50 | ፊቶ | ቤሬ | ግብርና | ተሳታፊ |
| 11. | አቶ አህመድ አሊ | ወ | 60 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | ባል ጫት ጀቢና ካዳሚ |
| 12. | አቶ አሊ ሰይድ | ወ | 40 | ቡልቡሎ | ዱሬ | ግብርና | የቸሪትና የቡልቡሎ ማሲንቆ ተጫዋች |
| 13. | አቶ አብዱ ረያን | ወ | 40 | ፊቶ | ቤሬ | ግብርና | ፊቶና ቁኖ አሏራፊ |
| 14. | አቶ አደም እንድሪስ | ወ | 65 | ፊቶ | ቀርሱ | ግብርና | የፊቶና ቁኖ ማሲንቆ ተጫዋች |
| 15. | አቶአደም አወል | ሴ | 55 | ሀራ | ቸሪት | ግብርና | የሀራና ቡልቡሎ አሏራፊ |
| 16. | ወ/ሮ ሀሊማ ዑመር | ሴ | 65 | ሀራ | ቸሪት | ግብርና | አሏራፊ |
| 17. | ወ/ሮ ሀድያ ሲራጅ | ሴ | 60 | ቡልቡሎ | ዱሬ | ግብርና | አሏራፊ |
| 18. | ወ/ሮ ሉባባ ሁሴን | ሴ | 55 | ፊቶ | ቤሬ | ግብርና | አሏራፊ |
| 19. | ወ/ሮ መይረማ እንድሪስ | ሴ | 70 | ሀራ | ቸሪት | ግብርና | ባለ ጉዝጓዝ |
| 20. | ወ/ሮ አሚናት አሊ | ሴ | 75 | ፊቶ | ቤሬ | ግብርና | የፊቶ አበጋር |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21. | ወ/ሮ አረጋሽ አህመድ | ሴ | 50 | ፊቶ | ቤሬ | ግብርና | ባለ ጉዝጓዝ |
| 22. | ወ/ሮ አንሻ ሰይድ | ሴ | 45 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | አሷራፊ |
| 23. | ወ/ሮ አንሻ አሊ | ሴ | 65 | ቡልቡሎ | ዱሬ | ግብርና | ባለ ጉዝጓዝ |
| 24. | ወ/ሮ ከድጃ ሁሴን | ሴ | 55 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | ባለ ጉዝጓዝ |
| 25. | ወ/ሮ ዘሀቡ ይማም | ሴ | 50 | ፊቶ | ቀርሱ | ግብርና | ባለ ጉዝጓዝ |
| 26. | ወ/ሮ ዘምዘም አሊ | ሴ | 63 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | አበጋር |
| 27. | ወ/ሮ ጦይባ መሀመድ | ሴ | 70 | ሀራ | ቸሪት | ግብርና | አበጋር |
| 28. | ወ/ሮ ፋጡማ ሰይድ | ሴ | 58 | ቁኖ | ዋዚ | ግብርና | ባለ ጉዝጓዝ |
| 29. | ወ/ሮ ወርቅነሽ አህመድ | ሴ | 40 | ቡልቡሎ | ዱሬ | ግብርና | ካዳሚ |
| 30. | ወ/ሮ ዚነት መኮነን | ሴ | 32 | ፊቶ | ቀርሱ | ግብርና | ካዳሚ |
| 31 | ሸኽ ሰይድ አደም | ወ | 50 | ፊቶ | ቤሬ | ግብርና | የሀይማኖት አባት |

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ  የገፈራ ክዋኔ ቃል ግጥሞች

## 1.1. የተለማምኖ ቃል ግጥሞች

### 1.1.1.  ለሴት ዛር የተባለ የተለማምኖ ቃል ግጥሞች

**11.1.1. ንግግራዊ ቃል ግጥም**

**ቃል ግጥም 1**

**እልልልል**

እልልልል...፣
አቤት ለበይክ ብያለሁ እናቴዋ፣
ወርቄዋ ልመናዋን ልትቀበያት፣
አዎ እናቴዋ ቃየዋን ልጠቢቂላት፣
ልጆቸዋን ልጠብቂላት፣
አቤት ብያለሁ ወርቄዋ፣
ለማኝ ሳታጪ ለመንኩሽ፣
በሚዜ ይሁንብሽ፣ በዱበርቲ ይሁንብሽ፣
በሴት በወንዱ ይሁንብሽ እናቴዋ፣
ሙሉ ጤና ልትሰጭልኝ፣
የጤሰውን ቤት ልታደምቂልኝ፣
አቤት ብያለሁ አቤት በይኝ እናቴዋ፣
መጀን ብየ ነው እናቴዋ፣
ሊላህ ብያለሁ ወርቄዋ ፣
አሜን፡፡

**1.1.1.2.የዜማ ቃል ግጥም**

**ቃል ግጥም 2**

**እርቅ በይ እርቅ በይ**

እርቅበይ እርቅበይ እርቅበይ እርቅበይ፣
እርቅበይ እርቅበይ እርቅበይ እርቅበይ፣
እርቅበይ እርቅበይ፣
እርቅበይ እርቅበይ፣
ቁጥቤዋ አንቺ ባለጨፌ፣
አንቺ ባለአልቦ፣
ባለላስታ ቅቤ፣
እርቅበይ እርቅበይ እርቅበይ እርቅበይ፣
ባለ ብር አንባሯ ፣
ባለ ገፈታይቱ፣
እርቅበይ፡፡ (4 ጊዜ)
አዝማች

**ቃል ግጥም 3**

***አገሯ ወዲያ ነው***

*አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፣*
*አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማንነው፣*
*አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማን ነው ፡፡*
*አገሯ አገሯ ወዲያ እንዲያ አረቦቹ ገንዳ፣* (2 ጊዜ)
*አገሯ ወዲያ እንዲያ፣*
*አረቦቹ ገንዳ፡፡*
*አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፡፡* (2ጊዜ)
*አገሯ ወዲያ ነው፣*
*አገሯ ወዲያ ነው፣* (2 ጊዜ)
*ሂጂ ያለብኝ ማንነው፡፡* (2 ጊዜ)
*አገሯ ወዲያ እንዲያ፣*
*አረቦቹ ገንዳ፡፡*
*አገሯወዲያ እንዲያ፣*
*አረቦቹ ገንዳ፡፡*
*አንቺ ባለ ጨሬ፣ አንቺባለላስታ፣*
*አገሯ አገሯ ወዲያነው ሂጂ ያለብኝ ማነው፡፡* (4ጊዜ)
*አገሯ አገሯ ወዲያ ነው ሂጂ ያለብኝ ማን ነው፡፡*
*አዝማች*

**ቃል ግጥም 4**

***አሜን አሜን አሜን***

*አሜን አሜን አሜን፣* (8 ጊዜ)
*አሜን እማማየ አሜን አሜን፡፡*
*አሜን አሜን አሜን  አሜን፣*
*አንቺ ባለሙዳ፣*
*አሜን አሜን አሜን፡፡*
*አንቺ ባለጨሌ አሜን አሜን አሜን፣*
*ባለ ብር አምባሯ  አሜን አሜን አሜን፣*
*አንቺ ባለ ጉዝጓዝ አሜን አሜን አሜን፣*
*ባለ ላስታ ቅቤ አሜን አሜን አሜን፡፡*
*አንቺ አይደለሽም ወይ፣*
*ባለ ጥልፍ ቀሚስ ባለ ድርብ ኩታ፣*
*አዝማች*
*እልልል.....*

### 1.1.2. የወንድ ዛር ተለማምኖ ቃል ግጥሞች

#### 1.1.2.1. በዜማ የሚባሉ

**ቃል ግጥም 5**

**አማን አውለን**

አማን አውለን አማን አውለን፣
አማን አውለን አማን አውለን፣
አማን አውለን አሜን አማን አውለን፣
አማን አውለን አሜን አማን አውለን፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 6**

**አውሊያው መረሀባ በለን**

አውሊያው መረሀባ በለን፣
አውሊያው መረሀባ በለን፣
አውሊያው መረሀባ በለን፣
አውሊያው መረሀባ በለን፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 7**

**በእንጉርጉሮ የሚባሉ**

**ኧረ ምነው ኧረ ምነው**

አሜን ኧረ ምነው ኧረ ምነው፣
አሜን አሜን (2 ጊዜ) ፡፡
ኧረ ምነው ኧረ ምነው፣
ኧረ ምነው እኔ ኧረ ምነው እኔ፡፡ (4 ጊዜ)
አዝማች
ኧረ ምነው መገን እንደው እኔ፣
ምን ጊዜ መጣና አንቺየ ምንግዜ ደረሰ፡፡
አሜን አሜን አሜን፣
በጠዋት ጥመድና በጊዜ ፍታቸው፣
የሰው አገሮች በሮች (በሬዎች) እራትም የላቸው፡፡ ( 2 ጊዜ)
አሜን አሜን እንደው አሜን ፣
እስከ መቼ ድረስ አንቺየዋ እክክ ብየው ፣
በጊዜ ሄደ አሉ ሳልሰበስበው፡፡
አሜን አሜን አሜን፣
ያወጋ የለም ወይ የሆዱን ጥራት፣
በላኢላሀሀኢለሏሁ የፈታው ምላሱን፡፡
የሚያንገሸግሸው እምቢ ያለውን፣
ኧረ ምነው ኧረ ምነው (2 ጊዜ)፡፡
ቡናችን አፈራ ጫቱም ለመለመ፣
ዱአችን መቅቡል ነው ሁሉም ሰላም ሆነ፡፡
አሜን አሜን  አሜን ፣
አሁን ብለው ያሙናል እኛን፣
አቦል ቡን ጠጥተን ቅጠል ለበላን፡፡

አሜን አሜን አሜን፣
ኧረ ምነው ኧረ ምነው፣ (2 ጊዜ)
እወዲያ በር ሆኖ የሚያዳምጠው፣
ወንዘኛው አውልያው ቁጥቡ እንደምን ነው፣
አሰላም አለይኩም እስኪ እንበለው፡፡
አሜን አሜን አሜን፣
ኧረ ምነው ኧረ ምነው፣ (2 ጊዜ)
ኧረ ተው አንተየ ኧረ ተው አንተየ፡፡
አዝማች
አሜን፡፡

**ቃል ግጥም 8**

**አሜን አሜን**

አሚን አሚን አሚን፣
እንደው አሜን አሜን፣ኧረ ምነው ኧረ ምነው ፣
ኧረ መጀን ኧረ መጀን፣ኧረ ማሬዋ ኧረ ማሬዋ፣
እንኳን በሾህና ቢታጠር በብረት፣
አሰላማላይኩም ብየ ልበለው፣
የዱበርቲ ድቤ የሚያዳምጠው፣
አሰላም አለይኩም ብሎ የገባው፣
ወረንሰላም አላ ብየ ልበለው፡፡
አዝማች
አሚን አሚን አሚን፣
ኧረ ማሬዋ ኧረ ማሬዋ፣
አንተ አትልም እንጂ አንተማ ስትል፣
ታበላ የለም ወይ ሳታመናትል፡፡
አሚን አሚን አሚን፣
አርግልኝ ያልኩህን አረክልኝ ለካ፣
ጌታው ለጌታው ጥሮ ግሮ ብልሀቱን፣
ሲለምን አደረ እንደውሻ እራቱን፡፡
አሜን አሜን አሜን፣
ማነው ትልቁ ማነው ትንሹ፣
እሱ አይደለም ወይ ሰጪና ነሹ፡፡
አሜን አሜን አሜን፣
ሕዱ እህቶቼ እኔ አልተኛም ተኙ፣
የሰው በሬ አርሼ ቀርቶብኛል እኙ፡፡
አሜን አሜን አሜን፣
አመረረ ሳሂቡ አመረረ፣
ሲያኮበኩብ ነበር ሰማይ በረረ፡፡
አሜን አሜን እደው አሜን፣
መች ይተርፋና በጫት የተመታ፣
እየነገርናቸው እያረጉት ዋዛ፣
የተለበለበው የተላጠው በዛ፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 9**

**ያው ግባ ያው ግባ**

ያውግባ ያው ግባ ያው ግባ፣
ኦወዎ አወዎ ፣
እውው እውው እውው ያው ግባ  ያው ግባ ፣
ብቻህንም  አይደል በመሊካ ጀባ፡፡
መጀን ባይ ነን መጀን ባይ ነን፣
ያው ግባ ያው ግባ፣
አንቱው መጀን አንቱ መጀን እውው፣
አዳኙ ግባ አዳኙ ግባ እህ እህ፣
አዳኙ ግባ አዳኙ ግባ፣
ብቻህንም አይደል በመሊካ ጀባ፡፡
አማን አውለን አማን አውለን፣
አሁን ይመጣሉ ሀድራው እሞቀው ላይ፣
አማን አውለን አማን አውለን፣
አዳኙ ግባ አዳኙ ግባ፡፡
እወዎ እወዎ ሰይዴዋ፣
እህ እህ አህህ፣
ጎራ ለጎራ ነው እሱ የሚሄደው፣
ያው ግባ ያው ግባ፣
ኦሆ አሆ ወገርትና ወይራ አጭሱ የሚለው፡፡
አዳኙ ግባ አዳኙ ግባ፣
አወዎ አወዎ፣
አማን አውለን አማን አውለን፣
ያው ግባ ያው ግባ፡፡
አዝማች

### 1.1.3. ለሁለቱም ፆታዎች የሚደረግ ተለማምኖ ቃል ግጥም

**ቃል ግጥም 10**

**ነገያ ነገያ**

ነገያ ነገያ፣ (4 ጊዜ)
ነገያ ነገያ፣
ነገያ አለሚቱ፣
ነገያ ቁጥቢቱ፣
አዝማች
ነገያ በይላት፣
ነገያ አሁን ነው፣
ነገይ ነገያ፣ (2 ጊዜ)
ነገያ ወንዘኛው፣
ነገያ ነገያ ፣
ነገያ ሦስት ነው፣
በአረተኛውማ ጠቅሎ መሄድ ነው፡፡
ነገያ ነገያ ፣ (4 ጊዜ)
ይሁን፡፡                    አሜን

# 1.2. ግቡና ሀድራ ተጋበዙልን ባይ

## 1.2.1. በዜማ የሚባሉ ቃል ግጥሞች

### 1.2.1.1. ለሴት ዛር የተገጠሙ ቃል ግጥሞች

**ቃል ግጥም 11**

**አሙማ አሙማ**

አሙማ አሙማ፣ (4 ጊዜ)
አሙማ  አሙማ አሙማ ለሙዳው፣
አሙማ  አሙማ አሙማ ቅጥቢቱ፣
አዝማች
ባለዝንዚቱ አሙማ አሙማ፣
ባለሎቃይቱ አሙማ አሙማ፣
ባለገፈታይቱ አሙማ አሙማ፣
ባለጨሌይቱ አሙማ አሙማ፣
አሙማ በይላት፣
አምመሽ ነይ ቶሎ በሰኪናው ላይ፣
አምመሽ ነይ ቶሎ በሙሽራት ላይ፣
አሙማ አሙማ፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 12**

**ግቡ ግቡ**

ግቡ ግቡ አሚናት፣ (2 ጊዜ)
የሰይዳችን እናት ግቡ ግቡ አሚናት፡፡
ግቡ ግቡ መይረሙ፣ (2 ጊዜ)
አላህ ሊያሽረን ከህመሙ ግቡ ግቡ መይረሙ፡፡
ግቡ ግቡ ከድጃ፣ (2 ጊዜ)
እንዲሆንልን ፈረጃ ግቡ ግቡ ግቡ ከድጃ፡፡
ግቡ ግቡ ሳረቱ፣ (2 ጊዜ)
አይሆንምና ካለአንቱ ግቡ ግቡ ሳረቱ፡፡
ግቡ ግቡ እሜቴ አንሻ፣ (2 ጊዜ)
የኸልቁ ሁላ መሸሻ ግቡ ግቡ እሜቴ አንሻ፣
ግቡ ግቡ ፋጢማ፣ (2 ጊዜ)
የአውገረዶቹ ኢማማ ግቡ ግቡ ፋጢማ፡፡
ግቡግቡ ሀዋየ፣ (2 ጊዜ)
ዱአችን ይሁን የለየ ግቡ ግቡ ሀዋየ፡፡
ግቡ ግቡ ሀሊማ፣ (2 ጊዜ)
የአው ገረዶቹ ኢመማ ግቡ ግቡ ሀሊማ፡፡
ግቡ ግቡ አይሂችሁ፣ (2 ጊዜ)
ግብራችሁን ይዛችሁ ግቡ ግቡ አይሂችሁ፡፡
እሰይ ፋጢማ ነቢይ፣ (2 ጊዜ)
እሰይ ፋጦ ነቢይ፣
እሰይ ፋጡማ ነቢይ፣

እሰይ ፋጦ ነቢይ፣
እሰይ ፋጡማ ነቢይ፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 13**
**የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ**
የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ፣
የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ፣
የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ፣
የበረሀይቱ የበረሀይቱ ነይ እቱ ነይ እቱ፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 14**
**ነይ ነይ በረኸኝት**
ነይ ነይ በረኸኝት ነይ ነይ በረኸኝት፣
ነይ ነይ በረኸኝት ነይ ነይ በረኸኝት፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 15**
**ወለል በይ ወለል**
ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ፣
ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ፡፡
ወለል በይ አንቺየ ወለል በይ ወለል በይ፣
ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ፡፡
ባለ ጉዝጓዚቱ ወለል በይ ወለል በይ፣
ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ፡፡
አንቺ ባለ ጨፌ ወለል በይ  ወለል በይ፣
ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ ወለል በይ፡፡
ወለል በይ አንቺየ ከነ አባወራሽ፣
ግቢልን እባክሽ የአረብ  እመቤት፣
አዝማች

**ለወንድ ዛር የተገጠሙ ቃል ግጥሞች**
**ቃል ግጥም 16**
**አርሂብ ወንዘኛው**
አርሂብ ወንዘኛው፣ (4 ጊዜ)
እስኪ ልነሳና አዝግሜ ልሩጠው፣
አገኘው እንደሆን ስንቡልና ከርቤ አጭሱ የሚለውን፡፡
አርሂብ ወንዘኛው፣ (4 ጊዜ)
እሱ የሚሄደው ጎራ ለጎራ ነው እሱ የሚሄደው፣
ወገርትና ወይራ አጭሱ የሚለው፡፡
አርሂብ ወንዘኛው (2 ጊዜ)
መቼ ሰማንና እንዲህ መቸገሩን፣

እጠብቀው ነበር ሀድራ አዘጋጅቼ፣
አርሂብ ወንዘኛው፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 17**
**ሀውሴው አሞራ መናኘ ቶሎ ና**
ሀውሴው አሞራ መናኘ ቶሎ ና፣ (4 ጊዜ)
ሀውሴው አሞራ የወደዱት ጋራ፡፡
ሀውሴው አሞራ ገዳዩ ናና፣
ሀውሴው አሞራ መናኘ ቶሎ ና፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 18**
**ናማ ናማ ናማ**
ናማ ናማ ናማ፣ (2 ጊዜ)
ኧረ ናማ ናማ፣ (2 ጊዜ)
ወደ ሀድራው ና ግባማ፡፡
ናልኘ ናልኘ ናልኘ፣ (2 ጊዜ)
ና ወደ እኔ ግባማ፡፡
ምን ያድርግልሀል የቆንጆ ጎደሎ፣
ናማ ናማ ናማ፣ (2 ጊዜ)
ናማ ናማ ናማ አንተ ድምድም ግባ፣
አበራሽ እያሱ ትመጣለች ማታ፣
እንደ ዶሮ መቅሉህ በአጭሩ ተሰርታ፡፡
ሀይለኛ ሲመጣ የለው መመለሻ፣
ናማ ናማ ናማ፣
ኧረተው አንተየ ባለ ጊሌው ናማ፣
ቶሎ ና ቶሎ ና፣
እሱ ባለ ጊሌ፣
መዋያው ሚሌ ነው ማደሪያው ጉራሌ፡፡
ኧረ ተው አንተየ አንተ ባለ ጊሌ፣
ናማ ናማ ናማ፣
ላይበላ እንጀራ ጋግሬ ጋግሬ፣
እሄዳለሁ የጁ ሚሌን ተሸግሬ፡፡
አዝማች

## 1.4. የሙገሳ ቃል ግጥሞች

### 1.4.1. የሴት ዛር ሙገሳ ግጥሞች

**ቃል ግጥም 19**

**አዘዞ ነው ቤቷ**
አዘዞ ነው ቤቷ አዘዞ ነው ቤቷ፣
አዘዞ ነው ቤቷ የሚያምረው አንገቷ፣
አዘዞ ነው ቤቷ ይቺ ባለአንባር፣
አዘዞ ነው ቤቷ ያምራል ቀለበቷ፡፡
አዘዞ ነው ቤቷ ባለጉዝጓዚቱ፣

አዘዞ ነው ቤቷ ይቺ ባለሙዳ፣
አዘዞ ነው ቤቷ የኔ መድሀኒቴ፣
እየው እየው መላ፣ (2 ጊዜ)
አዘዞ ነው ቤቷ፣ (2 ጊዜ)
ባለ ጥልፍ ቀሚስ ባለጥበብ ኩታ፣
ሀድራውን አሞቀጭ አለሚን አሚልታ።
አዝማች

**ቃል ግጥም 20**
**ለሙና ለሙና**
ለሙና ለሙና፣
ለሙና ለሙና ሸጋው ናና።
ለሙና ለሙና አንቺየዋ፣
ለሙና ለሙና ለሙና ታምራለች።
ለሙና ለሙና ለሙንየ፣
አዝማች
በመኪናው መንገድ በኮረሪማው፣
አንቺን ተከትየ ይብላኝ አሞራው ለሙንየ።
ለሙና ለሙና ለሙንየ፣
አዝማች

**የወንድ ዛር ሙገሳ ቃል ግጥሞች**
**ቃል ግጥም 21**
**እሰየው ነቢየ**
እሰየው እሰየው ነቢየ፣ (2 ጊዜ)
እሰይ ነቢ ነቢ እሰየው ነቢየ፣ (4 ጊዜ)
እሰየው ነቢየ የጦይባው ሙሽራ፣
ላነሳሳው እንጂ እንደምን ልረፍ፣ (2 ጊዜ)
የጦይባው ሙሽራ የጦይባው ሸሪፍ።
በሰባቱ ሰማይ ያደረገው ጉዞ፣
ሀሳቡን ይገድላል ወዝውዞ ወዝውዞ።
እሰየው ነቢ ነቢ እሰይ ነቢ፣
ማን ይነጋገራል ጫት ከቃመ ጋራ፣
ቁጭ ብሎ ካደረ እንቅልፉን ከጠላ።
አሰይ ነቢ እሰይ ነቢ ነቢ፣
ጤና የሌለው ሰው መች ይችላል ጎኑ፣
እያንጎራጎረ ይነግራል ለአንቱ።
መች ይተርፋል እና በጫት የተመታ፣
እትፍ እትፍ የሚል ካገኘ ባላንጣ።
እሰይ ነቢ ነቢ እሰይ ነቢ፣
እላይ እታች ብየ እከተላለሁ፣
የላይ ቤሬ ቁጥብ አዳኙ እንዴት ነሁ።
አንድ ፈረስ ነበር እንደኔ የከፋው፣

የሆዴን ባዋየው ለሁሉም ካልተፋው፣
እዚያው ቤሬ ወርዶ በመንታው በመንታው፡፡
እሰይ ነቢ ነቢ እሰየው ነቢየ፣
የማዶው ሰይዲ አዳኙ እንዴት ነሁ፡፡
እሰየው ነቢ እሰየው ነቢ፣
ኸረ ነብር ነብር ነብር ምን አለበት፣
በጎ ስራ ገብቶት አምስት አውቃ አለበት፡፡
አንቺ ጎረቤቴ ነይ እንነጋገር፣
ጥለን ልንሄድ ነው የማናውቀው አገር፡፡
እሰየው ነቢ ወዳጄ እንዴት ነሁ፣
የማዶው ሰይዲ ወዳጄ እንዴት ነሁ፣
ነው አሉ በደንቡ የሚርገበገቡ፡፡
እሰየው ነቢ እሴው ነቢየ፣
እላይ እታች ብየ እከተላለሁ፣
የላይ ቤሬ ቁጥብ አዳኙ እንዴት ነሁ፡፡
እኩሉም ከአንጀቱ እኩሉም ከአንገቱ፣
ጌታዋ ነቢ ለአንቱ ለወዳጁ፡፡
እንኳን ለጌታችን ለጀነቱ መሪ፣
ሰው ያገለግላል ለዚች አገር ኗሪ፡፡
ዞወር ዞወር ብላ አየችው ቀሚሷን፣
ረስተዋለች አሉ በአፈር መለወሷን ፡፡
ኸረ ቤሬ በሬ ቤሬ ረግረጉ፣
እንኳን ስፍራውና ያስፈራል አገሩ፡፡
እሰየው እሰየው ነቢ፣ (2 ጊዜ)
ቤሬ ላይ ያለው ትርጎው አፍርቶ፣
የሩቁ ይበላል የቅርቡ ተኝቶ፡፡
እሰይ ነቢ ነቢ እሰየው ነቢየ፣
እሴየው ነቢየ እሰየው ነቢየ፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 22**
**አንተ አረብ ሱማሌ**
አንተ አረብ ሱማሌ፣
አረብ ሱማሌ፡፡
አንተ አረብ ሱማሌ፣
አረብ ሱማሌ፡፡
አረብ ነው አረብ ነው፣
አረብ ሱማሌ፡፡
አዝማች
አረብ ሱማሌ ሱማልየው ናና፣
አረብ ሱማሌ፡፡
አረብ ሱማሌ አረብ ሱማሌ ፍየል፣
አረብ ሱማሌ ጆሮዉ ሰፋፊ ነው፣

አረብ ሱማሌ ሚበላው ጫት ነው ፣
አረብ ሱማሌ የሚጠጣው ጠላ፣
አረብ ሱማሌ አይበርድ አያሰክር፣
አጀብ ነው አጀብ ነው፡፡
አረብ ሱማሌ (2 ጊዜ)
አዝማች

**ቃል ግጥም 23**
**እይው ጎጃምን**
እይው ጎጃምን አረማመዱን፣
እይው ጎጃምን አረማመዱን፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 24**
**አሊ ሰላም ሰላም**
አሊ ሰላም ሰላም አሊ ሰላም፣
አሊ ሰላም ሰላም አሊ ሰላም፡፡
አዝማች

**ቃል ግጥም 25**
**አባ ሙና ሙና ወናፈኛ**
አባ ሙና ሙና ወናፈኛው፣
አባ ሙና ሙና ወናፈኛው ፣
አንተ አውሊያ አሁን የመጣሀው፣
እንደፈለክ አድርገህ የምትነዳው፣
የሀድራውን ለዛ የምታሳምረው፡፡
አዝማች

## 1.5. የዛርን ደህንነትና ሰላም ጠያቂ ቃል ግጥሞች

**ቃል ግጥም 26**
**እንደምን ውልሀል**
እንደምን ውልሀል? (4 ጊዜ)
ውልሀል ወይ? (4 ጊዜ)
ውልሀል ይለሉ ውልሀል ወይ?
ውልሀል ወይ?
አዝማች

**ቃል ግጥም 27**
**እንደምነው ነቢ**
እንደምነው ነቢ፣ (4 ጊዜ)
የማዶው ሰይዲ፣
እንደምን ነው ነቢ፡፡
ነቢ ነቢ ብየ፣

እንዴት ነህ ልበለው፣
የጦይባው ሙሽራ የጦይባው ሸሪፍ፣
እንደምን ነው ነቢ ፣ (2 ጊዜ)
ነቢ ስል ውየ ነቢ ስል ባድር፣
እንደው ደህንነቱን ሳልሰማ አላድር፡፡
ወይት ነሽ ይለኛል ያለሁበት ምድር፣
ጥርሱን ጉራማይሌ የተወቀረው፣
ባለቡራቡሬ በሳቅ ተጫዋቹ፣
አዳኙ እንዴት ነው?
እንደምን ነው ነቢ፣
አዝማች

***ቃል ግጥም* 28**
***እንዴት መጣህው በረህውን***
እንዴት መጣህው በረሀውን፣
እንደምን ችለሽው ዉሀ ጥሙን፡፡
እንዴት መጣህው በረሀውን፣
እንደምን ችለሽው ውሀ ጥሙን፡፡
እንዴት መጣህው በረሀውን፣
እንዴት ችለሽው ውሀ ጥሙን፡፡
አዝማች

## 1.6. ደስታን ገላጭ ቃል ግጥሞች

### 1.6.1. የሴት ዛር የተዜሙ ቃል ግጥሞች

***ቃል ግጥም* 29**
**እልል በሉ እስቲ እልል በሉ**
እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣
እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣
እልል በሉ ዛሬ ነው አሉ፣
እልል በሉ ደስታዋ ነው አሉ፡፡
እልል በሉ እስቲ እልል በሉ፣
እልልልል…
አዝማች

***ቃል ግጥም* 30**
**እልል በሉላት**
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፣ (4 ጊዜ)
ማሯ ፈላላት ማሯ ፈላላት፡፡
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፣
እልል በሉላት ቤቷ ሞላላት፡፡
አዝማች
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፣

እስቲ እልል በሉላት፣
ባለ ጉዝጓዚቱ፣
ይቺ በረኸኛ፣
ኧረ እልል በሉላት
ለባለ ሙዳይቱ፣
እስቲ እልል በሉላት፡፡
አዝማች
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፣
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፣
አሁን ይመጣሉ እነ ሁሉ አገሬ፣
ለዚች ባለ አልቦ እስቲ እልል በሉላት፣
ለዚች ባለ ግርዶ እስቲ እልል በሉላት፣
ለዚች ባለ ሽቶ እስቲ እልል በሉላት፣
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፣ (4 ጊዜ)
ቆለምላሚይቱ ፣
በረኸኛይቱ፣
እልል በሉላት ማሯ ፈላላት፡፡ (4 ጊዜ)
አዝማች

### 1.6.2. ለወንድ ዛር የተዜሙ ቃል ግጥሞች

**ቃል ግጥም 31**

**እየቀናው መጣ ደስ እያለው**

እየቀናው መጣ ደስ እያለው፣
እየቀናው መጣ ደስ እያለው፡፡
አዝማች

## 1.7. የሀድራን መድመቅ የሚያበስሩ ቃል ግጥሞች

**ቃል ግጥም 32**

**ሀድራው ኑር አለበት**

ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
የላይ ቤሬ ልጆች ቆንጆ ሲውልበት፡፡
ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
የዚህ ሀገር በሬ ጠይሙ ጠይሙ፣
የእርጎ ፍርፋሪ የሚመስለው ጢሙ፡፡
ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
አያል ጎበዞቹ አያል ጎበዞቹ፣
እበሸባቸውእረጋ አረጉት እንጂ፡፡
የሀድራው ልጅማ ቶሎና ቶሎና፣
ቶሎና ግባማ፡፡
ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
የሀድራ ጭብጦ ይዟል በቀኝ እጁ፣
አለ ወጣ ገባ ሊሰጥ ለወዳጁ፡፡

ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
አላወቁ አለቁ እነ ልክ አያውቁ፣
የማን መሄጃ ነው ብለው ሳይጠይቁ፡፡
ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
ኸረ ቤሬ ቤሬ በሬ አሻረችው፣
የታመመውን ሁሉ ሻር እያደረገችው፡፡
ኸረ ቤሬ ቤሬ ቤሬ አደባባይ ላይ፣
የሀድራው ኑር ይታያል፡፡
ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
የላይ ቤሬ ልጆች፣
የላይ ፊቶ ልጆች እቴዋ እንዴት ነሽ፣
አርሽ አደባባይ ላይ ጠሰምቷል ቃልሽ፡፡
ሀድራው ኑር አለበት፣ (2 ጊዜ)
ቤሬ አደባባይ ላይ ሀድራው ምን አለበት፣
ሀድራው ኑር አለበት፡፡ (4 ጊዜ)
አዝማች

**ቃል ግጥም 33**
**ዘው አለ ሀድራው**
ዘው አለ ሀድራው ዘው አለ፣
ዘው አለ ሀድራው ዘው አለ፡፡
አዝማች

## 1.8. የአወል ቡና መድረስን የሚያበስር ቃል ግጥም

**ቃል ግጥም 34**
አወሉ ነቢ፣ (2 ጊዜ)
አወሉ ጌታው፡፡
አወሉ ነቢ፣
አወሉ ሹሙ፡፡
አዝማች
አወሉ ነቢየ ኸረ አወሉ ጌታው፣
አወሉ ነቢየ ኸረ  አወሉ ሹሙ፣
ነቢ እለዋለው፣
ወይት ነሽ ይለኛል፣
ያለሁበት ምድር፡፡
ወዲያ ማዶ ሂዶ አነሳው መደዱን፣
አረግዋ አህመድ ቤት ያውቁታል መንገዱን፡፡
አዝማች
አወሉ ነቢ፡፡ ( ረዘም ባለ ድምፅ)

## 1.9. የመጀመሪያው ቀን የገፈራ ክዋኔ የፍፃሜ ሰአት መድረሱን(መጠናቀቁን) የሚነግሩ ቃል ግጥሞች

### 1.9.1. ለሴት ዛር የተገጠመ ቃል ግጥም

**ቃል ግጥም 35**
**ቁጥቤ መጥታለች ገፈራ ብላ**
ቁጥቤ መጥታለች ገፈራ ብላ፣
ቁጥቤ መጥታለች ግብር ልትበላ፡፡
አዝማች

### 1.9.2. ለወንድ ዛር የተገጠመ ቃል ግጥም

**ቃል ግጥም 36**
**ጎጃም ወረደ በበረሀ**
ጎጃም ወረደ በበረሀ፣
እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ፡፡
ጎጃም ወረደ በበረሀ፣
እሱም ጠጅ ይላል እኛም ውሀ፡፡
አዝማች

## 1.10. የዛር ሽኝት ቃል ግጥም

**ቃል ግጥም 37**
**እንሂድ ይላሉ እንሂደው**
እንሂድ ይላሉ እንሂደው፣ (4 ጊዜ)
በሲፊው መንገድ በጎዳናው፡፡
እንሂድ ይላሉ እንሂደው፣
በሲፊው መንገድ በጎዳናው፡፡
ቁጥቤ ዋድ እንነጋገር ፣
የቤትሽን ነገር፡፡
ዋድ እንነጋገር፣
የልጅሽን ነገር፡፡
ዋድ እንነጋገር፣
አዝማች

# አባሪ ሁለት
# የገፈራ ክዋኔ ምርቃት(እርፎ በረባ)
## 2.1. በክዋኔውሀድራ አጀማመር ላይ የተመረቁ
### ምርቃት 1

እርፎ በረባ፣ (2 ጊዜ)
እንግዲህ እኒህ ወርቆች፣
ይችን አይተው፣ቀማምሰው ይታረቋት፡፡
ቁጥቢቱ መጀን ፣ወንዘኛው መጀን፣
ልጆቿን ተብቀው፣ርዚቋን ሰጥተው፣
ጤና ትሁንልን፣ቁጥቢቱ በእርቅ ትግባላት፣
ደስ ይበላት፣በእኒሁ በልጆቿ ይለመኑላት፣
አላህ ያቆያት፡፡
ይሁን በይ እርፎ
ቀኑም ለየቱም ግጥሟ ይሁን፡፡
እናቶቿ መጀን፣ እህቶቿ መጀን፣
አላህ ያሽራት፣መሻሪያዋ ይሁን፡፡
መከበሪያዋ ይሁን፣ጤና ማግኛዋ ይሁን፣
ይሄ ቀየ እንግዲህ፣መውሊድ ማውጫዋ ይሁን፡፡
ቁጥቡ መጀን፣ወንዘኛው መጀን፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡ ( ድምፃቸውን ረዘም በማድረግ)
እርፎ መረባ፣ (2 ጊዜ)
አላህ ያቆያት፣ልጆቿ ጋር ደህና ትሁን፣
የላይቷ ላይ፣በእርቅ ይግቡላት፣ ይለመኑ፡፡
ቁጥቢቱ መጀን፣እናቶቿ መጀን፣
እህቶቿ መጀን መሻሪያዋ ይሁን፡፡
ልጆቿን የሚጠብቅ ይሁን፣ደህና ይሁኑላት፣
ልጆቿ ጋር ሰፊ ጤና፣ረጅም ሀያት አላህ ይስጣት፡፡
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡ (ድምፃቸውን ረዘም በማድረግ)

### ምርቃት 2

እርፎ መረባ፣
እርፎ በረባ፣
ጤናሽን አላህ ይስጥሽ፣
ልጆችሽ ጋር በደስታ ኑሪበት፣
የላይትሽ ላይ በእርቅ ይግቡልሽ፣
ይሄን ቀየ እንግዲህ መውሊድ አውጭበት፡፡
ቁጥቡ መጀን፣
ወንዘኛው በእርቅ ይግባልሽ፡፡
ደህና ሁኚ፣
እርዚቁን ይዞ ጤናውን ይዞ፣

ዕድሜውን ይዞ ወንዘኛው ይታረቅሽ፡፡
ሽኾቹ መጀን ቁጥቡ መጀን፣
የሴቱ እመቤት የወንዱ ጌታ፣
በእርቅ ይግቡልሽ፣
ይታረቁሽ፡፡
ዕድሜ ጀባ፣ጤና ጀባ፣እርዚቅም ጀባ፣
ላንቺ ይሁን፡፡
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡(ረዘም ባለ ድምጽ)
እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
የዛሬው ቀን ላንተም ግጥም፣
ለእናትህም ግጥም አላህ ያድርገው፣
በአውራጫው አላህ ያሽርህ፣
ጤና ጀባ ፣
እናትህም ደህና ትሁንልህ፣
በወርቅ ኑሩ፣
ይሄ ቤት እንግዲህ፣
የብር ቤት ይሁን፣
የጤና ቤት ይሁን፣
ያማረ ቤት ይሁን፣
ሽኾቹ መጀን፣ቁጥቡ መጀን፣ደጋጎቹ መጀን፣
ዕድሜህም ረጅም ይሁን፣
ደግ ከራማ ጀባ፣
ከቤተሰቦችህ ጋር አላህ ደህና ያድርግህ፣
እንግዲህ አላህ ያሽራችሁ፣
ይሁን በይ እርፎ ፣
ይሁን፡፡

## 3.2. ጫት ለሚጀባው ሰው የተመረቀ

**ምርቃት 3**

እርፎ መረባ፣
እርፎ በረባ፣
የዛሬው ቀን ላንተም ግጥም፣
ለእናትህም ግጥም አላህ ያድርገው፡፡
በአውራጫው አላህ ያሽርህ፣
ጤና ጀባ ፣
እናትህም ደህና ትሁንልህ፡፡
በወርቅ ኑሩ፣
ይሄ ቤት እንግዲህ ዱአ ያማረ ይሁን፡፡
የብር ቤት ይሁን፣
የጤና ቤት ይሁን፣
ያማረ ቤት ይሁን፡፡

ሸኾቹ መጀን፣ቁጥቡ መጀን፣ደጋጎቹ መጀን፣
ዕድሜህም ረጅም ይሁን፡፡
ደግ ከራማ ጀባ፣
ከቤተሰቦችህ ጋር አላህ ደህና ያድርግህ፡፡
እንግዲህ አላህ ያሽራችሁ፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡
**በሁለት ይሁን**
ማግኛህ ዛሬ ይሁን፣
ቁጥቢቱ ትታረቃት፣
ወንዘኛው ይታረቃችሁ፡፡
ሸኾቹ መጀን ወንድምህ ጋር፣
እናትህ ጋር በደስታ ኑርበት፡፡
የራበውን አጉርስበት፣
የጠማውን አጠጣበት፣
የታረዘውን አልብስበት፣
አላህ ያቆይህ፡፡
በልግ ከመኸር ብላ፣
ይግጠምህ፡፡
ብሩም እዚሁ ይሁን፡፡
ወንድሞችህ ጋር አኅቶችህ ጋር፣
ከሁሉም ጋር አላህ ያቆይህ፣
ይሄ እንግዲህ ወዳጃ፣
ዛሬ የገጠመ ይሁን፡፡
የተቀመጥንበት ነጠላ፣
የገባንበት ሰቀላ፣
ግጥም አላህ ያድርገን፣
ሁሉም ይግጠምህ፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡(ድምፃቸውን ረዘም በማድረግ)
**በሦስት ይሁን**
ማግኛህ ዛሬ ይሁን፣
ሁሉም ግጥምህ ይሁን፡፡
እናትህም ትሻርልህ፣
ይሄ ቤት እንግዲህ ያማረ ቤት ይሁን፣
ቀፎውም ከጓሮ ይቆረጥ፡፡
ይሄ ቀየ እንግዲህ፣
የክብረት ይሁንልህ፡፡
አገሩ ጋር ወንዘኛው ጋር፣
ከሁሉም ጋር ቁጭ ያድርግህ፡፡
ጤና ጀባ ፣
ጤና ጀባ ሙሄዋ፡፡
አላህ ያሽራት፣

እናትህ ጤና ትሁንልህ፡፡
ያማረችውን ጠባይ ያላትን፣
ለአንተ ይግጠምህ፡፡
ወንዘኛው ይታረቅህ፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡ (ድምፃቸውን ረዘም በማድረግ)

## 3.3. ከነገያ ነገያ ቃል ግጥም በኋላ የተመረቀ

**ምርቃት 4**

እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
ሁሉም ይታረቃችሁ፣
በላስታው ሻሩ፣
አላህ ያሽራችሁ፣
አብራችሁ ሻሩ፣
እሷም ደህና ትሁንልን፣
ልጆቿም ደህና ይሁኑልን፣
አማን አላህ ያድርገን፣
ሀያት ጀባ፣
ይሄ ቀየ ይሻር፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡
አላህ ያሽራችሁ፣ደስ ይበላችሁ፣
ቁጥቡ መጀን ወንዘኛው መጀን፣
ሁሉም ይታረቃችሁ፣
ላይቷ ላይ በእርቅ ይግቡላት፣
ይሁን በይ እርፎ ፣
ይሁን፡፡
አላህ ያሽራችሁ ፣
እሷም ደህና ትሁን፣
የገባንበት ሰቀላ የተቀመጥንበት ሰቀላ፣
ግጥም አላህ ያድርገን፣
ቁጥቡ መጀን፣
ይሄ ሀድራ እንግዲህ ያማረ ይሁን፣
ልጆቹ መጀን እህቶቹ መጀን፣
ሁሉም ይመር፣
ይሄ ቀየ እንግዲህ ያማረ ቤት ይሁን፣
የማር ቤት ይሁን፣
የጠየና ቤት ይሁን፣የክብረት ቤት ይሁን፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡

### 3.4. ከእራት ስነስርአት፣ከጫት ጀባታና ዱአ በኋላ የተመረቀ

**ምርቃት 5**

እረፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
መጥፎ ነገርን ያዥላት፣
አንሺ፡፡
በላን አንሺላት፣
እዚያው ጣይላት፣
አንሺ፡፡
ከዚህ ቤት ቁንጫንም ፣
ቱሀንንም አውጪ፣
አንሺ፡፡
እርፎ መረባ፣
መረባ፣
እንግዲህ ዛሬ ከማጀቷ አውጭላት፣
ጫት ቅሜም አላምጨም፣
እንግዲህ ሞኝ ነገርን አባሪላት፣
አንሺ፡፡
አንሺ እፍ አንሺ እፍ፡፡ (3 ጊዜ) (በእጃቸው ምልክት በማሳየት)

### 3.5. ከዱአው በኋላ አወል ቡና ሲቀርብ የተመረቀ

**ምርቃት 6**

እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
ቁጥቡ መጀን ወንዘኛው መጀን፣
ዕድሜ ጀባ ጤና ጀባ፣
ክፉ አይንካህ ደግ አይለፍህ፣
ወንዘኛው አይክዳህ የናትህም የላይቷላይ እርዚቅ ይዞ ይግባ፣
ዕድሜያችሁ ረዥምም ርዚቃችሁ ብዙ አላህ ያድርገው፣
ይሁን በይ አርፎ፣
ይሁን

### 3.6. ሁለተኛው ቡና(ቶና) ሲቀርብ የተመረቀ

**ምርቃት 7**

እርፎ መረባ ፣
እርፎ መረባ ፣
ፍራፍሬው የህልም ፍሬው፣
ብሩም ፈልጎ ይምጣ፣
እንግዲህ ዛሬ ጨርሶ ትሻር፣
ጤና ጀባ፣ዕድሜም ጀባ፣
እርዚቅም ጀባ፣ደግ ከራማ ጀባ፣
ይሄ ቀየ እንግዲህ ያማረ ቤት ይሁን ፣

ልጆቿም ደህና ይሁኑ፣
ይሄ ቃየ እንግዲህ ለራበው ማጉረሻ፣
ለታረዘው ማልበሻ ይሁን፣
ይሁን በይ እርፎ ፣
ይሁን።

### 3.7. ሦስተኛው ቡና ሲቀርብ የተመረቀ ምርቃት 8

እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
በጥንድ ውለጂ፣
ሽኾቱ መጀን፣ቂጥቡ መጀን፣
ይታረቁሽ በእርቅ ይግቡልሽ፣
ልጆችሽን ይጠብቁልሽ፣
አንቺም ደህና ሁኚ፣
አጀዝሽ ስብ ይሁን፣
ፍሬው የአንቺ ይሁን፣
እርዚቅሽ ብዙ ይሁን፣
ከራማሽ ጥሩ ይሁን፣
ልጆችም ደህና ይሁኑልሽ፣
ይውለዱልሽ፣ይክበዱልሽ፣
ሽኾቱ መጀን ወንዘኛው ይታረቅሽ፣
ቂጥቢቱ ትታረቅሽ፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን።

### 3.8. ለሚጁ ሙዳ ጀባ ሲባል የተመረቀ ምርቃት 9

እርፎ በረባ፣
እርፎ መረባ፣
በዚሁ በሙዳው አላህ ያሽርሽ፣
በጥንድ ውለጂ፣
ሽኾቱ መጀን፣ቂጥቡ መጀን፣
ይታረቁሽ በእርቅ ይግቡልሽ፣
ፍሬው የአንቺ ይሁን፣
እርዚቅሽ ብዙ ይሁን፣
ከራማሽ ጥሩ ይሁን፣
በላስታዉ ሻሪ፣
ይሁን በይ እርፎ፣
አሜን ። ፣ ይሁን።

### 3.9. በስነ-ስርአቱ የሚለየውና ቶናና በረካ ሌለው አወል ቡና ሲቀርብ የተመረቀ

**ምርቃት** 10

እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
የዛሬው ቀን ግጥማቸው ይሁን፣
ወንዘኛው መጀን ፣ይሄ ቃየ መጀን፣
እህቶቿ መጀን፣ወንድሞቿ መጀን፣
አላህ ያሽራት፣
ይቺ ቁጥብ እንግዲህ ቀማምሳ የምታኮብር ትሁን፣
የገባንበት ሰቀላ የተቀመጥንበት ነጠላ ግጥም አላህ ያድርገን፣
አላህ ያሽራት፣
አሻሪ እንሁን፣
አክባሪ እንሁን፣
ቁጥቡ መጀን አላህ ያሽራቸው፣
ረዥም ሃያት፣ሰፊ ጤና አላህ ይስጣቸው፣
ይሁን በይ እርፎ፣
አሜን፡፡ ፣ ይሁን፡፡

### 3.10. አወሉ ነቢ፣አወሉ ሹሙ ከሚለው ቃል ግጥም በኋላ አወል ቡናው ሊቀዳ ሲል የተመረቀ

**ምርቃት** 11

እርፎ መረባ፣
አወሉ ሞላ፣
የሞላ ጤና እዚህ ቤት ይሁን፣
የሞላ ዱኒያ እዚህ ቤት ይሁን፣
ሰፊ ማድ እዚህ ቤት ይሁን ፣
ሙሉ ጠየና አላህ ይስጣት፣
ደስ ይበላት፣
ይሁን በይ እቴ፣
አሜን፡፡ ፣ ይሁን፡፡

### 3.11. ሻይ ተፈልቶ እልልበሉላት የሚለው ቃል ግጥም ከተዜመ በኋላ

**ሻይው ሊቀዳ ማር ጀባ ሲባል የተመረቀ**

**ምርቃት** 12

እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
ማር ይሁን ቀለብሽ፣
ጤና ጀባ፣ እርዚቅ ጀባ፣ ዕድሜም ጀባ፣
አላህ ያሽራት፣
ይቺም ትሻር፣ያቺም ትሻር፣

ልጆቿ ጋር በደስታ ትኑር፣
ማሩም ከንሮ ይቆረጥ፣
ሆ ብላ ትምጣ፣
ቁጥቡ መጀን ወንዘኛው መጀን ከንሮ ይቁረጡ፣
እሷም ትሻር ፣
ይሄ ቤት እንግዲህ በማሩ ይሻር ፣
ይሁን በይ እርፎ
አሜን ። ፣ ይሁን።

### 3.12. የጠላና ቡቅሪው(የሚጁ) ገፈታ ሊከፈት ሲል ባለ ጉዝጓዟ ሚጁ ጀባ አለች ተብሎ ሲነገር የተመረቀ

ምርቃት 13

እርፎ በረባ፣ (2 ጊዜ)
እንግዲህ ዛሬ በሻሪያዋ ይሁን፣
ልጆቿ ጋር መክበሪያዋ ይሁን፣
ይታረቋት፣
እዛሬ ሁለት አመት ድረስ፣
ግጥሟ ይሁን፣
ይሁን በይ እርፎ ፣
አሜን ። ፣ ይሁን።

### 3.13. ሌሊት የዛር መንፈሶቹን ከገፈራው ድግስ ግብራቸውን አሷርፈው ሲመለሱ የመረቀ

ምርቃት 14

እርፎ በረባ፣
አርፎ መረባ፣
ዕድሜዋ ረጅም ይሁን፣
ከእንግዲህ በላይ ቁጥቡ መጀን፣
ሁሉም ይታረቋት፣
ይሄ ቀየ እንግዲህ መውሊድማውጫዋ ይሁን፣
ይሄ ቀየ እንግዲህ ሰደቃ መሰደቂያ ያድርገው፣
ሁሉም ይስማማት፣
ቁጥቢቱ ትታረቃት፣
ወንዘኛው ይታረቃት፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን።

### 3.14. በሦስተኛው ቀን ከጠረጋ በኋላ ቡና ስነ-ስርአት ላይ በተለያዩ ተሳታፊዎች የተመረቁ

2.15.1. በአበጋሯ የተመረቀ

ምርቃት 14

እርፎ መረባ፣

እርፎ መረባ፣
እንግዲህ በሽታ አይንካት፣
ቁጭ ብላ ትብላ፣
ዕድሜዋ ረጅም ይሁን፣
ከእንግዲህ በላይ ቁጥቡ መጀን፣
ሁሉም ይታረቋት፣
ይሁን በይ እርፎ
አሜን፡፡ ፣ ይሁን፡፡

### 1.15.2. በተሳታፊ የተመረቀ

**ምርቃት** 16
እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
አማን ኢማን ጀባ በረካ ጀባ፣ (2ጊዜ)
ወልዳችሁ ሹሙ፣
አባውራሽ ጋር፣
ጭቃና ጨፊቃ ፣
ሰምና ገላ አድርገናችኋል፣
ማርና ምላስ አድርገናችኋል፣
ወተትና ድመት አድርገናችኋል፣
ይሁን በይ እቴ፣
ይሁን፡፡

### 1.15.3. በተሳታፊ የተመረቀ

**ምርቃት** 17
እርፎ መረባ፣
እርፎ መረባ፣
ካሁኑ ጎራሽ፣
ከከርሞው ደራሽ ፣
አላህ ያድርገን፣
አማን ኢማን ጀባ፣
አገር አማን ይሁን፣
በለው ተብረድ ይሁን፣
ሹም ድልድይ ይሁን፣
መንገድ በዘንግ ይሁን፣
ገበያ ጥጋብ ይሁን፣
ይሁን በይ እርፎ፣
ይሁን፡፡

### 1.16. የጠረጋ ቀን( የዛር ሽኘት) ላይ ሻይ ሊቀዳ ሲል በአሷራፊ የተመረቀ

**ምርቃት** 18
እርፎ መረባ ፣
እርፎ መረባ ፣
በሙዳው ለመናቸው፣
በማሩ ለመናቸው፣
በዱበርቲ ለመናቸው፣
በልተው ጠጥተው፣
እሰፊው አገር፣
እባኒው አገር፣
እወርቁ አገር ሸኘናቸው፣
ይስማማት፣
ይታረቃት፣
አሷም ደህና ትሁን፣
ልጆቿም ደህና ይሁኑ፣
ይሁን በይ እቴ፣
ይሁን፡፡

## አባሪ ሦስት

## ለመረጃ ሰጪዎች የቀረቡ ዋናዋና ጥያቄዎች

### I. ለባለ ጉዝጓዞች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ስሙዎንና ዕድሜዎን ቢነግሩኝ?
2. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
3. ለርስዎ ገፈራ ማለት ምንድን ነው?
4. ለገፈራ የሚደረገው ልመና ላይ መሟላት ያለባቸው አደቦችን ቢነግሩኝ?
5. ልመናው የሚካሄደው ለስንት ጊዜ እና ከነማን ቤት ነው?
6. ከአሚኖች ቤት ግዴታ የሆነው ለምንድን ነው?
7. በብቅል ውሀ የምትታጠቡት ለምንድን ነው?
8. ጠላና ቡቅሪው ሲዘጋጅ ድፍድፉን እንኳ የማይቀመሰው ለምንድን ነው?
9. አንድ ሰው በዛር ለመያዙ ምክንያቱ ምንድንነው በምንስ ይረጋገጣል?
10. ገፈራ ማድረግ የጀመሩት መቼ ነው ለስንት ጊዜስ ገፈራ አድርገዋል?
11. ገፈራ በማድረግዎ የሚያገኙት ጥቅም ቢገልፁልኝ?
12. ገፈራ ባያደርጉ ምን ይገጥመኛል ብለው ይሰጋሉ?
13. ለገፈራ የሚደረግባቸውንና የማይደረግባቸውን ወቅቶች፣ዕለታትና ወራት ካሉ ቢነግሩኝ?
14. እነዚህ ጊዜያት ተመራጭ የሆኑባቸው እና ባልተመረጡት ጊዜያት ገፈራ የማይካድበት ምክንያት ምንድን ነው?
15. በገፈራ ላይ የሚሳተፉት ሰዎች እነማን ናቸው፣የሚጠሩትስ እንዴት ነው?
16. ለገፈራ የሚዘጋጁ ምግቦችና መጠጦች ምን ምን ናቸው፣እርስዎስ ምን ምን ያዘጋጃሉ?

17. እነዚህ ምግቦችና መጠጦች ለምን ተመራጭ ሆኑ?
18. ለገፈራ ሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ምን ምን ናቸው?
19. እነዚህ ቁሳቁሶች ፋይዳቸው ምንድን ነው?
20. የጨሌዎቹ ቀለማት ምንን የሚወክሉ ናቸው?

## II. ለተሳታፊዎች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ስሙዎንና ዕድሜዎን ቢነግሩኝ?
2. የሚኖሩበት አካባቢ ማን ይባላል?
3. በገፈራ ስርአት ላይ ለመሳተፍ የመጡት በጥሪ ነው ወይስ በፍላጎት?
4. እዚህ ስነ-ስርአት ላይ መሳተፍዎ የሚያገኙት ጥቅም ካለ ቢነግሩኝ?
5. ለገፈራ ስነ-ስርአት ያለዎን አመለካከት ቢገልፁልኝ?
6. ለባለ ጉዝጓዞች የሚሰጡ ጀባታዎች ምን ምን ናቸው?
7. እነዚህ ጀባታዎች ለምን ፋይዳ የሚሰጡ ናቸው?
8. ገፈራ የሚያደርጉት ሴቶች ብቻ ናቸው ወይንስ ወንዶችም ያደርጋሉ?
9. ወንዶች የሚያደርጉበት ጊዜ ከሴቶቹ ጋር ተመሳሳይ ነው?
10. ይህ ስነ-ስርአት ያለበትን ደረጃ ማለትም የሚያካሂዱት ሰዎች መጠን ከበፊቱ ጋር በማነፃፀር ቢነግሩኝ?
11. የቀነሰበት ምክንያት ምን ይመስለዎታል?
12. ይህ ስነ-ስርአት ቀጣይነት እንዲኖረው ምን እየተደረገ ነው?
13. ጠረጋው ቀን ላይ ቆሻሻው ሲደፋ ማውራት የማይቻለው ለምንድን ነው?

## III. ለቡድን ውይይት የቀረቡ ጥያቄዎች

1. ገፈራ የሚደረግባቸው ቀናት ፣ወራት ካሉ ቢነገርኝ?
2. እነዚህ ቀናት ለምን ተመረጡ ሌሎቹስ ያልተመረጡበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. ገፈራ የመጀመሪያው ቀን ማታ ማለትም ሌሊቱን ሙሉ መሆኑ ለምን ተመረጠ?
4. የገፈራ ጥቅም ምንድን ነው?
5. ዛር አንድ ሰው ላይ እንዴትና ለምን ይሰፍራል?
6. ዛር የሰፈረበትን ሰው እንዴት ማወቅ ይቻላል?
7. ለገፈራ የሚደረግ ልመና ስንት ጊዜ የሚካሄድ ነው?
8. ሁለቱም ልመና ለሀብታሞቹም ለደሀዎችም ግዴታ ነው ወይስ መተው ይችላሉ?
9. ከአሚኖች ቤት የሚካሄደው ልመና አይቀሬ የሀነበት ምክንያት ምንድን ነው?
10. የተለመነውን እህል ለሌላ ተግባር ማዋል ይቻላል?
11. በብቅል ውሀ የሚታጠቡት ለምንድን ነው?
12. በገፈራ ላይ የድቤና የማሲንቆ አገልግሎት ምንድን ነው?
13. የጭሳጭሶቹ ፋይዳ ምንድን ነው አንዱ እንኳ ቢጎደል ችግር አለው ወይ?
14. የጨሌዎቹ እያንዳዳቸው ቀለማት ትርጉም ምን ምን ነው?
15. ጨሌው ቅቤ ከተነከረ በኋላ ሲመለስ ግንባራቸውን ሦስት ጊዜ የሚያስነኩት ለምንድን ነው?
16. የወንዱ አሷራፊ የተሳትፎ ድርሻ ወይም ሚና ምንድን ነው?

17. ማሲንቆ ተጫዎቹ እና አሏራፊው ወደ ግርዶሹ ሲገቡ አገባባቸውና አቀማመጣቸው አደብ አለው ወይ?
18. አማን አውለን አማን አውለን የሚለው ቃል ግጥም ላይ ገፈራው ማታ ሆኖ አውለን የተባለው ለምንድን ነው?
19. ማታ ባለጉዝጓዚን ይዛችኂት የወጣችው ጃን ጥላ ዘርግታችሁ ነበር ነገርግን ዝናብም ፀሀይም አልነበረም ለምን ጃንጥላው ተዘረጋ?
20. ጠላ፣ ቡቅሪ፣ዳቦ፣ቆሎዎቹን ማታ የደፋችሁት ለምንድን ነው?
21. እሰይ ነቢ እና አማንየ አማኔው ነብየ የሚለው ቃል ግጥም ላይ የነብዩን ስም የምታነሱት ለምንድን ነው ወይም በዚህ ግጥም የምታወድሱትና ምትለማመኑት ማንን ነው?
22. ማታ ሹመት የተሰጠው ለማን ነው?
23. ሴቷ ዛር(ቁጥቢቱ) ብቻ የብትሾመው ለምንድን ነው ወንዱስ(ወንዘኛው) ለምን አይሾምም?
24. ሚጁዋ ላስታ ቅቤውን በሁሉም ፊት ስታዞር እስስ እስስ የሚባለው ምን ለማለት ነው?
25. ጥራጊው ሦስተኛው ቀን ድረስ ያልተጠረገው ለምንድን ነው?
26. ገፈራ የሚያደርጉት ሴቶች ብቻ ናቸው ወይንስ ወንዶችም ያደርጋሉ?
27. ወንዶች የሚያደርጉበት ጊዜ ከሴቶቹ ጋር ተመሳሳይ ነው?
28. ይህ ስነ-ስርአት ያለበትን ደረጃ ማለትም የሚያካሂዱት ሰዎች መጠን ከበፊቱ ጋር በማነፃፀር ቢነግሩኝ?
29. የቀነሰበት ምክንያት ምን ይመስለዎታል?
30. ይህ ስነ-ስርአት ቀጣይነት እንዲኖረው ምን እየተደረገ ነው?

# አባሪ አራት ሁለት ፎቶዎች



ምስል 1. አጥኝዋ ከአሏራፊ ሸህ አብዱ ረያን ጋር እና ከአበጋሪት ወ/ሮ አሚናት አሊ ቃለ መጠይቅ ስታደርግ የሚምስል 2. አጥኚዋ የቡድን ውይይት ስታደርግ



ምስል 3. ካዳሚ ሻይ ስትቀዳ እና የጠላና ቡቅሪ መጠጫ አቦሬን የሚያሳዩ ምስሎች



ምስል4. ገፈራ ተሳታፊዎችን አቀማመጥ የሚያሳይ ምስል



ምስል 5. በጠረጋ(ሽኘት) ቀን ቆሻሻ ሊደፉ ሲሄዱ ከቀኝ ወደ ግራ (አሷራፊ፣ባለጉዝጓዝ፣አበጋሪት፣ ሁለት ጨሌ ያስነከሩ ሚዜዎች እና አጥኚዋ) የአሰላለፍ ቅደም ተከተላቸውን የሚያሳይ ምስል



ምስል 6. በመጀመሪያው ቀን ማታ የሹመት ስነ-ስርአት ላይ ተሸማ የተቀመጠችው ዛር ግብር (ጨሌ የተነከረበት ቅቤ ዝቃጭ፣ወንፊት፣ቆሎ፣ዳቦ፣ፈንድሻ፣ቅንጨ)የያዘውሰፌድ እና አሷራፊዋ ቆሻሻ ስትድፋና ቅቤ የታሰረበትን ነጭ ሻሽ ውሀ ስታፈስ የሚያሳዩ ምስሎች



ምስል 7. በሸኘት ቀን ባለጉዝጓዟ ጠላና ቡቅሪ ይዛ፣ሷራፊዋ ተቀብላት ስታሽታትና ካሽተተቻት በኋላ ስታዞራት




ምስል 8. አሷራፊዋ ለባለጉዝጓዟ ጨሌው ከታጠበ በኋላ የጨሌውን ¼ኛ በመያዝ ግንባሯን አስነክታ ስታጠልቅላት፣ከዚያም ለአበጋሯ በተመሳሳይ ጨሌዋን ግንባሯን ሦስት ጊዜ አስነክታ ስታጠልቅላት እና አበጋሯ መጨረሻ ላይ ለአሷራፊዋ ጨሌዋን ስታጠልቅላት የሚያሳዩ ምስሎች



ምስል 9. በገፈራ ሁለተኛ ቀን ቆሻሻ ሳይጠረግ፣ ሙቀጫ ከዘነዘናውና ከብርኩማ(መቀመጫው) ጋር፣ ጀበና ከነማቶቱ(የጀበና ማስቀመጫ) እና ስኒ ረከቦት ላይ ተደርድሮ እና ቁኒ ቀዳዳን የሚያሳዩ ምስሎች




ምስል10. ድቤዎች



ምስል 11. ማሲንቆዎች



ምስል 12 ዳቦ፣የማሽላ ፈንድሻ፣ኑግ ፣ ቅንጨ የሚያሳዩ ምስሎች



ምስል 13. በቅድመ ዝግጅት ጊዜ ዳቦ፣ርጥብ ቡና ጀባታ ሲሰጥ፣ርጥብ ቡናና ሽንብራ፣የተቆላ ድፍን ቡና እና የስራው ተሳታፊ የተወቀጠውን ቡና ወደ ቅል ስትቆጥር የሚያሳዩ ምስሎች

# አባሪ አምስት

## ማረጋገጫ

ይህ የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ (ቴሲስ) የእኔ ወጥ ስራ (orginal) ሲሆን ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የዲግሪ ማሟያ ሆኖ ያልቀረበና በተለያዩ መፅሄቶች ላይ ያልታተመ መሆኑንና ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ፡፡

ሥም                                        ፊርማ

ዘቢባ መንግስቴ ይመር

አዲስ  አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ግንቦት 2008 ዓ.ም